# ዘጎሁ

T.me/goodamharicbooks

ዓሐመዋሁ ዋሌ ኑሸቴ

2009 ዓ.ም.

# ዝኒሁ

ዓለማዊሁ ዋሌ ኑሸቴ (R/C)

መጋቢት 2009 ዓ.ም

© ዓለማየሁ ዋሴ እሸቱ 2008 ዓ.ም
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
ALL RIGHTS RESERVED

ሁለተኛ ዕትም መጋቢት 2009. ዓ.ም.

አድራሻ

ዓለማየሁ ዋሴ እሸቱ (ዶ/ር)

E-mail:- Emegua2015@gmail.com

ባሕር ዳር

ኢትዮጵያ

ዋና አስፋፋይ:-
አማረ አበበ ሞላ
+251 0920 18 79 06

ባሕር ዳር

ኢትዮጵያ

# መታሰቢያነቱ

ክ ኳጽርገው ጽኩን ከናቁት ዎሀ

# ‹ ከሰው ሰው ›

ከሁሉ በማስቀደም ለሚያስጀምርም ለሚያስጨርስም ሁሉን ቻይ ለሆነው አምላክ ክብርና ምስጋና ማቅረብ ተገቢ ነው። በመቀጠልም በሀገራችን በተለይ በገጠሩ አካባቢ የሚነገር አንድ ወርቃማ ሥነ ቃል አለ፡-

"ስሙኝ ወገኖቼ እኔ ልንገራችሁ

ለሰው ሰው ነው ልብሱ ጨርቅ አይምሰላችሁ።"

ይህ ሥነ ቃል እውነት ሆኖ ሥራዬን ሥራቸው አድርገው ረቂቁን በማንበብ የጎደለውን በመሙላት የተጣመመውን በማቃናት ከፊደል ለቀማ እስከ ሐሳብ ማበልጸግ የደገፉኝን ወንድሞቼንና እህቶቼን ማመስገን እወዳለሁ። መርጌታ ዮሴፍ ዳኘው፣ ዲያቆን ዳንኤል ክብረት፣ ዲያቆን ሙሉቀን ብርሃኑ፣ ዲያቆን ሲሳይ ፀጋዬ፣ አቶ አማረ አበበ፣ አቶ ዐባይ ከንዴ እና ወ/ሮ መሠረት ሸፈራውን ከልብ አመሰግናለሁ። የማያልቅበት ፈጣሪ ዕደሜና ጸጋውን ያብዛላችሁ። ረቂቁን ለተየበችልኝ ለወ/ሮ ባንቺአምላክ ኢያሱና የመጽሐፉን የገጽና መልክ ቅንብሩን ለሠራችው ወ/ት አዜብ ጌታቸውም ምስጋና ይገባታል። በተለይ ወንድሜ ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ ያደረከልኝ ድጋፍ እጅግ ከፍ ያለ ነው። ያላንተ እንዴት ይሆን ነበር?

በየገዳማቱና በየአብያተ ክርስቲያኑ ለሥራ በዞርኩባቸው ጊዜያት ሁሉ ያገኘሁት መስተንግዶና ያየሁት ደግነት ምንጊዜም ከዐይነ ኅሊናዬ አይጠፋምና በዚያ ያላችሁ አባቶችና እናቶች በጽኑ ተስፋ የምታደርጉት አምላክ ሰማያዊ ክብርን ያድላችሁ።

እመኝ የተሰኘችውን መጽሐፌን አንብባችሁ በአካል በስልክና በኢሜል ያበረታታችሁኝን ሁሉ እግዚአብሔር ይስጥልኝ። ምናልባትም ይኸኛው መጽሐፍ የእናንተ ድጋፍ ውጤት ሳይሆን አይቀርምና ውጤቱን የጋራችን እናድርገው።

በመጨረሻ የቤተሰቤን ኃላፊነት በብቸኝነት የምትወጣውን ባለቤቴን ሲ/ር በላይነሽ መለሰንና ልጆቼን በስፋት ማመስገን የሚገባኝ ቢሆንም አንዳንዴ ግን እኔን ማመስገን ስለሚሆንብኝ በአጭሩ አመሰግናለሁ።

# ለዘሪህ መጽሐፍ

መግቢያ አያስፈልገውም። ጽሑፉ የፊደልና የሰዋስው ግድፈት ቢኖረው ታግሰው እንዲያነቡት በታላቅ ትሕትና ተጋብዘዋል። ይህ ትረካ ለፍልስፍና፣ ለምክር ወይም ለተግሣጽ ታስቦ አልተጻፈም። ይልቁንም እውነተኛ ገጠመኞችን መሠረት አድርጎ በልብ ወለድ መልክ የተዘጋጀ ጽሑፍ ስለሆነ በዚህ ወከባና ጥድፊያ በበዛበት ዓለም ውስጥ ቢሆኑም ጊዜ ወስደው ተረጋግተው ቢያነቡት እንዴት ደስ ባለኝ!

ጸሐፊው

መኮንም ንጉሀ!

# ለውር ትኽዛዝ

# የጨሐማው ንዳ ብርሃን ሊያገኝ

# ምዕራፍ ኻንዱ

ሚ/ር ራምዚ አንዶን አቡዳቢ ካረፍንበት ሆቴል ይዞኝ የምሥራቅ አቅጣጫን ተከትሎ አምስት ብለሎችን ከነዳ በኋላ አንድ ዘመናዊ ባለ20 ፎቅ ሕንጻ ሥር መኪናውን አቁሞ በአሳንሰር 18ኛው ፎቅ ላይ ከሚገኝ ሬስቶራንት ወሰደኝ። የፋርስ ባሕረ ሰላጤ አካል የሆነው ውኃ ተንጣለሎ ይታያል። "ግሩም የሆነ ምርጫ ነው፣ አመሰግናለሁ" አልኩት።

ምሳ ቀርቦልን እየበላን ሳለ እንዲህ አለኝ፡-

"አባቴ ስለ ኢትዮጵያ ብዙ ነገር ይነግረኝ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ በቂ ግንዛቤ የነበረው ይመስለኛል" አለ።

"መልካም ነገር እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ" አልኩት።

"እምን! ኢትዮጵያውያን በእምነታቸው ጠንካራ፣ ጀግኖችና ሀገር ወዳዶች ናቸው። እርግጥ ሲበዛ ምሥጢራውያን ናቸው" ይለኝ ነበር አለ።

ፈገግ አልኩና "እውነትም አባትህ በደንብ ያውቀናል" አልኩት።

ቀጥሎም "ኑሮማችን ውስጥ እናንተ እንደምትመጡ መርሳ ግብር ሊያዝና ማን ያስተናግዳቸው ሲባል በደስታ ነበር እራሴን ያዘጋጀሁት" አለኝ።

"እሙ! በጣም እናመሰግናለን። በእውነቱ ክብር ይሰማናል" አልኩት

"እንተም ታዲያ እንደ አባትህ አሁንም የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ነህ?" አልኩት።

"እንደ አባቴ እንኳን ማለት አልችልም። ይሁንና ራሴን እንደ ቤተ ክርስቲያኗ ተከታይ እቆጥራለሁ" አለኝ።

"ደስ ይላል" አልኩና ወደ ባሕረ ሰላጤው ዐይኔን ወረወርኩ።

"እኔ እምልህ ሚ/ር ሲሳይ፣ እንዲያው ቅር የማይልህ ከሆነ አንድ ጥያቄ ብጠይቅህ?" አለኝ በፍጹም ትሕትና።

"እንዴ ምን ችግር አለው? ጠይቀኝ" አልኩት።

"ከቅድም ጀምሮ በአእምሮዬ ሲጉላላ ስለነበር ነው፣ እና..." አለ እንደመጠራጠርና እንደማመንታት እያለ።

"እንዴ ምንድን ነው?" አልኩት በሚያደፋፍር ፈገግታ ታጅቤ።

"ቅድም ከሙዚዬሙ ስትወጣ ምን አጋጥሞህ ነው በድንገትና በጥድፊያ ወደ ሀገርህ ለመመለስ እንደዛ ያጨናንቅኽኝ?" አለኝ።

"አ! ረብሸህ ነበር ማለት ነው? ይቅርታ፣ ነገሩ እንኳ ቀላል ነበር" አልኩት።

"አይ ቀላልማ አልነበረም። ከፍተኛ የሆነ የመረበሽ ስሜት ውስጥ ነበርክ እኮ" አለ።

"ያን ያክል ሰሜታዊ ከነበርኩ አዝናለሁ። ነገሩ እንኳ ተራ ነገር ነበር" አልኩት።

"ልትነግረኝ አልፈቀድክም ማለት ነው?" አለ።

"አይ ያን ያክል ሊነገር የሚችል ብዙም ማራኪ ጉዳይ ስለሌለው እኮ ነው" አልኩት።

"እየሁ አባቴ ትክክል ነበር ማለት ነው። 'ኢትዮጵያውያን ምሥጢራውያን ናቸው ያለኝ"፣ አለና እርሱም ወደ ባሕረ ሰላጤው ፊቱን አዞረ።

"አይ እንደሱ አይደለም። ምሥጢር ለመደበቅ አይደለም" አልኩት። በውስጤ ደግሞ "አይ ምሥጢራዊነት እቴ፣ ምሥጢር መጠበቃችን ቀርቶ ያየነውንም ያላየነውንም መዘከዘከና ወሬ ማናፈስ ጠባያችን እየሆነ መምጣቱን ለአባትህ ማን በነገራቸው" አልኩ።

"ታዲያ ለምን አትነግረኝም? ምናልባትም እማርበት ወይም እገረምበት ወይም ዘና እልበት ይሆናል" አለኝ።

"አይ... ያን ያክል የሚደበቅም እኮ ሆኖ አይደለም፣ ግን ...ስልህ ...››

"እኔም እኮ ብዙ ላስጨንቅህና ግላዊ ምሥጢርን ለመስማት ፈልጌ አይደለም። ልትጎበኝ ሙዚዬም ውስጥ ካስገባሁህ በኋላ ድንገት ወጥተህ አሁኑ መመለስ እፈልጋለሁና ትኬት አስተካክልልኝ ስትል ድንገተኛ አደጋ የገጠመህ መስሎኝ ስለተጨነቅሁ ብቻ ነው" አለ መንተባተቤንና ማመንታቴን በማየት።

"በምታስበው መንገድ የተለየ ነገር አልገጠመኝም ነበር። ድንገት ባልገመትኩት ሁኔታ ሙዚዬሙ ውስጥ እንድ ነገር ስለገጠመኝ ነበር።"

"ምን? ምን ሁኔታ? እ...ንዴት" ድንጋጤና መደነቅ ባለው መንፈ
ሆኖ ወደኔ ላይ አፈጠጠ።

"ምንም የሚረብሽ ነገር አልነበረውም። ብቻ በሙዚዬሙ በእንደገ
ከፍል አስደናቂ ወረቀት ስላገኘሁ ነበር" አልኩት።

"እንዴት?" አለ ግራ በመጋባት።

"ወረቀቱ ስታየው ከላዩ ላይ ምንም የተጻፈ ነገር የለውም።"

"ታዲያ እርሱ ምን ያስደንቃል? ማለቴ አልገባኝም? ይቅርታ
እንግዲህ" አለ ከእፌ ላይ ነጥቆኝ ለነገሩ እየተጣደፈ።

"ልክ ነህ ሚስተር አንቶን፣ እኔም መጀመሪያ አልተደነቅሁም
ነበር። ለምን ባዶ አሮጌ ወረቀት ያስቀምጣሉ ብዬ አስጎብኝዬን
ሰጠይቀው ነበር አስገራሚው ነገር የተከሰተው" አልኩት።

"እንዴ! ምን አደረገህ?" አለ እየተጨነቀና ለመስማት እየቸኮለ።

"አይ ምንም አላደረገኝም" አልኩ በሁኔታው ፈገግ ብዬ፣ "ብቻ ነገሩ
ያልጠበቅሁት ነገር ስለነበረ ነው። በጣም ይገርማል፣ ልክ ..."

"በጣም ይቅርታ ሚስተር ሲሳይ! በጣም አንጎሸኘኝ እኮ›› አለ እንደ
ማፈር ብሎ።

"ወረቀቱ ለካ ያልተጻፈበት አልነበረም"

"እንዴት? አሁንስ እኔንም ግራ አጋባኸኝ ሚስተር ሲሳይ" አለኝ
ፊቱን ቅጭም አድርጎ።

"ምን መሰለህ ሚስተር አንቶን፡- አስጎብኝው የሆነ የተለየ መብራት
አምጥቶ ሲያበራበት፣ ጽሑፉ ልክ በማይክሮስኮፕ እንደሚታይ
ነገር ጎልቶ ታየኝ። ለካስ በልዩ ቀለም በስውር የተጻፈበት ነበር"
አልኩት።

"ኧረ እባክህ? እንዲህ ዐይነት ድንቅ ነገር ያለው ሙዚዬም መሆኑን እንኳ እኔም አላውቅም ነበር" አለና እየተደነቀ፣ ወዲያው መልሶ "ታዲያ ይህ ምኑ ነው ወዲያው ወደ ሀገርህ ለመመለስ ያስወሰነህ?" አለኝ፣ አሁንም የቸኮልኩበትን ነገር ለማወቅ እየፈለገ።

"ጉዳዩ ቀደም ብሎ በአእምሮዬ የቤት ሥራ ሆኖኝ ከቆዬ የግል ጉዳዬ ጋር አንዳች መዛመድ ስለነበረው ብቻ ነው" አልኩት እንደ መተከዝ ብዬ።

"እኮ ምንድን ነው ሚስተር ሲሳይ? ለምን አትነግረኝም?" አለ።

የሚስተር ራምዚ አንቶን ጉጉት እየናረ በመምጣቱ አሳጥረዋለሁ ያልኩት ነገር እየተራዘመ ሲሄድ ቢተወኝ ብዬ፡-

"እንዲያው የባህል፣ የሥነ ልቡና፣ የትውፊትና የቋንቋ ልዩነት ስላለን ታሪኩ ላይጥምህ ይችላል ብዬ ነው እንጂ ብነግርህ የሚያስቸግር ነገር የለውም" አልኩት።

"አንድ ነገር ልንገርህ? አንተ የምትነግረኝ ነገር አባቴ በልጅነቴ ስለኢትዮጵያ የሚያወራኝን ስለሚያስታውሰኝ በአባቴ ፍቅር ነው የምሰማህ። እባክህ ዝም ብለህ ንገረኝ" አለኝ።

በረጅሙ ተንፍሼ ሳበቃ "ታሪኩ ረጅም ነው" አልኩና ‹ሳይት 09› ብለን ከሰየምነው አንድ የቤተ ክርስቲያን ደን ውስጥ ሳይንሳዊ ጥናት ለማካሄድ የሄደው ቡድናችን ከገጠመው ከመጀመሪያው አስገራሚ ፈተና አንስቶ ከአባ መዝገበ ሥላሴ እጅ ሦስት ዐይነት ዕፆችን ከሦስት ቦታዎች እንዳመጣ የታዘዝኩበትን የብራና ወረቀት ተቀብዬ እስከ ተለያየሁበት ጊዜ ድረስ ያለውን በአጭሩ ተረኩለት።

ሚስተር ራምዚ አንቶን ረጅሙን ትረካዬን በጽሞና ሲያዳምጥ ቆይቶ "በጣም ይገርማል!" ከአለ በኋላ ቀጠለና፡-

"ታዲያ ወረቀቱ ላይ ምን ዐይነት ዕፅ ነበር እንድታመጣ የጠየቁህ?" አለኝ።

"የሚገርመው ነገር የሰጡኝ የብራና ወረቀት ጉዳይ ነበር" አልኩት።

"እንዴት?" አለኝ ወደ እኔ ሙሉ ትኩረቱን አድርጐ።

"እንደነገርኩህ አባ መዝገበ ሥላሴ ከሚባሉት አባት እጅ የብራና ወረቀት ተቀብዬ ከጓደኛዬ ዶ/ር ክብረ በዓል ጋር ወደ ቤቴ ወደ ባሕር ዳር ስጓዝ ከፍተኛ ድካምና ጭንቀት ውስጥ ስለነበርኩ ብራናውን ገልጬ አላየሁትም ነበር። ከቤቴ ደርሼ ዕረፍት አድርጌ በማግስቱ በጠዋት ቢሮ ገባሁና ብራናውን ገልጬ ሳየው ገና መደነቅም መደንገጥም ወደቀብኝ" አልኩና በረጅሙ ተነፈስኩ።

"ለምን?" አለኝ።

"ብራናው ላይ የተጻፈው እንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ዮሐንስ ራእይ 22 ፡ 5 የምትለው ብቻ እንጂ ሌላው ባዶ ነበር" አልኩት።

"እንዴ! የዕፆቹና የቦታዎቹ ዝርዝርስ?" አለ በጉጉት።

"ከጥቅሱ በስተቀር ምንም ነገር የሚታይ ጽሑፍ አልነበረም" አልኩና ተነፈስኩ።

ትንሽ ሲያስብ ቆየና "ምናልባት ከተጠቀሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ውስጥ ተካቶ ከሆነስ?" አለ እርሱም የእንቆቅልሹ ተካፋይ እየሆነ ይመስላል።

"እኔም ገምቼ ነበር፤ ይሁንና ራእይ 22፡5 ላይ የተጻፈው እንዲህ የሚል ነው፡-

*‹ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይሆንም፣ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፣ ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ።›*

እርሱም እንዲረዳው ከሞባይሌ ላይ የተጫነውን መጽሐፍ ቅዱስ ከፍቼ ጥቅሱን አስነበብኩት።

"ምንም የዕፅ ወይም የቦታ ስም አያመለክትም" አለኝ።

"አዎን ልክ ነህ። ምናልባትም መታየትንና አለመታየትን ለመረዳት ከብርሃን ጋር በማያያዝ በፊዚክስ ሕግ መሠረት በመመራት እነርሱን ለማየት መሞከሬን በማስታወስ የእኔ እሳቤና መላምት ስሕተት መሆኑን ለማሳየት ከዚህ ዓለም ተፈጥሮና ከፀሐይ ብርሃን ውጭ በሆነ ዓለም እንደሚኖሩ ለማመላከት ይሆናል እንጂ ስለተሰጠኝ ትእዛዝ ግን የሚያግዝ አልነበረም" አልኩት።

"ግሩም! ከዚያስ?" አለኝ ሚ/ር አንቶን አገጩን እጁ ላይ እያስደገፈ።

"በአንድ በኩል በቶሎ ዕፆቹን ለይቼና ቦታዎቹን አውቄ ካላመጣሁ ዕድሜዬ እያጠረ መሆኑን በማወቄ፣ በሌላ በኩል ብራናው ላይ ተጽፎልሃል ማለታቸው ግራ መጋባቴን በመጨመሩ ትልቅ መረበሽና ውዥንብር ውስጥ ገባሁ" አልኩና በረጅሙ ተነፈስኩ።

"ምናልባት ፍንጭ ቢሰጠኝ ወይም ወደ ፊት የሚያራምደኝ መላ ያመጣልኝ ይሆናል ብዬ ዶ/ር ክብረ በዓል ለሚባል ጓደኛዬ ጉዳዩን አዋየሁት። ይህ ጓደኛዬ ግን በጣም የተረጋጋ ሰው ስለሆ በተለመደው እርጋታው ‹ምንድን ነው ያሉህ?› አለኝ"

"ዕዖቼን ከተጠቀሱት ቦታዎች ፈልጌ ካልያዝኩ በስተቀር በምንም መልኩ ተመልሼ እንዳልሄድ እንዲሁም በቸልተኝነት ብተወው እንደ ምንጣፍ ዕድሜዬ እየተጠቀለለ እንደሚቀርብ እንደነገሩኝ ነገርኩት። እርሱም በጽሞና ካዳመጠ በኋላ፡-

‹በእርግጥ ትእዛዙ የምትፈልገውን ነገር ለማወቅ የተሰጠህ የወደፊት ቅድመ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ምናልባትም በጥበብህ ምሥጢራቸውን ለመፍታት በመሞከርህ የተሰጠህ የውዴታ ግዴታ ወይም ቀኖና መሆኑ ግልጽ ነው› አለኝ ።"

"እኔም መልሼ ‹ዕድሜህ እንደምንጣፍ እየተጠቀለለ ወደ አንተ ይቀርባል ማለታቸውስ?› ስለው፡-

‹ወንድም ሲሳይ! በግልጽ ቋንቋ ለመናገር ይህን ነገር ለማሟላት አንድ ቀን በዘገየህ ቁጥር ከዕድሜህ ላይ አንድ ቀን ትቀንሳለህ ማለት ነው› አለኝ ኮስተር ብሎ" ብዬ ገለጽኩለት።

ሚ/ር አንቶን በጸጥታ ከቆየ በኋላ፡-

"ማንኛችንም ቢሆን በየዕለቱ የምንኖረው በየቀኑ ከሕይዎታችን አንድ ቀን እየቀነስን ነው" አለኝ፤ ለማረጋጋት ብሎ ይመስላል።

"አዎን! ማንም ሰው ከፊት ከፊት አንድ ቀን ከዕድሜው እየኖረ ከዘመኑ ርዝመት አንድ ቀን እየቀነሰ በተስፋ ይኖራል። የእኔ የሚለየው ግን ከሁለቱም ጫፍ በየቀኑ እየቀነስኩ በመሆኑ ዕድሜዬን በፍጥነት እያሳጠርኩ እንደሆነ ይሰማኛል አልኩት" ትክዝ ብዬ።

እርሱም ቀጠል አድርጐ "ለመሆኑ ለጓደኛህ ለዶ/ር ክብረ በዓል ብራናውን አሳይተኸዋል?" አለኝ።

"ብራናውን ዘርግቶ ሲያይ ፈገግ እያለ ‹አስደናቂ ነው› ብቻ ብሎ እንደመለሰልኝ አስታውሳለሁ" አልኩት።

“ጥበብን በጥበብ ለመብለጥ ያደረኩት ሙከራ ጥልቅ እሳቤንና

"በጣም ይገርማል! እኔም ገባኝ፤ ወረቀቱን በስውር ጽፈው ነው የሰጡህ ማለት ነው?!" አለኝ ጭንቅላቱን ወደ ላይና ወደታች እየነቀነቀ።

"አዎን! በጣም እርግጠኛ ነኝ። በስውር ጽፈው፣ ሞኝነቴን አግዝፈው፣ አላዋቂነቴን አስምረው እንደሰጡኝ ስለገባኝ ነበር ለመሄድ የተመኘሁት" አልኩት።

"ያለበትን ሁኔታ ለማመልከት በስውር ጽፈው ሊሰጡህ ያስባሉ ብሎ መገመት ምክንያታዊና አሳማኝ ይሆናል" አለኝ።

"ምንም ጥርጥር የለኝም። በቃ ትእዛዛቸው ምሁራዊ ብቃቴን ምናልባትም ሞራሌንና አካላዊ ብቃቴን ጭምር የሚፈትሽና አጠቃላይ አቅሜን እንድገነዘበው ሊያደርጉ ያሰቡ ይመስላል" አልኩት።

"ግሩም ነው!" አለና "በእውነት ቀናሁብህ" አለኝ።

"እንዴ! ምን የሚያስቀና ነገር አለው? እንዲያውም አሳዝናለሁ እንጂ" አልኩት

"ሚ/ር ሲሳይ በፍጹም አይምሰልህ" አለኝና በዝምታ ተዋጠ።

እኔ ደግሞ ባሕር ዳር ደርሼ ብራናውን ለማየት እንደገና ልቤ ይጋልብ ጀመር፣ አእምሮዬም ያኮበኩብ ያዘ። ከዝምታችን ተመልሰን ሌሎች ጉዳዮችን እያወጋን ከተማዋን ሲያስጐበኘኝ ልክ ለረጅም ጊዜ እንደምንተዋወቅ ጓደኞሞች ሁነን አምሽተን ማታ ከእራት በኋላ በማግስቱ ዱባይ ድረስ እንደሚሸኘን ነግሮ ሆቴሌ አደረሰኝ። እንቅልፍ በዐይኔ ሳይዞር እንዲሁ ስገላበጥ አድሬ በጠዋት ተነሣሁ።

ከቀጠሯችን ሰዓት ሚ/ር አንቶን መጣ። ከሥራ ባልደረባዬ ጋር ከሳፍሮን በተንጣለለው አውራ ጎዳና ላይ ዘመናዊ ካዲላክ መኪናውን ወደ ዱባይ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ያስጓራው ጀመር።

የእኔ ልብ ግልቢያ ግን ከመኪናው ፍጥነት በላይ ነበር።

ኤርፖርት ደርሰን ሻንጣችንን አውርደን ወደ ውስጥ ልንዘልቅ ስንዘጋጅ አንቶን መጀመሪያ የሥራ ባልደረባዬን ሞቅ ያለ የእጅ ሰላምታ አቅርቦ ከተሰናበተ በኋላ ወደ እኔ ጠጋ ብሎ እጆቹን ዘርግቶ ጥብቅ አድርጐ እቅፍ ካደረገኝ በኋላ፡-

"መልካም ዕድል እመኝልሃለሁ። በምንም ምክንያት ግን የታዘዝከውን እንደ ዕዳ አንዳትቆጥረው፤ ይልቁንም እንደ መባረክ አድርገህ ቁጥረው!" አለኝ።

"እሺ የእኔ ወንድም! ስላደረክልኝ መስተንግዶ በጣም አመሰግናለሁ" አልኩትና ሻንጣዬን እየጎተትኩ ወደ ውስጥ ልገባ ስል ድንገት፡-

'ወንድም ሲሳይ!" አለኝና ዘወር ስል፡-

እባክህ አንድ መልካም ነገር አድርግልኝ?" አለኝና ጠጋ አለ።

ምንድን ነው?" አልኩት ፈገግ ብዬ በአግራሞት።

ዐይኑሳኖቹን ስታገኛቸው፡-

*ከድንግል ማርያም ሀገር ከሊባኖስ የመጣው ራምዚ አንቶን ፈጣሪ በዚያች ቀን ምሕረት ያደርግልኝ ዘንድ አስቡኝ" ብሏል ብለህ ንገርልኝ አለኝ"።*

ግያዊ ዐይኖቹ እንባ ተሞልተው ስመለከት አንጀቴ ስፍስፍ አለ። ፍ አደረኩትና፡-

ነችንንም ያስቡን" አልኩት። የእኔም ዐይኖች በእንባ ሞላታቸውን ያወኩት የሥራ ባልደረባዬ፡-

ዴ! ከመቼ ጀምሮ የተፈጠረ ጓደኝነት ነው?" ሲለኝ ነበር።

# ምዕራፍ ሁለት

ከዱባይ ተመልሼ ባሕር ዳር ኤርፖርት እንደደረስኩ በፍጥነት ወደ ቤቴ ሄድኩ። ቤት ውስጥ በተገቢው መንገድ ሰላምታ እንኳን ሳላቀርብ ቆልፌ ካስቀመጥኩበት ኮመዲኖ ብራናውን አውጥቼ ዘረጋሁ። ያው ከላይኛው ጠርዝ መካከል ላይ ከተጻፈው ራእይ 22÷5 በስተቀር አሁንም ሌላ ነገር የለም።

አቡዳቢ እስከ ሄድኩበት ጊዜ ድረስ በተአምር ጽሑፍ ያመጣልኝ ይመስል ብራናውን ጧትም ማታም ሌሊትም ነቅቼ ሳየው እንደነበር አስታውሼ ፈገግ አልኩ። የሚገርመው ግን አቡዳቢ ሆኜ ካየሁት በመነሣት ወረቀቱ በስውር ተጽፎበት ይሆናል ከሚለው ፍንጭ በስተቀር በስውር ተጽፎ ቢሆን እንዴት ነው ፊደላቱን ካለመታየት ወደ መታየት ማምጣት የሚቻለው የሚለውን በደንብ አለማሰቤ ነው። እናም እንደ ‹አል አይን ብሔራዊ ሙዚዬም› በተለየ መብራት ከመጠቀም ውጭ በሌላ በምን ዘዴ እንደሚገለጽ አለመጠየቄን ሳስበው በቃ በጣም ስሜታዊና ግልብ፣ በቀላሉ የምደሰት፣ በቀላሉ የማዝን መሆኔን ተገነዘብኩ።

"የሆንኩ እንከፍ ነገር ነኝ" አልኩና በመዳፌ ግንባሬን ገጨት አደረኩት። ወዲያው አንድ ዘዴ ብልጭ አለልኝና ወደ ቢሮዬ ሮጥኩ።

ከበይነ መረብ /ኢንተርኔት/ ዘዴዎቹን ለመፈለግ ነው። ቢሮዬ ደርሼ በፍጥነት በሩን ብርግድ አድርጌ ስገባ ጸሐፊዬ ባልተለመደ ድርጊቴ ተገርማ፡-

"ደኅና መጣህ?" ምነው ደኅና አይደለህም?" አለችኝ።

"አ ይቅርታ! እንዴት ሰነበትሽ፤ ደኅና ነኝ፤ አስቸኳይ ጉዳይ ገጥሞኝ ነው" አልኩና ኮምፒውተሩን አስነሣሁ።

ቢሯችን ገመድ አልባ ፈጣን የበይነ መረብ አገልግሎት የተዘረጋለት ስለሆነ ኮምፒውተሩ ለሥራ ዝግጁ ሲሆን አብሮ የዚሁ አገልግሎት ወዲያውኑ ይጀምራል። ጐንበስ ብዬ ኮምፒውተሩ መስኩት የታችኛው ቀኝ ጠርዝ ላይ ስመለከት የበይነ መረብ ግንኙነት መቋረጡን የሚያመለክት የኤክስ ምልክት አየሁ።

"ኮኔክሽን የለም እንዴ?" አልኳት።

"ጠዋት ነበር፤ አሁን ተቋርጧል ማለት ነው" አለችኝ።

"አይ ቴሌ!" ብዬ ወንበር ላይ ደገፍ አልኩና የሚጨሰውን ጨጓራዬን የበለጠ አብሽቆ ጸጥ ለማድረግ "እባክሽ ቡና አስመጭልኝ" አልኳት። የቴሌ ኔትወርክ ለወትሮም ቢሆን ዓላማው ደንበኛን ማስደሰት ሳይሆን ማበሳጨት ይመስል ትንሽ ቆይቶ መስመሩ እንደተለቀቀና ኮምፒውተሩ ከበይነ መረብ ጋር እንደተገናኘ አመለከተኝ።

የመረጃ መፈለጊያውን ሞተር ከፈትኩና ‹የማይታዩ ጽሑፎች እንዴት እንዲታዩ ማድረግ ይቻላል› የሚሉ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮችን እያቀናጀሁ እንዲፈልግ አደረኩ። ከብዙ ሙከራ በኋላ በልዩ የብርሃን ኃይል ከመጠቀም በተጨማሪ የሎሚ ወይም የሆምጣጤ ጭማቂ ጽሑፉ ላይ በማፍሰስና በሞቃታማ ነፋስ በማድረቅ እንዲታይ ማድረግ እንደሚቻል ተረዳሁ።

ኮምፒውተሬንና ቢሮውን እንኳን ሳልዘጋ መኪና አስነስቼ ወደ ገበያ በረርኩ። ባሕር ዳር መኻል ከተማ የምግብ ሰብል፣ አትክልትና ፍራፍሬ ወደ ሚሸጥበት ተራ ሄድኩ። ከችኮላዬ የተነሣ መኪናዬን መሀል መንገድ ላይ አቁሜ ወደ አትክልት ተራ አመራሁ። መንገድ ዳር ድንች፣ ሽንኩርት፣ ሌላም ጉልት ከሚሸጡት መካከል አንዲት ልጃገረድ ሎሚ ደርድራ ተመለከትኩ።

“ሎሚው ይሸጣል የእኔ እኅት?” አልኳት።

“እወን ጋሼ፤ ብቻ አሁን ሎሚ ስለጠፋ ተወዷል። እና ...” ንግግሯን ሳላስጨርሳት ሁለቱን አነሣሁ።

“ያው ተወዷል... ምን ይደረግ? አንድ ብር ገብቷል” አለችኝ። ዐሥር ብር አወጣሁና መልስ ሳልጠብቅ ወደ መኪናዬ ሮጥኩ።

“ጋሼ ኧረ መልስ አለህ፣ ጋሼ ...”

ብሰማትም እንዳልሰማ ዝም ብዬ እሮጥኩ። በገንዘብ የማልገዛውና በየጊዜው እየተንሸራተተ ያለው እድሜዬን ለማቆም እንደምሮጥ እርሷ መቼ ገባትና። ዳገት ላይ ስትራኮ እያደረገ ያለን አሮጌ ኤንትሪ መኪና ለማቆም ጐማ ሥር ታኮ ለማድረግ አሮጌ ቱታ ለብሶ እንደሚኳትን አውታንቲ (ረዳት) የሆንኩ መሰለኝ።

ቤቴ ደርሼ ከአባ መዝገበ ሥላሴ እጅ የተቀበልኩትን ብራና ጠረንጴዛ ላይ በጥንቃቄ ዘረጋሁ። የባለቤቴን የጸጉር ማድረቂያ ሞቃታማ አየር እንዲያወጣልኝ አዘጋጀሁ። ሎሚውን በጣቶቼ

ጫን ጫን እያደረኩ ካለፋሁ በኋላ መሃል ለመሃል በቢላዋ ቆርጬ ብራናውን በጥንቃቄ መቀባት ያዝኩ። በደንብ በለመጪው ካረጠብኩ በኋላ የጸጉር ማድረቂያውን ሶኬት ላይ ሰክቼ ለማስነሣት ቁልፉን ስጫን ጸጥ አለ።

የፈጣሪ ያለህ! መብራት ሂዷል ለካ።

"ኡ ኡ" ብዬ መጮህ አማረኝ።

"አይ መብራት ኃይል! አይ ቴሌ!"

"የአባቴ አምላክ..." ብዬ የእርግማን መዓት ለማውረድ ሳስብ "ምን አሁን አሁን እኮ እርግማን ምርቃት፣ ምርቃትም እርግማን ሆኖአል" የሚል ሐሳብ ተሟገተኝ። እና ረግሜ መመረቅ አልፈልግም አልኩና ራሴን ይገር ቁጭ አልኩ። ሲያንቆራጥጠኝ ቆይቶ ከአርባ ደቂቃ በኋላ መብራት መጣ።

እንደገና ለመጪውን እያፈረጥኩ ብራናውን እስኪርስ ቀባሁ። ከዚያም በማድረቂያው ቀረብ ራቅ እያደረግሁ ማድረቅ ያዝኩ።

ትንሽ ቆይቶ ቢጫ መሳይ ቀለም ያላቸው ፊደላት መስመር በመስመር መታየት ጀመሩ። ልቤ በደስታ ዘለለ። መቀቱን እየጨመርኩ በሄድኩ መጠን ቁልጭ ያለ ጽሑፍ ታየኝ።

"ከቶ ለምን ይሆን ይህን ሁሉ ምሥጢርና ጥበብ ከእኛ የደበቃችሁት?!" አልኩኝ ይሰሙኝ ይመስል። ጽሑፉ ድጋሚ እንዳይጠፋብኝ በጥንቃቄ በሌላ ወረቀት ገለበጥኩ። ለማንኛውም ብዬ ደግሞ በአይፓድ ደጋግሜ ፎቶ ግራፍ አነሣሁት። ከዚያም በጥንቃቄ ብራናውን አጣጥፌ አስቀመጥኩና ወደ ዶ/ር ክብረ በዓል ደወልኩ።

"ወንድም ሲሳይ እንኳን ደኅና ገባህ!" አለኝ። ሁሌም ሲጠራኝ ወንድም ሲሳይ ብሎ ነው።

"አመሰግናለሁ" አልኩትና "አሁኑኑ ላገኝህ እፈልጋለሁ!" አልኩት ትእዛዝም ጭምር ነበር።

"በጣም ደስ ይለኛል፤ እንዲያውም የአቦካዶ ጭማቂ የሚጋብዘኝ ሰው እየፈለኩ ነበር" አለ።

"ግዴለም፤ ዛሬ ጭማቂ ሳይሆን እንዳለ ዛፉንም ግዛልኝ ብትል እገዛልሃለሁ" አልኩት።

"አሃ! ዱባይ የተገኘ ነገር አለ ማለት ነው?" አለ። የምንገናኝበትን ቦታ ተነጋግረን ወደዚያው አመራሁ።

ዶ/ር ክብረ በዓል እስካሁን በሥራና በትምህርት አጋጣሚ ከማውቃቸው ሰዎች ለየት ያለ ሰብእና ያለው ሰው ነው። መካከለኛ ቁመት ያለው ሲሆን የሰውነት ቅርፁ ቀጥ ያለና ቀጭን ነው። አፍንጫው ሰልካካና ወፍራም ከንፈር ያለው ሆኖ ፍንድቅ ብሎ ባይሥቅም ጥርሶቹ በአጋጣሚ ሲታዩ የወተት አረፋ ይመስላሉ። ጸጉሩ ግንባሩ ላይ በመጠኑ ገባ ገባ ያለ ሲሆን ከፊቱ ልጅነት ጋር የማይመጣጠን በዛ ያለ ሽበት አለው። በተረፈ ከላይኛው ከንፈሩ ላይና ከአጋጩ ላይ ከበቀለውም ሞላ ያለ ጸጉር በስተቀር ፊቱ ለስላሳና ፈገግታ የማይለየው የልጅ መልክ አለው። ዕድሜው እንደነገረኝ 40ዎቹ ውስጥ ነው።

ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በባዮሎጂ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪውን ከአገኘ በኋላ ለድኅረ ምረቃ ትምህርት ወደ አሜሪካ ተጉዞ ኦክላሆማ ስቴት ዩኒቨርሲቲ የማስተርስና የፒኤችዲ ዲግሪውን በማዕረግ ተቀብሏል። በባዮሎጂ ሙያ ለተወሰኑ ዓመታት በዚያው በኦክላሆማ ዩኒቨርሲቲ በፕሮፌሰርነት ሲሠራ ከቆየ በኋላ ወደ ሀገሩ መጥቶ መኖር በመፈለጉ ዩኒቨርሲቲው በአመቻችለት የምርምር

ፕሮጀክት ዕድል ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ባሕር ዳር መኖር ከጀመረ ሦስት ዓመታትን አስቆጥሯል።

የድኅረ ምረቃ ተማሪዎችን ማማከርና ዐልፎ ዐልፎ በባሕር ዳርና ጎንደር ዩኒቨርሲቲዎች ኮርስ ከመስጠት ባለፊ አብዛኛውን ጊዜ የሚያሳልፊው በመስክ የምርምር ሥራዎችን በመሥራት ነው። በዓመት አንድ ጊዜ ለአጭር ጊዜ ወደ አክላሆማ ዩኒቨርሲቲ ይሄዳል። ዐልፎ ዐልፎ ወደ ተለያዩ ሀገሮች የምርምር ሥራውን ለማቅረብም ይጓዛል። ከእኔ ጋር የተዋወቅነውም ሁለታችንም ካምፓላ ኡጋንዳ ላይ በተካሄደ የምርምር ጉባዔ ላይ በተገናኘንበት ወቅት ነበር። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በውጭ ሀገር ሲተያይ እንደሚያደርገው በፊገግታ ተጠራራንና:-

"እንደምን አለህ የእኔ ወንድም? ክብረ በዓል እባላለሁ" አለኝ።

"ደኅና እንደምን አለህ ሲሳይ እባላለሁ" አልኩት።

"እ" አለና ሙሉ ስሜን እስከ አባቴ ጠርቶ ሲያበቃ "እንተንማ በሥራዎችህ በደንብ ነው የማውቅህ። በአብያተ ክርስቲያንና ገዳማት ደኖች ላይ አይደል የምርመር ሥራ የምትሠራው?" አለኝ።

"አዎን ልክ ነው" አልኩት።

"የተወሰኑ ሥራዎችህን አንብቤአለሁ። ከሥነ ምህዳር ምልከታ አንፃር ተገቢ የምርምር መስክ ለይተሃል" አለኝ።

"ሞክሬአለሁ" አልኩት።

"እኔም እንዳንተው የባዮሎጂና የሥነ ምህዳር ባለሙያ ነኝ። በቅርቡ ነው ወደ ኢትዮጵያ መጥቼ መኖር የጀመርኩት። ልሠራ ያቀድኩትም እንደ አጋጣሚ አንተ በምትሠራበት የሰሜን ምዕራብ ክፍል ነው" አለኝ።

"በጣም ደስ ይላል፣ አብረን ብዙ እንሠራለን" አልኩት እጁን በደንብ ጨብጬው። በዚህ መልኩ ትውውቃችን ኡጋንዳ ጀምሮ ይኸው ወደ ባሕር ዳር ቀጥሎ ዋና አማካሪዬና ጓደኛዬ ለመሆን በቃ።

የመስክ ምርምር ሥራዎችን በጋራ እንሠራለን። ወደ ተለያዩ ሀገሮችም አብረን ሄደንም እናውቃለን። እየቆየን በሄድን ቁጥር በወዳጅነታችን በጣም ተጠቃሚና ደስተኛ በመሆኔ በተቻለኝ መጠን ቶሎ ቶሎ ላገኘው እጥራለሁ። ከእኔ ያገኘው መልካም ነገር ስለመኖሩ እርግጠኛ ባልሆንም እርሱም ዐልፎ ዐልፎ፡-

"ወንድም ሲሳይ ዛሬ አንገናኝም?" ይለኛል።

ይሁን እንጂ በሰንበት ቀንና በዐበይት በዓላት አግኝቸው አላውቅም፡ ተንቀሳቃሽ ስልኩም አይመልስም። የት ሄዶ እንደነበር በጠየኩት ቁጥር የሚሰጠኝ መልስ ግን፡-

"የማርያምን ብቅል ልፈጭ ሄጄ" ይለኛል።

"እንተ ደግሞ በበዓላትና በሰንበት ነው እንዴ የማርያምን ብቅል የምትፈጨው?" ስለው፡-

"ምናለበት ልጄ እኮ የበዓላት ጌታ ነው" ይላል።

የትም ቦታ ብቀጥረው ይመጣል። ሆቴል ወይም መናፈሻ ሄደን የማዘዙን ቅድሚያ ለእኔ ይሰጣል። ከዚያም እኔ ያዘዝኩትን "ጥሩ ምርጫ ነው" ይልና እርሱም ያዝዛል። ማንኛውም መጠጥ ሲቀርብለት እምቢ አይልም። ብቻ ግን ከአንድ በላይ አይጠጣም። ከደገመ ንጹሕ ውኃ ነው ማለት ነው። እንዲህ የሚል የተለመደ አባባል አለው፡

"Take always not more than one!" መርሑን ብወድለትም እንዳለ ለመውሰድ ስለቸገረኝ እኔ ደግሞ "Take always not more than two!"

ብዬ ከአቅሜ ጋር አገናዝቤ መመሪያዬ ለማድረግ ሞክሬአለሁ።

መሸቀርቀርና መብለጭለጭ አይወድም። ይሁን እንጂ በአግባቡ ታጥበው የተተኮሱ ልብሶችን ይለብሳል። የንተበና የወየበ ልብስ የለውም። ንጽሕናውንም ይጠብቃል። እናም ሁልጊዜ አብረውት ለመሆን የማይከብድ የማይቀል ሰው ነው። ስለሃይማኖት ብዙ አያወራም። ድርጊቱንና ፍልስፍናውን ላስተዋለ ግን በጥብቅ የሃይማኖት መርሕ የሚኖር ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

መተዋወቃችን እየጠነከረ ሲሄድ ቤቱ ወሰጄ ከባለቤቴና ከልጅቼ ጋር አስተዋወኩት። በደስታና በአክብሮት የተቀበለው ይመስላል። አንድ ቀን ከእኔ ቤት ቆይተን ስሸኘው፡-

"እኔ እምልህ ዶ/ር ክብረ በዓል አንተስ መቼ ነው ባለቤትህንና ቤተሰብህን የምታስተዋውቀኝ?" አልኩት።

ፊገግ አለና "የመልስ ምት መሆኑ ነው?" አለኝ።

"አንተ አትቀልድ!" አልኩት።

"እሺ፤ እንዳልክ፤ በቅርቡ አስተዋውቅሃለሁ" አለኝ።

በሚቀጥሉት ቀናት ጥያቄዬን ለማስቀየስ ቢሞክርም በውዴታ ግዴታ ወደ ቤቱ ወሰደኝ። ጣና ሐይቅን እንዲያሳዩ ተደርገው ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ባሠራቸው አፓርትመንቶች ውስጥ ሁለተኛ ፎቅ ላይ ወደሚገኝ መኖሪያ ቤቱ ወሰደኝ።

ቤቱ መኝታ ቤትም ሳሎንም ሆኖ የሚያገለግል አንድ ክፍል፣ ጣናን በደንብ የሚያሳይ በረንዳ ፣ መታጠቢያ ቤትና አንድ መዝጊያ የሌለው ዘመናዊ የምግብ ማብሰያ ክፍል አለው። ክፍሉ ሲከፈት ደስ የሚል መዐዛ ያለው ሲሆን አንድ ጥግ ላይ አንድ ሜትር ስፋት ያለው በአግባቡ የተነጠፈና የራስጌ መብራት ያለው አልጋ፣

መጻሕፍት በአግባቡ የተደረደሩበት ሽልፍ፣ አንድ የተቆለፈ የልብስ ማስቀመጫ የሚመስል ቁም ሳጥን፣ መኻል ወለል ላይ አራት ወንበሮች ያሉት ሰፊ ጠረንጴዛ ይታያሉ። በአንድ ጥግ ደግሞ የሙያ መሣሪያዎቹ በሥርዐት ተደርድረዋል። ከዚህ በተቃራኒው ባለ ጥግ ደግሞ የሚያምር የአበባ ምንጣፍ ግድግዳውን ተጠግቶ ወለል ላይ ተነጥፏል። በቃ! ከዚህ የተረፈ ቤቱ ዕቃ የለውም፤ ቴሌቪዥን፣ ሶፋ ምናምን የለም።

ቤቱ ውስጥ ብቻውን እንደሚኖር ወዲያው እርግጠኛ ሆንኩና፡-

"ባለቤትህን ይዘኻት አልመጣህም እንዴ?" አልኩት በመገረም።

"አላመጣኋትም?" አለ ወደ ወጥ ቤት እየገባ።

"እዚህ ለመኖር ወስኛለሁ አላልከኝም ነበር?"

"አዎን ብየሃለሁ።"

"ታዲያ ተለያይታችሁ እንዴት ይሆናል?" አልኩ።

ዝም ብሎ ወጥ ቤት ውስጥ ይንጎዳጎድ ጀመር።

"ማምጣት አለብህ፤ አለበለዚያ ከባድ ነው!" አልኩት።

ፈገግ አለና "አትመጣም!" አለኝ።

"እንዴት? ለምን?" አልኩት።

"ስለሌለች ነዋ" አለ አሁንም ፈገግ ብሎ።

"እንዴት ነው ስለሌለች ማለት?"

"ሚስት ስላላገባሁ ሚስት የለኝም፤ ስለዚህ አትመጣም" አለ አሁንም ፈግግ ብሎ።

"ታዲያ እንዲህ ብለህ አትናገርም በግልጽ" አልኩት እንደመቆጣት ብዬ።

"እንዴ! መጀመሪያ ነገር አንተ ማግባቴን መቼ ጠየከኝ? ቢቃ ዕድሜዬን ብቻ አይተህ፣ ማግባት እንዳለብኝ ፈርደህ፣ ሚስት እንዳለኝ አሰረግጠህ፣ ልተዋወቃት ትለኛለህ" አለ በሙሉ ፈገግታ።

"እንዴት በዚህ ዕድሜህ ትቀልዳለህ ብዬ ላስብ?" አልኩት።

"አለማግባት መቀለድ ነው እንዴ?"

"ታዲያ ዕድሜህ ቆሞ ይጠብቅሃል መሰለህ?"

"አርጅቼ ሚስት እንዳላጣ ብለህ ነው?"

"ባዮሎጂስት አይደለህም እንዴ? ማግባት እኮ ልጅ መውለድ፣ ማሳደግ፣ ለቁም ነገር ማብቃትን ያካትታል። እናም አቻ የሆነችና ወላድ ሚስት ለማግኘት ዕድሜ ወሳኝ ነው" አልኩት።

"ዕድሜ ችግር የማይሆንባት ሚስት እፈልጋለሁ አትጨነቅ" አለ ኮስተር ብሎ።

"እንዴት?"

"በቃ! ሳረጅ የበለጠ የምመቻት ሚስት አገኛለሁ አትሰጋ" አለ።

"በል አትቀልድ፤ ለባለቤቴ ላማክራትና ክብሯን የጠበቀች በዕውቀት የምትቀራረቡ እጎት ፈልገን እንድርሃለን፤ራስህን አዘጋጅ" አልኩት።

"እንደ ፊታውራሪ መሸሻ አንገቴን ይዘህ በግድ ልትድረኝ ነው መሰል" አለና "ለማንኛውም አያስፈልግም" አለ ኮስተር ብሎ።

"እንዴ ለምን?"

"ለእኔ የምትሰማማኝን ሚስት መርጬ ጨርሻለሁ"

"ይሄ ግሩም ነገር ነው። እና ምን ትጠብቃለህ?"

"ጥሩ ባል መሆን መቻሌን አስካረጋግጥ ድረስ።"

"መቼ ነው ያሰብከው" አልኩ በጉጉት

"ግዴለም፤ ቀኑ ሲደርስ እነግርሃለሁ እስከዚያው ግን ይህ ርእስ እስከ ዝርዝር እጀንዳው በዚሁ ይዘጋ" አለና በእጁ አፉን በመሸርገጊያ መልክ ዘግቶ አሳየኝ።

ከዚያ በኋላ ስለትዳርና ሚስት አንስቼበት አላውቅም። የመ.ያ ሥራ ካልሆነ በስተቀር የግል ኑሮውን ለመጠየቅም እፈራለሁ። እኔ ግን ሁሉንም የከበደኝን ነገር ለሚስቴ ከሚነገረው ውጭ እዘክዝክለታለሁ።

ንግግሩ ከባድ ነው። ጎሊናህን የሚሸረካከት ነገር ሊናገርህ ይችላል። ግን በቁጣና በግልፍተኝነት አይደለም። ምክንያታዊ ሆኖ ስለሚናገር የመሟገት አቅም ይሰልባል። ሲጽፍም ጠንከር ያሉ ቃላትን ይጠቀማል። ለምሳሌ፡- አንድ ጊዜ በእርሱ ፕሮጀክት ወጪ የሩዋንዳን የዐፈርና ውኃ ጥበቃ ሥራ ልምድን ለመጎብኘት ሄደን ስንመለስ አውሮፕላኑ አዲስ አበባ ለማረፍ ሲሞክር የትራፊክ መጨናነቅ እንዳለ ስለተነገረው ይህንኑ ለተሳፋሪው ገልጾ አዲስ አበባ ሰማይ ላይ ይዞር ጀመር። ዶ/ር ክበረ በዓል ማስታወሻውን አውጥቶ መፃፍ ጀመረ። አውሮፕላኑ ዐርፎ ሆቴል ይዘን በረንዳ ላይ ዐረፍ እንዳልን መጻፉን ቀጠለ።

"በል አቁም አትደብረኝ!" አልኩት።

"አይ ብዙ አይደለም፤ ልቋጨው ብዬ ነው" አለና ትንሽ ቆይቶ እውነትም ማስታዎሻውን አጥፎ አስቀመጠ። ሳብ አድርጌ የጻፈውን አነበብኩት።

እንዲህ ይላል፡-

"አይ አዲስ አበባ!

ባሕታዊ ነኝ ባይ ከዲጄ ጋር፣

የሚያናፋ ሀብታም ከመናጢ ደሃ ጋር፣

ቀማኛ ከለጋስ ጋር፣

ማይም ከምሁር ጋር፣

ቪላ ከጎጆ ቤት ጋር መሳ ለመሳ ማኖር የቻልሽ ምትሐታዊት ከተማ።

ቆሻሻና ፅዳት፣ ዳንስና ሱባዔ፣ ዘፈንና ሙሾ፣ ትዕግስትና ትዕቢት ጎን ለጎን አድርገሽ ምሥጢር የተደባለቀብሽ እንቆቅልሽ ከተማ!

መንታ ልጆች ወልደሽ አንዱን ክንድሽ ላይ አንተርሰሽ ፍትፍት እያዋጥሽ፣ ሎሽን እየቀባሽ ሰታቀማጥይው፤ ሌላውን ልጅሽን ደግሞ ከቅርጭጭታም እግርሽ በታች ጥለሽ የመሶብ ጥራጊ እንኳን ስትነፍጊው ቅር የማይልሽ ጉራማይሌ ከተማ!

ለታናናሽ እኅቶችሽ ርኅራኄ የሌለሽ!

ከቀበሌ እስከ ፓርላማ፣

ከቲያትር ቤት እስከ ግብርና ሚኒስቴር፣

ከወሀኒ ቤት እስከ ቆንስላ ጽ/ቤት፣

ከእህል ጎተራ እስከ ባሩድ ጎተራ፣

ከላንቲካ እስከ ፋብሪካ፣

ካባጃጅ እስከ ባቡር፣

ከማዕከላዊ አስከ ብሔራዊ ሁሉንም ልያዝ ባይ፣ ሁሉንም ለእኔ ባይ ስስታም ከተማ!

እንደ ስምሽ በየቀኑ የምታብቢ ቢሆንም የአበባሽ መዐዛው ከኢትጵያዊነት ይልቅ ምዕራባዊነትን ሲያውድ፣ ከቻይና እስከ ዱባይ፣ ከአውሮፓ እስከ አሜሪካ እየቃረምሽ የተለቀለቅሽው የዘመናዊነት ቅባት ፊትሽን አብልዞ ጠረንሽን ሳያከረፋው ፈጣሪ ማስተዋሉን ይላክልሽ። የተገባሽ የእናቴ የወገቧ መቀነት የራሷ ላይ አክሊል ትሆኝ ዘንድ!" ይላል።

በጣም ተገርሜ "አዲስ አበባን አትወዳትም እንዴ?" አልኩት

"ለምን እንደዚህ አልክ? ይህ ጽሑፍ የጥላቻ ይመስላል እንዴ?" አለኝ።

"እኔ እንጃ ይመስላል" አልኩት።

"አዲስ አበባን የምጠላበት ምክንያት የለኝም። እንዲያውም በምኞት ከምታስተናግዳቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ነኝ። በውስጧ መኖር ብፈልግ ድሎትን የምትነሳኝ አይመስለኝም" አለ።

"ታዲያ ለምን እንዲዚህ ጻፍክ?" አልኩት።

"አዲስ አበባ በጣም ታስገርመኛለች፤ ታሳዝነኛለችም። እናም ስሜቴን ነው የጻፍኩት። ከዚህ በላይ ግን ለጊዜው ላብራራልህ አልፈልግም" አለኝና ማዶ ማዶ ያይ ጀመር።

# ምዕራፍ ሦስት

በተቀጣጠርንበት ቦታ ስንገናኝ ዶ/ር ክብረ በዓል ጥብቅ አድርጐ አቀፈኝና፡-

"ወንድም ሲሳይ! ከዚህ ሆኜ አንተ ወደ ውጭ ሀገር በሄድክ ቁጥር የሆነ አካሌ ተቆርጦ የሄደ ይመስለኛል" አለኝ።

"እንዴ በዚያው ብቀር እንዴት ልትሆን ነው?" አልኩት ወንድማዊ ፍቅሩ አንጀቴን እያንሰፈሰፈው።

"እንጃ! ብቻ መጥቼ አንጠልጥዬ የማመጣህ ይመስለኛል" አለኝ እየሣቀ

"ይልቅ ደስ ብሎኛል" አልኩና እጁን ጠበቅ አድርጌ ጨብጬው አወዛወዝኩት።

"ምን ተገኘ?" አለኝ።

“የዚያን የብራና ምሥጢር ፈታሁት እኮ” አልኩት።

“እውነት?” አለኝ ፊቱ እየበራ።

“አዎን ፤ በስውር ቀለም ነበር የጻፉት።”

“ለመሆኑ በስውር መጻፉን እንዴት አወቅህ?”

በአቡዳቢ ጉብኝቴ ወቅት ፍንጭ እንዳገኘሁና በዚያ ተምርኩዤ እንደፈታሁት ስነግረው፡-

“ምን ዐይነት ፍንጭ?” አለኝ።

“ምሥጢር ነው” አልኩት ፈገግ ብዬ።

እርሱም ፈገግ ብሎ “ምሥጢር መቋጠር ተጀመረ እንዴ?!” አለና “ከምር በዝርዝር እንደትነግረኝ እፈልጋለሁ” አለኝ ኮስተር ለማለት እየሞከረ። አስከትሎም “ዱባይንና አካባቢውን እንዴት እንዳገኘኸውና ትዝብትህ ምን እንደሆነም መስማት አፈልጋለሁ” አለ፤ እኔን ለመገምገም እየተዘጋጀ በሚመስል ሁኔታ።

“መቼም አንተ ስለ አዲስ አበባ ባለፈው እንደጻፍከው ዐይነት ነገር እንደማልነግርህ ታውቃለህ ፤ግን ስሜቴንና ገጠመኜን ልነግርህ ዝግጁ ነኝ” አልኩት።

“እንደፈለግህ አድርገህ ንግረኝ” አለ ወደ ኋላው የወንበሩ መደገፊያ እየተጠጋ።

“ዱባይ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ የደረስነው በሀገሩ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ነበር። አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያውን ቀደም ብዬ የማውቀው ቢሆንም ውበቱ አሁንም እንደ አዲስ ይማርካል። የሕንጻው መዋቅር፣ ከረጃጅምና ወፋፍራም ጌጠኛ ምሰሶዎቹ ጋር ሲታይ ኤርፖርት ሳይሆን ንጉሥ ያሠራው

የቅንጦት ቤተ መንግሥት ይመስላል። የፍተሻና ጉምሩክ ጣቢያውን ዐልፈን ወደ ውጭ ስንወጣ ሞቃታማው የዱባይ አየር እንደተለመደው ወበቁን ለቀቀብን። ከሥራ ባልደረባዬ ጋር ከተደረደሩት ታክሲዎች ተረኛውን ይዘን የሀገሪቱ ዋና ከተማ ወደሆነችው አቡዳቢ አመራን።

አቡዳቢ ከዱባይ ወደ 150 ኪሎ ሜትር ገደማ ትርቃለች። አቡዳቢ የተባበሩት ዐረብ ኢምሬትስ የፖለቲካና የባህል መዲና ስትሆን ዱባይ ደግሞ የኢኮኖሚ እንብርት ነች። የሀገሪቱ መንግሥት ሁለቱን ከተሞች በመሠረተ-ልማት ከማስተሳሰር ዐልፎ በተቋማት ግንባታ በማያያዝ ወደ አንድ ግዙፍ ከተማነት (ሜትሮ ፖሊታን ከተማ) ለመቀየር ዓለም አቀፍ ኤክስፖ አዘጋጅቶ በትጋት እየሠራ ነው። በዚህ መሠረት ትልልቅ የገበያ ማዕከላት፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ ሆቴሎችና ሪዞርቶች፣ የሕክምና ማዕከላት፣ የኪነ ጥበብ ሰገነቶችና ሙዚዬሞች፣ የምርምር ጣቢያዎችና ዩኒቨርሲቲዎች፣ ኤርፖርት እንዲሁም ቅንጡ የመኖሪያ ስፍራዎች ሊገነቡ ታስቧል። ያለው ማማሩ ብቻ ሳይሆን ባለራእይ ድንቅ ነው ያስብላል።"

ዐይን ዐይኔን እያየ ዘና ብሎ መስማቱ ምኞት ስለጨመረልኝ ሪፖርቴን በትረካ መልክ ቀጠልኩ።

"ከዱባይ እየወጣንና እየራቅን በሄድን ቁጥር የተከመረ ደረቅ አሸዋ ዐይን እስኪታክት ድረስ ሰማይ አድማስ ጥግ ተዘርግቷል። እያቆለቆለች በምትሄደው ጀንበር ሲታይ የራሱ የሆነ ውበትና መስህብ ቢኖረውም አንዳች ሕይወት ያለው ነገር የሚኖርበት ግን አይመስልም።

የተንጣለለውንና ማለቂያ የሌለውን የአሸዋ ክምር እያየን "እንዲያው ይህች ሀገር እንዴት ሆና ሀብታም መሆን ቻለች?" የሚል ጥያቄ አንስተን የየራሳችንን መልስ ስንሰጥ ቆየን። ያው የማይቀረውን ጥያቄ ደግሞ "እንዲያው ከቶ ኢትዮጵያ ሀገራችን ለምን ድሀ ሆነች?" ብሎ መጠየቁ ግድ ነበር። "መወለድ ጣጣ ነው" ይላል ያገሬ ሰው።

የተባበሩት ዐረብ ኢምሬትስ እንደ ሌሎች ዐረብ ሀገራት የነዳጅ ሀብት ያላት መሆኗ ብቻ ሳይሆን ያላትን ነዳጅ ተጠቅማ የኢኮኖሚ መሠረቷን አሥፍታለች። የነዳጅ ሀብቷን በጥንቃቄ በጤና ጥበቃ፣ ትምህርትና መሠረተ ልማት ላይ በማዋል የዓለምን ንግድና ኢንቨስትመንት ለመሳብ መሠረት ጥላለች። በአሁኑ ወቅት ከዐረብ ሀገራት መካከል የኢኮኖሚ መሠረቷን ከነዳጅ ውጭ በማስፋት ቀዳሚ ሆናለች። የጅአግራፊ አቀማመጧና የባለራእይ መሪዎቿ ትጋት ታክሎበት የዓለም የንግድ፣ የፋይናንስና የመዝናኛ ማዕከል ለመሆን በቅታለች። ኑሮን ለማሸነፍ ከሚኳትኑት ስደተኞች ጀምሮ ዓለም አቀፍ ቱጃሮች፣ ታዋቂ የሕክምና፣ የፋይናንስ፣ የንግድ ባለሙያዎችና አማካሪዎች፣ ስፖርተኞች ሀብት ለማካበት የሚሯሯጡባት እንዲሁም የሀገራቸውን ሕዝብ የሚዘርፉ ባለሥልጣናትና ተባባሪዎቻቸው የሚምነሸነሹባት ሀገር ነች።በተጨማሪም ዱባይ በተለይ የዓለም የአየር በረራ መተላለፊያ ማዕከል ሆናለች። በአጠቃላይ 9.2 ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርባት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1.4 ሚሊዮን ብቻ የሀገሪቱ ዜጐች ሲሆኑ ቀሪው 7.8 ሚሊዮን ጭንቅላቱንና ጉልበቱን ለመሸጥ ከአራቱም ማእዘናት የጎረፈ ሕዝብ ነው።

ከነዳጅ በስተቀር ይህ ነው የሚባል የተፈጥሮ ሀብት ሳይኖራት ዜጎቿን አንደላቃ የምታኖረው ትንሽዬ ሀገር ከከተሞቿ ወጣ ሲባል የሚንቀለቀል በረሓ ላይ የተጣደች የአሸዋ ገበታ ነች። አንድ ዛፍ ለማሳደግ ዐፈር ከሌላ ሀገር ማምጣት አለበለዚያም ንጥረ ነገር እየበጠበጡ ልክ ለበሽተኛ ከንድ ላይ እንደሚተከል ግሉኮስ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማጠጣት ግድ ይላል። ያም ሆኖ ከተሞቿ ጽዱ ብቻ ሳይሆኑ በአበቦች ያሸበረቁ አረንጓዴ ናቸው። በዚህ መካከል የኢትዮጵያን ተራሮች፣ ሜዳዎች፣ ዐፈሩንና ወንዞችን አስታውሶ በድርቅ የምትሳቀል ደሀ ሀገር መሆኗን ማሰብ በታ አልቅስ አልቅስ ያሰኛል።

ሳላስበው፡-

"እረ ተው ፈጣሪ! የብልጽግና መከፈቻውን ቁልፍ ስጠን? የት ይሆን የተደበቀው? ራስ ደጀን ተራራው አናት ላይ ወይስ ኦሞ ሸለቆ ውስጥ፣ ባሌ ተራሮቹ ላይ ወይስ አሚባራ መተሐራ ላይ፣ ሰላሌ ሜዳ ላይ ነው ወይስ ዋግኽምራ ሰሀላ ሰየንት፣ ከፋ ሚዛን ቴፒ ከጥቅጥቅ ጫካው ውስጥ ነው ወይስ ኦጋዴን አሳይታ ዱፍቲ ነው፣ ከቀዝቃዛው ስፍራ ጎጃም ጮቄ ደጋ ዳሞት ነው ወይስ ዐለት እንደ ሽሮ ወጥ ከሚንተከተከበት ኣርታኣሌ፣ ጣና ወይስ ሻላ ሐይቅ ሥር ነው፣ ዳዋ ገናሌ ሸበሌ ወንዝ ውስጥ ወይስ ሶፍሞር ዋሻ ጥግ፣ ጦሳ አምባሳል አድዋ ተራሮች ላይ ነው ወይስ ጋምቤላ ቤንሻንጉል ጉምዝ፤ የተቆለፈበትን ቁልፍ ያስቀመጥከበትን እባክህ ንገረን! እባክህ አሳየን!" እያልኩ ሳጉረመርም እንባዬ እየፈሰሰ እንደሆነ ያወኩት ይገርመሃል የሥራ ባልደረባዬ "ምን ሆነኻል?" ሲለኝ ነበር።

"እረ ደኅና ነኝ ትንሽ፤ አሸዋው አጥበረበረኝ መሰል" አልኩትና ጥቁር መነጽሬን አደረኩና እሮሮዬን ቀጠልኩ።

"ከየትኛው ገዳም ሱባዔ እንግባልህ? ደብረ ሊባኖስ፣ ዝቋላ፣ ደብረ ቢዘን፣ ሬማና ራማ፣ ምሁር ኢየሱስ፣ ሐይቅ እስጢፋኖስ፣ ዳጋ፣ ወይስ አባጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ ከየትኛው ደብር ቁመን ምሕላ እንያዝልህ? ተድባበ ማርያም ወይስ መርጡለማርያም፣ አክሱም ጽዮን ወይስ አራዳ ጊዮርጊስ፤ ወንድሞቻችንስ እውነት በመሰላቸው መንገድ ከየትኛው መስጊድ አዛን ይጥሩልህ፤ አል-ነጋሽ፣ ጀጎል፣ አንዋር ወይስ ሾኔ መስጊድ፤ ስንት ግዜ ሶላት ያድርሱልህ? ሰባቱ አጽዋማት አነሱህ ጌታ ሆይ? መራብ ለምደነዋል እንጨምርልሃለን። የወንድሞቻችን በቀን አምስት ጊዜ ሶላት ካነሰ እነሱም ይጨምራሉ ላለፈ ላገደመው ለወጣው ለወረደው ሁሉ ቁጭ ብድግ ማለት መስገድ መሰለፍ እንደሆነ ለምደነዋልና። ንገረን ጌታ ሆይ የምትፈልገውን!"

"በደላችን በዝቶ ተቀይመኸን፣ ተለያይተን ጉራማይሌ ሆነንብህ ለእኛ ለሕዝቦችህ የማትነግረን ከሆነ ከተራራው ጥግ እንቆይሃለን፣ ከመካከላችን ሙሴን አስነሣና ወደ ተራራው ጫፍ አውጥተህ ንገረው። የተባረከ በትር ስጠውና የድህነቱን ባሕር ከሁለት ከፍሎ ያሻግረን። ወይም ኢትዮጵያዊ ዳዊት አስነሣና ግርግር ሳንፈጥር እርስ በርሳችን ሳንገዳደል በባረክህለት ወንጭፍ ድህነትን ግንባሩን ይፍለጠው። ወይ ኢትያጵያዊ ኢያሱን አስነሣና በየዐሥር ዓመቱ እየተመላለሰ እንደ ዛር ውላጅ አሰጎርቶን የሚሄደውን ድርቅ ተመልሶ እንዳይመጣ እንደገባኦን ፀሐይ አቁሞ ያስቀረው"።

"እንዴት ውኃ ላይ ተኝተን በውኃ ጥም ስንሞት ዝም ትላለህ? እንዴት ውብ ሀገር ሰጥተኸን ስታበቃ ጐስቋሎች እንድንሆን ትፈቅዳለህ? ለዘመናት ባዕዳን በሀብቷና በልምላሜዋ ተማርከውና ጎምጅተው ጦር ሰብቀው ሊወሯትና ሊደፍሯት የቋመጡላትን ሀገር ጀግኖቿ አናስደፍርም ብለው በየተራራው በየሸንተረሩ ደማቸውን ያፈሰሱላትን አጥንታቸውን የከሰከሱላትን ውብ ሀገር በፈቃዳችን ትተን ለመሰደድ በባሕር በየብስ ስንንከራተት እንዴት ዝም ብለህ ታያለህ?"

"የራሳችንን ፊደል እንዳስቆጠርከን፣ የቀን፣ የዘመን መቁጠሪያ እንዳስጠናኸን፣ አክሱምን እንድናቆም፣ ላሊበላን እንድናንጽ እንዳስተማርከን፣ ቅኔ፣ ዜማ፣ ውብ ባህልና ሀገር እንደሰጠኸን ሁሉ እባክህ እንደገና የረሳነውን በአክሱም በላሊበላ ዘመን የነበረውን ሥራ መሥራትን አስተምረን። ሥራውን የሚመራ የሥራ ስልት የሚያውቅ ሙሴን ስጠን"።

"እባክህ! ቁስላችንን የሚቀረፉ ሳይሆን የሚያክም፣ ትናንት ጠማችንን አደርን ስንለው ዛሬም ድግሙ የማይለንን፣ ተቆነጠጥን ስንለው የማይኮረኩመንን፣ ከፋን ስንለው የማያስለቅሰንን፣ የምንፈራው እርሱም የሚፈራን ሳይሆን ሁላችን እንደ አባት የምናየው አንድ ሙሴ ስጠን። ሕዝቡን አስከትሎ በኢትዮጵያ ተራሮች፣ ሸለቆዎች፣ ሜዳዎችና ሸንተረሮች የተቆለፈበትን

ቁልፍ የሚፈልግ፣ የአድባራቱንና የገዳማቱን ቡራኬ የሚቀበል የአዛውንቶቹን የሸኾችን ምርቃት የሚያከብር፣ የምዕራብን ካፒታሊስት የምሥራቅን ሶሻሊስት ርዕዮት እንደወረደ ተግቶ ኑ ልጋታችሁ የማይል የዚህችን ድንቅ ሀገር ምሥጢር የሚፈታ አንድ ሙሴ ስጠን"።

"ላይበለጽጉበት ከቆላ እስከ ደጋ ምድር፣ ላይጠጡት የውኃ ማማ፣ ላያመርቱበት ለም ዐፈር፣ ላይከብሩበት ውብ ባህልና ቅርስ ሰጣሃቸው ብለው ሌሎቹስ ለምን ያሙሃል? እኛስ ሳታጐድልብን ለምን እናማርርሃለን?"

"በሰፊው መስታዎት ወደፊት እያየን ከመጓዝ ይልቅ በጠባቧ የኋላ መስታዎት አብዝተን እያየን ከኋላ ታሪካችን ጋር ግብግብ ገጥመን ከፊት ለፊት ያለውን ተስፋችንን ለማጨለም እንዳክራለን። ትንሽ የሄድን ሲመስለን ተንገራግጨን እንቆማለን ወይ ወደ ኋላ እንመለሳለን። የሠራነውን እናፈርሳለን፣ የገነባነውን እንንዳለን፣ ቁመን ያጨበጨብንለትን ቁጭ ብለን ለማየት እንጠየፋለን። በጭፍን እንደግፋለን፣ በደምሳሳው እንቃወማለን፣ ሰውን ወይ መልኣክ አለበለዚያ ሰይጣን እናደርጋለን። ሚዛናችንን ስተን እንንገዳገዳለን። ከአንድ ሙሉ ሰው ብልቶች ውስጥ ከዐይን ጆሮን አቅርበን፣ ከእግር እጅን አስበልጠን አድልዎ እንፈጽማለን። ከተወለድንበት መንደር ማዶ ካለው ጋራ ወዲያ የለውን ሰፊ ሀገርና ወገን መዋጀት አቅቶን ድክ ድክ እንላለን። ምነው ዝም አልከን?" እያልኩ በውስጤ እየተብከነከንኩ መጓዜን ስነግረው :-

"ምነው ለሁሉ ነገር ፈጣሪን ተጠያቂ አደረግከው?" አለኝ:: በጉዞዬ ወቅት አብሮኝ የነበረና ከግላዊ ውይይቴ ያነቃኝ ይመስል ደንገጥ ብዬ :-

"ታዲያ ፈጣሪን እንጂ ማንን ማማረር እችላለሁ? ባማርርስ ማን ይሰማኛል"አልኩት::

"እርሱም በል እሺ ተወው ዝም ብለህ ቀጥል" አለኝ::

"እንዲህ እየተብከነከንኩ ወደ ምሽቱ አካባቢ አቡዳቢ ደረስን። ቀደም ብሎ ከተያዘልን ሆቴል ዐረፍን። በወቡቁ የደከመውን ሰውነቴን በቀዝቃዛ ውኃ ተለቃልቄ ከእራት በፊት የመኝታ ክፍሌ ከሚገኝበት ስድስተኛ ፎቅ ላይ በመስኮት አቡዳቢን አየኋት። በጎብረ ቀለማት ያሸበረቁት ሕንጻዎቿና በብርሃን ጮርፍ የተሞሉት ሰፋፊ መንገዶቿ ብልፅግናዋን ያንቦገቡጋሉ። ለሠርግ የተዘጋጀ የአዳራሽ መድረክ ትመስላለች።

በማግስቱ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ጀምረን እስከ ቀኑ ዐሥር ሰዓት ተኩል ድረስ የሄድንበትን የምንሠራበትን ድርጅት በ.ዝነሰ ጉዳይ አሰልቺና ረጅም ድርድርና ውይይት ስናካሂድ ዋልን። በጣም ተዳክመንና ተሰላችተን ወደ ሆቴላችን አመራን። ከመመለሳችን በፊት የአንድ ቀን ዕረፍት ስለነበረን በጠዋት መጥተው አካባቢውን እንደሚያስጎበኙን ቃል ገብተውልን ተለያየን።

በማግስቱ ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን አስጎብኛችን የሚያምር ጥቁር ካዲላክ መኪና ይዞ ሆቴላችን ደረሰ። የሥራ ባልደረባዬ በጣም ድካም ተሰምቶት ስለነበር እዛው ሆቴሉ ውስጥ ማረፍ እንደሚፈልግ ስለነገረኝ ለጉብኝቱ ዝግጁ የነበርኩት እኔ ብቻ ነበርኩ።

ከአስተናጋጅ ኩባንያችን ከተላከው አስጎብኚ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ በድጋሚ "ራምዚ አንቶን እባላለሁ። ምንድን ነው መጎብኘት የምትፈልገው?" አለኝ በትሕትና በታጀበ ፈገግታ። ጥርት ያለ እንግሊዝኛ ይናገራል።

ሚ/ር ራምዚ አንቶን እንደነገረኝ ከሆነ በዜግነት የፈረንሳይ ፓስፖርት የያዘ ቢሆንም በትውልድ ግን ሊባኖሳዊ ነው። በቤሩት የፈረንሳይ ኤምባሲ ባልደረባ የነበሩት አባቱ የሊባኖስ የእርስ በርስ ጦርነት ሲጀመር ቤተሰባቸውን ጠቅለለው ወደ ፈረንሳይ ፓሪስ በማቅናታቸው አንቶን አብዛኛውን የወጣትነት ዕድሜ ያሳለፈው ፓሪስ ውስጥ ነው። ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛና ዐረብኛን አቀላጥፎ የሚናገረውና በ30ዎቹ የዕድሜ ክልል የሚገመተው አንቶን

አቡዳቢ ውስጥ የአንድ የፋይናንስ ተቋም ዓለም አቀፍ ግንኙነት ክፍል የሥራ ባልዳረባ ሆኖ እየሠራ ይገኛል።

አባቱ የግሪክ ኦርቶዶክስ ተከታይ በመሆናቸው ልጆቻቸውም በዚሁ መርሕ ተቀርፀው እንዳደጉ ይናገራል። ስለሆነም ከተገናኘንበት ለዓት አንስቶ ሳስተውል ጠባዩ ከአውሮፓዊነት ይልቅ መካከለኛው ምሥራቅ፣ ከፈረንሳያዊነት ይልቅ ሊባኖሳዊነቱ ያመዝናል።

ራምዚ አንዶን ራሱን ካስተዋወቀኝ በኋላ "የጉብኝት ምርጫህን ማወቅ እችል ይሆን?" አለ በድጋሚ።

ያው እንደምታውቀው ወደ ተለያዩ ሀገራት የመሄድ አጋጣሚ ባገኘሁ ቁጥር ለመጎብኘት የምፈልገው ብሔራዊ ሙዚዬሞችን ነው። ምክንያቴ ደግሞ ከሚታዩት ሰማይ ጠቀስ ፎቆች፣ ከተንጣለሉት መንገዶችና ከተቀላጠፈው የመገናኛና የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ከውስብስብ የምርምርና የትምህርት ተቋማቸው ጀርባ ምን መከራ እንደታለፈ፣ ምን ያክል መሥዋዕትነት እንደተከፈለ፣ ከየት ተነሥተው የት እንደደረሱ፣ ከዚህ ሁሉ ጀርባ አንቀሳቃሽ ሞተሮቹ እነማን እንደነበሩ በአጭር ጊዜ ለመረዳት አመቺው ስፍራ ሙዚዬሞች ስለሆኑ ነው። የሰለጠኑና ያደጉ አገሮች ደግሞ መረጃዎችንና ቅርሶችን በሚስብና በሚማርክ እንዲሁም ለመረዳት በሚያስችል መልኩ በፎቶ፣ በቅርፃ ቅርፅ ሞዴል፣ በተንቀሳቃሽ ምስል፣ በጽሑፍ በጥንቃቄ አደራጅተው ለህዝብ ክፍት ያደርጋሉ። በዚህ ልምዴ መሠረት "ከተቻለ ብሔራዊ ሙዚዬም ብጎበኝ ደስ ይለኛል" አልኩት።

"ምንም ችግር የለም" ብሎ ወደ ፋርስ ባሕረ ሰላጤ አቅጣጫ ነዳ። ወደ ባሕሩ እየተጠጋን ስንመጣ ወደ ውኃው ገባ ብሎ የሚያስደንቅ የኪነ ሕንጻ ውበት ያለው ግዙፍና ውስብስብ የሕንጻ ሞዴል እያመለከተ፡-

“ያ ወደፊት የሚሠራው ትልቁ ብሔራዊ ሙዚዬም ይሆናል። ‹ዛይድ ብሔራዊ ሙዚዬም› ይባላል። የተባበሩት ዐረብ ኤምሬትስ መሥራችና አባት በነበሩት በሼህ ዛይድ ቢን ሱልጣን ዛናህያን የሚጠራ ሲሆን የእሳቸውም መታሰቢያ እንዲሆን ነው” አለችና “ለአሁኑ ግን ወደ ሌላ ሙዚዬም ልውሰድህ ብሎ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሃምሳ ኪሎ ሜትር ተጉዘን በዘንባባዎች የደመቀች የበረሓ ገነት (Oasis) የሆነች ከተማ ደርሰን ወደ ‹አል አይን ብሔራዊ ሙዚዬም› አቀናን።

ሙዚዬሙ በበርካታ ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን ስብስቦቹም የበረሓ አደንና ጥበቃን፣ ሕዝብንና ቅርስን፣ ታሪክንና የማኅበረሰብ እድገትን፣ ሳይንስንና ትምህርትን፣ የእስልምና እምነትን ዘርፍ ይዘው የተደራጁ ናቸው። እነዚህ ስብስቦች በመካነ ጥናት ግኝቶች፣ በሥነ ጽሑፍና በበርካታ ቅርሶች ማስረጃነት ከቤተ መጻሕፍት ጋር የተሟላለት ነው። አጠቃላይ የሙዚዬሙን ይዞታ ከአስጎብኚው ገለጻ ከተረዳሁ በኋላ አንድ በአንድ እየተዘዋወርኩ በእርጋታ መመልከት ያዝኩ።

ታሪክና የማኅበረሰብ እድገት በሚለው ክፍል ውስጥ የዐረቡ ዓለም ፊደላት፣ ሥነ ጽሑፍና ሥነ ጥበብ በተለይም የኢምሬቶቹን በዘርፉ ያሳለፉትን ጉዞ የሚያስዳስስ ንዑስ ክፍል አካባቢ ስደርስ በርካታ የጥንት ዘመን ጽሑፎችን የያዙ ብራና መሣይ መጻሕፍት፣ ጠማሮችና ጥቅልል ድርሳናት ተቀምጠዋል። ከመካከላቸው ለጽሑፍ የሚጠቀሙባቸው ጥንታዊ ቀለሞች በተለያዩ ብልቃጦችና ቀንድ መሳይ ዕቃዎች ተደርድረዋል። አንድ ነገር ትኩረቴን ሳበው።

አንድ በዕድሜ ብዛት ጫፎቹ አካባቢ የተቆረማመጠ የሚመስል

ብራና መሳይ ወረቀት በልዩ ሁኔታ ተቀምጠ አየሁ። ከጐኑ ደግሞ ጥቁር ብልቃጥና ጥንታዊ ብዕር ተቀምጧል። ወረቀቱን ጠጋ ብዬ ሳየው ምንም ዐይነት ጽሑፍ ከላዩ ላይ የለም።

"ይህ ወረቀት እንደዚህ ሌጣውን በክብር የተቀመጠው ከተለየ ነገር የተሠራ መሆን አለበት" ብዬ ገመትኩ። ይሁንና የሆነ ጉጉት አደረብኝና "ለምን አልጠይቅም" ብዬ ጥግ ላይ ከቆሙት የሙዚዬሙ ባልደረቦች መካከል ወጣት ወደ ሆነው ጠጋ ብዬ፡-

"ይቅርታ! የሆነ ማብራሪያ ፊልጌ ነበር፤ መጠየቅ ይቻል ይሆን?" አልኩት በእንግሊዝኛ።

"ምንም ችግር የለም፤ ምን ልርዳህ?" አለኝ መልሶ የዐረብኛ ቃና ባለው እንግሊዝኛ።

እየመራሁ ወደ ወረቀቱ ወሰድኩትና "ይህ ወረቀት ከምን የተሠራ ቢሆን ነው እንዲህ በክብር የተቀመጠው?" አልኩት።

ፈገግ አለና "ወረቀቱ እንኳን እንደማንኛውም የጥንት ወረቀት ከፓፒረስ የተሠራ ወረቀት ነው" አለኝ።

"ታዲያ ምን የተለየ ታሪክ ቢኖረው ነው በዚህ ሁኔታ የተቀመጠው?" አልኩት።

"አስደናቂ ጽሑፍ ስለተጻፈበት" አለኝ።

እራሴን ተጠራጥሬ ጠጋ ብዬ ሳየው ምንም ጽሑፍ ከላዩ ላይ የለም።

"እንዴ! ለእኔ የሚታየኝ ምንም ዐይነት ጽሑፍ የለም። የት ነው አስደናቂው ጽሑፍ?" አልኩት ግራ በመጋባት።

"አስደናቂ ጽሑፍ የተባለውም ለዚህ ነው" አለ አሁንም በፈገግታ።

"እንዴት?" አልኩት ግራ መጋባቴ እየጨመረ።

"ጽሑፉ በስውር የተጻፈ ስለሆነ ነው" አለ።

"ምን? እንዴት?"

"አዎን! በዐይን ባይታይም ይህ ወረቀት ሙሉውን ታሪካዊ ጽሑፍ ይዟል" አለ።

"ይህ የማይታመን ነው" አልኩት አፌን በእጄ ይዤ

"አንዴ ጠብቀኝ" አለና በአሻጋሪ ካለ ቢሮ መሳይ ክፍል ውስጥ ገብቶ ውኃ ሰማያዊ ቀለም ያለው የሸንበቆ መብራት ይዞ መጣና ቁልፉን ተጭኖ አበራው። ወረቀቱ ላይ በአግድም አስጠግቶ ከላይ ወደ ታች ቀስ አድርጎ ሲያወርደው መስመር በመስመር ቁልጭ ያለ የዐረብኛ ጽሑፍ ታየኝ።

"በጣም ይደንቃል!" አልኩት።

"አዎን! በዚያ ዘመን እንዲህ ዐይነት ስውር የሥነ ጽሑፍ ቀለም ፈጥሮ በስውር መላላክ እውነትም አስገራሚ ነው" አለና "እንደዚህ የሚጻፉት እጅግ ምሥጢራዊ ደብዳቤዎችና ሠነዶች እንደሆኑ ይታመናል" አለኝ።

የመጨረሻውን ዓረፍተ ነገር እንደ እውነቱ ከሆነ በሙሉ ልቤ አልሰማሁትም። አእምሮዬ ውስጥ አንድ ትልቅ የጨለማ ክፍል ተከፍቶ አስደናቂ ብርሃን ገብቶ ወለል ብሎ የሚታየኝ ነገር ነበር።

"በጣም ይገርማል!" አልኩ በዐማርኛ ቀጠልኩና "ወይኔ!" አልኩ።

አስጐብኚዬ "ይቅርታ ምን አልክ? አልሰማሁህም" አለ በትሕትና።

"ምንም አይደለም። አመሰግናለሁ" አልኩትና እየተጣደፍኩ ወደ ውጭ ወጣሁ።

"የፈጣሪ ያለህ! እንዴት ያለሁት ደንቆሮ ኑሬያለሁ። አሁን እኔ የተማርኩ ነኝ ብዬ መናገር እችላለሁ?" እያልኩ በደስታም በመገረምም እየተብተከተኩ ይዞኝ የመጣውን አንቶንን መፈለግ ያዝኩ።

"እንዴት ሠሩልኝ?" እላለሁ ወዲያ ወዲህ እየተራወጥኩ።

ሚ/ር አንቶን አይቶኝ ኖሮ "ሚ/ር ሲሳይ እዚህ ነኝ፤ ጉብኝትክን ጨረስክ እንዴ?" አለኝ።

"እምን ጨርሻለሁ አመሰግናለሁ" ስለው፡-

"ሌላ ማየት የምትፈልገው ምንድን ነው?" አለኝ።

"አመሰግናለሁ። ማየት የምፈልገውን አይቻለሁ፤ አሁን የምፈልገው አንድ ነገር እንድትረዳኝ ነው" አልኩት በጥድፊያ።

"ምንም ችግር የለም? ምን ልርዳህ?" አለኝ።

"የመመለሻ ጉዞዬ ነገ ከሰዓት በኋላ ነው። እባክህ ወደ ዛሬ አስቀይርልኝ?" አልኩት። መቼም ከንፍ ቢኖረኝ ወይም ደመና የሚጠቅስ ኃይል ቢታደለኝ እንደ ቶማስ በደመና ሰረገላ ወደ ሀገሬ ብበር በወደድኩ።

ዶ/ር ከበረ በዓል ይህን ጊዜ ሣቅ አለና "እጅሬ መቸም ፍንጭ ያገኘህ ሲመስልህ ወዲያው ወደ ተግባር ካልገባህ አይሆንልህ አይደል" አለኝና "እሺ የኔ እብድ ከዚያስ" አለኝ።

ራምዚ አንቶን "ሚ/ር ሲሳይ አሁን እኮ ምሳ ሰዓት ነው። የቀረህ እኮ አንድ ሙሉ ቀን አይሞላም። ምነው ምን የሚያስቸኩል ነገር ገጠመህ? ቤተሰብ ደኅና አይደለም?" አለኝ እየተጨነቀ። "አይ እንደዚያ አይደለም፤ ሁሉም ነገር ሰላም ነው፤ ብቻ የምቸኩልበት ጉዳይ ኑሮኝ ነው" አልኩት።

"ካልክ ምን ቸገረኝ ብቻ የትኬት ማስቀየሪያ 300 ዶላር ያስከፍላ
አለኝ።

"ምንም ችግር የለም፤ ብቻ ሞክርልኝ" አልኩት። በልቤ ደግ
ወዳጄ የአንድ ቀን ዕድሜ በ300 ዶላር አይገኝም እላለሁ።

ስልክ በተደጋጋሚ ሞክሮ የአየር መንገድ ትኬት ቢሮን ተገናኘና
በዐረብኛ ብዙ ሲያወራ ቆይቶ፡-

"አዝናለሁ ሚ/ር ሲሳይ፤ ምንም ቦታ የለንም ነው የሚሉት" አለኝ።

"በቃ ተወው ምን ይደረጋል" አልኩትና ወደ አቡዳቢ ወደ
አረፍኩበት ሆቴል አደረሰኝ።

"ምሳ እዚሁ ሆቴል ወይም ደስ ያለህ ቦታ አብረን ልንበላ
እንችላልን። ዛሬ ቀኑን ሙሉ እናንተን እንዳስተናግድ ታዝዣለሁ
አለኝ በፈገግታ። በዚህ ወቅት ፍላጐቴ ብቻዬን መሆን ቢሆንም
አብሮኝ ያለው የሥራ ባልደረባዬም እንዲሁ ማረፍ የሚፈልግ
በመሆኑ ሁለታችንም መስተንግዶውን ስንተወው የሚሰጠው
ትርጉም ጥሩ አይሆንም ብዬ ስለገመትኩ፡-

"እሺ ለመስተንግዶው ክብር ይሰማኛል። አንዴ ክፍሌ ደርሼ
ልመለስ?" አልኩና ወደ ክፍሌ አመራሁ።

ክፍሌ ውስጥ ካለው ሶፋ ላይ ጭንቅላቴን በሁለት እጆቼ ይዤ
በአግራሞት፡-

"በስውር ጽፈው እንደሰጡኝ እርግጠኛ ነኝ። እንዴት ያሉ ረቂቃን
ናቸው? እንዴት አድርጌ አሳንሼ ገምቻቸው ኖሯል?" እያልኩ
እንደ እብድ እለፈልፍ ጀመር።

አንዳንዴ የአግራሞት ሣቅ እሥቃለሁ። ሌላ ጊዜ ደግሞ "እንዴት መጠርጠር አቃተኝ"

"እንዴት ዶ/ር ክብረ በዓልስ አልታየውም፤ ለነገሩ ቢታየውም ላይነግረኝ ይችላል" አልኩና አስታወስኩህ። በጣም የገረመኝ ደግሞ ስለዚህ ጉዳይ ባነሣሁብህ ጊዜ ሁሉ፡-

‹ይሄ ያንተ የምርምር ሥራ ነው። ከሰው ምርምር ደግሞ ዘው ተብሎ አይገባም› እያልክ በቀልድ መልክ የሸሸት ይሁን የአክብሮት ሊገባኝ በማይችል መልኩ የምትመልስልኝ ሁሉ ትዝ አለኝና እንደ እብድ አደረገኝ አልኩት።

ዶ/ር ክብረ በዓል እንደ መሳቅ እያለ አገጩን እጁ ላይ አሰደግፎ በትኩረት ያዳምጠኛል።

እኔም ትረካዬን ቀጠልኩ።

"እየተብተከተኩ ሳላስበው ብዙ ጊዜ እንደወሰድኩ ሲገባኝ "አይይ! ሰው አስጠበኩ" ብዬ በፍጥነት ወደ አንቶን ሄድኩ።

"ይቅርታ" አልኩና "አሁን አንተ ደስ ወደ ሚልህ ስፍራ ውሰደኝ" አልኩት

"በእኔ ምርጫ ትስማማለህ?" አለ ራምዚ አንቶን ፈገግ ብሎ። በጣም ትሑት ሰው መሆኑ ይታወቃል።

"እንደምደሰትበት ተስፋ አደርጋለሁ" አልኩትና ተያይዘን ወደ መኪናው አመራን። ከዚያም በፋርስ ባሕረ ሰላጤ በኩል ወደሚገኝ አንድ ትልቅ ሆቴል ወሰደኝ። ምሳ እየበላን ሳለን ሙዚዬሙ ሰዉጣ በነበረኝ መረበሽና በሁኔታዬ ተገርሞ አስጨንቆ ሲጠይቀኝ ጊዜ ሁሉንም ነገር ተረኩለት" አልኩት።

ዶ/ር ክብረ በዓል ቀበል አደረገና " አይ ያንተ ነገር! እንዴት እንደ ባዕድ ሳትቆጥረው ሁሉን ነገር ነገርከው?" አለኝ።

"በቃ ትሕትናው፣ ስለኢትዮጵያም ያለውን አክብሮት ሳይ ገዢ ምሥጢሩን ልሸሽገው አልቻልኩም። ደግሞስ ድንበር የሚያበጅ ምድራዊ ዜግነት እንጅ ሃይማኖት አይደለም" አልኩት።

"እርሱስ እውነትክን ነው" አለ ዶ/ር ክብረ በዓል።

"እና... ከሙዚዬሙ ባገኘሁት ፍንጭ ተነሰቼ ጽሑፉን ካለመታየት ወደ መታየት ማምጣት ቻልኩ" በዬ በድል ስሜት ገለጽኩለት። አስተያየቱን ሳየው ግን ትንሽ ቅር ያለው መሰለኝና፡-

"ምነው?" አልኩት።

"የምሥጢሩን መፍቻ ከምንጩ ርቀህ ከጅረቱ ላይ ማግኘትህ ገርሞኝ ነው እንጂ!" አለ።

"ምን ይደረግ! ምንጩማ በምሥጢር ሐረግ ተተብትቦ አይደል ይህን ያክል መከራ የማይ?" አልኩትና ድንገት ብሶቴ ገንፍሎ "ግን ለምን ያን ያክል ምሥጢራዊ መሆን አስፈለጋቸው? ለምን ይሰወሩብናል?" እያልኩ መብተክተኬን ስቀጥል፤

ዶ/ር ክብረ በዓል በተለመደው እርጋታው ውስጥ ሆኖ፡-

"በገጠር ዕፅዋቱ ተጨፍጭፎ፣ ተራራው ተራቁቶ፣ የውኃ ምንጮችና አፍላጋት ደርቀው፣ ዐፈሩ ተከልቶ፤ ከተማው በዘመናዊነት ሰበብ አመንዝራነትና ውንብድና ተሞልቶ፣ የከተማው ልማት ቂጥ ጥሎ ኩንብንብ ሲሆን፤ የሥራ ቦታዎች ትጋትና ቅንነት ርቋቸው ልግመትና ጥመት ተሞልተው፣ በውስብስብና ትብንትብ አሠራር ተጠላልፈው የጉመሮና ቆንጥር አጥር ሲሆኑ፤ ፈጠራ መከኖ ኩረጃ ሲነግስ፣ ውስጣዊ አቅምና ማንነት ተንቆ ወደ ውጭ ማማተር ሲበዛ፤ የወደፊቱን ቸል ብለን ካለፈ ታሪካችን ጋር ጦርነት ገጥመን በመንደር ተቧድነን መነታረክና መናናቅ እንዲያም ሲል

መጠፋፋት እንጂ መደማመጥና መከባበር ሲቀር፣ ጅብ እንግዳ ሆኖ ቁርበት ሲነጠፍለት፣ ቀበሮ ባሕታዊ ነኝ ብላ መቁጠሪያ ስታጠልቅ፣ ድመት መነኮስኩ ብላ ገዳም ስትገባ፣ ከዚህ ኮተት ከሞላበትና አዙሪት ከያዘው ኑሮ ራሳቸውን አላቅቀው ገለል ቢሉና በራሳቸው እውነት ቢኖሩ ምኑ ላይ ነው ጥፋቱ?" አለ።

"እኛስ? ወጣቱስ? አናሳዝናቸውም?" አልኩት በስሜት።

"እኛማ የመረጥነውን ሕይዎት እንኖራለን፣ የዘራነውን እናጭዳለን፣ ወደንና ፈቅደን ለመረጥነው ኑሮ፣ ለምንመካበት ፍልስፍናችን፣ ለምናምቧርቀው ርእዮታችን ለበረከቱም ለመከራውም ሐላፊዎቹ እኛው ራሳችን ነን" አለና "ለማንኛውም ምሥጢሩን ስለደረስክበትና ዕረፍት ስላገኘህ ደስ ብሎኛል" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ።

"አንድ ደረጃ ወጣሁ እንጂ ዋናው ትእዛዙ መች ተፈጸመ" አልኩት።

"ቢሆንም" አለ።

"እኔ እምልህ ዶ/ር ክብረ በዓል! በስውር በተጻፈልኝ ጽሑፍ ላይ ከተገለጹት ቦታዎችን ሁለቱን በአካል አንዱን ደግሞ ቢ.ያንስ በስም አውቃቸዋለሁ። የዕዮቹን ስም ግን ሰምቻቸውም አላውቅም" አልኩት። ገልብጬ የጻፍኩበትን ወረቀት አውጥቼ የሦስቱን ዕዮች ስም አነበብኩለትና፡-

"ከእነዚህ ውስጥ የምታውቀው ይኖር ይሆን?" አልኩት።

"በበርካታ ገዳማትና አድባራት እየተዘዋወርክ ጥንታዊና ነባር ዕፅዋትን ያጠናኸው አንተ ሳታውቀው እንዴት እኔ ላውቀው እችላለሁ?" አለኝ መልሶ።

"አይይ! በተለይ መድኀኒት ነክ የሆኑ ዕፅዋትን ከእኔ የበለጠ ላንተ የሠራህበት አይደለም እንዴ?" አልኩት ባለመስማማት።

"ቢሆንም እነዚህን ስሞች ሰምቼ አላውቅም" አለና ማዶ ማዶ እያየ "በዚህ ምርምርህና ፍለጋህ ውስጥ ከሎጅስቲክ ድጋፍ ውጭ ለመሣተፍ አቅሙም ዕውቀቱም ያለኝ አይመስለኝም" አለ።

"ኤዲያ! አንተ ደግሞ! አሁንስ አባ መዝገበ ሥላሴን ሆንክብኝ ብዬ ስመናጨክ ዶ/ር ክብረ በዓል ከጣራ በላይ ከት ብሎ ሣቀ። እንደዚህ ሲሥቅ አይቸው አላውቅም!

የሣቁ ምክንያት የገባኝ ግን ሰነባብቼ ነበር።

# የውዴታ ግዴታ

መርኬ ኬላረ ማሊኣ ቢያነቅኒው ኸያየውም

# ምዕራፍ ኻሁት

አስፈሪውንና አስደናቂውን ትእዛዝ ከተቀበልኩ በኋላ እጅግ መረበሽና መጨነቅ ጀመርኩ። ያም ሆኖ አጉል ደፋሩና ምሥጢር የሚያቃትተው ልቤ ያመጣብኝ በመሆኑ እንደተነገረኝ ከመፈጸም ውጪ አማራጭ አልነበረኝም።

የታዘዝኩትን ዕያች ዐይነትና የሚገኙበትን ስፍራዎች በብዙ ድካም በአስገራሚ ሁኔታ ከተጻፈው የብራና ማስታወሻ ላይ ከተረዳሁ በኋላ ለፍለጋው ከምሠራበት መሥሪያ ቤት የዐሥር ቀን ፈቃድ ወሰድኩ። ፍለጋውን ለመጀመር ሁሌም ለምርምር ሥራዬ መስክ ስወጣ መኪና የሚያከራዬኝ ወዳጄ ዘንድ ሄጄ 2H ላንድክሩዘር ተከራየሁ።

"አውላላ ሜዳ ላይ ቆሜ እንዳልቀር መኪናውን በደንብ ፈትሸልኝ። ቢበላሽ መጠገን ይቅርና ምኑ እንደተበላሸ እንኳን ማወቅ የምችል አይመስለኝም" አልኩት የመኪና አከራዬን።

መኪና በጥሩ ሁኔታ አሽከረክራለሁ ብዬ አምናለሁ። ነገር ግን የመኪና ውስጣ ውስጥ ዕውቀት የለኝም። ለነገሩ የመኪና የውስጥ አካል ይቅርና የራሴን የውስጥ የአካል ክፍሎችና ብልቶች እንኳን በደንብ የማውቃቸው አይመስለኝም።

እኛ ሰዎች ስለ ብዙ ውጫዊ ምሥጢር ለማወቅ እንጥራለን። ስለ ውስጣዊ የአካል ብልቶቻችን አገልግሎት፣ አሠራርና ችግር ሲገጥማቸው ምን እንደሚሰማን አናውቅም። ብቻ እዚህ አካባቢ ቆረጠኝ፣ ፈለጠኝ፣ ሳጨኝ፣ ፎረሸኝ፣ ወጋኝ፣ ጠዘጠዘኝ፣ በላኝ፣ አቃጠለኝ፣ ነፋኝ ወዘተ ከማለት ውጭ የጉበት ሥራው፣ የጣፊያ አገልግሎት፣ የኩላሊት ተግባር፣ የአንጀት የሥራ ድርሻ ምን እንደሆነ አንረዳም። ጉበት ሲቃጠል፣ ኩላሊት ሲበሰብስ፣ አንጀት ሲታጠፍ ምን ምልክት እንደሚሰጥ አናውቅም። ጤናችን ሲታወክ ብቻ የሐኪም ርዳታ ለማግኘት እንጥራለን። በውስጣችን የተሸከምነውን ብልት ጉዳት ከውጭ ያለው ሐኪም አውቆ እንዲነግረን ተስፋ እናደርጋለን። ሕይወት ለባለቤቱ ለራሱ ምሥጢር ናትና!

ማኅበረ ሥላሴ ገዳምን የመጀመሪያ የጉዞ መዳረሻዬ እንዲሆን ወሰንኩ። የገዳሙን መግቢያና ስለመንገዱ ለመጠየቅ ሳስብ አንድ ወዳጄ ገዳሙ ያሳተማትን ስለገዳሙ አመሠራረትና አጠቃላይ ይዞታ የምታትት ትንሽ መጽሐፍ አምጥቶ ሰጠኝ። ከመጽሐፏ ላይ ከተዘረዘሩት የስልክ ቁጥሮች መካከል ስሞክር አንደኛው ጠራልኝ።

አንድ ረጋ ያለ የወንድ ድምጽ።

"ሃሎ" አለኝ።

"ጤና ይስጥልኝ! ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ነው ?" አልኩኝ።

"አምን አባቴ" አሉ በእርጋታ።

"አባቴ እባክዎትን መረጃ ፈልጌ ነበር?"

"ምን ዐይነት መረጃ?" አሉኝ።

"እየውለዎት አባቴ! እኔ ሲሳይ እባላለሁ። ወደ ገዳሙ መጥቼ ከአባቶች ዘንድ መገናኘት እፈልግ ነበር። እንዴት እንደምመጣ ግን መረጃው የለኝም" አልኳቸው።

"ማን አሉኝ ስምዎትን?" አሉ።

"ሲሳይ እባላለሁ።"

"እ .... ደኅና ነው" አሉ። ስሜ አዲስ የሆነባቸው አይመስልም። ቀጠሉና

"አይይ! ታዲያ በታኅሣሥ ማለቂያ አይሻልም። አሁን መንገዱ በሙሉ ዳዋ ለብሷል። ዐልፎ ዐልፎም ገበሬዎች በእርሻ ዘግተውታል" አሉ። ምክንያቱም የደወልኩት ጥቅምት ወር አጋማሽ ላይ ስለነበረ ነው።

"አባታችን አማራጭ የለኝም። እስከዚያ ድረስ መቆየት አልችልም" አልኩና በውስጤ ደግሞ፡-

"ዐባይ ጉደል ብለው አለኝ በታኅሣሥ

የማን ልብ ይችላል እስከዚያው ድረስ"

አለ ያገሬ ሰው። በየቀኑ የዕድሜዬን ማጠር ማን በነገራቸው?" አልኩኝና፡-

"እባክዎትን በሚችሉት ሁሉ ይርዱኝ" ብዬ ተማፀንኳቸው።

"ኧረ ምን ችግር አለው አባቴ፤ ብቻ እንዳይንገላቱ ብዬ ነው እንጂ"

## አሉና

"እኔ አብሬዎት እንዳልንዝ ጎንደር ላይ ሥራ ታዝዤ ነው። እና ግንዳውኃ ከተማ ከመድረሳችሁ በፊት ‹ደረቅ ዐባይ› የምትባል ትንሽ ከተማ ላይ ተገንጥላችሁ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ነው የምትሄዱ። መኪና እስካስገባላችሁ ሞክሩና የቀረውን በእግራችሁ ሂዱ። ግንዳውኃ አድራችሁ ቀደም ብላችሁ ሂዱ። ‹ደረቅ ዐባይ› ላይ ቄሰ ገዳሙ የሚባሉ ሰው አሉ፤ እነግራቸውና ይጠብቋችኋል" አሉኝ።

"እግዚአብሔር ይስጥልኝ አባታችን። ማን ልበል እርሰዎትን ግን? የገዳሙ አበምኔት ነዎት?" አልኳቸው።

"ኧረ አባቴ እኔስ የገዳሙ ተላላኪ ረድ ነኝ። አባ ክንፈ ሚካኤል እባላለሁ" አሉኝ በፍጹም ትሕትና። አበምኔት የሚለውን መዓርግ በግድ የጫንኩባቸው ያክል እየተሳቀቁ።

በዚህ መልክ የጉዞ መስመሬን አስተካከልኩ። ቀደም ብዬ ወደ መተማ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ለመሄድ እንዳሰብኩ ለዶ/ር ክበረ በዓል ስነግረው እርሱም ወደ አካባቢው መሄድ እንደሚፈልግ ነግሮኝ አብረን የጉዞ ቀን በወሰንነው መሠረት ለጉዞ ተዘጋጅቷል። በዚህ መካከል የዶ/ር ክብረ በዓል አብሮ አደግ ጓደኛ የሆነ ኮንትራክተር እኔም ተዋውቄው ወዳጄ የሆነው ሺፈራው አብሮን ‹ጭልጋ አይከል› ድረስ እንደሚሄድ ነግሮን ሦስት ሁነን ከባሕር ዳር በጠዋት ተነሣን።

"እኔ እምላችሁ! በተለመደው በፎገራ አድርገን በጎንደር ከምንሄድ ለምን በቁንዝላ በኩል አንሄድም?" አልኳቸው።

"ለምን? አስፓልቱ አይሻለንም?" አለ ሺፈራው።

"አውቃለሁ። ግን በዚያ በኩል ሄጄ አላውቅም። ጣና ሐይቅን በስተምዕራብ አቅጣጫ ምን እንደሚመስል ባየው ብዬ ነው" አልኩኝ

"ግሩም ሐሳብ ነው" አለ ዶ/ር ክብረ በዓል። በዚህ መሠረት ጉዟችንን ከባሕር ዳር ከተማ በስተምዕራብ አቅጣጫ ጀመርን።

ከሃያ ኪሎሜትር በኋላ ግልገል ዐባይ ስንደርስ እጅግ ጭቃ ሆኖ አገኘነው። ከየማሳውና ተራራው ተሟጠ የመጣ ለምና ምርታማ ዐፈር የተበጠበጠበት በሶ ሆኗል።

ዶ/ር ክብረ በዓል ይህን ሲያይ፡-

"ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከምትልካቸው ምርቶች መካከል ቡና፣ አበባ፣ ጥራጥሬ፣ የቅባት እህሎች፣ ቆዳና ሌጦ እና የዐፈር ደለል ጥቂቶቹ ናቸው። ለሌሎቹ ምርቶች በውጭ ምንዛሬ የምታስከፍል ቢሆንም የዐፈሩን ደለል ግን በነጻ የምታበረክተው ነው። ምራቂ ማለት ነው" አለ በምፀት። ቀጥሎም፡-

"እንደ ሀገር ድክመታችን የሚጀምረው ለተፈጥሮ ሀብታችን በተለይም የሁሉ መነሻ ለሆነው ለዐፈርና ለውኃ የምንሰጠው ትንሽ ግምት ነው። በምዕራባውያን ሀገራት በተዘዋወርኩበት ሁሉ ወንዞቻቸው ዐልፎ ዐልፎ የኬሚካል ብክለት ቢያጋጥማቸውም የዐፈር ደለል ግን እንዲወስዱ በፍፁም አይፈቀድላቸውም። ስለዚህ ኩልል ያሉ ንጹሕ ናቸው። አለበለዚያ የኬሚካል ብክለት ቀለም ጥቁር ወይም ወደዚያ የቀረበ ቀለም ይኖራቸዋል እንጂ ቡናማ ወይም ቀይ ቀለም የላቸውም ።"

"ስለዐፈር መሸርሸር ካነሳሁ አይቀር የሚገርም መረጃ ልንገራችሁ" አለና "በአሁኑ ወቅት ከስሜን ምዕራብ ደጋማው የኢትዮጵያ ክፍል ብቻ 1.2 ቢሊዮን ቶን ዐፈር በየዓመቱ ከተራሮችና ከእርሻ መሬቶች በጎርፍ እየተጠረገ ወደ ጎረቤት ሀገራት እንደሚጓዝ ጥናቶች ያመለክታሉ። 1.2 ቢሊዮን ቶን ዐፈር በሁለት ሜትር ጥልቀት ብናከማቸውና ወደ ጎን ብናነጥፈው 1000 ካሬ ኪሎሜትር ወይም 100 000 ሄክታር ቦታ ያካልላል። ይህም በአሁኑ አወቃቀር በአማካይ አንድ ትልቅ ወረዳ ይሸፍናል።

ስለዚህ በየዓመቱ በወንዞቻችን አንዳንድ ወረዳ እናጣለን ማለት ነው። ይህ በድንበር መግፋት በጎረቤት ሀገር ቢወሰድብን ምን ያክል እንደሚያበሳጨንና ተደፈርን ብለን ወደ ጦር ግንባር በወጌ ለመሄድ እንደምንነሣሣ መገመት ይቻላል። እኛ ኢትዮጵያውያን ለዳር ድንበራችን የምናሳየውን ጀግንነታችንን ያክል ለመኸል ሀገር መሬት መጎሳቆል ሲሆን ግን ጅላጅልነታችን መታየቱ አልቀረም አለና እራሱን በቁጭት ከመኪናው ወንበር መደገፊያ ጋር መታ መታ አደረገው። በንግግሩ ብርታት ሁላችንም በዝምታ ተዋጥን።

በመካከል ጨዋታ ለመቀየር በማሰብ "ሻፊ ለምን ጉዳይ ነው ጭልጋ የምትሄድ አልኩት?" ሻፊራውን ።

"ምን እባክህ አንድ ጤና ጣቢያ ለመገንባት ጨረታ አሸንፌ ሥራውን አጠናቅቄ ቀሪ ገንዘብ ለማስለቀቅ ርክክብ ሲደረግ አንድ ግጣማ የሆነ ተቆጣጣሪ መሐንዲስ ነኝ ባይ አስቸገሮኝ ለእርሱ እየሄድኩ ነው። ከእናንተ ጋር ለመጫወት ብዬ ነው እንጂ የሳይት መሐንዲሴ ትናንት መኪናዬን ይዞት ሂዶ እየጠበቀኝ ነው" አለ።

"ምንድን ነው ችግሩ? በዲዛይኑ መሠረት አልሠራችሁትም እንዴ?" አልኩት።

ሻፊራው የማያሳምን ነገር ለረጅም ሰዓት ሲነገረን ቆየና "ባክህ ተወው ዱሮም ሀበሻ ምቀኛ ነው፤ አሁን ትንሽ ሳልሰው አፉን ይዘጋል" አለ።

ዶ/ር ክበረ በዓል የሻፊራው ንግግር ስላልተመቸው ማዶ ማዶ ሲያይ ነበር። በመካከል ‹ሀበሻ ምቀኛ ነው› ሲል ግን ፊቱ ልውጥውጥ አለና፡-

"ስማ ሻፊራው! በጣም ታሳዝነለህ! ያልዘራኸውን ስታጭድ፣ ያልከመርከውን ስትወቃ፣ ያላቦካኸውን ስትጋገር፣ ያላነጎትከውን ስትጐርስ ‹ለምን?› ሲልህ ‹ሀበሻ ምቀኛ ነው› ትለዋለህ እንጂ ሀበሻ

እኮ ፍትሐዊ ነው"።

"የሕፃኑን ጡጦ፣ የአረጋዊውን ከዘራ፣ የእሙሀይቷን ምርኩዝ ስትቀማ፣ የድሀውን ጉሮሮ ስትዘጋ ‹ለምን?› ሲልህ ምቀኛ ትለዋለህ! ስማ! ሀበሻ ፍትሐዊ እንጂ ምቀኛ አይደለም ።"

"ከጭንቅላትህ በእጅጉ የገዘፈ ባርኔጣ ደፍተህ፣ ከእግርህ የረዘመ ጫማ አድርገህ፣ ከትከሻህ የሰፋ ካባ ደርበህ ልትኮፈስ ስትሞክር እርግጥ አያዳንቅልህም ይልቁንም ሊሸረድድህ ይችላል። ያን ጊዜ ‹ተወው እባክህ ሀበሻ ድሮም ምቀኛ ነው› ትለዋለህ ።"

"አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቡን እንኳን በአግባቡ የማያስተዳድር ሰው የሀገር ሚኒስትር ሲሆን፣ ስሙን በአግባቡ መግለጽ የማይችል ሉዓላዊትና ጥንታዊት ሀገር እንዲወክል አምባሳደር ሆኖ ሲሾም፣ ምን ገዝቶ እንዴት ሸጦ ስንት አትርፎ እንዳደገ ሳይታወቅ በአቋራጭ የሀብት ማማ ላይ ሲቀመጥ፤ ‹እንዴ እንዴት ነው ነገሩ?› ሲል ‹ተወው እባክህ ዱሮም ታዳጊ ሀገር መፈጠር መከራ ነው› ትላለህ።"

"ጅማትህ እሰኪኮማተር፣ ሳንባህ እስኪወጠር፣ ተረከዝህ እስኪነቃ፣ ወዝህ እሰኪንቆረቆር እንደ ኃይሌ ተፈትለክ፣ እንደ ደራርቱ ሩጥና ክበር ማን ይመቀኝሃል? ደራርቱ ወርቅ ብትለብስ ጥሩነሽና መሠረት ሀር ቢያገለድሙ ማን ይቃወማቸዋል። ቀነኒሳ የወርቅ ዝናር ታጥቆ ቢዞር ኃይሌ በሕንጻ ላይ ሕንጻ በፎቅ ላይ ፎቅ ቢያቆም ማን ቅር ይለዋል? ማንስ ዐይኑ ደም ይለብሳል? አንተ ግን የሕዝብን ሀብት ዘርፈህ፣ የመንግሥትን በጀት ሞጭልፈህ፣ አየር በአየር ተንሣፈህ፣ በሀብት ለመንሳፈፍ ስትሞክር ‹ለምን?› ብሎ ሲጠይቅህ ‹ምቀኛ› ትለዋለህ።"

"እውነታው ግን ከግብጽ ብትመጣም በመልካም ሥራህ ‹አቦ አቡዬ› ይልሃል። ግፈኞች ታሪክህን ቢሰቅሉት፡-

"ተሰቀለ ቢሉኝ ዝናሩ ነው ብዬ

ለካስ በላይ ኖሯል ትልቁ ሰውዬ"

እያለ ስምህን ከመቃብር በላይ ያውላል ።"

"ሀበሻ ውለታ የማይረሳ የዘመን ነፋስ የማይወስደው ሚዛናዊና ፍትሐዊ ሕዝብ መሆኑን አትርሳ። ሞለጭላጫ ዘመነኛ ጥቂቱ የራሱን የረከሰ ምግባር ለመሸፈን የወጣበትን ባሕር ቢመርዘውም የውኃው ጣዕም የማይቀየር ጣፍጭ ነው" አለ አመልካች ጣቱን ወደ ላይ አንሥቶ እያወዛወዘ።

ዶ/ር ክብረ በዓል እንደ ደጋ በረዶ በአንዴ መዐቱን ሲያፈሰው ሺፈራው ግብረ-ገብነት የሚጠብቅ ሰው ባይሆንም ቀናና ገራገር ነውና በዶ/ር ክብረበዓል አልተቀየመም።

ዶ/ር ክብረበ ዓልና ሺፈራው አብሮአደግ ጓደኛሞች ሁነው ከአንድ ትምህርት ቤት የጨረሱ ቢሆኑም የሕይዎት ፍልስፍናቸውና መርሐቸው የሰሜንና የደቡብ ዋልታን ያክል የተራራቀ ነው። ሺፈራው በሲቪል ምሕንድስና ሙያ በውጭ ሀገር የተማረ ሲሆን የራሱ የኮንስትራክሽን ተቋራጭነት ድርጅት አቋቁሞ አጭር በሚባል ጊዜ ውስጥ ባለሀብት ለመባል በቅቷል። ከዶ/ር ክብረ በዓል ጋር የሚለያያቸው ጉዳይ ቢኖር ይኸው የሀብት ጉዳይ ነው። ለሺፈራው ገንዘብ እስካስገኘ ድርስ ማንኛውንም ስልትና መንገድ መጠቀም ብልኀነት ነው። ለዶ/ር ክብረ በዓል ደግሞ ሀብት ማግኘት ብቻ ሳይሆን ሂደቱም ከሞራልና ከሕግ አንጻር መታየት አለበት ባይ ነው። በብዙ ነገር የሚግባቡ ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ግን ክብረ በዓል ሺፈራውን ሁልጊዜ ይነቅፈዋል፣ እንዲያውም ስኬቱን ይጠየፈዋል ማለት ይቀላል።

"ሲሳይ ጠላቴ አንተነህ! ከዚህ አብሿም ደብተራ ጋር ይዘኸኝ የመጣህ። መርጌታ ዐይነኩሉ በልጅነቱ የሰጡት አብሾ ሳይበዛበት

አልቀረም መሰል ሜዳና ተራራ ሲያይማ "ጭራሽ ይነሣበታል" አለ ሽፈራው።

በዚህ ስንሣሣቅ ቆይተን ክብረ በዓል ድንገት "አቁም... አቁም" አለኝ። አንድ አርሶ አደር ከማሳው መኸል ያለች ቁጥቋጦ እየጨፈጨፈ አይቶ ነው።

መኪናውን በፍጥነት ለማቆም እየሞከርኩ እያለ በሩን ከፍቶ ዱብ አለና ወደ ገበሬው ሲሄድ፡-

"እንደ እኔ መስሎህ ብትሮህበትና ብዙ ብትፈላሰፍ በያዘው መጥረቢያ እግርህን እንዳያሳጥርልህ" አለው ሽፈራው።

ዶ/ር ክብረ በዓልም ዘወር አለና መልሶ፡- "ለአንተ ቢጤው ጥባቴ የሚሰጥ ሕክምና መራራ ክኒን እንዲያም ሲል ሰርጅካልና አምፑቴሽን ነው (ቀዶ ጥገናና ቆርጦ መጣል)። ለዚህ ምስኪን አርሶ አደር ግን እንደ ማሳጅ ያለ ነው አታስብ" አለ።

መቼም ንግግሩ ከእርሱ እይታ ጎን ለቆመ ቅቤ ሲያጠጣ በተቃራኒው ለቆመ ግን አጥንት ድረስ ዘልቆ ይጠዘጥላል።

እኔም የሥነ-ምህዳር ባለሙያ ብሆንም ዶ/ር ክብረ በዓል በተለይ ስለ ሥርዓተ ምህዳርና ብዝኃ ሕይዎት ሲናገር ጣልቃ መግባት አልፈለግም። ሙያውን የላይኛው የሳይንስ ጫፍ አድርሶ አወሳስቦ ማቅረብም ሆነ ምንም ግንዛቤ ለሌለው ቀለል አድርጐ ማቅረብ ተክኖበታል። እንዲያው በጥቅሉ ለሁሉም በልኩ እየሠፋ የማቅረብ ችሎታው ሁሌም በጣም ይገርመኛል። በአንድ ሙያ ውስጥ ያለን ሰዎች ከሙያ ባሕር አንዳንዶቹ በበርሜል ሲቀዱ የእኔ ቤጤ ደግሞ በቀዳዳ ጣሳ ይቀዳና መግለጽም መተግበርም ላይ ይውተፈተፋል።

ከአርሶ አደሩ ጋ እንደደረስን በትሕትና ሰላምታ ካቀረበለት በኋላ፡-

"ለምንድን ነው ዕዕዋቱን የምትጨፈጭፈው?" አለው በእርጋታ

"ምን ያረጋል? የነፍሳት፣ የአይጥና የአራዊት መሸሸጊያ ይሆ
እንጂ" አለ አርሶ አደሩ።

"እና ነፍሳትና አራዊቱ ቢኖሩ ምን ይጎዱሃል?"

"ኦሯ! ነፍሳትና አራዊት ደግሞ ምን ጥቅም አላቸው? የነሱ ቁረቢ
ደግም አይደል" አለ።

ዶ/ር ክብረ በዓል በረጅሙ ተነፈሰና፡-

"እንደሱ መረዳትህ ትክክል አይደለም። እየውልህ ምን መሰለህ፣
ሰብልህ ምርት የሚሰጠው በሴትና በወንድ አበባ ተራክቦ
ተፈጽሞና ተክሎቹ እርስ በርሳቸው ተዳቅለው ነው። ዕፅዋቶች
ዘር ለመስጠት እንደ እንስሳት ተንቀሳቅሰው ወንዱ ወደ ሴቷ
ሄዶ ተራክቦ መፈጸም አይችሉም፤ የተተከሉ ስለሆነ። ስለሆነም
ዘር ለመስጠት ተራክቦ መፈፀም አለበት። ተራክቦ ለመፈጸም
ደግሞ ዘረመል አሸጋጋሪ ረዳት ያስፈልጋቸዋል። አንተ አራዊት
ወይም ነፍሳት የምትላቸው ደግሞ በተፈጥሮ ምሥጢር ይህን
የሚያከናውኑ ናቸው። ባቄላ ወይም አተር ወይም ኑግ ዘርተህ
ጥሩ ዝናብ ስለጣለልህ፣ በደንብ አለስልሰህ ስላረስክ ወይም በቂ
ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ስለተጠቀምክ ብቻ ምርት አይገኝም።
በአበባ ወቅት እነዚህ ነፍሳት ተክሎቹን ካላዳቀሏቸው አነስተኛ
ምርት በጊዜ ሂደትም የመከነ ዘር ታገኛለህ" አለው።

አርሶ አደሩም በመገረም እየተከታተለው ነበር።

"እናም እነዚህ ነፍሳት በማሳው መካከልም ይሁን ድንበር ላይ
በየሀዳጉ ባሉ ሣርና ቁጥቋጦ ይኖራሉ። አንተ ሰብልህን ዘርተህ

ሲያብብ ተፈጥሮአዊና መሠረታዊ የዘረመል አሸጋጋሪነት ሥራቸውን ይሠራሉ። ለዚህ አገልግሎታቸውም አንተን ዋጋ አያስከፍሉህም። ሲሆን ክብርና እንክብካቤ መስጠት እንጂ እነርሱንም ሆነ መኖሪያቸውን ማውደምህ የኋላ ኋላ በራስህ ላይና በጥቅምህ ላይ አደጋ መፍጠርህን ተረዳው" አለው።

"አረግ አረገኝ! እኛ የት አውቀን" አለ አርሶ አደሩ ቀጥሎም "ያልተማረ መቼም ማጥፋት ነው" አለ ከልቡ በሚመስል።

"እስከአሁን ልክ ነው ያልተማርክ ስለሆነ ነው። አሁን ግን መረጃውን ስለአገኘህ በጉዳዩ ላይ ከእንግዲህ አዋቂ ነህና ሜዳውን፣ ሸንተረሩን፣ ጋራውን፣ ቁጥቋጦውንና ዛፉን ማራቆት ማቆም አለብህ" አለው።

"እሯ ተንግዲህማ እንዴት ሁኖ። እንዲውም እኛ እኮ ምነው የጥራጥሬ ምርት እምቢ አለን? ዘመኑ ይሆን እያልን? ነበር" አለ ዜማ ባለው ቃና።

"አዎን ልክነው የጥራጥሬ ምርት በተለይ ሊቀንስ ይችላል። ለምን ብትል የጥራጥሬ ተክሎች ዘረመላቸው የሚሸጋገረው በነፍሳት ስለሆነ ነው። ማንኛውም ቀለም ያለው አበባ የሚያወጣ ዕፅዋት በነፍሳት ወይም በአዕዋፋት ርዳታ የሚሸጋገር ነው። የአበቦቹ ቀለምም እነዚህን ፍጥረታት ለመሳብና ለመማረክ ነው። አበባቸው ቀለም ከሌለው ግን ለምሳሌ እንደ ጤፍና በቆሎ ያሉት በነፋስ ርዳታ ይሸጋገራሉ ወይም ይዳቀላሉ ማለት ነው። እና ልብ በል! እነዚህ ነፍሳት የግብርና ሥራህ አጋዥ መሆናቸውን ተረድተህ ርጎራጌ ማድረግ አለብህ ቢያንስ ለምርትህ ስትል" አለው።

"እሯ ተንግዲህ ደሞ ነካውን! ጊዮርጊስ ይወቅ! እንኳን ለራሴ ለአካባቢው አስተምራለሁ። ሰው እንዴ ተተስተማረ ወዲያ ማጥፋትማ ደግም አይደል" አለ።

አርሶ አደሩን ተሰናብተን ጉዟችንን ቀጠልን። ወደ ቁንዝላ ስንጠጋ የመሬቱ አቀማመጥ፣ ውበትና የሀፊሩ ለምነት እየጨመረ መጣ። በስተምሥራቅ የጣና ሐይቅ ውኃ በሰፊው ይፈልቃል። ይህ ደግሞ በበረሓ የምትጐመጅለት ሚራዥ ሳይሆን የእውነት ቅዱስ ውኃ እንደሆነ ጎሊናህ ያውቀዋልና ልብ ይሞላል።

መኪናውን ዳር አቁሜ ወረድንና ነፋሻማውን አየር ማግ ሳብ አደረኩት። ዙሪያውን ቃኝቼ ሳበቃ "ውበት ከለምነት ጋር ያደለው ስፍራ ነው!" አልኩና ለራሴ፡-

"ስማ ክብረ በዓል!"

"ፈጣሪን አግኝቸው ‹ለምነኝ ከአሜሪካ ካሊፎርኒያን፣ ከፈረንሳይ ሞናኮን፣ ከመካከለኛው ምሥራቅ ኳታርንም ቢሆን እርስት አድርጌ ልስጥህ› ቢለኝ ‹ጌታ ሆይ ከሰጠኸኝስ አይቀር ከጣና ሐይቅ ጀርባ ከአቤ ጎበኛ ሀገር ከዱርቤቴ-ይስማላ ጀምረህ በስተሰሜን ደንቢያን አካለህ፣ መንዳባ ገዳምን ጨምረህ፣ በምዕራብ የቴምድሮስን አገር ቋራን አሳፍተህ ስጠኝ እንጂ" እለው ነበር አልኩት በስሜት።

"ያንተ ነገር! ይሄማ የሰጠህ እናት ምድርህም አይደል?" አለና፡-

"ከዚህስ በላይ የረጃጅሞቹ አንበሶች ምድር ጋምቤላ፣ የሐመሮች ምድር አሞ፣ የጌዲዮን አረንጓዴ ተራራ፣ ጊቤ ባሻገር የአባ ጅፋር ምድር፣ የማንጎ ጥላ የሸፈነው ባለወርቁ የሼህ ወጀሌ ምድር አሶሳ፣ ራያና አዘቦ ቆቦና ጊራና በደም የተሣሠርክበት ማንነትህ የፈለቀበት ሀገርህም አይደል?!"

"ባለማዕድኑ የዓሊ ሚራ ሀገር አፋር፣ የበላይ ሀገር ቢቸና፣ የኢያሌው ብሩ ሀገር ሰሜን ጃናሞራ፣ የአሉላ መፍለቂያ ተምቤን፣ የጀግኖቹ

ምድር የአድዋ ተራራሮች፣ ከቡር ድንጋይ የሞላው ተንታና ደላንታ፣ የታደሰ ብሩ ሀገር ሰላሌ ሜዳውን ማን ወሰደብህ ?"

"የተንጣለለ ሜዳ ነው ወይስ የሰማይ ጥግን የሚታከክ ተራራ ያጣኸው፣ በረዶ የሚፈላበት ቀዝቃዛ ሰፍራ ወይስ ሞው ያለ በረሓ ግመል የሚጎማለልበት ሀገር፣ ውኃ የሚተኛበት ረግረግ ወይስ የተንጣፈፈ መሬት፣ ዓሣ የሞላባቸው ሐይቆች ወይስ ጨው የሚሚበት ሐይቅ አፍዴራ፣ የዕጣንና ሙጫ የበረሓ ደን ወይስ ዝግባና ቀረሮ ያለበት ጫካ፣ ምን ጎደለብህ?" አለኝ ።

በዚህ መካከል ሺፈራው እየሣቀ፡-

"ሲሳይ! ክብረ በዓልን አትሰማው። የሌላ ክልል ሁሉ እየጠራ ሀገርህ ነው እያለ እያነሳሳህ ነው። ከአሜሪካ ሲአይኤ ይዞት የመጣው ድብቅ ተልዕኮ ሳይኖረው አይቀርም" አለ ።

"ታዲያ የተለያየ ክልልስ ቢሆን ያው አንድ ሀገር አይደለም እንዴ?" አልኩት በአነጋገሩ እየሳቅሁ።

"በቃ እንግዲህ! አንተም ከተጨመርክ ጭልጋ ስንደርስ ሕገ መንግሥቱን በኃይል ለመናድ ሲመካከሩ አገኘኋቸው ብዬ እንደማስቀፈድዳችሁ እወቁ" አለን።

ዶ/ር ክብረ በዓል ቀበል አደረገና "እንዴ! ሕገ መንግሥት የአንድ ሀገር ዜጎች አብሮ የመኖር ቃል ኪዳን ሰነድ መሆኑ ቀርቶ ዝንጀሮ የሚንደው የገብስ ነዶ ክምር አስመሰልከው እኮ!" ሲል ሁላችንም ተያይዘን ሣቅን።

"ለማንኛውም እኔ እንጃ! ብቻ ይህ ሁሉ ጸጋ የሞላበት ሀገር የእኔ አልመሰልህ አለኝ። ፈጣሪ ምናልባት በሙሉ ልቡ መርቄ አልሰጠንም ማለት ነው" አልኩት ዶ/ር ክብረ በዓልን ወደ መጀመሪያው የውይይታችን ርእሰ ተመልሼ።

"እንዴት?" አለኝ።

"ታዲያ በዚህ ስፍራ ድህነት ምናባቱ ይሠራል? ጉስቁልናስ ማን ፈቀደለት?" አልኩት።

"እርሱስ እውነትክን ነው። ይህን ምሥጢር ከመፍታት የማርስን ምንነት ማወቅ ሳይቀል አይቀርም" አለና "ዋናው ችግራችን ግን የራሳችን የሥራ ሰልት፣ የኛ የሆነ የሥራ ቀመር፣ ከማንነታችን የሚመነጭ የእድገትና ብልፅግና እሳቤ ሳናዳብር ሁሉንም ከውጭ ለመቅዳትና ለመኮረጅ መሞከራችን አንዲሁም በቸገረን ቁጥር ፈጣሪን እያማረርን ለልመና እጃችን መዘርጋት እንደ ሰልት ማሰባችን ይመስለኛል" ሲል ሺፈራው ጣልቃ ገብቶ "በችግርህ ጊዜ ርዳታ መጠየቅ ወይም ልምድ ከውጭ መቅሰም ምን ክፋት አለበት?" አለ ።

ዶ/ር ክብረ በዓል ቀበል አድርጎ፡- " በእርግጥ ልምድ መቅሰም ነውር አይደለም። ነገር ግን ያለህንና የጎደለህን ሳታውቅ ሁሉንም አግበስብሰህ ከውጭ እማራለሁ ብትል ውጤት አያመጣም። ከውጭ የተቀዳውም እኮ በአግባቡ አይታወቅም" አለና አስከትሎም፡-

"ከገና ዛፍ እስከ ኢንጂነሪንግ፤ ከወይዛዝርት የቁንጅና ውድድር እስከ እርሻ መካናይዜሽን፤ከእንግሊዝ የገበታ ሥርዐት እስከ ጃፓኑ ካይዘን ፍልስፍና ሁሉንም ሳንመርጥ እንደወረደ መቅዳት ሆነ እንጂ ። እርግጥ ሞያ ከጎረቤት ልትማር ትችላለህ። መሥራት

የምትችለው ግን ቤትህ ባፈራው ብቻ ነው። ቤትህ ያፈራውን ሳታውቅና ሳታገናዝብ ሞያ ከጎረቤትህ ብትማር በእውነት የሚጠቅም ነገር አልተማርክም"።

"በአንድ ወቅት የጎንደርን የጥምቀት በዓል ‹የጎንደር ካርኒቫል› ብለው ሰይመው ለዓለም ቱሪስት ለማስተዋወቅ የሞከሩ የዋሆች ነበሩ። አየህ! በራቁት ዳንስ የሚታጀበውን ፍጹም ዓለማዊና ዘማዊ የሆነውን የላቲኑን ፌስቲቫል መጠሪያ ካርኒቫልንና ሥርዐቱን ጥንግ ድርብ ካባ በለበሱ ካህናት ሽብሸቦ ከሚመራው የጎንደር መንፈሳዊ የጥምቀት በዓል ጋር ስታዳቅለው ይጨነግፋል። እናም በዚህ መልክ ከውጭ ሳንመርጥ ለማዳቀል እየሞከርን ስንጨነግፍ ነው የኖርነው። አንድ ምሁር እንዳለው ሥራችን ሁሉ ‹በGrafted Aborted› አዙሪት ውስጥ መሽከርከር እጣ ፈንታው ሆ'ል" አለና የቁጭት ረጅም ትንፋሽ ተነፈሰና "ያም ሆነ ይህ ግን የምሥጢሩ መፍቻ ዘመን መምጣቱ አይቀርም" አለ ፍርጥም ብሎ።

"መቼ ይሆን እርሱ ዘመን?" አልኩት በምጸት መልክ ።

"ዕውቀት ከሃይማኖት

ታማኝነት ከኃላፊነት

ጥበብ ከሱባኤ

ጀግንነት ከትጋት

ሹመት ከችሎታ

እውነት ከርእዮት ጋር የሠመረች ዘመን እውን ይሆናል። እስከዚያው ግን በንጋት ጨለማ መዳከራችን ግድ ነው" አለ።

ምንም እንኳን ዐልፎ ዐልፎ የጉዞዬ ዓላማ መሳካት ትዝ እያለኝ ቢያስጨንቀኝም በዚህ መልክ እያወጋን ዛፍ የተከበረበትን የአለላ ወረዳን በሻውራ በኩል አቋርጠን የቅመሙን አገር ‹ጣቁሳን› አልፈን ‹አይከል› ከጠዋቱ አምስት ሰዓት አካባቢ ደረስን። የጭልጋ ወረዳ ዋና ከተማ የሆነችው ‹አይከል› ስሟን ያገኘችው የዚህ ጉዞዬ መዳረሻ ከሆነው ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ምሥረታ ጋር በተያያዘ መሆኑ ይነገራል።

አብርሃና አጽብሃ ከጻጻሱ አቡነ ሰላማ ጋር ሁነው የክርስቶስ ነገረ ሥጋዌ እንዲገለጽላቸው ቢጠይቁ ወደ ሃገረ ቋራ ተጉዘው ከሚዳቋ አፍ እንደሚሰሙ ተነገራቸው። በዚሁ መሠረት ከአክሱም ተነሥተው ጭልጋ አፋፍ ላይ ደርሰው ወደ ታች በረሓውን ሲያዩ ጊዜ ‹የአክለነ› ብለው ለመመለስ አሰቡ። ‹የአክለነ› ማለት ‹ይብቃን› ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ ይህን የተናገሩበት አካባቢ ‹አይከል› ተባለ። እግዚአብሔር ግን በዚያው ሌሊት አሁን ገዳሙ ካለበት ተራራ ላይ ታቹ ሦስት የሆነ አንድ የብርሃን አምድ ከሰማይ እስከ ምድር ተተክሎ አሳያቸው። በዚሁ መሠረት ብርሃኑን ወደ አዩበት ተራራ ተጉዘው ገዳሙን ለመመሥረት በቁ በማለት የገዳሙን አመሠራረት ከአይከል ከተማ ሰያሜ ጋር አያይዘው ሊቃውንቱ ይተርካሉ።

በሸፈራው ጋባዥነት ምሳ ከበላን በኋላ ሸፈራውን እዛው አይከል ትተነው እኔና ዶ/ር ክብረ በዓል ወደ መተማ ጉዟችንን ቀጠልን። ወይናደጋማ አየር ንብረት ካላት አይከል ከተማ በትንሽ ርቀት ቁልቁል ወደ መተማ በረሓ መውረድ ልዩ የሥርዐተ ምህዳር ትዕይንት ይፈጥራል። ማራኪው መልክአምድር ከልዩ የዕፅዋት ስብጥሩ ጋር አስደሳች የመሆኑን ያክል ከዚህም ከዚያም ተራራው ላይ ያለጊዜው የሚጨስ የሚቃጠል ዛፍ መመልከት ግን ጨንገራ ይልጣል፣ ልብ ያሳዝናል። ዐልፎ ዐልፎ እየቆምን ሙያዊ ክርክርና ውይይት እያደረግን፣ አንዳንዴም ነዋሪውን እያነጋገርን ተጉዘን

ወደ ዐሥር ሰዓት አካባቢ የመተማ ወረዳ ዋና ከተማ ከሆነችው ሞቃታማዋ ጎንዳ ውኃ፡ ከተማ ደረስን።

ከዶ/ር ክብረ በዓል ጋር ማታ ካረፍንበት ሆቴል እራት በልተን የጎንዳ ውኃን ወበቅ ለመቋቋም በረንዳ ላይ ቁጭ ብለን ለሰላሳ በአምቦ ውኃ እየጠጣን ሰናወራ፡-

"ሁልጊዜ እጠይቅሃለሁ እያልኩ የረሳሁት ጥያቄ ነበረኝ" አልኩና

"ብዙ ሰው አሜሪካ ሄዶ ለመኖር በሚቃትትበት በዚህ ዘመን በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የፕሮፌሰርነት ቦታ ያገኘ፣ የተደላደለ ሙያና ሥራ ባለቤት የሆንክ እንዴት ይህን ሁሉ ጥለህ ወደ ኢትዮጵያ መጣህ?" አልኩት ።

ፈገግ አለና "አንተ እንኳን ይህን ጥያቄ ትጠይቀኛለህ ብዬ ገምቼ አላውቅም ነበር" አለኝ።

"እንዴት?" አልኩት ።

"ሰውን ወደ ሀገሩ እንዴት መጣ ብለው ከሚደነቁ ሰዎች መካከል ስለማትመስለኝ" አለ ።

"ያው ብዙ ሰው አሜሪካ መኖር ለራስ ባይመች ልጅ ወልዶ ጥሩ ትምህርት አስተምሮ የኢትዮጵያን ስም የሚያስጠሩ ዜጐች ማውጣት ይቻላል ስለሚባል ነው እንጂ" አልኩት ።

"ስማ ሲሳይ!" አለ በሰፊው ለማስረዳት እየተመቻቸ።

"ስማ ሲሳይ! ሀገሬን እወዳለሁ ከሚል ከእንዳንተ ዐይነት ወንድም የማልጠብቀው ጅላጅል ጥያቄ ቢሆንም ስለጠየከኝ መመለስ ይኖርብኛል"።

ሁልጊዜ አመለካከቱንና ፍልስፍናውን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ሲቀርብለት መጀመሪያ ዝምታን ይመርጣል። ከቆሰቆሱት ግን እስከ ጥግ ድርስ ሂዶ እንደሚገልጽ ስለማውቅ እኔንም ጭምር የሚነካ ቢሆንም ስለማይምረኝ ተረጋግቼ "ተቀበል እንግዲህ" አልኩት ራሴን።

"ማንም ሰው ከሀገሩ ለምን ወጣ? እንዴት ሀገሩን ጥሎ ይሄዳል? ተብሎ ሊወቀስ አይችልም፤ አይገባምም። ምክንያቱም ኢትዮጵያዊነት ዕዳ ፍዳ፣ ኢትዮጵያም እስር ቤት አይደለችምና። ይልቁንም ኢትዮጵያዊነት ክብር፣ ኢትዮጵያም ፍቅር ናት እንጂ ። ይሁን እንጂ በምዕራቡ ዓለም ወይም በሌላ ውጪ ሀገር ስትኖር ለኢትዮጵያ እንደምትኖር አስበህ መመፃደቅ የሚገባ አይመስለኝም። አሜሪካና ካናዳ፣ እንግሊዝና ጀርመን ወይም አውስትራሊያ ልጆች ወልደህ ብታሳድግ ለወግ ለማዕረግ ብታበቃ መልካም ሊሆን ይችላል። ግን ‹ኢትዮጵያን እንዲያስጠሩ ብዬ ነው› ማለት ግን ግብዝነት ይመስለኛል ።"

"በአሜሪካ የትምህርት ሥርዐት ተምሮ በአሜሪካ ተቋማት ተቀጥሮ ውጤታማ ቢሆን የሚጠቅመው አሜሪካን እንጂ ኢትዮጵያን ሊሆን አይችልም። ‹ትውልደ ኢትዮጵያዊው አሜሪካዊ የሠራው ሮኬት ወደ ጎዋ መጠቀ› ቢባል ለኢትዮጵያ ጥቅሙ ምንድን ነው? ውጤታማዎች የማይኖሩባት ሀገር ሆና ከመታየት በስተቀር ትርፏስ ምንድን ነው?። አንድ ትውልደ ኢትዮጵያዊ በኦሎምፒክ ሜዳ ሮጠ የፊንላንድን ማሊያ ለብሶ ለፊንላንድ ሜዳሊያ ቢያስገኝ ኢትዮጵያ የምታገኘው ጥቅም ምንድን ነው? ከፍ ብሎ የሚውለበለበውስ ባንዲራ የማን ይሆናል?"

"‹ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ› የሚሉ የሚያማምሩ ሕፃናትን ወልደህ ብታሳድግ የዕድሩን ድንኳን፣ የሠርጉን ዳስ፣ የሰንበቴውንና የድግሱን ጉዝጓዝና ጨፌ መቼ አዩት። ኢትዮጵያዊ ሲከፋው ጃሎ ሲል፣ ሲነሽጠው ሲያቅራራ፣ ሲያዝን ወዬ ሲል፣ ደስ ሲለው

ሲደልቅ፣ መቼ ሥነ-ልቦናውን ተረዱት?! ሕመምክን የማያውቅ በለመድኀኒት፣ ልክህን የማያውቅ አልባሽ፣ አምሮትክን የማያውቅ አጉራሽ፣ ስሜትክን የማይረዳ አጽናኝ፣ የኑሮ ድቀትክንና ግፍህን ከጎንህ ሆኖ ያላየ ተቆርቋሪ ደግሞ የሚጠቅም አይመስለኝም" ሲል

"በለው እንግዲህ" አልኩ ለራሴ።

"አየህ! አሜሪካ ተምሮ በአሜሪካ ሆስፒታሎች የተራቀቀ የልብ ሰርጅን ልጅ ከምታወጣ ይልቅ በፎገራ ሜዳና በአሞ ሽለቆ ለሚኖሩ ሕዝቦች የወባ ንዳድን ኪዩኒን ሰጥቶ የሚያክም ነርስ ለኢትዮጵያ ብታወጣ የበለጠ ጠቅመሃታል። የአሜሪካ ጠፊር ምርምር ‹ናሳ› ውስጥ የአስትሮ ፊዚክስ ሊቅ ልጅ አውጥተህ ‹ትውልደ ኢትዮጵያዊ› ከሚባለው ይልቅ ውኃ ከከርሰ ምድር አውጥቶ የከብት ጭራ ተክትሎ የሚንከራተተውን አፋር ወይም ሶማሌ ጥም የሚቆርጥ መለስተኛ ቴኪኒሻን ብታበረክት ርዳታህ ከፍ ያለ ነው ።"

"ኢትዮጵያን ቁስሏን በጨው ውኃ አጥቦ፣ ዘይት ቀብቶ፣ በንጹሕ ሻሽ የሚያስርላት እንጂ ባሕር ማዶ ሆኖ በትውልዱና በደሙ ብቻ ያውም ወረቀት ላይ የማይሰፍር ማስተዋወቅ ብዙ ይጠቅማታል ብዬ አላምንም። ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በባዕድ ሀገር ሄደው በስኬታቸው ለባዕዳን በረከት አምጥተው ስማቸው ከገነነው ይልቅ አስትሮ-ጀርመናዊው ካርል ሃይዘን የተደላደለ ኑሮውንና ዝናውን ረግጦ ‹መርሐ ቤቴን› ቤቴ ብሎ የገባ፣ የጀማ ወንዝ ላይ የብረት ድልድይ የዘረጋው ለኢትዮጵያ የቁም ነገር ልጅ ነው ብዬ አምናለሁ። ያለዕድሜ ጋብቻ በፈጠረው ቀውስ በወሊድ ተጐድተው ሽንታቸውን መቆጣጠር ተስኗቸው ‹ከረፋችሁ› ተብለው የተገፉ በሺህ የሚቆጠሩ ሴቶችን ሕይወት ለመቀየር የምዕራቡን ዓለም የሞቀ ኑሮ ትተው የቀረውን ዘመናቸውን ለዚች ውብ ሀገር ኢትዮጵያ ያበረከቱት ጥንዶች ዶ/ር ሃምሊንና ባለቤቱ ለኢትዮጵያ የበለጠ ይቀርቧታል። የጎንደሩን የቀዶ ጥገና ሐኪም ዶ/ር በርናንድ

እንደርሰንን ታውቀው የለም? ኢትዮጵያዊት ሚስቱን ‹ሀገሮሽ ሀገሬ
ሕዝብሽ ሕዝቤ› ብሎ የትውልድ ሀገሩን ጃማይካን፣ የእንጀራ ሀገሩ
አሜሪካን ትቶ ሳንደርና የከተመ፤ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል ሕዝቡን
ያገለገለ፣ ብዙ ኢትዮጵያዊያንን በሙያም በምግባርም የወለደ
እርሱ ነው ኢትዮጵያን ከልቡ የወደዳት። በአንድ ወቅት እንዲት
እናት ከደቄአቸው ሰለፈወሳቸው፣ ከሰቃይ ሰለገላገላቸው ተደሰተው
የተባረኩትን የሙያ እጆቹን ሰመው ሲያበቁ መቀነታቸውን
ፈትተው ዐሥር ብር አወጡና ‹በል በዚህ ምሳህን ብላ› ይሉታል።
ታላቁ ሰው ዶ/ር በርናንድ በምሳ ሰዓት ከቤቱ ደውሎ ለምሳ ቤቱ
እንደማይሄድ አስታወቀ። የዐሥር ብር ምሳ ሊገኝበት ከሚችልበት
ስፍራ ከቀን ሠራተኞች ምግብ ቤት ሄዶ ከብሩንና ማዕረጉን ረስቶ
የዐሥር ብር ምሳ በላ።"

"በል እስቲ ንገረኝ ሲሳይ! ማነው እንደዚህ ሰው የዚያችን ገጠሬ እናት
ችግር የፈታ? ማነው ፍቅሯንስ የተረዳ? ማነው ፍቅሯንስ ያከበረ?
ማነው ምርቃቷስ ልቡን የነካው? ለእኔ ኢትዮጵያን መውደድና
ኢትዮጵያዊነት ጥልቅ በሆነ ሥነ-ልቡና ትስስርና አብሮ በመኖር
የሚገኝ እንጂ በደም ብቻ የሚተላለፍ ነው ብዬ አላምንም።"

"የምዕራቡ ዓለም ነፍሱኝ ሳይሆን፤ ትቼው ወደዚች ሀገር ስመጣ
በቀን ሦስት ጊዜ የምታጠብበት ሙቅ ውኃ፣ ከፈለክበት ቦታ
በፈለክበት ሰዓት የሚያደርስህ የከተማ ውስጥና ውጪ የሕዝብ
ትራንስፖርት፣ የሚደላ የመሬት ውስጥ ባቡር፣ ረጅም ሰዓት
በሠራህ ቁጥር የሚታፈሰው ቁና ቁና ዶላር፣ ጉዳይ ኑሮህ ወደ
ተቋማት ስትሄድ "what can I help you" የሚለው የሰለጠነው የሕዝብ
አገልጋይነት ሲቀር በኑሮዬ ምኞትን ሳያጎድል ቀርቶ አይለም።"

"በተቃራኒው እዚህ ሀገር ስትኖር ጠዋት ፊትክን ልትታጠብ
ስትነሣ ውኃ ሄዳለች፣ ማታ ቤት ስትገባ መብራት ጠፍቷል፣ ጉዳይ
ልታስፈጽም መሥሪያ ቤት ስትሄድ ‹አልገቡም፣ ሰብሰባ ላይ ናቸው፣
መመሪያው አይፈቅድም ፣ ያስጠይቀኛል፣ ሳምንት ተመለስ፣

አይቻልም› የሚሉ ከሰው ሳይሆን ከአጋንንት አፍ የሚወጡ የሚመስሉ መልሶች ሳያስከፉኝ ቀርተው አይደለም። ያም ቢሆን የድከመታችንም ተጠያቂ፤ መፍትሄ አምጭም፤ የበረከታችንም ተካፋይ እራሳችን ነን ብዬ አምናለሁ። ከማዶ ሆነን በረጅም እንጨት እያማሰልን የሚጣፍጥ ወጥ መሥራት አይቻልም።"

"ያም ሆኖ ግን አንድ እውነት አለ! ምን መሰለህ!" አለ። ሲናገር ደርዝ አይለቅም።

"ኢትዮጵያ ውስጥ ኑሮ በእሾህ የተከበበ ጽጌረዳ ነው። የተወሰነ ጊዜ ቆይተህ በእርጋታ እሾሁን በጥንቃቄ አልፈህ ጽጌረዳውን ስታገኝ በቃ ዘላቂ ፍቅርና ውበት፤ ደስታና ሰላም ይሰጥሃል። ደስታህንና ፍቅርህንም የሚጋራልህ ብዙ ሰው በዙሪያህ አለ። ሰው ነህና ብታገባ ይዘፈንልሃል፤ ብትታመም ይታዘንልሃል፤ ብትሞት ይለቀስልሃል። እናም ሰው መሆንህ ያኮራሃል። በምዕራቡ ዓለም ጽጌረዳው ቅርብህ ነው። እስከሠራህ ድረስ ለማግኘትም በእሾህ አልተከበበም። ችግሩ ግን ብቻህን ሩጠህ ጽጌረዳውን እንዳገኘህ መዐዛውን ልትሰብ ብቻህን ስትመቻች ውስጡ በእሾህ የተሞላ እንደሆነ ትረዳለህ። አንተ በምዕራቡ ዓለም ከቁጥሮች መካከል የምትኖር ቁጥር ነህ። ያኔ ኑሮህ ጎምዛዛ ወይም ጣዕም አልባ ይሆንብሃል። እንደ ሰው መብቶችህ በእጅጉ የተከበሩ ቢሆኑልህም ብቻህን ነህና ሰው መሆንህ ያስጠላሃል!"

"እና በዚህ ምክንያት ነው ወደ ሀገሬ የመጣሁት። በመምጣቴም በሕይወቴ ትክክለኛ ውሳኔ እንደወሰንኩ ይሰማኛል" አለና በረጅሙ ተነፈሰ።

"ይገርማል!" አልኩና "ነገ በጠዋት ስለምንነሣ አሁን እንግባና እንተኛ" ብየው ተነሣሁ። እንደ እውነቱ ግን መተኛት ፈልጌ አልነበረም። የነገረኝን ሁሉ ወንፊት አእምሮዬ ሳያፈሰው ወደ ማስታወሻዬ ለማስፈር ነበር እንጂ።

# ምዕራፍ ኻምሳት

ቀደም ብዬ ወደ መተማ ለመምጣት ከአባ ክንፈ ሚካኤል ጋር ከተነጋገርኩ በኋላ የገዳሙን የቆላ ቀርቀሃ ልማት በተመለከተ ከገዳሙ አባቶች ጋር ለመወያት ከክልሉ የደን ባለሙያዎች እንደሚሄዱ መረጃው ስለበረኝ የጉዞ ቀኑን ከእነርሱ ጋር ባቀናጀሁት መሠረት ገንዳ ውኃ ከተማ ተገናኘን።

በማግስቱ ቀደም ብለን ለመሄድ በተስማማነው መሠረት ከገንዳ ውኃ ከተማ ተነሥተን ደረቅ ዐባይ ከተባለችው መንደር ስንደርስ ገና ከጠዋቱ 12፡20 ነበር። አባ ክንፈ ሚካኤል በነገሩኝ መሠረት ቄስ ገዳሙን አጠያይቀን አገኘናቸው።

ቄስ ገዳሙ ጠይም ቀጠን ብለው ረዘም ያሉ ከአለባበሳቸው አንጻር ሲታዩ ደግሞ ጨዋ ነጋዴ እንጂ ካህን አይመስሉም። በኋላ ላይ ትሕትናቸውንና ቅንነታቸውን ሳስተውል ግን ‹እውነትም ካህን› ብያለሁ። በንግድ ሥራ የሚተዳደሩ ሲሆን በአካባቢው የሚገኘው ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪም ሆነው እያገለገሉ ሲሆን በተጨማሪ ለማኅበረ ሥላሴ ገዳም መነኮሳት እንደ ወደብ ወይም መናኸሪያ ሆነው ያገለግላሉ። የእኛ ቢጤ እንግዳ ሲመጣም ሥራቸውን እርግፍ

አድርገው ትተው በዚያ በረሓ ሳይሳቀቁ ገዳሙ ድረስ መርተው ያደርሳሉ። ይሄ የተሰጣቸው ጸጋ ይመስላል። እኛም ስንጠይቃቸው አላንገራገሩም:: በዕለቱ የሚሠሩትን የግል ሥራቸውን ሌላ ሰው ወክለው በዐሥራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ከእኛ ጋር ለመሄድ ዝግጁ ሆኑ።

መንገድ ከመጀመራችን በፊት "ከዚህ ጀምሮ እስከ ዋናው የገዳሙ ቤተ ክርስቲያን ድረስ በአጭር የሚያስኬድ የእግር መንገድ አለ ለጊዜው ልዘነጋው እችላለሁ እንጂ። ለማንኛውም የገዳሙ ትራክተር የሚመላለስበትን የጎማ ምልክት ተከትለን በመኪና መሄድ እንችላለን። ምናልባት ከዚያ በኋላ የሚቀረን ትንሽ ይሆናል" አሉ።

እኔ ከባለሙያዎቹ መኪና ስለምሳፈር የመጣሁበትን መኪና ለዶ/ር ክብረ በዓል ሰጥቼ ወደ ዐሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ እዛው ደረቅ ዐባይ እንዲጠብቀኝ ተቀጣጠርን። የተወሰነውን የገዳሙን መንገድ በመኪና ተጉዘን ድካም መቀነሱ ጥሩ ሐሳብ ስለመሰለን በዚሁ ተስማምተን ጉዟችን ተጀመረ።

ዋናውን የጎንደር መተማ ሱዳን አስፓልት መንገድን ደረቅ ዐባይ

የሹፌሩ ፍላጎትና ብርታት ታክሎበት ከጠዋቱ አራት ሰዓት ሲሆን የገዳሙ ክልል ወሰን ከሆነው የገንዳ ውኃ ወንዝ ደረስን። ለአራት ሰዓት ያክል ብንጓዝም የመጣነው ግን ዐሥራ ሦስት ኪሎ ሜትር ብቻ ነበር።

መኪናዋ እስክትሻገር እኔ በእግሬ ወደ ወንዙ ገባሁ። አካባቢው የጋለ ምድጃ ወደመሆን እየተቃረበ ነው። በዚህ ቦታ የፀሐይ ሙቀቷ፣ ብርሃኗና ውበቷ ሳይሆን ጭካኔዋ የበለጠ ይታሰባል። ልክ ለልምምድ እንደወጣና ዐርፎ የተቀመጠን ሜዳና ተራራ በመድፍና በሮኬት እያነደደ እንደሚለማመድ ወታደራዊ ቡድን ፀሐይም ኃይሏን ለመሞከር መላ ሙቀቷን የለቀቀችው ይመስላል። ሰውነቴ ያጠራቀመውን ስብና ውኃ ማቅለጥ ይዟል። ከነጫማዬ ውኃ ውስጥ ገባሁና እስከ ጉልበቴ ተነከርኩ።

ምድርስ ምኗ ሞኝ ነው። እንደ እኔ በፀሐዩ ሐሩር መርገብገቧን ትታ የፀሐዩን ሙቀት መጠን እንደ ቁጣና ውርጅብኝ መቁጠሩን ረስታ እንደ ጸጋና ኃይል የሚያዩትን ልዩ ዕፅዋቶቿን አብቅላና ተላብሳ ‹ፀሐይ ሆይ ስለዚህ ሁሉ ኃይልሽ እናመሰግንሻለን› የምትል ትመስላለች።

ወደ ገዳሙ ክልል ሲገባ ሁሉ ነገር ይለወጣል። 19 ሺህ ሄክታር ስፋት ያለው የገዳሙ ክልል ለእርሻ ከዋለው በጣም ጥቂት ስፍራ በስተቀር በደን የተሸፈነ ነው። በአካባቢው ሥርዐተ ምህዳር መሠረት ዛፎቹ በጣም የተጠጋጉ ሳይሆኑ በመካከላቸው መጠነኛ ክፍተት ያለ በመሆኑ የሰንበሌጥ ሣርና የቆላ ቀርቀሃ /ሽመል/ ጥቅጥቅ ብሎ በቅሎበታል። የሣሩ ርዝመት ከሰው ቁመት በላይ በመሆኑ ወደ ውስጥ እየዘለቁ በሄዱ ቁጥር የሚታየው ሰማይ ብቻ ነው። ከአካባቢው ከባድ ሙቀት ጋር ተዳምሮ ልብ ያርዳል፡ ሆድ ያባባል!

በዚህ በሣርና ዛፎች ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ እንደ ዘንዶ የተዘረጋውን የአባ ክንፉ ሚካኤልን ትራክተር ጎማ ዱካ መፈለግ እጅግ አስቸጋሪ እየሆነ መጣ። አብረውኝ ያሉት ተስፋ ወደመቁረጡ ቢያዘነብሉም ቄስ ገዳሙ ግን ተስፋ አልቆረጡም። ወደፊት እንድንጓዝ ያበረታቱናል። በጣም ወደድኳቸው። በዚያ ሰዓት ወደ ኋላ እንመለስ የሚለኝን መስማት አልፈለኩም።

ከተወሰነ ጉዞ በኋላ ሞራሽ የዛፎቹ ቁመት በእጅጉ የረዘመ ሣሩ ወደ ዳዋነት የተለወጠበትና ሰማዩም የማይታይበት አካባቢ ገባን። ቀስ እያልን ስንኳተት ድንገት በሹፌሩ በኩል ያለው የመኪናዋ የፊት ጎማ ሸርተት ብሎ ጉድጓድ ውስጥ ሲገባ መኪናዋ በግራ ፊት በኩል መሬት ላይ ተተከለች። ድንጋጤያችን መጠኑን ከማለፉ በፊት መኪናዋ የከፋ ነገር ሳይደርስ ባለችበት ተጋድማ ቆመች። ወርደን ስናስተውል የትራክተሩን መስመር ለቀን ወደ ግራ ታጥፈናል። ሦስቱ ጎማዎች መሬት እንደቆነጠጡ ስለነበር መኪናዋን በከባድ ማርሽ መንጭቆ ለማውጣት አልተቸገርንም።

ትንሽ ርቀት እንደተጓዝን ሣሩ በሥርዐት የተቃጠለበት ገላጣ ስፍራ ደርሰን ‹ተመስገን› አልንና ከመኪናዋ ወርደን ለመናፈስ ሞከርን። ይሁን እንጂ ወበቁና ሙቀቱ የሚቀየር ነገር አልሆነም።

“ይህንን አካባቢ ማነው ያቃጠለው?” አልኳቸው ቄስ ገዳሙን።

“መነኮሳቱ ይሆናሉ። የማያቋርጥና ከፍተኛ የሆነ ሰደድ እሳትን ለመከላከልና ፍጥነቱን ለመቀነስ አለፍ አለፍ እያሉ በጥቃት በቀዝቃዛው ያቃጥሉታል” አሉ ።

እሳትን ቀድሞ በእሳት መከላከል ሳይንሳዊ የደን መጠበቂያ ዘዴ እንደሆነ ስለማውቅ “ገባኝ” አልኳቸው።

በአካባቢው እሳት የሥርዐተ-ምህዳሩ የተፈጥሮ ክስተት አንዱ አካል ነው። አካባቢው ካለው ከፍተኛ መቀትና ከተከማቸው ተቀጣጣይ የዕፅዋት እርጋፊ የተነሣ የዛፎችና ቁጥቋጦዎች ቅርንጫፎች በንፋስ ሲወዛወዙ በሚፈጠር ሰበቃ በቀላሉ እሳት ሊፈጠርና ሊያያዝ ይችላል። በአካባቢው በተፈጥሮ የሚነሣው እሳት በፍጥነት በነፋስ እየተገፋ ከአንድ አካባቢ ብዙ ቆይታ ሳይኖረው ስለሚሄድ በሥርዐተ ምህዳሩ ላይ የከፋ ጉዳት አያደርስም። እንዲያውም በዕፅዋቱ መቃጠል በሚፈጠረው አመድ መሬቱ የፖታሽ የምና ፎስፎረስ ክምችቱ በመጨመር አካባቢው እንዲታደስ ሊያደርግ ይችላል። መሬት ውስጥ ተቀብረው የነበሩ ዘሮችም አጋጣሚውን ተጠቅመው በመብቀል የትውልድ ቅብብሎሽና መተካካት እንዲኖር ያደርጋል። በአካባቢው የሚበቅሉት ዕፅዋትም በተለይ ዛፎች ለማይቀረው የተፈጥሮ ክስተት ‹ሲሊካ› የተባለውን ብርጭቆማ ንጥረ ነገር በቅርፊታቸው ላይ በማከማቸት የከፋ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ይከላከላሉ። እናም ቀድሞ በማቃጠል ዐልፍ ዐልፎ ገላጣ ስፍራ መፍጠር የእሳቱን መጠን በማውረድ አደጋውን በእጅጉ ይቀንሰዋል።

ይሁን እንጂ እሳት ሆን ተብሎ ለእርሻ ወይም ለመኖሪያ ተብሎ በጭካኔ ሲለኮስ ግን በዝግታ እየተቆሰቆሰ ስለሚነድ የዕፅዋቱ የህዋስ መራቢያ ቀለበት (Cambium) ይሞታል። የውኃና የምግብ ማስተላለፊያ ሻንዳዎቻቸው (Zylem and Phloem) ይቃጠላሉ። የዐፈሩ የላይኛውና በብስባሽ የዳበረው እንዲሁም ከፍተኛ የዕፅዋት ዘር ባንክ ክፍል ጭምር አብሮ ይነዳል። በዚህ ጊዜ ከፍተኛ የሥርዐተ ምህዳር መቃወስ ይፈጠራል። የቆላማዎቹ አርማጭሆ፣ መተማ፣ ቋራና ጃዊ አካባቢ ተደጋጋሚ ችግርም ከዚህ ይመነጫል።

እነዚህ አካባቢዎች ከሥርዐተ ምህዳሩ ጋር በተጣጣሙ ልዩ ልዩ ዕፅዋቶች የተደራጁ ልዩ የደን ቦታዎች ናቸው። ደጋማውን የሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ ከበረሓማው የሱዳን መሬትና በቅርብ ርቀት ከሚገኘው የሰሃራ በረሓ ወላፈን እንዲታደጉ፣ ነበልባሉን

እንዲጋርዱ የተፈጠሩ የተፈጥሮ ዘቦች ናቸው። ከዚህ የተነሣ በሳይንሳዊ መጠሪያቸው አረንጓዴ መቀነት (Green belt) የሚባል የደጀንነት የማዕረግ ስም አላቸው። እነዚህ ደኖች ባይኖሩ የሰሜን ተራሮች፣ ጉናና ጮቄ ቅዝቃዜአቸውን ተገፈው የውኃ ማማነታቸው ይመክን ነበር። እንዲሁም ጣና ሐይቅ ከፍተኛ የትነት አደጋ ስለሚያጋጥመው የሱዳን በረሓ እራሱን አስፋፍቶ ደጋ ዳሞትና ሰከላ፣ ወገራና ጃናሞራ በደረሰ ነበር።

እዚህ ግባ የማይባል የውጭ ምንዛሬና መሠረታዊ የአካባቢ ልማት ባላመጣ ኢንቨስትመንት ስም ለትውልድ በማያስቡ ግለሰቦች ያለርኅራኄ እየተመነጠረ ከታሰበው የኤክስፖርት ምርት ይልቅ ከሠል እየተመረተ ጥቂቶች ሀብት በሚያግበሰብሱበት ትዝብት መካከል የማኅበረ ሥላሴ ገዳም መነኮሳት ከ19 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ የሆነውን ይህን ብርቅዬ ደን እንደ ዐይናቸው ብሌን እንደሚንከባከቡት ማየት ተስፋ ሰጪ ብቻ ሳይሆን መተማመኛም ነው። ለዚህ ድርጊታቸውም ከፌደራሉ መንግሥት ፕሬዚዳንት እጅ የአረንጓዴ ዋንጫ ተሸላሚ ሆነዋል። ከዚያ ያለፈ ያገኙት ድጋፍ ግን ያለ አይመስለኝም። ያም ቢሆን እነርሱም የሀገርና የትውልድ አደራ፣ የሃይማኖት ቃል-ኪዳን ሆኖባቸው በተጋድሎ መኖሩን በጸጋ የተቀበሉት ይመስላል።

ለእነዚህ መነኮሳት ያለኝን አድናቆት እየገለጽኩ ሕንፃ

መኪናዋን ቆላልፈን ፈፋውን ተከትለን በስተደቡብ ወደ ተራራው አቅጣጫ መጓዝ ጀመርን። አንድ ሁለት ኪሎ ሜትሮች ዳዋ እየጣሰን እንደተጓዝን የትራክተሩ ጎማ ፈፋውን የሚያቋርጥበት ግልጽ ቦታ ደረስን። የጉዞ መላምታችን ትክክል መሆኑን ስላረጋገጠልን በጣም ተደሰትን። ስለሆነም ፈፋውን ለቀን ወደ ደቡብ ምሥራቅ ታጥፈን የትራክተሩን ጎማ ተከትለን እንደገና ተጓዝን። የገጸ እንስሳት የሠፈሩበት አካባቢ ደረስን። ትልቅ እፎይታ ነበር። በዚህ ሁሉ ድካም የገጸሞቹን ጊደሮች፣ ላሞች፣ ወይፈኖችና በሬዎች መመልከት ልዩ ትዕይንት ነበር።

ከዚህ በፊት በሆላንድ ሜዳዎች ላይ ንጽሕናቸው የተጠበቀ ነጭና ጥቁር ቀለም ያላቸው ላሞችን ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይ ቀንቼ ነበር። የማጎበረ ሥላሴ ገጸምን ላሞችና ወይፎኖች ባየሁ ጊዜ ግን በቀላዋጭነቴ ፈጣሪ እንዳይፈርድብኝ ፈራሁ። እጅግ ንጹሕ፣ መልካቸው ያማረ፣ ሰውነታቸው የሞላ፣ ዠርጋዳ አቋም ያላቸው፣ ለብቻ መንጋ ሰርተው የሚጠበቁት እምቦሶቻቸው ደግሞ እንደ ሕፃን ልጅ አንሥቶ አቅፎ ለመሳም የሚገፋፉ ናቸው።

አብረውኝ ከነበሩት ባለሙያዎች አንዱ አጅግ መመሰጤን ሲያይ በአድናቆት "ያስጎመጃሉ አይደል?" አለኝ።

"የየመንደሩ አድባር፣ የዐባይ ቆሌ፣ የዘንገናው ጋኔል፣ የቢሾፍቱ ቆሪጥ፣ የገናሌው ሞቴ፣ የጅሩዋ አተቴ፣ የዱበርቲ መጀን ሰራን ወይም ሶለላ ዶሮ፣ ነጭ ወይም ዳንግሌ በግ ካላመጣህ እንጀራህን አልሰጥህም፣ ጤናህን አልመልስም፣ አዱኛህን አልከፍትም እያሉ የሚያስደነክሯቸውን አማኞቻቸውን እነዚህን ጊደሮችና ወይፈኖች አይተው ቢሆን ኖሮ ‹ተማጎበረ ሥላሴ የከብት መንጋ፤ ሻኛው የቆመውን ወይፈን ወይም አለላ የመሰለች ጊደር አምጣ ባሉ ነበር›" አልኩት።

እነዚህ በሬዎች፣ ወይፈኖች፣ ላሞችና ጊደሮች እንዲሁም ጥጃዎችና እንቦሶች ከውበታቸው በተጨማሪ እንደ መናንያኑ በጥብቅ ሥርዐት የታነጹ መሆናቸውን መስማት ለእኔ ቢጤ ሰው ለማመን ይከብድ ይሆናል። በአካባቢው የአገኘናቸው ጠባቂ ሲያስረዱን፡-

"ማታ ላይ ጥጃዎችና ላሞች ከተጣቡ በኋላ ‹ወገን ወገን› እያልን ስናጨበጭብ ጥጆቹ ከእናቶቻቸው ተለይተው የራሳቸውን መንጋ ይሠራሉ። ወዲያው ደግሞ ‹አጎድ አጎድ› ተብሎ ሲጨበጨብ ሁሉም ወደ ማደሪያቸው ይገባሉ። የገዳሙን ሣር በሥርዐት ለማስጋጥ ሲባል እንስሳቱቹ በተወሰኑ ቀናት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ አንዲሰፍሩ ይደረጋል። ታዲያ ጠባቂያቸው ‹ጉዞ ጉዞ› ብሎ ሲያጨበጭብ ሁሉም ተከትለውት ወደሚመራቸው ይጓዛሉ። ከሚፈለገው ስፍራ ሲደረስ ‹ሰፈር ሰፈር› ብሎ ሲያጨበጭብ አዲሱ የግጦሽ አካባቢያቸው መሆኑን ተረድተው ለግጦሽ ይሰማራሉ" አሉ።

የእነዚህ ከብቶች ዝርያና ዘረመል ምንነት በሀገራችን ባለሙያዎች መጠናታቸውን እጠራጠራለሁ። በገዳሙ ቆይታዬ የተረዳሁት ግን ከአውስትራያ ዩኒቨርሲቲዎች የእንስሳት ሳይንስ ተመራማሪዎች በተደጋጋሚ እየመጡ ጥናት እንደሚያደርጉ ነው። ንብ የአበባ መገኛን፣ ዝንብም የቆሻሻ ስፍራን አስሰው እንደሚያገኙ ሁሉ ምዕራባውያን የሀብትና የብልጽግና መገኛ አካባቢ ማነፍነፍ የዕድገታቸው አንዱ ምሥጢር ነውና።

ወዲያው ብዙም ካልራቀው ‹የገዳሙ ሞፈር ቤት› ወይም በእነርሱ አጠራር ‹መሸሮ› ደረስን። ‹መሸሮ› ቃሉ ዐረብኛ ሲሆን ‹እርሻ› ማለት እንደሆነ ተረድቻለሁ። አንድ ወጣት መነኩሴ ተቀበሉን። ሁኔታችንን ሲያዩ እጅግ አዘነው "አይ.... እንዲያው ከእኛ ሰው ሳትይዙ በዚህ በረሓ፣ በዚህ ሰዓት እንዴት መጣችሁ?" አሉ።

ቄስ ገዳሙ ቀበል አድርገው "ጥፋቱ እንኳ የእኔ ነው። አውቃለሁ

ብዬ ይገር መጥቼ አለፋኋቸው። ስንትና ስንት ጊዜ የተመላለስኩበት መንገድ ጠፋብኝ። ግሩም እኮ ነው" አሉ በቁጭት።

ሁላችንም እየተቀባበልን "እንዴ ከዚህ በላይ መንገድ መምራት እንዴት ነው? በእውነቱ በጣም ሊመሰገኑ ይገባል" ብለን ከልብ አጽናናናቸው።

"ከዚህ በኋላስ መንገዱ ያስቸግር ይሆን?" ሰል ጠየኳቸው።

"አይ ከዚህ በኋላ እንኳን በጣም ግልጽ መንገድ ነው። እንኳን ከዚህ ደረሳችሁ እንጂ" አሉን።

መኪናውን ያቆምንበትን አካባቢ ምልክት ስንነግራቸውም ሰው ልከው እንደሚያስጠብቁት ነግረው ቀሪ ጉዟችንን መንገዱን አሳይተው ሸኙን።

ይህ መንገድ ግልጽ ሲሆን ከፍታው ቀስ በቀስ እየጨመረ የሚሄድና በዛፎች መካከል የሚያልፍ በመሆኑ ለጉዞ ምቹ ነው። ከተወሰነ ጉዞ በኋላ ስንዳክር የዋልንበት በጫካ የተሸፈነ አውላላ ሜዳ በገንዳ ውኃ ወንዝ ታጥሮ መመልከት ቻልን። ቁልቁል ሲመለከቱት ከሚንቀለቀለው የፀሐይ ብርሃን ሞገድ፣ አረንጓዴው ዕፅዋት፣ ከደረቀው ሣር ጋር ሲታይ ለዐይን ምግብ ነው።

ይሁንና በዚህ ዐይን አስኪታክት ድርስ በተንጣለለው የበረሓ ደን ውስጥ ከተጻፈልኝ ስሙ በስተቀር ለይቼ የማላውቀውን አንድ ዕፅ እንዴት አድርጌ ፈለጌ ማግኘት እንደምችል ሳስብ ሀሞቴ ፍስስ አለ። ያለችኝ አንዲት ተስፋ መናንያኑን መጠየቅ ነው። ያውስ የተቆለፈው ምሥጢራዊ ልባቸው ቢከፈትልኝ አይደል?!

ከአንድ ሰዓት የእግር ጉዞ በኋላ ‹ግዝት በር› ከሚባለው ደረስን። ከግዝት በር ሆኖ የገዳሙ ቤተ ክርስቲያን ከትልቅ ተራራ አናት ላይ ጥቅጥቅ ያለ አረንጓዴ ካባ ለብሶ ይታያል። ‹ግዝት በር› ከዚህ

ተራራ ሥር የሚገኝ የተራራው መውጫ ሰርጥ መጀመሪያ ነው። በሰፊ ኮንክሪት መደብ ላይ የተተከለ ትልቅ የብረት መስቀል አለው። ከጎኑ በቆርቆሮ በጉልህ የተጻፉ ማስጠንቀቂያዎች አሉ።

1. ቅዳሜና እሑድ ከዚህ ዐልፎ ወደ ቤ/ክኑ መሄድ አይቻልም፤
2. ለሴቶች መግባት ክልክል ነው፤
3. ማንኛውም የበሰለ ምግብና የታሸገ መጠጥ ይዞ መግባት አይፈቀድም፤
4. ጫማ አድርጐ መግባት ክልክል ነው ይላል።

"የፈጣሪ ያለህ!" አልኩ።

አሁን ባለሁበት ሁኔታ ሰውነቴ በበረሓሃው ጥማት ውስጥ (Dehydrated) ነው። እንኳን ጫማ አውልቄ ቀርቶ እስከ ጫማዬም እግሮቹ ዝለዋል። "ይባስ ደግሞ ጫማ አውልቆ መሄድ!" አልኩ ለራሴ በምሬት።

ይሁን እንጂ ትእዛዙን አክብሮ ከመቀጠል በቀር አማራጭ አልነበረኝም። ቄስ ገዳሙ መቸገራችንን ሲያዩ "አይዟችሁ የገዳሙ በረከት እንዲደርሳችሁ እኮ ነው፤ ቀላል ነው" አሉ።

አብረውኝ ከተጓዙት መካከል ዳዊት የሚባለው የገዳሙ ደን በሕግ ዕውቅና ሲሰጠው በፈቃደኝነት 19 ሺህ ሄክታሩን በእግራቸው እየዞሩ ከከለሉት ሁለት በጎ ፈቃደኛ ባለሙያዎች አንዱ ነው። ቀጭንና ጠንካራ አቋም ያለው ወጣት የደን ባለሙያ ነው። እርሱ ከፊት ለፊት መምራቱን ተያያዘው። የመሬቱ ግለት የጋለ ብረት ምጣድ የመርገጥ ያክል ይሰማል። ባዶ እግርን መሬት ላይ አሣርፎ መቆየት አይቻልም፤ ሙቀቱ ይለመጥጣል። በተቻለ ፍጥነት እግርን እያፈራረቁ በማንሣት ወደፊት መገስገስ ብቻ ነው አማራጩ። ችግሩ ቀጥ ያለው ዳገት ደግሞ ልብ ያጠፋል።

ከዳገቱ መካከል ስደርስ ስቃዩ ልቤ ድረስ ዘልቆ ተሰማኝና፡-

"ወደዚህ ቦታ የላኩኝ፣ በዚህ ሁኔታ እንድራመድ ያዘዙኝ ምን ያክል ቢቀየሙኝ ነው?" አልኩ። እጅግ ተዳፍሬአቸው ትዕግስታቸውን እንደተፈታተንኩት ገባኝና ተጸጸትኩ።

ከአርባ ደቂቃ የሰቃይ ጉዞ በኋላ ገላጣውና ዓለታማው የተራራ መጀጠጥ መንገድ አልቆ ከቤተ ክርስቲያኑና ከመነኮሳቱ መኖሪያ ጥቅጥቅ ባለ ደን ወደ ተሸፈነው ሰፍራ ዘልቀን ገባን። በቃ የመሬቱ ቅዝቃዜ፣ ነፋሻማው አየር፣ ከሲኦል ወደ ገነት የመግባት ያክል ዕረፍት ይሰጣል። በረገፉ ቅጠላቅጠሎች ከተሞላው መሬት ላይ በጀርባዬ ተዘረርኩና እግሮቼን ወደላይ ዘርግቼ የውስጥ እግሮቼን ከቀዘቀዘው አየር ላይ አናፈስኳቸው። አፌ ደርቋል፣ ምላሴ ከጉሮሮዬ የተጣበቀ መሰለኝ፣ ሰውነቴ በከፍተኛ ጥማት ውስጥ እንዳለ ተረድቻለሁ። እንደዚህ ያለ ድካምና የሰውነት ዝለት ገጥሞኝ አያውቅም።

ለጥቂት ደቂቃዎች ዕረፍት ካደረግን በኋላ ስንነጋገር ሹፌራችን እንዳልደረሰ ተረዳን። ጠበቅን፤ ግን ብቅ አላለም። በዚህ ሰዓት ተመልሶ ወደ ተራራው ግርጌ በመውረድ ርዳታ ለማድረግም ሆነ ደኅንነቱን ለማረጋገጥ አቅም ያላቸው ሰው ቁስ ገዳሙ ብቻ ነበሩ። እንደፈረደባቸው ተመልሰው ሄዱና እያበረታቱና እየደገፉ ይዘውት ደረሱ። በቃ ሙትት ብሏል።

ከድካሜ ዐርፌ ትንሽ አቅም ያገኘሁ ሲመስለኝ አካባቢውን ቆሜ መቃኘት ጀመርኩ። በቀዝቃዛውና ጥቅጥቅ ባለው ደን ውስጥ ግድግዳቸው ከቆላ ቀርቀሃ ጣራቸው በሣር ክዳን የተሠሩ ቤቶች በሥርዐት ተደርድረዋል። ሁሉም ቤቶች ከጀርባቸው አነስተኛ መፀዳጃ ቤቶች አሏቸው። የተራራውን ተዳፋት በመቀነስ ጎርፍን ለመከላከል በድንጋይ የተሠራው ጎዳግ በየረድፉ ሲታይ ዐይን ይማርካል። በርካታ ገዳማትን የማየት ዕድል ቢገጥመኝም እንደዚህ ፅድት ያለና ሥርዐት የሞላበት ማየቴን አላስታውስም።

ቀስ እያልኩ ወደ ተራራው ጫፍ ወደ ቤተክርስቲያኑ ሳመራ ሌሎቹም ተከተሉኝ። ከቤተ ክርስቲያኑ ከመድረሳችን ጥቂት ቀደም ብሎ በስተግራ በኩል ከቆርቆሮና ከሣር ክዳን የተሠሩ ሰፋፊ ቤቶች ይታያሉ። ‹የተግባር ቤት› የሚባሉት መሆናቸው ነው። በገዳማት ሥርዐት መሠረት ለመናንያኑ ምግብና መጠጥ በአንድነት የሚዘጋጅባቸው ቤቶች ‹ተግባር ቤት› ይባላሉ። ከአቅራቢያቸው በማምት ዐሥር ሜትር በሰድስት ሜትር የሚሆን በጥቁር ፕላስቲክ የተለበደ ውኃ የተሞላ ማቆሪያ አለ። እርሱን ዐልፈን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አመራን። በድንጋይና በስሚንቶ በተገነባ ግንብ ዙሪያውን የታጠረ ሲሆን ሰማያዊ የብረት በር ተገጥሞለታል። ወደ በሩ ተጠግቼ በግንባሬ ተደፍቼ ተሣልሜ ቀና ስል በብረት ሰሌዳ ላይ በጉልህ የተጻፈ ጽሑፍ አየሁ። ጠጋ ብዬ ሳነበው ወሸመጤ ቁርጥ አለ።

> “ከውጭ የመጣ ማንኛውም መንገደኛ ሰባት ቀን ሳይሞላው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅፅር ግቢ መግባት አይቻልም” ይላል።

“ወይ ፈጣሪዬ! አሁን እንዳመጣ የታዘዝኩት ዕፅ ከቅፅር ግቢው ውስጥ ቢሆን ከዚህ ቦታ ሰባት ቀን ልቆይ ነው ማለት ነው? ሥራዬስ? ኑሮዬስ?” ብዬ በጣም ተማረርኩ። በሰማያዊው በር አጮልቄ ወደ ውስጥ ስመለከት ከቅፅሩ ውስጥ ያሉት ዛፎች በሙሉ ከውጭ ካሉት ጋር አንድ ዐይነት መሆናቸውን ሳይ ተጽናናሁ።

ወዲያው ቄስ ገዳሙ ከአንድ ወጣት መነኩሴ ጋር መጡና “ወደ ተግባር ቤቱ እንሂድ” አሉን።

በቆርቆሮ ከተሠራው አዳራሽ በረንዳ ላይ ሁለት መነኮሳት በገበታ ውኃ አዘጋጅተው ይጠባበቃሉ። “እግራችሁን ታጠቡ” ተባልን። በዚህ ወቅት በቀዝቃዛ ውኃ እግርን መታጠብ ፍቱን መድኃኒት ነው።

ችግሩ ግን እግራችንን የሚያጥቡን መነኩሳቱ መሆናቸው ነው። አይሆንም ብለን ብንከራከርም የገዳሙ ሕግ ስለሆነ አይቻልም ተባልን።

እኔ እንድታጠብ ቅድሚያ ተሠጠኝ። ሱሪዬን ወደ ላይ ከፍ አደረጉና ተንበርክከው ጭኔ ድረስ እሸት አድርገው አጠቡኝ። ማሳጅ ማለት ነው። ቀዝቃዛው ውኃ እግሬን ሲነካው አፌ ውስጥ ከፍተኛ ጥማት ተሰማኝ፤ ጭራሽ ጉሮሮዬ ደረቀ።

"ጉሮሮዬ ደረቀ" አልኩ ሰፈራ ስቸር።

ቄስ ገዳሙ ቀበል አድርገው፡-

"ከዘጠኝ ሰዓት በፊት ከዚህ ቦታ ምንም ነገር መቅመስ አይፈቀድም ትንሽ ታገስ" አሉኝ።

ሰዓቴን ሳይ 8፡25 ይላል። ስገምት በቀረችው 35 ደቂቃ ውስጥ በውኃ ጥም የምሞት መሰለኝ። እግሬን አጥበውኝ ሲያበቁ የእግሬን ጫማ ከፍ አድርገው ሲስሙት፤

"ወይ ፈጣሪዬ! ምነው ጎጠአቴን ባታበዛው" አልኩና

"ፊቴን ልታጠብ እባክምት?" ብዬ እጄን ዘረጋሁ። በእፍኜ እየሞላሁ ፊቴን ልታጠብ ስል የበረሓ ልምድ ያለው ባለሙያው ዳዊት፡-

"እንዳትታጠብ! ፊትህ ይበልዛል ትንሽ ቆይ" ሲለኝ ተጐነጨሁና አፌን ተጉመጠመጥኩ። ድጋሚ በእፍኜ ሲያደርጉልኝ ተጐነጨሁና ረዘም ላለ ጊዜ በጉንጬ ያዝኩት። ልውጠው ዳዳኝና ብቀሰፍስ፣ የመጣሁበት ጉዳይ ቢበላሽብኝስ የሚሉ ሐሳቦች ደግሞ አስጨነቁኝ። ውኃ ጥሙ ደግሞ ባሰብኝ። በጉንጭ ያለ ውኃ የማይጠጣበት ጊዜና ሁኔታ ያጋጥማል ብዬ አስቤ ስለማላውቅ ተፈተንሁ። ፍርሀቴና ጥማቴ ሲታገሉ ከቆዩ በኋላ ሚዛናዊ የሆንኩ መስሎኝ ግማሹን

ወደ ውጭ ተፍቼ የቀረችውን ሰርቄ ወደ ጉሮሮዬ ላኳት። ነፍሳ
የተመለሰች መሰለኝና "እፎይ" አልኩ።

ሁላችንም ታጥበን እንዳበቃን የገዳሙ ግምጃ ቤት ኃላፊ ሊያናግሩን
እንደሚችሉ ተነገረንና ሄድን። ከቤተ ክርስቲያኑ አጥር ጋር ተያይዞ
የተሠራ ትልቅ ዕቃ ቤት ያለ ሲሆን የእንግዳ መቀበያና ማረፊያ
ሰፋ ያለ እልፍኝ አለው።

ሰልካካ ፊት ያላቸው፣ ጠይም፣ ቀጭን፣ በግምት 45 ዓመት አካባቢ
የሚሆናቸው ሰው ቁመው በትሕትናና በፈገግታ ተቀበሉን።
በመስቀላቸው ከባረኩን በኋላ፡-

"አባ ኪዳነ ማርያም እባላለሁ፤ እንኳን ደኅና መጣችሁ" አሉና
ዳዊትን በተለየ ሁኔታ አቅፈው በፍቅርና በናፍቆት ሳሙት።
ዳዊት በዚህ ገዳም ውስጥ በባለውለታነቱ በናፍቆት የሚታሰብ
የተባረከ ወጣት ሆኗል።

ቁጭ እንድንል ከጋበዙን በኋላ "የገዳማችን አስተዳዳሪ አበምኔቱ
ለጊዜው የሉም። እርሳቸውን ተክቼ የማነጋግራችሁ ቢሆንም የሥራ
ድርሻዬ ግምጃ ቤት ወይም በእናንተ አጠራር ስቶር ኪፐር ነው"
አሉ ፈገግ ብለው። ፈገግ ሲሉ በፍሎራይድ የበለዙት ጥርሶቻቸው
ያደጉበትንና ትተውት የመጡበትን አካባቢ በሚያሳብቅ ሁኔታ
ከታዩ በኋላ ቶሎ ወደ ጓዳ እንደምተገባ ዐይንአፋር ልጃገረድ
በከንፈራቸው ውስጥ ድብቅ አሉ።

የክፍሉ ቅዝቃዜ መተማ በረሓ ውስጥ ሳይሆን የሆነ ማቀዝቀዣ
የተገጠመለት የስብሰባ አዳራሽ ይመስላል። የሆነ ሰላም ይሰጣል።

ወዲያው አባ ኪዳነ ማርያም ስለገዳሙ ገለጻ ያደርጉልን ጀመር።
እኛም በንቃት መከታተል ያዝን።

ገዳሙ በአራተኛው ክፍለ ዘመን እንደተመሠረተ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በውጭ ጠላቶች ከሰባት ጊዜ በላይ ተቃጥሎ እንደነበር በሐዘኔታ ገለጹልን።

"የገዳሙ ዋና አባት አቡነ አምደ ሥላሴ በ15ኛው ክ/ዘመን ዐፄ ሱስንዮስን የፈወሱና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ብሔራዊ ሃይማኖት ሆ' እንድትቀጥል ያስቻሉ አባት ናቸው" አሉ።

"እንዴት? አልኳቸው ጣልቃ ገብቼ።

"ዐፄ ሱስንዮስ በሚሲዮናውያን ግፊት የካቶሊክ እምነትን ተቀበሉ። መቀበል ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን አወጁ። በዚህ የተነሣ ከፍተኛ ደም መፍሰስን አስከተለ። የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ሊቃውንትና መነኮሳትም የሞትና የመሰደድ እጣ ገጠማቸው። አባታችን አቡነ አምደ ሥላሴ ጥቂት የመንፈስ ልጆቻቸውን አስከትለው ወደ ግብጽ ተሰደዱ። ይሁን እንጂ ብዙም ሳይቆዩ ዐፄ ሱስንዮስ በጸና ታመመ። ምላሳቸው ተጐልጉሎ ወጥቶ እንደ ውሻ ማለክለክ ዕጣቸው ሆነ። ጣና ሐይቅ ውስጥ በሚገኘው የዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም በመንፈሳዊ ትምህርት ተኮትኩቶ ያደገው ልጃቸው አቤቶ ፋሲልም ‹አባቴ ምናለ የአባቶቻችንን የዘርዐያዕቆብን፣ የዐፄ ዳዊትን ሃይማኖት ብንከተል?› እያለ ቀደም ብሎ ያሳስባቸው ነበር። ሕመማቸው ሲጸና ይቅርታ እንዲደረግላቸው፣ ጸሎት እንዲደረስላቸው ወደ ገዳም አባቶች ተላከ። በዚህ ጥሪ መሠረት አባታችንም ከስደት ተመልሰው ሌሎች አባቶችን አስከትለው ሰባት ቀን እየጸለዩ ሲያጠምቋቸው ዐፄ ሱስኒዮስም ከደዌያቸው ተፈወሱ። በመጨረሻ ቀድሰው አቆረቧቸው። ንጉሡም ስሕተታቸውን አምነው፣ በተደረገላቸው ምሕረት ተደስተው ‹ተዋሕዶ ሃይማኖት ይመለስ፤ ፋሲል ይንገሥ› ብለው ዙፋናቸውን ለልጃቸው ለዐፄ ፋሲል አወረሱ። እና በዚህ የተነሣ ይህ ገዳም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ልዩ ክብርና መወደድን አተረፈ" አሉና

"በአሁኑ ሰዓት ከ250 በላይ መናንያን የሚኖሩበት ገዳም ሲሆን ዋና መተዳደሪያችንም እንስሳት በማርባት ነው። በመጠኑም ቢሆን እርሻም አለን" ብለው ገለጻቸውን ያጠናቀቁ ሲመስለኝ።

"ከደኑ የምታገኙት ጥቅምስ?" አልኳቸው።

"ደኑን የምንጠብቀው የሀገር ሀብት፣ የአባቶቻችን ቅርስ ስለሆነ ነው እንጂ እስከ ዛሬ ድረስ በገቢ ምንጭነት አስበነው አናውቅም" አሉ።

"ምን ያክል ከብቶች አሏችሁ?" ሁለተኛ ጥያቄ ነበር።

"ያው ወይፈኖች በየጊዜው ስለሚሸጡ ወዲያውም የሚወለዱ ጥጆች ስላሉ በቁጥር ይህን ያክል ነው ማለት አልችልም፤ ብቻ ገዳሙ ራሱን ችሎ ለመኖር በቂ ናቸው" አሉ አባ።

ቁጥሩን ለመናገር የፈቀዱ አይመስልም። በኋላ ላይ እንደተረዳሁት ግን ከ600 በላይ ላሞችና ወይፈኖች እንዲሁም ለዕቃና ለእህል ማጓጓዣ የሚያገለግሉ ከ200 በላይ አህዮች እንዳሏቸው ይታመናል።

በዚህ መልኩ የገዳሙን ሥርዐትና ሌሎች እጅግ የሚገርሙ አደረጃጀቶቻቸውን ሲነግሩን ቆዩ። በእኔ በኩል ግን የመጣሁበትን ጉዳይ ለመጠየቅ ብቻችንን የምንሆንበትን አጋጣሚ መጠበቅ ነበረብኝ። በመጫል እነዳዊት የመጡበትን የቆላ ቀርቀሃ ልማት ጉዳይ አነሡ። የቆላ ቀርቀሃ ለወረቀት ፋብሪካ ግብዓት ሊሆን እንደሚችልና በአሁኑ ወቅት በተፈጥሮ ለምዶ ከሚገኝበት አካባቢ አንዱ የማጎበረ ሥላሴ ገዳም እንደሆነ በማብራራት ትኩረት አድርገው እንዲያለሙትና እንዲንከባከቡት ለመወያየት እንደመጡ አስረዱ።

አባም በፈገግታ "እኛ እስከ አሁን ስንጠብቀው የነበረው እንደማንኛውም ዕዕዋት መጠበቅ ስላለበት እንጂ ለፋብሪካ ጥሬ ዕቃ ሆኖ ጥቅም ይሰጠናል ብለን አልነበረም። ለወደፊቱ በዚያ መልኩ የሚያገለግል ከሆነ ለእኛ ከሚሰጠው ጥቅም ይልቅ ለሀገር ልማት አስተዋፅኦ ማድረጉ ትልቅ ደስታ ይሰጠናል። እናም መልካም ዜና ነውና እንክብካቢያችንን እናጠናክራለን" ብለው ቀና ፍላጐታቸውን ገለጹላቸው።

በጉዳዩ ሰፋ ያለ ውይይት አድርገው ሲጨርሱ፡-

"ሌላ የምትጠይቁት ጥያቄ አላችሁ?" አሉ በትሕትና። እኔም ቀበል አደረኩና፡- "አባታችን በዚህ ገዳም ውስጥ በርከት ያሉ የተማሩ ሰዎች ከሀገር ውስጥም ከውጭም ከዩኒቨርሲቲና መሰል ከፍተኛ ሙያ ትተው የመጡ አሉ ይባላል፤ እውነት ነው?" አልኩ።

አባ ጺማቸውን እያፍተለተሉ በፈገግታ ወደ እኔ ሲመለከቱ የማይረባ ጥያቄ እንደጠየኩ ገባኝ። አባ እንዲህ አሉ፡-

"አየህ የእኔ ወንድም! አንድ ሰው ወደዚህ ስፍራ ለምናኔ ሲመጣ የሚጠየቀው ነገር ቢኖር የገዳሙን ሕግና ሥርዐት አክብሮ ለመኖር መወሰኑንና ፈቃደኛ መሆኑን ብቻ ነው። በቅድስናም ይሁን በበደል፣ በባለጸጋነትም ይሁን በድህነት፣ በዕውቀትም ይኑር በማይምነት ያለፈ ታሪኩ አይጠቅምም። እኛም አንጠይቅም፤ እርሱም አይነግረንም። እና ጥያቄህን ለመመለስ ሊኖሩም ላይኖሩም ይችላሉ" አሉ ፈገግ ብለው።

ጥያቄያችንና ውይይታችን ማለቁን ሲረዱ የስጋጃ ምንጣፍ አስነጠፉና እንድንንበረከክ ጠየቁን። ከሌሎች ሁለት መነኮሳት ጋር ሆነው ጸሎት ካደረጉ በኋላ በትልቅ የእንጨት መስቀል ጀርባችንን እየዳሰሱ ጸሎት አደረጉልን። የሆነ ነገር ከላዬ ላይ ለቆኝ የሄደ መሰለኝና፡-

"እንደ ውኃ ባልዲ በራሴ ላይ አጋንንት ተሸክሜ ነበር እንዴ የምዞር! ወይ ጉድ!" ስል ዳዊት "ምን አልክ?" አለኝ። በልቤ የማንሾካሹክ መስሎኝ ለካስ ከአፌም ተሰምቶ ኖሯል።

"አይ! የጸበሉ ነገር ገርሞኝ ነው እንጂ" አልኩ እንደማፈር እያልኩ።

# ምዕሁፍ ለዓለት

ኣሎቱ ሲ,ያበቃ ሰው ወደ ውጭ ሲወጣልኝ የመጣሁበትን እጠይቃለሁ እ,የልኩ ስዘ,ጋጅ አባ ኪዳነ ማር,ያም፡-

"እስኪ አካባቢውን ላስጐብኛችሁ ተከተሉኝ አሉና ከሰሜን አቅጣጫ ከሚገኘው ቤታቸው የምዕራብ አቅጣጫን ይዘን የቤተ ክር቎,ያኑን የግንብ አጥር በስተውጭ ተከትለን መራመድ ጀመርን። ከዱር እንጨት የተዘ,ጋጀች ቀጭን ከዘራ ይዘዋል። ከፊት ለፊት ሲራመዱ መሬቱን የሚረግጡት አይመስልም። በቃ ረ,ጋ ያሉ ሲናገሩ ፊገግታ የማይለያቸው ናቸው።

አባ ቀጠሉና "ሁሉም መናኝ የራሱ መኖሪያ በኣት አለው። በተጨማሪም መፀዳጃ ቤት እንዲኖረው የግድ ነው" አሉ።

አካባቢው ዛፎች ከፊጠሩት ቀዝቃዛ ድባብ በተጨማሪ ዕዳቱ ልዩ ግርማን አላብሶታል። ከወፍ ጫጫታ ውጭ የሚሰማ ቢኖር ‹እሽም እሽም› የሚለው በእጅ የሚገፉ የድን,ጋይ ወፍጮ ድምፅ ብቻ ነው።

የመናንያኑ ቀለብ የሚፈጨው በእጅ ነው። በስተደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ስንደርስ አንድ ሰው ከውጭ ወደ ቤት ሲገባ ተመልከቺ ሰውነቴ ስንጥቅ አለ። የማውቀው ሰው መሰለኝ። ይሁን እንጂ እዚህ ሊመጣ የሚችልበት አጋጣሚ ስለሌለ በአጋጣሚ መመሰሉ ነው ብዬ ተውኩት።

በዚያው አቅጣጫ ስንደርስ ከቆምንበት ትንሽ ራቅ ብሎ በድንጋይና በኖራ ተሠርቶ የነበረና የፈራረሰ የውኃ ማጠራቀሚያ ተመለከትን። እንደ አባ ገለጻ ከሆነ የገዳሙን ውኃ ችግር ለመቅረፍ በንግሥት ዘውዲቱ መልካም ፈቃድ የተገነባ የውኃ ማቆሪያ ነበር ። የገዳሙ አጠቃላይ ክልል በሁለት ቋሚ ወንዞች የተከበበ ነው ። በስተሰሜን በኩል ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የገዳሙን ደን እያካለለ የሚፈሰው የገንዳ ውኃ ወንዝ እንዲሁም በስተደቡብ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የሚፈሰው የሸንፋ ወንዝ አለ። እነዚህ ወንዞች ዓመቱን በመሉ የሚፈሱ ትልልቅ ወንዞች ቢሆኑም ዋናው ገዳም ማለት ቤተ ክርስቲያኑና የመናንያኑ መኖሪያ ከተራራው አናት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ከአንድ ሺህ ሜትር በላይ የከፍታ ልዩነት ያለ ሲሆን ከሰምንት ኪሎ ሜትር በላይም ከቤተ ክርስቲያኑና ከመነኮሳቱ መኖሪያ አካባቢ ይርቃሉ። ከእነዚህ ወንዞች ውኃ ቀድቶ ወደ ተራራው እያጓጓዙ ለመጠቀም እጅግ ከባድ በመሆኑ በወቅቱ ንግሥት ዘውዲቱ ሦስት መቶ ሜትር ኪዩብ ውኃ የማጠራቀም አቅም ያለው የግንብ ጋን አሠርተውላቸው የክረምቱን ውኃ ጋኑ ውስጥ በማቆር ቢጋውን ሲገለገሉበት ነበር ።

በጣልያን ወረራ ጊዜ የኢትዮጵያ ገዳማት የአርበኞችን የሀገር ፍቅር ስሜት በማነሣሣት፣ ሞራላቸውን በመገንባት እንዲሁም ሲል መሸሸጊያና የቁስለኛ ማገገሚያ በመሆን ከፍተኛ ድጋፍ ይሰጣሉ በሚል እሳቤ የጣሊያን ጀኔራሎች ይህን የውኃ ማጠራቀሚያ ጋን በሁለት የጦር አውሮፕላኖች በቦምብ እንዲፈራርስ አደረጉት። በዚህም ሠልጥነናል ከሚሉ ሀገሮች የማይጠበቅ አረመኔአዊ ድርጊት ፈጽመው አልፈዋል። በእርግጥ እንደ አባ ገለጻ አውሮፕላኖቹ

ድብደባውን ከፊጸመ በኋላ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ የግዳመ ክልል ውስጥ መከስከሳቸውንና ስብርባሪያቸውም እስከ አሁን ድረስ እንደሚገኝ ገልጸውልናል። ከዚህ በኋላ ለረጅም ጊዜ በውጭ ሽግር ሲሠቃዩ ኑረው በቅርብ ጊዜ ከፊራረሰው ጋር ተቀራራቢ የሆነ አቅም ያለው የውኃ ማጠራቀሚያ ጋን አሰገንብተው ሕይወት በገዳመ ውስጥ በተረጋጋ ሁኔታ እንዲቀጥል አስችለውታል ።

በስተደቡብ አቅጣጫ ስንደርስ የቤተ ክርስቲያኑ የግንብ አጥር በር ተከፍቶ አገኘነው። አባ በያዙት ከዘራ የሆነች ትንሽ ቤት አመለከቱን። ከቤተ ክርስቲያኑ በስተምሥራቅ አቅጣጫ በሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑና በግንብ አጥሩ መካካል ላይ የተገነባች ግድግዳዋ ከቆላ ቀርቀሃ የተሠራ ጣራዋ ደግሞ በክብ ቅርፅ በቆርቆሮ የተከደነ ሲሆን በዕድሜ ብዛት ይመስላል ቆርቆሮው ዝጓል።

"የምን ቤት ነች?" አልኳቸው።

" የዐፄ ቴዎድሮስ መቃብር ቤት ነው" አሉ።

"እንዴት ሆኖ ?" አልኳቸው በመገርም።

"አምን ጥያቄህ ይገባኛል" አሉ።

ዐፄ ቴዎድሮስ እንደሚታወቀው ከእንግሊዞች ጋር በአደረጉት ጦርነት ድል ለእንግሊዞች መሆኑን ሲረዱት እጄን ለጠላት አልሰጥም በማለት ከምሽጋቸው መቅደላ ላይ ራሳቸውን እንደገደሉ፣ መቃብራቸውም በዚያው በመቅደላ አምባ እንደሆነ ስለአነበብኩ ነበር መገረሜ የመነጨው ።

አባ በተለመደው እርጋታቸው.

"እርግጥ ዐፄ ቴዎድሮስ ሕይወታቸው ያለፈውና ዘመጀመሪያ የተቀበሩትም በመቅደላ አምባ በአሁኑ ደቡብ ወሎ ነው። ይሁንና

ከጊዜ በኋላ በልጅ ልጃቸው ደጃዝማች መሸሻ አማካኝነት ወደዚህ አጽማቸው ፊልሶ እንዲመጣ ተደርጓል" አሉ።

" ለምን? ማለት ምክንያቱ ምንድን ነው?" አልኩኝ ቀጥዬ።

"ያው በታሪክ እንደሚታወቀው ዐፄ ቴዎድሮስ የልጅነት ጊዜያቸውን በዚህ ገዳም በትምህርት አሳልፈዋል። የቤተ ክህነቱን ትምህርት ከመማራቸው በተጨማሪ የግእዝና የዐረብኛ ቋንቋን ጠንቅቀው የተማሩት በዚህ ገዳም ነበር። ከታላላቅ አባቶች ጋር በነበራቸው ቅርበት የአስተዳደር ዘይቤን፣ የማዕከላዊ መንግሥት አስፈላጊነትንና የጥበብንና የዕውቀትን ጥቅም የተረዱበት ቦታ ነበር ። ከገዳሙ ከወጡ በኋላ ደጃዝማች ተብለው በቋራና አለፋ ሲንቀሳቀሱ ከሠራዊታቸው መካከል ጥቂቶች ወደ ገዳሙ መጥተው ሳያስፈቅዱ የገዳሙን ከብቶች አርደው በሉ። በዚህ ድርጊት የገዳሙ አባቶችም ‹እንዴት ያሳደግነው ልጅ ሲሆን ሲሆን የገዳሙ ጠበቃ ይሆን ነበር አለበለዚያ ለምን በውንብድና የመናንያኑን ንብረት ይቀማል› ብለው እጅግ አዘኑ። የገዳማያውያኑን ሐዘንና የወታደሮቻቸውን ነውር የተረዱት ደጃች ካሳ የገዳሙ አባቶች መቀየም ምን ሊያስከትል እንደሚችል ስለሚያውቁ እየደበሉ ወደ ገዳሙ መጡ። ድርጊቱ ከእርሳቸው ዕውቅና ውጭ የተፈጸመ በመሆኑ የታረዱትን ከብቶችም እጥፍ አድርገው እንደሚመልሱ ቃል ገብተው ይቅርታ እንዲደረግላቸው ተማፀኑ። አባቶችም ቅያሜያቸውን አነሡ ። ደጃች ካሳም አስከትለው እንዲህ አሉ፡-

‹አባቶቼ በእውነት ይቅርታ አድርጋችሁልኝ ከሆነ ቃል ግቡልኝ› አሉ።

አባቶችም የተጠየቁትን ሊያደርጉ ፈቃደኛ መሆናቸውን ሲገልጹ፤ ካሳም እንዲህ አሉ፡-

‹እኔ ወታደር ነኝ። የት እንደምወድቅ አላውቀውም። ነገር ግን በሞትኩ ጊዜ ሥጋዬ ከሥጋችሁ ዐፅሜ ከዐፅማችሁ ጋር አብሮ እንዲያርፍ የትም ቢሆን አስመጥታችሁ በዚህ ቦታ እንድታሳርፉኝ› ብለው ቃል ያስገቧቸዋል። በዚህ መሠረት የገዳሙ አባቶች የልጅ ልጃቸውን አሳስበው ዐፅማቸው ወደዚህ መጥቶ በኑዛዜያቸው መሠረት ከሚወዱቸው አባቶቻቸው ጋር በክብር እንዲያርፍ ተደርጓል” አሉኝ።

መቃብራቸው ላይ ሂጄ ባለቅስ ደስ ባለኝ። ነገር ግን ሰባት ቀን ስላልሞላኝ ቅጽር ግቢው ውስጥ መግባት አልተፈቀደልኝም ። የዚህች ሀገር ዜጎች ቃል ኪዳንና ፍቅር ድርና ማግ ሆኖ ኖሮ አሁን ከእኛ ዘንድ ሲደርስ ውሉ የጠፋበት የማግ ልቃቂት የሆነ መሰለኝና በቃ ሆድ ባሰኝ።

ብቻ በርቀት ሳየው መቃብሩ የኢትዮጵያን አንድነት የመለሰ ጀግና፣ ለሥልጣኔና ለጥበብ ዕድሜውን ሙሉ የደከመ ብልህ፣ የምእተ ዓመቱ ምርጥ መሪ እያልን በየሚዲያው የምንለፍፍለት፣ በየዘፈኑ አንስተን የማንጠግበው ተምሳሌት፣ የታላቁ ሰው መቃብር ለመባል አይመጥንም እያልኩ ሳንሾካሸክ አብረውኝ ከነበሩት አንዱ የእኔ ስሜት ተጋብቶበት ነው መሰለኝ፦

“አይ ጉድ! እንዲያው ምናለበት ዐፅማቸው በመስታዎት ሳጥን ሆኖ ቢቀመጥ?” አለ።

አባ ፈገግ ብለው “ወደፊት ይሆን ይሆናል” አሉ። ቀጠል አድርገውም፦

“ለማንኛውም ጀግናው ሰው የመጨረሻው ማረፊያው እዚህ እንዲሆን የነበረው ምኞቱ ተፈጽሞለት የልጅነት ጊዜውን በዕውቀት ፍለጋ ካሳለፈበት ገዳም ከሚወዳቸው መናንያን ጋር በሰላም ማረፉ በቂ ይመስለኛል” አሉ።

አባ ወደፊት መራመድ ሲጀምሩ አሁን አብረውን የመጡትን ራቅ እንዲሉልኝ አስፈቅጄ የመጣሁበትን የዕውን ጉዳይ መፈለግ አንዲረዱኝ ለመማፀን እያሰብኩ እያለ፡-

"አንድ ትልቅ አባት አሉ። ወደ እርሳቸው ሂደን ቡራኬያቸውን ብትቀበለ መልካም ነው" አሉና የእኛን ምላሽ ሳይጠብቁ ወደ ታች ወደ ደኑ ወረድ ብለው መሄድ ጀመሩ፡ እኛም ተከተልን።

አንዲት ዕድት ያለች ጎጆ ቤት ደረስን። ዙሪያዋ በስሚንቶ የተሠራ የውኃልክ ያላት ሲሆን ወለሏም በስሚንቶ በጥሩ ሁኔታ ሊሸ ሆኗል። መቀቱን ለመከላከል ይመስላል ግድግዳው በቆላ ቀርቀሃ ነፍስ እንዲያስገባ ተደርጎ ተገርግሯል። ብቻ በአካባቢው ከከበቧት የጥላ ዛፎች ጋር ተዳምሮ ልዩ ግርማ አላት። አባ ወደ በሩ ጠጋ ብለው፡

"አባታችን እንደምን ዋሉ?" አሉ።

"እግዚአብሔር ይመስገን፤ ማነህ?" የሚል መልስ መጣ።

"አባ ኪዳነ ማርያም ነኝ፤በኔ ዋሉ?" አሏቸው።

"ይመስገነው ደኅና ነኝ፤ ብቻ ይፀኞ ወባ ደግሞ ተነሣችብኝ መሰል።"

"እንግዶች ሊያገኙዎት ይፈልጋሉ።"

"ግቡ እንጂ ታዲያ ምን አለ?" አሉ። አባን ተከትለን ገባን።

በትንሽ አልጋ ላይ አባ ተጣጥፈው ተኝተዋል ። መጻሕፍቶቻቸው በአግዳሚ ዕንጨት ላይ ተደርድረዋል። እንድ ቀሚስ፡ አንድ ፎጣ፡ አንድ ጋቢ ብቻ በገመድ ላይ ተንጠልጥለዋል። ከበኣታቸው ሲወጡ የሚለብሷቸው መሆናቸው መሰለኝ። በአንድ ጥግ ደግሞ ኩባያና ጎድጓዳ ሳህን ብቻ የሚታዩ ሲሆን በተረፈ ቤቱ ንጹሕና ባዶ ነው።

ከመኝታቸው ተነሥተው አልጋቸው ላይ ቁጭ ብለው ሁላችንንም አላለሙን። ተቀምጠውም ቢሆን ረጅም ሊባሉ የሚችሉ መሆናቸው ከእጅ ጣታቸው ሎጋንትና የእግራቸውን ቅልጥም እርዝማኔ በማየት መገመት ይቻላል። በጣም ቀጭን ሲሆኑ ጠይም ፊታቸው ጥጥ በመሰለ ረጅም ፂም ተሸፍኗል ። ዐይኖቻቸው በደንብ እንደማያዩላቸው ሲገልጹልን እንዲህ አሉ፡-

"ዐይኖቼ፡- እስከዛሬ በደንብ አገለገልንህ አሁን ግን አንተ ባትደክምም እኛ ደክሞናል ብለው ከንባብ ለዩኝ" አሉን ፊገግ ብለው።

ታመው የሰነበቱ ሳይሆን በምኞት የቆዩ ይመስል በአንድ ጊዜ ፍሥሓ ሆኑ። የሚገርመው ጥርሶቻቸው የመሸራረፍ ወይም የመወላለቅ ወይም የመብለዝ ምልክት ፈጽሞ ያላሳዩ ሲሆኑ ፅድት ያሉ፣ ደርዛቸውን የጠበቁ፣ የሚያምሩ የጎረምሳ ጥርሶች የሚመስሉ ናቸው።

አባ ኪዳነማርያም ጣልቃ ገብተው "አባታችን ዳዊትን ያስታውሱታል?" አሏቸው

"ዳዊት ማን?" አሉ። እጃቸውን ቅንድባቸው ላይ አድርገው ከመካከላችን የሚያውቁት ሰው እንዳለ ለመፈለግ ጥረት እያደረጉ።

"ዳዊት የገዳማችንን ደን የከለለልን" አሉ አባ ኪዳነማርያም

ያን ጊዜ ከተቀመጡበት አልጋ ተስፈንጥረው እየተነሡ፡-

"የእኛ ዳዊት!" አሉ እጆቻቸውን ዘርግተው። በዚህ ጊዜ ዳዊት ከእግራቸው ሥር ተንበርክኮ ጫማቸውን ሳመ። እርሳቸውም ትክሻውን ይዘው ቀና አደረጉትና አቅፈው ከአንገቱ ሥር ሳሙት።

ዳዊትና ንጀኛው በዚህ ጥንታዊ ገዳም ውስጥ ከፍተኛ ተወዳጅነትን አትርፈዋል ። የሚናደፉ መርዛማ እባቦችን፡ አጥመልምሎ የሚውጥ ዘንዶን፡ ሥጋን ቦጫጭቀው የሚበሉ የዱር አራዊቶችን፣ እንዲሁም በቀያ ጥያት አናት የሚያፈርሱ ሸፍቶችን ሳይፈሩ የበረሓውን ዋዕይ ታግሰው ሳምንት ሙሉ ከገዳሙ መነኩሳት ጋር በእግር እየዞሩ ከዚያው ከበረሓው ድንጋይ ተንተርሰው እያደሩ የገዳሙን የደን ክልል ለመጀመሪያ ጊዜ ከመንግሥት ተልከው የከለሉ ለሙያቸው ያደሩ ወጣት ፕሮፌሽናሎች ናቸው ።

አባ ዳዊትን ስመው ሲያበቁ አልጋቸው ላይ ቁጭ አሉና የሚያምሩ ሎጋ ጣታቸውን ወደ እርሱ ቀሰረው፡-

"ስማ ዳዊት!" አሉ ፈገግታቸው ጠፍቶ በጣም ኮስተር ብለው።

"በዚህ ዕድሜዬ ልዋሽ አልችልም፡ መዘላበድም አልሻም። አሁን የምነግርህ ግን የሆነውንና የሚሆነውን ነው። ስለፈጸምከው በጎ ሥራ እግዚአብሔር ይስጥህ ማለት አልፈልግም። ምክንያቱም ፈጣሪ ዋጋህን እንዳዘጋጅልህ አውቃለሁና" ሲናገሩ በሙሉ ስሜት እንደሆነ ይታወቃል ።

"ስማ የኔ ልጅ!

"ጀኑን እየዞራችሁ በምትከልሉበት ወቅት ሁለት መላእክት ከፊትና ከኋላ ሁነው ይጠብቋችሁ ነበር። በሕይወት ዘመንህ አንድ ቀን እግዚአብሔር በደን የተከበበች የምታምር አረንጓዴ ቦታ እንደ መሶበ ወርቅ ከፍ አድርጎ ያሳይሃል። ያን ጊዜ አንተም ‹ጌታ ሆይ! ይህ ምንድን ነው? የትስ ነው?› ትለዋለህ። እርሱም ‹አንተ በእግርህ እየዞርክ በጥምና በድካም የከለልካት፡ ያከበርካት ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ናት› ይልሃል። ያን ጊዜ ነፍስህ ሐሤት ታደርጋለች" አሉት።

ዳዊት እንባውን መቆጣጣር አልቻለም። እንደ ጎርፍ እያወረደው እግራቸው ሥር ሄዶ ተንበረከከ።

አባ ኪዳነ ማርያምን ጨምሮ ሁላችን በእንባ ተራጨን ።ሁሉም የየራሱ ምክንያት ይኖረው ይሆናል። እኔ ግን ያለቀስኩት በራሴ ሕይወት ነበር ።

በአሥሌው በአባከንኩት ዘመኔ፣ የግል ኑሮዬን ለመመሥረት የኳተንኩበት እጅጉን ግላዊ በሆነው ሕይወቴ፣ በመ.ያዬ ሰበብ የማገኘውን ጥቅምና ክብር እንጂ ለሀገርና ለማኅበረሰብ እዚህ ግባ የሚባል መልካም ሥራና ታሪክ የሌለኝ፣ መኖሬም ማለፌም የማይታወቅ ብኑን ሕይወት ያለኝ እኔ፣ "ለመሆኑ ፈጣሪ ለእኔ ከፍ አድርጎ የሚያሳየኝ ምን ይሆን? ድካሜን፣ ድቀቴንና መተላለፌን የሚያመለክቱ ካልሆኑ በስተቀር ሀገራዊና ማኅበራዊ የሆነ የሠራሁት ምን ቁም ነገር አለኝ?" አልኩና ራሴን ናቅኩት። ለዳዊት የተነገረውን ስሰማ ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ቅናት አደረብኝ ።

ከአዛውንቱ መናኝ ቤት ባዶነቴን ይገፍ ስወጣ አባ ኪዳነ ማርያም ተከተሉኝና በአንድ እጃቸው ከዘራቸውን በሌላ እጃቸው ትክሻዬን ይዘው ከቤተልሔሙ ጀርባ ከሚገኝ አንድ ዛፍ ሥር ከሌሎቹ ነጥለው ወሰዱኝ።

"ተመልከተው ይህን ዛፍ " አሉ።

ዛፉ በገዳሙ ተራራማ ክፍል በተለይ ቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ በብዛት የበቀለ አውራ ዛፍ መሆኑን ተገንዝቤዋለሁ። የዐማርኛ ስሙን ባላውቀውም ሳየው ግን ሳይንሳዊ ስሙን የማውቀው መሆኑን ተገነዘብኩ።

አባ ቀጥለው እንዲህ አሉ፡-

"የሚገርምህ ይህ ዛፍ ከክረምት ይልቅ በበጋ በእጅጉ ይለመልማል። በበጋ በመለምለሙ አካባቢውን በጣም ቀዝቃዛ እንዲሆን አድርጎታል። ሁሉም ዕፅዋት በበጋ ሲደርቁ እርሱ በምንፈልግበት ወቅት ይለመልምልናል። በሌላ ብዙ ጥቅሞቹና ጉዳዮቹ የተነሳ ተወዳጅ ዛፋችን ሆኗል" አሉኝ።

አጋጣሚውን ተጠቅሜ ወደ እኔ ጥያቄ ለመንደርደር ፈለኩና፡-

"ስሙ ምን ይባላል?" አልኳቸው።

"ሲና እንለዋለን" ሲሉኝ ሰውነቴ ስንጥቅ አለና፡-

"ሲና? ዕፀ ሲና የሚባለውስ?" አልኩኝ በጥድፊያ።

አባ ፈገግ ብለው "ዕፅ ማለት እኮ እንጨት ወይም ዛፍ ለብዙ ሲሆን ደግሞ ዕፅዋት እንደማለት ነው። እና..." ሲሉ ነጠቅ አድርጌ

"እና ዕፀ-ሲና ማለት ይሄ ነው አልኳቸው?"

"አዎን ተወዳጅ የበረሓ ጥላችንና ምሥጢራችን ዕፀ ሲና የሚባለው ይህ ነው" አሉኝ።

በሳይንስ ብቻ የማውቀውን ዛፍ ጠጋ ብዬ ሳስተውል ከዚህ በፊት አስተውየው የማላውቀውን የቅጠሎቹ አበቃቀል እንዲሁም በአንድ ወቅት የድህር ምረቃ ትምህርቴን ስከታተል የዛፍ ዝርያዎችንና ስሞችን ስታስተምረን የነበረችው እንግሊዛዊት ሳይንቲስት ስለዚህ ዛፍ ሳይንሳዊ ስም መነሻ የነገረችን ትዝ አለኝና አፌን ከፍቼ ቀረሁ። በምሥጢር ከተጻፈልኝ ወረቀት ላይ ስለዚህ ዕፅ ከተጻፈው ጋር ሳገናዝበው በራሴ ሙያ ሳይቀር እንዴት አልፈውኝ እንደ ሄዱ ተረዳሁና በአግራሞት ፈገግ አልኩ።

## "ዕፀ ሲና ዘማንበረ ሥላሴ ገዳም ስሙ ለተክለ ሃይማኖት ጻድቅ ወይፈክር ነገረ ሥላሴ"

እንግሊዛዊቷ የድሀረ ምረቃ መምህራችን እንደተረከችልን ይህን ዛፍ መጀመሪያ ያገኘው ሳይንቲስት ያገኘበት ቦታ ደብረ ሊባኖስ ገዳም አካባቢ ስለነበር ከገዳሙ መስራች አባት ጋር በማያያዝ ‹Tekele Haimanot The Noble› ‹ምርጡ ተክለ ሃይማኖት› ብሎ ማስታወሻ በመያዙ ወደ ላቲን ተሰቦ የዚህ ዕፅ ሳይንሳዊ መጠሪያ *Teclea noblis* ተባለ። ይህንን ነው ‹ስሙ ለተክለ ሃይማኖት ጻድቅ› ያሉት። ሌላው አስደናቂ ነገር የዛፉ የቅጠል መዋቅር ነው። ሁሉም ቅርንጫፎች የተዋቀሩት ሦስት ቅጠሎች በአንድ ቅጠለ ግንድ ላይ በቅለው ነው። ብቻውን የበቀለ ቅጠል ወይም ሁለት ወይም አራት ሳይሆኑ ከላይ እስከታች ሦስት በአንድ የተዋቀሩ ናቸው። ይህንን ለመግለጽ ደግሞ ‹ወይፈክር ነገረ ሥላሴ› ማለትም የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የሚናገር በማለት ተክለ መዋቅሩን *(Tree Morphology)* ተጠቅመው ለእኔ የቤት ሥራ የሰጡኝ መሆኑ ነው።

በኪሴ የያዝኩትን ሰንጠ ላጥ አድርጌ ከቅርንጫፉ ልቆርጥ ስል አባ ኪዳነ ማርያም፡-

"ቆይ እንደሱ አይደረግም!" አሉና "ፊትህን ወደዚያ አዙር አሉኝ"። ፊቴን እንዳዘዙኝ ከዛፉ በተቃራኒ አቅጣጫ አዞርኩ። ከዚህ ዛፍ ሥር ከአባ ጋር ከቆምኩበት ጊዜ ጀምሮ ግን ከሌሎች ዛፍ ሥር ከመቆም በተለየ አካልና አእምሮ ላይ የሚፈጥረው ነገር እንዳለ ግን አላጣሁትም ነበር።

የተወሰኑ ደቂቃዎች ካለፉ በኋላ ይኸውልህ ብለው እንዲት እንደቆረጡት ሳላይ አንድ ዘለላ ሰጡኝና ተቀብዬ በርሳዬ ውስጥ ስከት አባ ፊገግ ብለው ትክሻዬን መታ መታ አደረጉትና፡-

"ድንቅ ነው!" አሉ።

ዐይኖቼንና እጆቼን ወደ ላይ አቃንቼ "ተመስገን!" አልኩና "አባታችን በጣም አመሰግናለሁ!" አልኳቸው።

አባ ቀጠሉና "መቼ ነው መሄድ የምትፈልገው?" አሉኝ።

የመጣሁበት ጉዳይ በቀላሉ የተሳካልኝ ቢሆንም እጅግ ድካም ስለተሰማኝ፡-

"አባታችን ዛሬን እዚሁ ዐርፈን ነገ በሌሊት ለመመለስ ነው ሐሳቤ" አልኳቸው።

"ነገ ሰንበት ነው። ከገዳሙ መውጣትም ሆኖ መግባት አይቻልም። ያለህ ምርጫ ወይ እስከ ሰኞ ጠዋት መቆየት ነው አለበለዚያ ዛሬውኑ መመለስ ነው" አሉኝ።

"የፈጣሪ ያለህ!" አልኩ። እስከ ሰኞ መቆየት አልችልም። ቶሎ ወደ ቅዱሱ ስፍራ መመለስ አለብኝ። ያለኝ አማራጭ ዛሬውኑ መመለስ ነው። ችግሩ መንገዱስ፣ በረሓውስ እያልኩ በጭንቀት ስብሰለሰል፡-

"አይዞህ ራስህን አታስንፈው" አሉና "ባይደንቅህ አንተ ከግማሽ በላይ የሆነውን መንገድ በመኪና ተጉዘህ ዛሬውኑ መጥተህ በተለየ ምክንያታችን ዛሬውኑ ይህን ድንቅ ዕፅ እንድታውቅ አድርገን ብንሸኝህም ብዙዎች ግን ይህን ምሥጢር ለማወቅ ባሕር አቋርጠው በየብስ ተጉዘው መጥተዋል፤ ብዙ ደጅ ጠንተዋል" አሉ።

"እነማን ?" አልኳቸው በግጉት።

"እ..." አሉና " ጀምስ ብሩስ ስለሚባል ሰው ሰምተሃል?" አሉኝ።

"አዎን" አልኩና "የዐባይ ወንዝን መነሻ ለማዬት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረ ተጓዥ አይደል?" የሚል የማረጋገጫ ጥያቄ አቀረብኩ።

"ልክ ነው። ብዙ ሰው የሚገምተው የስኮትላንዱ ተጓዥ ጀምስ ብሩስ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የዐባይን መነሻ ለማወቅ እንደሆነ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ይህ እጅግ ድብቅና ራስ ወዳድ የነበረ ሰው ፍላጎቱ ከዚያም ከፍ ያለ ነበር። የታቦተ ጽዮንን ማረፊያ ስፍራ ማወቅ፣ ጥንታዊ ጥበባትን መመርመር፣ ጥንታዊ መጻሕፍትንና አስደናቂ ዕፅዋትን ፍለጋም ጭምር ነበር።"

"በዚህ ጉዞው የአክሱምንና በአቅራቢያ የሚገኙ ገዳማትን፣ የጣናንና የዘጌ ገዳማትን ብርብር አድርጐ ተመልክቷቸዋል። በቆይታው ግእዝን አጥንቶ መጽሐፈ ሔኖክንና ሌሎችን መጻሕፍትንም በእጁ ገልብጦ በርካታ ቅጅዎችን ወስዷል። በጣም የሚደንቀው" አሉና ዝም ብለው ቆይተው።

"ከጥቂት ሊቃውንት በስተቀር በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዘንድ ከነመፈጠራቸው የማይታወቁትን አስደናቂ ዕፅዋት ቅጠላቸውን፣ አበባቸውን፣ ቅርፊታቸውን፣ ሥራቸውንና ዘራቸውን ሳይቀር ለቅሞ መውሰዱ ነው" አሉና ፈገግ ብለው ወደ እኔ በምፀት እያዩ፡-

"አንተ ለአንድ ቀን ደርሶ መልስ የተማረርክበትን ይህን ገዳም እርሱ በ1764 ዓ.ም መጥቶ ለሦስት ወራት ተቀምጦበት ነበር። በቆይታውም አንተ ትኩረት ስለማትሰጠው ስለሚሰለችህ በአባቶች ፈቃድ እንደድካምህ መጠን በቀላሉ የተነገረህን ዕፅ እርሱ በብዙ ደጅ ጥናት ደርሶበት ዘሩን ጭምር ዘርፎ በግብጽ አድርጐ ወደ አውሮፓ ተመልሷል" አሉ።

“አቤት እኔ! ደግሞ ቀሪው ነገር ስለአስቸኮለኝ ነው እንጂ” ብዬ ሸምቅቅ ስል

አባም መልሰው “ነገሩን ነው እንጂ እንዲሰማህ አስቤ አይደለም” አሉና ቀጠሉ።

“በወቅቱ በቀጥታ ወደ ሀገሩ ከመጓዝ ይልቅ ወደ ፈረንሳይ አምርቶ በወቅቱ ለነበረው ንጉሥ ሊዊስ 14ኛ የዚህን አስደናቂ ዕፅ ዘር አበረከተለት። ብዙም ጤና ያልነበረው ንጉሡ እጅግ ከመደሰቱ የተነሣ ጀምስ ብሩስን በፈረንሳይ አቀማጥሎ አስተናገደው። ጀምስ ብሩስ በምን ምክንያት የዚህን ዕፅ ዘር ለፈረንሳዩ ንጉሥ እንደሰጠው አይታወቅም። አስገራሚው ነገር ቀጥሎ የተጓዘው ደግሞ ወደ ጣሊያን ሲሆን ከወቅቱ የቫቲካኑ ሊቃነ ጳጳሳት ከነበሩት ፖፕ ክለመንት 14ኛ ጋር ተገናኝቶ አሁንም ከአስደናቂዎቹ ዕፆች መካከል የተመረጡትን አበረከተላቸው”።

“ለምንድን ነው ለእነርሱ የሰጣቸው?” አልኩኝ።

“ጀምስ ብሩስ በምን ምክንያት የዚህን ዕፅ ዘር ለፈረንሳዩ ንጉሥና ለሮማው ፓፓ እንደሰጣቸው ያንተና የመሰሎችህ የቤት ሥራ ይሆናል” አሉ ፈገግ ብለው ትክሻዬን መታ እያደረጉ። ቀጠሉና፡-

“ከዚህ ሁሉ በኋላ ዘግይቶ ወደ ሀገሩ ታላቋ ብሪታንያ ሲመለስ የሚጠብቀውን ክብር ሳያገኝ ትኩረት ተነፍጐት ኖረ። ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላ አብዛኛውን ዘመኑን በብቸኝነት ያሳለፈው ጀምስ ብሩስ ራስ ወዳድ ከመሆኑ የተነሣ በኢትዮጵያ ያየውን ድንቅ ነገርና ከተዓምራት የሚተካከሉትን ጉዳዮች ደብቆ ሌሎች ተጓገሮች ተደፋፍረውና ተነሣስተው ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጡ አሳፋሪና አስቀያሚ ታሪኮችን ይነግር ነበር”። አሉና ፈገግ ብለው “ለምሳሌ ‹የኢትዮጵያ መኳንንቶች ላሟ ሳትታረድ በቁሟ ሣር እየበላች እነርሱ ከታፋዋ ሥጋ ቆርጠው ጥሬውን ይበላሉ› የሚል አሳፋሪ ነገር ጽፎ የተሳሳተ ገጽታ ለመፍጠር ሞክሮ ነበር። እንዲያውም

ይህን ተከትሎ በለንደን፡-

*"Nor have I been where men (what loss alas!)*

*Kill half a cow and turn the rest to grass"*

**"አወይ የኔ ነገር! ወንዶች ባልዋሉበት የጉዞ ኪሳራ**

**ላም በከፊል አርዶ በከፊል አቁሞ ሣር እንድትበላ"**

**ተብሎ ስንኝ ተቋጥሮበት ነበር ይባላል" አሉና፡-**

**"ይኸውልህ እንግዲህ የካህኑ ዮሐንስ ሀገር** (The Land of Prester John) **ተብላ ትታወቅ የነበረችውን ኢትዮጵያ ‹የብሩስ ጉዶች› ሀገር** (The Land of Prestigidator Bruce) **አስመስሎ አቀረባት። የዚህ ሁሉ መዘዝ ፈጣሪ ባደለን አስደናቂ ዕፅዋት ምክንያት ነበር።" አሉና ትክሻዬን መታ መታ አደረጉኝ።**

**ይህን ሲነግሩኝ ከታሪኩ አስደናቂነት ይልቅ የእርሳቸው ይህን ሁሉ ማወቅ ገርሞኝ በሕልሜ ነው ወይንስ በእውኔ እያልኩ ፈዝዤ ነበር።**

**"ለማንኛውም ዘጠኝ ሰዓት ስለሞላ ወደ ተግባር ቤት ሂዱና እህል ቀምሳችሁ በጊዜ ሂዱ" ብለው ወደ ተግባር ቤት ከእነድንዛዜዬ መሩን።**

**ተግባር ቤቱ አካባቢ ስንደርስ አብረውኝ የመጡት ጓደኞቼ ሲጠብቁን አገኘናቸው። አባ ጸሎት አደረጉልንና ሁላችንንም በመስቀል ባርከው "በሰላም ግቡ" አሉን። ሌሎች መነኮሳት መጥተው ወደ ተግባር ቤት እንድንሄድ ተቀበሉን። እኔ ግን የጀምስ ብሩስን ታሪክ አድንቄ አልጨረሰኩም ነበርና አካሌም አእምሮዬም ዝም ብሎ ያዘግም ነበር።**

**ወደ ተግባር ቤት ልሄድ ስል እጄን ሳብ አድርገው አስቀሩኝና "አንዴ ቆየኝማ" ብለው ወደ አዳራሻቸው ገቡ። ወዲያው የሆነ**

ነገር ይዘው ተመልሰው መጡና ወደ እኔ ጠጋ ብለው ዝቅ ባለ ድምፅ ፡-

"አባ ወልደ አረጋዊን ‹የሠርጉ እንዳይቀሩ አደራ› በላቸው። ይህንን ደግሞ ለአባ ተክለ ጽዮን አድርሰልን" አሉና በላስቲክ የተጠቀለለ አንድ ኪሎ የሚሆን ነጭ ዕጣን ሰጡኝ ።

"ማናቸው አባ ወልደ አረጋዊ፣ አባ ተክለ ጽዮንስ?" አልኩ።

ዝም....

"የት ነው የማገኛቸው?" አልኳቸው ደግሜ። መልስ ሳይሠጡኝ በእጃቸው የደጎና ሁን ምልክት አሳይተውኝ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ገብተው ተሰወሩ።

"ወይ ጣጣ! እንዲያው ሰው ይጨነቃል የማይሉ፤ ምን እንዲያው!" ብዬ አጉመተመትኩ።

ተግባር ቤት አካባቢ ለእንግዳ ማረፊያ ተብሎ ከተሠራ ጎጆ የተዘጋጀልንን እህል ውኃ ለመቅመስ ጓደኞቼን ተከትዬ ገባሁ። በትልቅ ገበታ የውኃ ዳቦ የመሰለ ተሸርክቶ ተፈጭቶ የተጋገረ የዘንጋዳ ጎበስት ቀረበልን። በእነርሱ አጠራር ‹መኮሪታ› ይባላል። ሲያዩት የሚከብደውን ያክል ሲበሉት ግን ለስላሳና ለአፍ ቀላል ነው። ያም ሆኖ ጉሮሮዬ በጣም ከመድረቁ የተነሣ ለመጉረስ አልቻልኩም። ከዚያ ይልቅ የሱፍ ጭልቃ በትልቅ ፋጋ ( ትልቅ ቅል እኩል ቦታ ተሰንጥቆ የተዘጋጀ የሾርባ ሳህን የመሰለ ዕቃ) ተሞልቶ ተሰጠኝ። ግጥም አድርጌ በአንድ ትንፋሽ ጠጣሁት። ተስገብግቤ መጠጣቴን ያዩት አስተናጋጅ መነኩሴ ድጋሚ ሞልተው ሰጡኝና አሁንም ግጥም አድርጌ ጠጣሁት። በቃ ሰውነቴ ተቃጥሏል ለሦስተኛ ጊዜ ተሞልቶ ሲሰጠኝ ጥም ባይቆርጥልኝ ሆዴ ግን

ሞልቶ ነበር። እንዲያም ሆኖ ሦስተኛውን ጨረስኩ። በዚህ ገዳም ውስጥ ሥጋ በዓመት አንድ ጊዜ የልደት (የገና) ዕለት ብቻ የሚበላ ሲሆን ከዚያ ውጭ በጋራ ተዘጋጅቶ በቀን አንድ ጊዜ ለእያንዳንዱ መናኝ የትልቅ ሰው መዳፍ የሚያክል ሁለት መኮሪታ ከሱፍ ሞልቃ ጋር ደወል ተደውሎ ይታደላል። እርግጥ እርሻ ለሚያርሱ ወይም ከባድ የጉልበት ሥራ ለሚሠሩ እንደ ድካማቸው መጠን ሁለት ጊዜ ሊሠጣቸው ወይም ‹ሊቆነኑ› ይችላል። ሕመማንም እንደ ድካማቸው ይስተናገዳሉ። ምክንያቱም ‹በገዳመ ሕግ በቀን አንድ ጊዜ የሚበላው ሰውነትን ከጥጋብ ተከላክሎ ለፈጣሪ ለማስገዛት እንጂ ሰውን ለማሰራብ ተብሎ አልተደረገም› ይላሉ የገዳመ አባቶች። የአስተናገዱንን መነኮሳት አመስግነን የማይቀረውን የጉዞ እዳችንን አብዝቼ በጠጣሁት ሞልቃ ሆዴ እየተንበጫበጨ ተያያዝነው።

ከቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ያለውን ደን ጨርሰን ገላጣው ስፍራ ስንደርስ መሬቱ እሳተ ጎሞራ የፈነዳበት ይመስል ግሏል። ቁልቁለት መውረድ የሰውነት ሚዛንን በሙሉ ከእግር ጫማ ላይ ማሳረፍን ስለሚጠይቅ የጋለው መሬት ከጠጠሩ ጋር ተዳምሮ ስቃዩ ልቤ ድረስ ዘልቆ ተሰማኝ። በቃ ‹ቶርች› የተደረኩ መሰለኝ።

“እንዲያው ያለአቅሜ ለዘመናት ተቆልፎ የኖረ ምሥጢር ነካክቼ ልሰቃይ” አልኩና በምሬት፡- “አይ ፕሮፌሰር ሃሮልድ! እግዜር ይይለዎት። በሞኝ ክንድ የዘንዶ ጉድጓድ ይለኩበታል የተባለው ተረት በእኔ ደረሰ” አልኩ። ስቃዩን በሙሉ ዋጥ አድርጌ ራሴን እጅግ እየተራገምኩ እንዳይደረስ የለም ‹ግዝት በር› ላይ ደረስን። ከአንድ ዛፍ ሥር ቁጭ አልኩና የውስጥ እግሬን ሳየው የተጠበሰ ሥጋ መስሏል፣ ዐልፎ ዐልፎ ደግሞ ውኃ ቋጥሯል ።

ቄስ ገዳሙ "አይዟችሁ እንደምንም በርቱና ሳይመሽ መኪናው ዘንድ መድረስ አለብን ። ጀንበር ከጠለቀች ጭራሽ መንገድ ይጠፋብናል" አሉ።

"ወዲያው እናንተ እንደሄዳችሁ ነው" አሉ።

ምን ችግር ገጠመው ብዬ ወረቀቱን ገልጬ ሳነብ፡-

> "ወንድም ሲሳይ! በጉዞህ እንደተደሰትክ ተሰፋ አደርጋለሁ። አስቸኳይ ጉዳይ ገጥሞኝ ወደ አንድ ቦታ ሄጃለሁ። እኔን ሳትጠብቅ ጉዞህን ቀጥል። ሰላም ላንተ ይሁን" ይላል ።

ትንሽ በስጨት አልኩ። በዚህ ሁኔታዬ መኪና መንዳት የምችል አልመሰልህ አለኝ። ለማንኛውም ወደ ገዳሙ የወሰደንን ሹፌር እየተጠባበቅን እንድንሄድ ተነጋግረን ወደ ገንዳ ውኃ ከተማ ነዳሁ።

ገንዳ ውኃ ስንደርስ ሰውነቴ ጨርሶ ዝሎ ነበር። ጠረኔም ተቀይሯል። ምግብ የመብላት ፍላጎት ጨርሶ አልነበረኝም። ሰውነቴ በቃ ተቃጥሏል። አልቤርጎ ከያዝኩበት ሆቴል በቀዝቃዛ ውኃ ገላዬን ታጠብኩና በጀርባዬ አልጋው ላይ ተዘረርኩ። ይሁንና ሰውነቴ ማረፍ ሲጀምር ውስጥ እግሬን ግን እንደ እሳት ይፈጀኝ ጀመር። ተነሣሁና ሁለት ባለ አንድ ሊትር በደንብ የቀዘቀዘ የታሸገ ውኃ አዘዝኩ። ሲመጣልኝ በጫማዬ ማሠሪያ የታሸጉትን ውኃዎች እያንዳንዳቸውን ከውስጥ እግሬ ጋር አሠርኩና በትራስ ወደ ላይ ቀና አድርጌ ተዘቅዝቄ ለመተኛት ሞከርኩ። እንቅልፍ ግን የሚታሰብ አልሆነም።

"ይህ ዕፅ ምን ጥቅም ቢኖረው ነው ጀምስ ብሩስ ለሦስት ወራት በዚሁ ገዳም ተንከራቶ ለመውሰድ የጓጓው? እንዴትስ ምሥጢሩን ደረሰበት?"

"ለፈረንሳዊው ንጉሥ ሊውስና ለሮማው ፆፕስ ለምን ሰጣቸው?" የሚሉት ጥያቄዎች ቅዠት ሁነውብኝ አደሩ።

በማግስቱ የበረሓ ጓደኞቼን ተሰናብቼ ወደ ጎንደር አቀናሁ። ጎንደር አንድ ቀን ካረፍኩ በኋላ ሁለተኛውን ዕፅ ወደማገኝበት ገዳም መሄድ አለብኝ።

"ወደ ቅዱሱ ቦታ ለመመለስ በዘገየህ ቁጥር የኋለኛው ዘመንህ እንደምንጣፍ ወደ አንተ እየተጠቀለለ ይቀርባል!"

የተባልኩት ከአእምሮዬ የሚጠፋ አልሆነም። ዕድሜ ነውና መሸቶ በነጋ ቁጥር እያጠረ መሆኑን ማሰብ ያስጨንቃልና!

# ምዕራፍ ሰባት

ከጎንደር ከተማ በጠዋት ቀደም ብዬ ጉዞ ጀመርኩ። ረጅምና አድካሚ ጉዞ ይጠብቀኛል። እንደ ዕቅዴ ከሆነ የሊማሊሞን ቁልቁለትና የተከዜን በረሓ ከሰዓት በፊት አቋርጬ ከሰዓት በኋላ የሽሬ ሜዳዎችን ዐልፌ አመሻሽ ላይ አክሱም ገብቶ ለማደር ነው። የጉዞ መዳረሻዬ አክሱም አቅራቢያ የሚገኝ ጥንታዊ ገዳም ነው።

አምባ ጊዮርጊስ ከተማን ሳልፍ ፀሐይ ሙሉ ለሙሉ የወጣች ቢሆንም ሊማሊሞ አፋፍ ላይ ከምትገኘው ደባርቅ ቁርስ ለመብላት ፈለኩ። ስለዚህ የወገራ ሜዳን እያደነቅሁ መንዳቴን ቀጠልኩ። ይህ አካባቢ

"እኔስ እሄዳለሁ ከአያሌው ብሩ አገር

ጎፈሬው ተንዶ ተይዟል በማገር"

ተብሎ የተገጠመለት ነው። የሚገርመው የደጃች አያሌው ብሩ የትውልድ አካባቢ በጌምድር ጋይንት ቢሆንም ‹የሰው ልጅ ሀገሩ ተግባሩና ምግባሩ› እንደተባለው በጀግንነትና በቅንነት

ያስተዳደሩትን ሀገር ወገራንና ስሜንን የእርሳቸው ሀገር ተደርጎ እስከ መቆጠር አድርሶታል።

ከዚህ አካባቢ በእርሳቸው ስም የሚነገር ሥነ-ቃልና የተለመደ የዘፈን ግጥም አለ። ደጃች አያሌው የእትጌ ጣይቱ ወገን ናቸው። በወቅቱ የማዕከላዊ መንግሥት የሥልጣን ሽኩቻ እቴጌ ጣይቱ ከባለቤታቸው ከሀዬ ምኒልክ በጸና መታመም በኋላ ዐልጋውን ሙሉ በሙሉ ሊይዙ ፈልገዋል ተብለው ተገምተውና ተፈርተው ሳለ ሥልጣን ወደ ልጅ አያሱ ሀረ። እቴጌይቱ ወደ እንጦጦ ሲጋዙ በዐይነ ቁራኛ ከሚታዩትና የስጋት ምንጭ ከሆኑት የጦር አበጋዞች ውስጥ አንዱ ደጃች አያሌው ነበሩ። በኋላም ልጅ ኢያሱ ተሸረው ራስ ተፈሪ ወደ ሥልጣን ሲመጡ ልጅ ኢያሱን ለመያዝ ወደ ምሥራቅ ዘምተው መኢሶ አካባቢ ከልጅ ኢያሱ ሰዎች ጋር ተዋግተው ድል አድርገው የተመለሱ ቢሆንም በራስ ተፈሪ ዘንድ ታማኝነትን አላገኙም።

የሥልጣን ግብግቡ ጡዘ የበጌምድሩ ገዥና የንግሥት ዘውዲቱ የሕግ ባል የነበሩት ራስ ጉግሣ በማዕከላዊው መንግሥት ላይ አመጹ። ራስ ጉግሣ የንግሥት ዘውዲቱ የሕግ ባል ሆነው ሳለ ንግሥቲቱ ሲነግሡ እርሳቸው ንጉሥ ተብለው ዘውድ መድፋት ሲያስቡ የማዕከላዊው መንግሥት መሳፍንቶችና መኳንንቶች፡-

"ንግሥቲቱ ተእንግዲህ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው በጸምና በጸሎት የሚማልዱ እንጂ በትዳር ውስጥ ሊቀብጡ አይፈልጉም" በሚል ሰበብ ሰሜነኛውንና የእትጌ ጣይቱን የወንድም ልጅ ራስ ጉግሣን ከአዲስ አበባ ገሸሽ ስላደረጓቸው ነበር።

ራስ ተፈሪ ለረጅሙ የሥልጣን ጉዟቸው ሥጋት የሆኑትን የራስ ጉግሣን አመፅ በፍጥነት መግታት ነበረባቸው። ይህን ጦርነት እንዲመሩት የተደረጉት ደግሞ ደጃች አያሌው ነበሩ። ዋድላ ላይ በተደረገው ጦርነት ደጃች አያሌው ማዕከላዊውን መንግሥት

ወግነው ተዛማጃቸውን ራስ ጉግሣን ወግተው ድል አደረጉ። ራስ ጉግሣም በጦርነቱ ተገደሉ።

አሳዛኙ ቅኔ ግን ራስ ተፈሪ ‹ኃይለ ሥላሴ› ተብለው ሲነግሡ የራስነት ማዕረግን ለዕምሩ ኃይለ ሥላሴና ለሌሎች መኳንንቶች ሲሰጡ ደጃች አያሌውን መዘለላቸው ነበር። ይህም አልበቃ ብሎ በቤተመንግሥቱ ግብር ሲገባ ቀድሞ የነበራቸው የፕሮቶኮል አቀማማጥ ደረጃው ተቀነሰ። በወቅቱ ደጃች አያሌው በእጅጉ ስሜታቸው እንደተጎዳ ይነገራል። ይህን ተከትሎ የወገራ አቀንቃኞች ይህንን የታሪክ ምፀት፡-

“አያሌው ሞኙ

ሰው አማኙ፣ ሰው አማኙ”

“አያል ሞኝ ነው

እንደኔ ሰው አማኝ ነው”

ብለው ገልጠውታል። እስከ አሁን ድረስ በሚጥም ዜማ የሠርግና የድግስ ማድመቂያ ዘፈን ሆኖ ዘመናትን ተሻግሯል።

ጣሊያን ኢትዮጵያን በ1928 ዓ.ም. ስትወር ደጃች አያሌው ለአውሮፕላን ድብደባ የሚመጥን ስልጠናን ጨምሮ በአንፃራዊ መልኩ የተደራጀ ሰንቅ የነበረው ጦር አዘጋጅተው እንደነበር ሐኪማቸው የነበረው ስዊድናዊው ዶክተር ሓራልድ ኂስትሮም በያዘው ማስታወሻ ገልጠታል። እራሳቸው ደጃች አያሌውም የተዋጣላቸው የጦር መሪ እንደነበሩ መስክሮላቸዋል።

በዚሁ ስዊድናዊ ሐኪም ማስታወሻ ላይ የሰፈረ አስደናቂ ታሪክም አላቸው። ጣሊያኖች ውጊያውን ወደ መኻል ሀገር ለመግፋት ሲያስቡ በወቅቱ በማዕከላዊው መንግሥት ላይ ቅሬታ የነበራቸውን

የአካባቢ ገዥዎችንና የጦር አበጋዞችን በመለየት ለማባበል ሞክረዋል። ጣሊያኖች ደጃች አያሌው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ላይ ቅያሜ እንዳላቸው ጠንቅቀው ያውቁ ነበር። በዚሁ መሠረት አንድ የዐረብ ነጋዴ በንግድ ሥራ ሽፋን ከኤርትራ የመረጣቸና የተከዜ ወንዝን ተሻግሮ ወደ ደጃች አያሌው ብሩ ምሽግ ደረሰና የመጣበትን መልእክትም በስውር ለደጃዝማቹ ገለጸ።

ጣሊያኖች ደጃች አያሌው ከጦርነት ግንባሩ እራሳቸውንና ሠራዊታቸውን ካገለሉ የጣሊያን መንግሥት የራስነት ማዕረግ ሰጥቶ አሁን የያዙትን የግዛት አገራቸውንና ተጨማሪም በጌምድርን አክሎ እንደሚያጸድቅላቸው መልእክተኛው ዐረብ ገለጸላቸው። ይህን ሐሳብ እንደድፍረት የቆጠሩት ደጃች አያሌው ብሩ በጣም ተባሳጩ። ይህንኑ መልእክት ለስዊድናዊው ሐኪማቸው ጠርተው ሲነግሩት እንዲህ ብለው ነበር፡-

"ጣልያን እንዴት ቢገምተኝ ነው እባክህ? እርግጥ ነው ከንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ቅያሜ አለኝ፤ ከአንድ ሁለት ጊዜም ቃላቸውን አጥፊው ልቤን አሳዝነውታል። ይሁን እንጂ ሀገር ሌላ ንጉሥ ሌላ፤ ሕዝብ ሌላ ኃይለ ሥላሴ ሌላ። እንዴት በዚህ ወቅት ሀገሬንና ሕዝቤን ይክዳል ብለው ይገምቱኛል?" ብለው በታላቅ እልህና ብሥጭት እንደነገሩት ዘግቧል።

በርግጥም ይህች አገር በየዘመኑ ለፍትሕ ያደሩ ከራሳቸው በላይ የሚወዱት ጀግኖች እንደነበሯት አይጠረጠርም።

"አያል በጎንደር

ሽር እንበል ብሎኝ ነበር"

ብላ የተቀኘችው ዘፋኝም ተርታ ነገር አለመሆኑ የገባኝ ያኔ ነበር።

ደባርቅ ከተማ ሊማሊሞ አፋፍ ላይ የምትገኝ ከተማ ስትሆን ወደ ሰሜን ብሔራዊ ፓርክ ለሚሄዱ ቱሪስቶች ማረፊያ ናት። አሁን

አሁን የቱሪስቱን ፍሰት መጨመር ተከትሎ ራሷን ለማንቃት እየሞከረች ይመስላል። ዐልፎ ዐልፎ ፎቆችን ሠርታ ወደ ላይ መንጠራራት ጀምራለች። ከቱሪስት ማረፊያ ከሆኑት ሆቴሎች አንዱን ገብቼ ከበድ ያለ ቁርስ በላሁ። የመኪናዬንም ከርስ ማደያ ገብቼ ሞላሁ። ከተማዋን ለቅቄ የሊማሊሞ ቁልቁለት አፋፍ ላይ ስደርስ በስተምሥራቅ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ እያሉ ፉክክር የያዙ የሚመስሉት የሰሜን ተራሮች ከፀለምት ጀምረው ወደ በየዳ የሰማይን ጣሪያ የሚታከኩ ይመስላሉ። ወደ ምዕራብ የአዲርቃይ፣ የጠገዴ፣ የወልቃይትና መላው የተከዜ በረሓ ዐይን ያማልላል። ይህን የሰሜን መልክአምድር የተመለከቱ ምዕራባዊ ተጓገሮች፡

"The play Ground of Gods" ብለውታል።

"የአማልክት የገበጣ መጫወቻ ምድር" ለማለት ነው።

ደባርቅ ከተማ በ2900 ሜትር ከባሕር ወለል በላይ የምትገኝ ሲሆን ተከዜ ድልድይ ላይ ደግሞ 850 ሜትር ነው። 2000 ሜትር ወይም 600 ፎቅ ያለው ሕንጻ ላይ እንደመውረድ ማለት ነው። የሊማሊሞ ቁልቁለት የመኪና ማሽከርከር ልምድንና ድፍረትን የሚጠይቅ ፈታኝ መንገድ ነው። እንደ ዝሀ ዘጊ እየተመላለሱ በዚያውም ከፍታ እየቀነሱ መውረድን ይጠይቃል።

"የወለዱት ባይሞት ያመኑት ባይከዳ

ሊማሊሞ ገደል ይሆን ነበር ሚዳ"

ተብሎ የተገጠመለት ሊማሊሞ በመንገዱ በስተምዕራብ በኩል ለማየት አያስደፍርም። ማለቂያ የሌለው የሚመስል ገደል ከዛፎቹ ሽፋን አምልጦ ሲታይ አናት ያዞራል፤ ሆድ ያባባል። ይህን ሳይ "ከፊለክ በሊማልሞ ገደል ማቋረጥ ትችላለህ!" የሚለው አባበል "ከፊለክ ገደል ግባ!" እንደማለት ሆኖ ተሰማኝ። ያም ሆኖ የሊማሊሞ ገደል የሚማርክ የደን ሽፋን አለው። ደን የሀገር ልብስ፣ የሀገር

ካባ፣ የሀገር ጸጋ ነውና ሊማሊሞን ከአስፈሪነቱ ይልቅ ግርማ ሞገ
አላብሶታል። እናም የአካባቢው መልክአምድር ውበት በልጠብኝ
ነው መሰል ያለምንም ችግር ሊማሊሞን ጨርሼ ከደልዳላው ሥፍራ
‹ድብ ባሕር› ደረስኩ።

ቁልቁል መውረድ በጨመርኩ ቁጥር ሙቀቱ እያየለ መጣ። ወደ
ታሪካዊውና ቅዱሱ ገዳም ‹ዋልድባ› የሚወስደው የእግር መንገድ
መጀመሪያ የሆነችውና፡-

“አትገኝም እንጂ ከተገኘችማ

ሊማሊሞ በታች እንዴት ነች ዛሪማ”

የተባለላት ትንሽዬ ከተማ ‹ዛሪማ› ደረስኩ።

እንዲህ ዐይነት ግጥሞችን፣ ዘፈኖችንና ሽለላዎችን ሲሰማ “መቼም
ሀገራችንንና የተወለድንበትን አካባቢ ስንወድና ስናንቆለጳጵስ
ወደር የለንም። ታዲያ ምን ያደርጋል የፍቅራችንን ያክል ሀገር
ለመለወጥ ሲሆን የሥራ ትጋት ይጎድለናል!” የሚለውን የዶክተር
ክብረ በዓልን ንግግር አስታውሼ ከት ብዬ ሳቅሁ።

ቅዝቃዜዋ የሚያኮማትረው ደባርቅ ትዝታዋ ሳይጠፋ በ30 ኪሎ
ሜትር ርቀት ላይ ቆላማዎቹ አዲርቃይና ማይፀምሪ ደግሞ በቅናት
ይመስላል ለደባርቅ የተለበሰውን ልብስ ከላይ ላይ ያስወልቃሉ።
ማይ ፀምሪ ስደርስ ከረፋዱ 5፡30 ሆኗል። ሙቀትና ወበቁ አይጣል
ነው። ቀዝቃዛ ውኃ ገዝቼ ግማሹን ራሴ ላይ አፍስሼ ግማሹን
እየጠጣሁ ወደ ተከዜ ወረድኩ። ግራና ቀኝ የዕጣን ዛፍ የሞላበት
የበረሓ ደን አልፌ እንደ መቀነት ከሚተጣጠፈው ተከዜ ወንዝ ላይ
ስደርስ ምድሩ ነዷል!

“ወይ የፈጣሪ ስጦታ! ራስ ደጀንን በየዳ ላይ በረዶ አልብሰህ እዚህ
ደግሞ ተከዜን በዋዕይ ግርማ ታስፎክረዋለህ” አልኩ።

ይህ ሁሉ የመልክአ ምድር መለዋወጥ የሚከሰተው በወፍ በረራ በ40 ኪሎ ሜትር ልዩነት ነው። እንደዚህ ዐይነት የመልክአ ምድር ለውጥ አውሮፓ ውስጥ ለማየት ከኒዘርላንድስ ተነሥቶ ጀርመንን አቋርጦ ሲዊዘርላንድ ገብቶ የአልፕስ ተራራሮችን መውጣት ያስፈልጋል። የሦስት ሀገር ቪዛ ይጠይቃል ማለት ነው። እዚህ ልብ ካለህ ‹ጃሎ› እያልክ በቀበሌ መታዎቂያ ብቻ ከተከዜ ተነሥተህ በአዲርቃይ አድርገህ፣ ፀለምትን ተቃንተህ፣ በየዳ ራስ ደጀን መድረስ ብቻ ይበቃኻል።

የተከዜን ወንዝ ተሻግሬ እንደገና ከፍታ መውጣት ጀመርኩ። የመኪናው ጮማ መቀርናት ይዟል። የመኪናው መሪ ሳይቀር እጅ ይጠብሳል። መኪናዬ ከሙቀቱ ጋር ተዳምሮ ከፍታ መውጣቱ አዳጋታት መሰል ዐልፎ ዐልፎ ታቃስታለች። ዳገቱ ማገባደጃ ላይ ‹እንዳ አባጉና› የተባለችውን ከተማ ዐልፌ አንድ አምስት ኪሎ ሜትር እንደነዳሁ ጥቂት ቤቶች ያሉበት አካባቢ ስደርስ ድንገት የመኪናው ሞተር ጠፍቶ ጉልበቱ አቅመ ቢስ ሲሆን ታወቀኝ። በፍጥነት ወደ ዳር ወጣ አድርጌ በፍጥነት አቆምኳት። ከፍተኛ ጢስ ከመኪናዋ የሞተር ኮፈን ሲወጣ ተመለከትኩ። በፍጥነት ወረድኩና ኮፈኑን ከፍቼ ሳይ ራዲያተሩ ጭስ መሳይ እንፋሎት በኃይል እያወጣ እንደሆነ ተረዳሁ።

“የፈጣሪ ያለህ! የፈራሁት ደረሰ” አልኩ።

ሕፃናት እየተሯሯጡ መጡና ከበቡኝ።

“ዋይ! እንታአይ ኮይና ዛመኪና” (ይህች መኪና ምን ሆነች)።

“ዋይ! ደኺምዋ እዩ” (ደክሟት ይሆናል) እየተባባሉ ይሣሣቁ ጀመር።

በቅርብ ርቀት ዐልፌው የመጣሁት ማርቼዲስ የጭነት መኪና ትዝ አለኝና እርሱን መጠበቅ ያዝኩ። ምሽቱ መቃረቡም ጭንቀቴን ከፍ ቢያደርገውም አማራጭ አልነበረኝም። እስከዚያው ከልጅቷ ጋር እኔ በተሰባበረ ትግርኛ እነርሱ በተሰባበረ አማርኛ ጨዋታ ጀመርን። ቀኑ ወደ 11 ሰዓት እየተጠጋ ነው። ከግማሽ ሰዓት ጥበቃ በኋላ ማርቸዲስ መኪናው እያገሣ ደረሰ። የእጅ ምልክት ሳሳየው ሹፌሩ ጥግ ይዞ ቆመ። በሹፌሩ በኩል ጠጋ አልኩና፡-

"እባክህ መኪናዬ ተበላሽብኝ። ከማሽከርከር ውጭ ደግሞ የመካኒክነት ዕውቀት የለኝም" ስለው፡-

ከረዳቱ ጋር ከመኪናው ዱብ ብለው ወረዱና ወደ እኔ መኪና መጡ።

"ዋይ! ራዲያተር ውኃ አፍልቶ ነው። የመውቀቱን ጌጅ አልተከታተልከውም ማለት ነው" አለና ጌጁን ሲያየው ከፍተኛ መውቀት ከሚያሳየው ቀይ መስመር የመጨረሻ ጥግ ደርሷል።

በአሮጌ ፎጣ የራዲያተሩን ክዳን አላለና በረጅም እንጨት ራቅ ብለው ሲከፍቱት በከፍተኛ መውቀት ራዲያተሩ አቀረሸ። የፊላው ውኃ ፈሶ ሲያልቅ በፎጣው ጠራረጉና እንዲቀዘቅዝ ከፍተው ተውት።

"ውኃ ሞልቼ ጉዞዬን ብቀጥልስ? አክሱም መግባት ነበረብኝ" አልኳቸው።

"አይሆንም አይሆንም። አሁን እንዲህ እንደጋለ ቀዝቃዛ ውኃ ብትጨምርበት የሲሊንደር ሄዱ ይቃጠላል" አለ ሹፌሩ

"ታዲያ ምን ተሻለኝ?" አልኩት በጭንቀት።

"ያለህ አማራጭ መኪናው ሙሉ በሙሉ እስኪቀዘቅዝ ጠብቆ ውኃ መሙላት ነው። ቢያንስ ሁለት ሰዓት መጠበቅ ያስፈልጋል" አለኝ

"እንዴ እንደዚያማ ከሆነ ይመሽብኛል" አልኩት።

"እንግዲህ ያለው አማራጭ መኪናውን ቆላልፈህ እዚሁ ትተህ ከእኛ ጋር ሽሬ እንሂድና አድረህ ጠዋት መጥተህ መውሰድ ነው አለበለዚያ ደግሞ ..." ሲል

"አለበለዚያ ደግሞ ምን?" አልኩት።

"አለበለዚያ ደግሞ ያው እንደ በረኸኛ ሹፌር ከዚሁ ከመኪናህ ላይ ማደር ነው" አለኝ ፈገግ ብሎ።

"የሰው መኪና መንገድ ላይ ትቼማ አልሄድም። እንደፈረደብኝ እዚሁ አድራለሁ እንጂ" ብዬ እነርሱን አመሰግኜ ሸኘኋቸው።

ጀንበር በምዕራብ በኩል ደም ለብሳ ከሽሬ ተራሮች ጀርባ ልትወሸቅ ትጣደፋለች። እርሷ ማንም ሜዳ ላይ ቢቀር ደንታዋ አይደለምና!

የበረሓ ጓደኞቼ የሆኑትን የከበቡኝን ልጆች ስመለከት የትም እንዳልወደቅሁ ተገነዘብኩ።

ቢያንስ እነዚህ እምቦቃቅላዎች የሚበሉትን በልቼ፣ በሚተኙበት ቦታ ላይ ተኝቼ ለማደር መሳቀቅ እንደሌለብኝ ወሰንኩ።

"ልጆች ከየትኛው ቤት ሂጀ ማደሪያ ብጠይቅ ይሻላል?" አልኳቸው

እንደተማከሩ ሁሉ፡-

"አብዚ ገዛ አደይ አብረኸት" አሉኝ።

የመኝታ ከረጢቴንና ቦርሳዬን ይዤ መኪናውን ቆላለፍኩና በልጆቹ መሪነት ወደ አደይ አብረኸት ቤት አመራሁ። እንደ አብዛኛው የትግራይ የገጠር ቤቶች በሚያምር የድንጋይ ግንባ ተሠርቶ ጣራው ወፋፍራም ግንድ ከተረበረበበት በኋላ ከላዩ ላይ ዐፈር ተደልድሎ መሬት መስሎ ከሚሠራው ጣራ የተዋቀሩ ቤቶች መካከል ከዋናው የመኪና መንገድ ዳር ወደ አለች ቤት ወሰዱኝ።

ሁሉም ልጆች እየተሻሙ "አደይ! አደይ!" አሏቸው።

በግምት ወደ 60ዎቹ ዕድሜ የሚጠጋቸው ሽበት የወረረውን ጸጉራቸውን ቁንዳላ የተሠሩ ቀይ ፊታቸው ተሸብሸበ የኑሮ ዳገታቸውን የሚያመለክት እናት

"ምን ሆናችሁ ልጆች?" እያሉ ወጡ።

ተለቅ ያለው ልጅ እኔንና መኪናዋን በየተራ እያመላከተ "መኪናው ተበላሽታበት ማደሪያ ፈልጐ ነው" አላቸው በትግርኛ።

አደይ አብረኸት ደረታቸውን እየደቁ፡-

"ዋይ አነ፤ አታ ወዲ ሂጅ እኮ አዴሃ ይጭነቃ ይሀለዋ!" (እኔን! ይሄኔ እኮ እናትህ እየተጨነቁ ይሆናል) አሉና መጥተው አቅፈው ሳሙኝ። የመኝታ ከረጢቴን ተቀብለው

"ና ግባ ና ግባ" እያሉ ወደ ቤት ይዘውኝ ገቡ። ልጆቹም ተከታትለውኝ ገቡና አንድ ጥግ ተኮልኩለው ቁጭ ብለው ዐይን ዐይኔን በሥሥት ያዩኝ ጀመር።

የአደይ አብረኸት ቤት ፅድት ያለች ነች። እቃ ማስቀመጫ ጓዳ ያላት ሲሆን ዋናው ክፍል ዙሪያውን መደብና በአንድ በኩል ምድጃ አለው። ከጭቃ የተሠራና ቁመቱ 70 ሳ.ሜ. የሚሆን የዱቄት

ማስቀመጫ ጉስጉሻ ወደ ጓዳ መግቢያ በሩ ላይ ተቀምጧል። አንድ እግሩ የተዛባ ጠረንጴዛ ላይ የሻይ ብርጭቆዎች፣ የአረቄ መለኪያዎችና የምኒሊክ ኩባያ የሚባሉት የጠላ መጠጫዎች ተደርድረዋል። ምድጃው ላይ አሮጌ የሻይ በራድ ተጥዶ የፈላው ሻይ እንፋሎት ክዳኑን ያንከበከበዋል። አደይ ሻይ፣ አረቂና ጠላ እየሸጡ የሚተዳደሩ መሆኑን መገመት ቻልኩ።

"አደይ እባክዎት ለእነዚህ ልጆች ለሁሉም ሻይ ይስጡልኝ" አልኳቸው።

"ዋይ አንተ ለራስህ መንገድ አይደለህ" አሉ።

"ወጭ የሚበዛብህ መንገደኛ ነህ" ማለታቸው ነው።

ልጆቹም ተቀብለው "ይሓህለና፣ ጸግቢና" አሉ።

"ግዴለም ግብዣ ነው፤ ሰው ሲጋብዝ ጠግበናል አይባልም" አልኳቸው። አደይ ለሁሉም ሻይ ቀድተው ሲጨርሱ

"ዳቦ ካለ ቢጨምሯቸው?" አልኳቸው።

አደይ ጓዳ ገቡና የዳቦ ማስቀመጫ ከሰበዝ የተሠራ ባለ ክዳን እግር የሌለው መሶብ ወይም ‹ሞሆዶ› ይዘው መጡና ክዳኑን ከፍተው ለሁሉም ማደል ያዙ። ከአንድ አምባሻ ላይ በሥርዐት የተዘጋጁና የተቆረሱ የአምባሻ ክፋይ /ፓይ/ ናቸው። ሁሉንም አዳርሰው አንድ ልጅ ሲቀር አምባሻው አለቀ።

"ዋይ! አለቀ ተካፈሉ እንጂ" አሉ አደይ። ሁሉም ለቀረው ልጅ እየቆረሱ ሰጡ። የሚገርመው ከሁሉም የበለጠ የደረሰው መሰለኝ። ለማንኛውም እየተሣሣቁ አምባሻቸውን በሻይ እያማጉ በልተው ሲጨርሱ ምሽቱ ተቃርቦ ለዐይን ያዝ እየደረገ ነበር። ልጆቹ ተነሥተው

እኔን "ጋሽ የቀንየልና" አደይን ደግሞ "አደይ አብረኸት ዳኅና ሕደራ" እያሉ ሲወጡ።

"በጠዋት እንድትመጡ እንድትረዱኝ" አልኳቸው። ያው ጓደኝነታችንን ለማጥበቅ ብዬ እንጂ እንደ እውነቱ ከሆነ የሚያግዙኝ ነገር አልነበረም።

ጨለማው እየነገሠ ሲመጣ የአደይ አብረኸት ቤት ከፅዳቱ ይልቅ ጥቁረቱ፣ ከጥላው ይልቅ የጨለማው ግርማ የሚከብድ ስሜት ይፈጥራል። ከምድጃው የሚወጣው በጢስ የጠወለገው የእሳት ፊገገንና ማዶ ግድግዳው ላይ ተሰቅላ ጨለማ ከሚሳለቅባት የኩራዝ ብርሃን ጋር ያን ያክል የሚያወላዳ ብርሃን አይገኝም።

አደይ የሻይ በራዱን ከምድጃው አንስተው ትንሽዬ ብረት ምጣድ ከጓዳ አምጥተው አጥበው ጣዱ። ጐድጓዳ የፕላስቲክ ሳህን እንዲሁ አጥበው አዘጋጁና ከዱቄቱ ጉስጉሻ እጃቸውን ከተው በእፍኛቸው ዱቄት እያወጡ ከሳህኑ ላይ አድርገው ማቡካት ጀመሩ። ለእኔ አንባሻ ለመጋገር እንደሆነ ተረዳሁ። ወዲያው ልጆቹን በምሽት ሻይና ዳቦ ጋብገፍ አደይን ከዕቅድ ውጭ እንዳደረኳቸው ገባኝ።

"ይሄኔ ለእኔም ለእርሳቸውም እነዚያ አንባሻዎች በቂዎች ስለነበሩ አሁን በጨለማ ከእሳትና ከጭስ ጋር አይታገሉም ነበር" ብዬ በጣም ተጸጸትኩ። ‹ይተውት› ብላቸው አንዳች የሚበላ ነገር ሳይሰጡኝ ለማሳደር የእናት አንጀታቸው እንደማይፈቅድ አውቃለሁ። ከሁሉም በላይ አእምሮዬን የፈተነው ጉዳይ ግን ዱቄቱን ለማውጣት እጃቸውን ሲያስገቡ ከዱቄቱ ማለቀመጫ ዕቃ /ጉስጉሻ/ ቁመት አንጻር ሳየው ዱቄቱ እያለቀ እንደሆነ መገመቴ ነበር።

ሳልታሰብ መጥቼ የእኒህን አዛውንት እናት ዱቄት እያራቆትኩ እንደሆነ ተሰማኝ። "ለመሆኑ እንዲህ ጠብ እርግፍ ብለው አስተናግደውኝ ነገ አስታውሳቸው ይሆን?" ብዬም ራሴን ጠየኩ።

አደይ እፍኝ ከማትሞላ ዱቄቷ ቀድማ ጋግራ ለነቢዩ ኤልያስ የሰጠችውን የሰራፕታዋን መበለት መስለው ታዩኝ። ደግነታቸውን አድንቄ ሳልጨርስ የእኔን ማንነት ሳስበው ፊቴ በሐዘን ተጨማደደ። አደይ ዱቄቱን አውጥተው ዘወር ብለው ሲመለከቱኝ ሁኔታዬን ተገንዝበውት ኖሮ "ምነው? ምን ሆንክ ወደይ?" ሲሉኝ

በድንጋጤና በፍጥነት "እረ ደህና ነኝ አደይ" አልኳቸው። እርሳቸው ሥራቸውን ሲቀጥሉ እኔም በሐሳብ ባሕሬ ውስጥ ሰመጥሁ። የጀመርኩት ሐሳብ ስለጎተተኝ ስልኬ ላይ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ አፕ አውጥቼ ተመለከትኩት።

በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተተረከው ኤልያስ የተባለው የእግዚአብሔር ነቢይ ወደ አንዲት ባልቴት ቤት ሄዶ ‹እንጎቻ አንጉቺልኝ› ያላታል። ሴትዮዋም ‹የእግዚአብሔር ሰው ሆይ! በቤቴ ለእኔና ለልጄ ብቻ የምትሆን እፍኝ ዱቄትና እንጥፍጣፊ ዘይት ነው ያለኝ። እርሷኑ በልተናት ልንሞት ነው› አለችው። እርሱም መልሶ ‹እኮ ቢሆንም አስቀድመሽ ለእኔ አንጉቺልኝ› አላት።

እርሷም የእግዚአብሔር ሰው ነውና ከእርሷና ከልጇ አስበልጣ አንጉታ አቀረበችለት። የእግዚአብሔር ነቢይ ኤልያስም እንጎቻውን በልቶ እንዳበቃ የዱቄት ማድጋዋንና የዘይት ማሰሮዋን ባረከላት። ‹ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዱቄቱ ከማድጋው አላለቀም፤ ዘይቱም ከማሰሮው አልጐደለም› ይላል።

አንብቤ ስጨርስ አደይ አቡክተው እየጋገሩ ነበር። የእርሳቸውን ፍቅርና ልግሥና እያየሁ ራሴን መውቀስ ጀመርኩ፡-

"አደይ እርስዎ እንደዚያች መበለት ነዎት። እኔ ግን ነብዩ ኤልያስን አይደለሁም! ያጎደልኩትን የዱቄት ማድጋና የዘይት ማሰሮ በላይ በላዩ የሚያበረክት ኃይል ወይም ጸጋ የለኝም። አራቱቹ ከመሄድ ውጭ ሌላ ምን እፈይዳለሁ?" አልኩና በልቤ ሐዘኔ ከበደ።

አደይ ከጭስና ከጨለማ፣ ከእሳት ወላፈንና ከእርጅና ጋር ታግሎው የሚጣፍጥ ቂጣ ጥቅጥቆ በበርበርሬ ድልህና በቅባኑግ ቀብተው አበሉኝ። አብዛኛውን ለእኔ ሰጥተው እርሳቸው ትንሽ ቆርሰው ቀመሱ። የጨለማው ክብደት፣ የአደይ አጠቃላይ ኑሮ፣ ዕድሜያቸው፣ ብቸኝነታቸውና ደግነታቸው ተቀላቅሎ አእምሮዬን በትልቅ መዶሻ ይወቅረው ጀመር።

አደይ እንዳጫወቱኝ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሯቸው። ባለቤታቸውን በሕመም ሁለቱን ልጆቻቸውን ደግሞ በጦርነት ተነጥቀው ያለደጋፊ ጧሪና ቀባሪ ቀርተው አውላላ ሜዳ ላይ እርጅናና መዘዙን ከድህነት ኑሮ ጋር ይጠብቃሉ።

ከመደቡ ላይ የመኝታ ከረጢቴን አንጥፌ ጋደም አልኩና ለራሴ ማውጋቴን ቀጠልኩ።

"ለመሆኑ የእኒህን እናትና መሰሎቻቸውን ሕይወት ከዚህ የጨለማ ኑሮ የሚያላቅቃቸው ማነው? በድሆች ስም በተለገሠ እስኩላርሽፕ ተምሮ ሲቪን እያሳበጠ የሚኖር የኔ ቢጤ አውደልዳይ ግብዝ ባለሙያና ምሁር ነኝ ባይ፣ ስንዝር ያክል ሠርቶ የክንድ ያክል የሚደሰኩር ፖለቲከኛ በሞላባት ሀገር የእነዚህ እናቶች ሕይወት እንዴት ይቀየራል?" የሚል የፈጠጠ ጥያቄ ራሴን ከጠየኩ በኋላ ሌላ ሰው የጠየቀኝ ያክል ደነገጥኩህ።

አእምሮዬ በአደይ ኑሮ ክፉኛ ተሠቃዬ። የጎሊና ወቀሳውን የምችለው አልሆነም። እኔስ የእነዚህ እናቶችና መሰሎቻቸው ሕይወት እንዲቀየር በዘመኔ ምን አስተዋፅኦ አበረከትሁ? የሚለው ጥየቄ መልስ የማገኝለት አልነበረም። ከሌላ የዐፈር መደብ ላይ በመተኛቴ ከሚሰማኝ ጉርባጤ ጋር ተዳምሮ እንቅልፍ የሚታሰብ አልነበረም። በዚህ ሰዓት የሚያስፈልገው አእምሮን የሚያደነዝዝ፣ ጎሊናዬ ውስጥ የሚንጫጫውን ወቀሳ ፀጥ የሚያደርግ ነገር ነው።

"አደይ" አልኳቸው።

"አቤት ወደይ" አሉኝ።

"እባክዎት አረቂ ይስጡኝ" አልኳቸው ።

"ዋይ! ከበረሓ ውለህ ንምንትአይ አረቂ?" አሉኝ።

"ሆዴን ቆርጦኝ ነው" አልኳቸው።

አደይ አመመኝ ስላልኳቸው እየተጨነቁ ቀድተው ሰጡኝ። መለኪያውን ተቀብዬ በደንብ ሳብ አደረኩት።

"አረቂ፣ ውስኪ ብላክ ሌብል፣ ኩርቫይዘር ወይም ቮድካ ብለህ ስሙን ብትቀያይረው፤ ከተራ ቤት ወይም ሸራተን አለበለዚያም ሂልተን ሆነህ በክርስታል ብርጭቆም ተጠጣ በመለኪያ እውነተኛ ሥራው የጎሊና ጥዝጣዜን ለመርሳት፣ የበደል ቁስልን ለማደንዘዝ እንጂ ውስኪ ጠጣሁ ብሎ ደረጃን ከፍ ለማድረግ መፎከር ባዶ ጉራ ነው። እንዲያውም ለጎሊና ቁስል ማስታገሻ ከሆነ ‹ኦርጋኒክ› የሆነው የሀገር ቤት አረቂ በቁርጡ ይሻላል" የሚለውን የዶክተር ክብረ በዓል ትችት እያስታወስኩ ጭልጥ አደረኩት።

አረቂው ከቀኑ ድካም ጋር ተዳምሮ እራሴን እያጃጃለና እያንገላጀጀ ለእንቅልፍ አሳልፎ ሊሰጠኝ ሲደራደር ታወቀኝ።

"የታባኸን!" አልኩት እኔነቴን። "ለእንዳንተ ዐይነት አውደልዳይ ምሁር ነኝ ባይ በመኝታ ሰዓት ጣፋጭ ትርክትና ተረት ሳይሆን የሚነገረው በጎሊና ወቀሳ መደሻ ኮርኩሞ በአልኮል አደንዝዞ ማስተኛት ነው" ይልሃል ዶ/ር ክብረ በዓል አልኩና ለራሴ ነገርኩት።

እንዳይነጋ የለም ነጋና በጠዋት ተነሥቼ ከአደይ ቤት ውኃ ወስጄ የመኪናዬን ራዲያተር ሞልቼ ሞተር አስነሣሁ።

"የከፋ ነገር ሳይመጣ ቢያንስ አክሱም እደርሳለሁ። ከዚያ ጣጣዬን እስክጨርስ ከአንዱ ጋራዥ ወስጄ ያስተካክሉልኛል" አልኩና ተበረታታሁ። ሕፃናቱ በአንዴ ከበቡኝ። የመኪናዋ ሞተር መነሳቱን ሲያዩ በጣም ደስ አላቸው።

"አጆኋ አጆኋ! ንፉዕ ዕቡቕ!" ይባባሉ ጀመር። ሁሉንም ልጆች ስሚ ‹ለእስክብሪቶ መግዣ ብቻ› እያልኩ ለሁሉም ፍራንክ ሰጠኋቸው። በቃ ፍንድቅ አሉ!

ለጉዞ ዝግጁ መሆኔን ሳረጋግጥ ወደ አደይ አብረኸት ሂድኩ።

"አደይ! መኪናዬ ደኅና ሁናለች ልሂድ ነው" አልኩና፡ "እግዚአብሔር ይስጥልኝ አደይ!" ብዬ ጥቂት ብሮች አውጥቼ ከእጃቸው ላይ አስቀመጥኩ። ለእርሳቸው ብዙ ሆነና እቅፍ አድርገው ሳሙኝ።

ምናልባት በዚህ ሰዓት እንደወጡ የቀሩትን ልጆቻቸውን እያሰቡ ይሆናል፤ በእኔ በኩል ግን በልጅነቴ በሞት የተለየችኝ እናቴን አስቤ አንገታቸው ሥር ሽጉጥ አልኩ። ከፊረንሳይ ሽቱ፣ ከአሜሪካ ሎሽን ይልቅ ጭስ ጭስ ከሚለው ጠረናቸው ጋር የሚወጣውን የእናትነት ፍቅር እየማኩ ብዙ ብቆይ በወደድኩ።

ወደ መኪናዬ ሳመራ፡-

"ቀልጢፍካ ተመለስ እሺ! አዴኻ ከይትሻቐል" (ቶሎ ተመለስ እሺ እናትህ እንዳይጨነቁ!) አሉኝ። አንጀቴ ተላወሰ።

"አይ ጦርነት! ዐይንህን ጨለማ፣ ጉልበትህን ቁጠማ ያድርገው" አልኩኝ በምሬት። አደይን እየራቅኩ በሄድኩ ቁጥር የተናገሩት ነገር እውነትነቱ ጐልቶ ታየኝ።

"እንደ ወጡ መቅረት ግብራችን አይደለምን? የተወለድንበትን አካባቢ፣ ያደግንበትን ቀዬ ትተን ስንወጣ ሁልጊዜ መመለስን እንዳቀድን ገሚሱ በምኞት ባሕር ሰጥሞ ሌላው በመከራ አሮንቃ

ተዘፍቆ መቅረት ዕጣችንስ አልሆነምን?!" አልኩና ሆድ ባሰኝ።

ሽፌ እንዳሥላሴ ስደርስ ትናንት የረዱኝን ሰዎች ማርቸዲስ መኪና ቆሞ አየሁት። ከፊት ለፊቱ ሄጄ አቆምኩና ወርጄ ሰላምታ ለጠኋቸው።

"ሰላም አደርክ? እንኳን ደኅና መጣህ" እያሉ እየተቀባበሉ አቅፈው ሳሙኝ፤ ቀጥለውም "ጥሩ ሰዓት ነው የደረስክ። እኛም ወደ አክሱም ነው የምንሄድ ከኋላህ እንከተልሃለን። ረጋ ብለህ ንዳ። አክሱም እንደገባን ጥሩ ጋራዥ አለ፤ እኛ እንወስድሃለን" አሉኝ። በዚህ መሠረት ያለስጋት እነርሱን ከኋላዬ አስከትዬ ከጠዋቱ 3፡40 አካባቢ አክሱም ከተማ ገባን።

ወደ ከተማው መኻል ከመዝለቃችን በፊት የማርቸዲሱ መኪና የመብራት ምልክት ሲያደርግልኝ አየሁና ዳር ይገፍ ቆምኩ። ዐልፎኝ ሄደና ወደ ቀኝ ታጥፎ አንድ ሀምሳ ሜትር እንደሄደ ቆመና ከመኪናው ወረደ። እኔም ተከታትዬ ወረድኩ። በስተቀኝ በኩል በርከት ያሉ መኪኖች የቆሙበት ሰፊ ግቢ ያለው ጋራዥ ተመለከትኩ።

"ስማ አታኽልቲ ና እሞ" አለው ።

ቀይ መልከ መልካም ለግላጋ ወጣት የቆሸሸ ቲታ እንደለበሰ መፍቻ በቀኝ እጁ ይዞ ብቅ አለ።

ሞቅ ያለ ሰላምታ ከሹፌሩ ጋር ከተለዋወጡ በኋላ።

"ስማ እስኪ! እርሱ ማርያም ጽዮን ሊሳለም ከጎንደር ሞጥዬ መኪናው ራዲያተር አፈላበት። በደንብ አስተካክልለትማ" አለው።

"ዋይ ችግር የለም" አለና ሰላምታ ሰጠኝ።

"እቃህን አውርድና ቁልፉን አምጣው፡ ነገ ተመለስ ተሠርቶ ይቆይሃል" አለኝ።

"እሺ" አልኩና ፊጠን ብዬ ሻንጣዬንና የመኝታ ከረጢቴን አውጥቼ ቁልፉን ሰጠሁት።

ገባና መኪናዋን አስነሥቶ ወደ ጋራዥ ይዟት ሲገባ

"በቃ! ወደ ማርያም ጽዮን" አለኝ በእጁ እያሳዬ።

ዋጋ ሳልነጋገርና ሳልደራደር መሄዴ ቅር እያለኝ ማረፊያ ሆቴል ፍለጋ ሄድኩ ። ቀደም ብዬ የማውቀውና የተለዬ ግርማ ሞገስ ካለው ‹የሃ ሆቴል› ሄጀ አልቤርጎ ያዝኩ። በተከዜ ጠረሓ የተንቆረቆረው የሰውነቴ ወዝ ገማሮ ጠረኔም ለራሴ ስለከበደኝ ገላዬን ታጥቤ በቂ ዕረፍት ወስጄ ምሳ በላሁ።

የጉዞዬ መዳረሻ ከአክሱም ከተማ ምሥራቃዊ ዳርቻ ላይ የሚገኝ ጥንታዊ ገዳም ስለሆነ በማግስቱ በጠዋት ለመሄድ ወሰንኩ። በዕለቱ ግን ወደ ማታ ባለው ጊዜ አክሱም ጽዮንና አካባቢውን በደንብ መጎብኘት ፈለኩ። ካረፍኩበት ‹የሃ ሆቴል› ሆኖ የአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያንና ሐውልቶቹ ቁልጭ ብለው ይታያሉ።

‹የሃ ሆቴል› ከሕንጻ ዲዛይኑ ጀምሮ የፀጥታ ድባብ እንዲኖረው ተደርጐ የተሠራ ማለፊያ ሆቴል ነው። ምሳ ከጥሩ ቡና ጋር ራሴን ከጋበዝኩ በኋላ ቦርሳዬን አንግቼ ጉብኝቴን የንግሥተ ሳባ መዋኛ ተብሎ ከሚታመነው ማይሹም አካባቢ ጀመርኩ።

አክሱምን በተደጋጋሚ የመጎብኘት ዕድል ገጥሞኛል። ሁሌም አዲስ፣ ሁሌም ምሥጢሯ የማይፈታ ደርባባ ከተማ ናት። ሐውልቶቹን እንደ አዲስ በአድናቆት ጎብኝቼ ወደ ሙዚዬሙ ሄድኩ። በቁፋሮ የተገኙ በርካታ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች፣ የመገበያያ ሳንቲሞች፣ የቤተ-መንግሥት መገልገያዎች፣ የጦርና የጌጥ ቅርሶች፣ የአቅጣጫ አመልካች መሣሪያዎች ያስደምማሉ። የአክሱማዊያንና የሳባውያንን ጥበብና ደርሰውበት የነበረውን ከፍታ ላየ ሰው አሁን ላይ ሆኖ ‹የኛ ታሪክ ነው› ብሎ ለመቀበል ቢከብድ አይገርምም።

ታሪካችንን ለመሸከም የሚከብደን ይመስለኛል። ስለሚከብደንም ይሆናል ከጎሊና ወቀሳ ለመዳን ያለፈ ታሪካችንን ለመካድ ወይም ደካማ ጎኑን ብቻ ለማንሣት የምንገደድ!

ቀጥሎ ያመራሁት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በእብነ በረድ በግሩም ሁኔታ ወደታነጸችው የድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ነበር። ለረጅም ጊዜ በግንባሬ ተደፍቼ ቆየሁ። ምን ብዬ እንደጸለይኩ አላውቅም፤ ብቻ ዝም ማለት አሰኝቶኝ ነበር። ከዚህ ቤተክርስቲያን በስተደቡብ በዐፄ ፋሲል ዘመነ-መንግሥት በፋሲል ግንብ አምሳል የተሠራ ለወንዶች ብቻ የተፈቀደ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል። ወደዚያው አመራሁ። አክሱም ከተማ ቅድስናዋን ጠብቃ ለክርስቶስ ብቻ ተሞሽራ ለመኖር የወሰነች ከተማ ናት። አክሱም ሌላ ባል ወይም ውሽማ አለመፈለጓን ዘመናት የፈተኑት ታሪኳ ምስክር ነው። በተለይ በዚህ ግቢ ውስጥ ሁሉም ነገር በእርጋታና በምሥጢር ይከናወናል። በሁለቱ አብያተ ክርስቲያን መካከል መለስተኛ ባለጉልላት ሕንጻ ዙሪያውን በብረት አጥር ተከልሎ ይታያል። ይህ የታቦተ-ጽዮን ማደሪያ ነው። ከማደሪያው በስተሰሜን ምሥራቅ የቤተ ክርስቲያኑ ሙዚዬም ይገኛል። የታቦተ-ጽዮንን ማደሪያ ከመሳለሜ በፊት ወደ ሙዚዬሙ አመራሁ። የቀኑ ውሎዬን ማሳረጊያ ለታቦተ-ጽዮን ማደሪያ መደብኩ።

በአንድ ወጣት ዲያቆን አማካኝነት ሙዚዬሙን አንድ ባንድ ጐበኘሁ። እውነት ለመናገር ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ካየኋቸው ሙዚዬሞች በአግባቡ የተደራጀው የአክሱም ጽዮን ሙዚዬም መሆኑን መመስከር ይገባኛል። ያም ሆኖ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እናትና እምብርት (ርእሰ አድባራት ወገዳማት) ለሆነችው አክሱም ጽዮን ያንሳት እንደሆነ እንጂ አይበዛባትም።

የእያንዳንዱን ቅርስ ታሪክ በሚገባ እየመዘገብኩ ጉብኝቴን አገባደድኩና ወደ ፅላተ-ሙሴ ማደሪያ አመራሁ። ሰዓቱ ወደ 12፡00 ገደማ ሆኗል። ማደሪያው በጥርብ ድንጋይ በጥበቅ የተገነባ

ሲሆን በስተምሥራቅ በኩል ምንም መግቢያ የለውም። የብረት አጥሩ በርና የማደሪያው በር በስተምዕራብ በኩል ነው። ወደዚያው አመራሁና የአጥሩን በር ተደግፌ ዐይኔን ጨፍኜ በዝምታ ቆየሁ።

በአእምሮዬ የሚመላለሰው ነገር የጸሎት ቃላት ሳይሆን በቃ አድናቆትና መደመም ነው። ከቆምኩበት በሃያና ሠላሳ ሜትሮች ርቀት በእርግጥም ታቦተ-ጽዮን (የቃልኪዳኑ ታቦት) እንዳለች ማሰብ ድንቅ ነገር ነው። ከእነዚህ ሜትሮች ባነሰ ለመቅረብ ለማንም ያልተፈቀደ መሆኑን አውቃለሁ። በዚህ ርቀት መቆም በራሱ ግን ትልቅ መባረክ እንደሆነ ከበርካታ የጥንት ዓለም አቀፍ ተጓዦችና አሳሾች ጅምሮ የተረዳ ነገር መሆኑንም አጥንቻለሁ። እነዚሁ አሳሾች የእኛን የሀበሾችን ክብርና መመረጥ ማጉላት እንዳይሆንባቸው ለአደባባይ ሳያበቁት ተቀብሮ ቀረ እንጂ በየግል ማስታወሻዎቻቸው አክሱምን ሲረግጡ በግንባራቸው ተደፍተው መሬቱን እንደሳሙ፣ አሁን ከቆምኩበት አካባቢ ሆነው በተመስጠና በአድናቆት እንዳነቡ ጽፈዋል። ‹እኔም እዚህ ቦታ መቆም የማይገባኝ ቢሆንም ፈጣሪ ምሕረቱ ብዙ ነውና ቆምኩ!› ብዬ ሳስብ ውስጤን የዝምታ ደስታ ዋጠው።

ድንገት “እንደምን ዋልክ የእኔ ልጅ?” የሚል ልስልስ ያለ ድምፅ ሰማሁና ዐይኔን ስገልጥ ከተዘጋው የብረቱ አጥር በር በስተውስጥ በኩል ዕጣን ዕጣን የሚሸት ቢጫ የመነኩሴ ልብስ የለበሱ አዛውንት መስቀላቸውን ዘረጉልኝ።

“የፈጣሪ ያለህ! ሌላ ማንም ሰው ከዚህች ቤተ መቅደስ ሊወጣ አይችልም።የቃል-ኪዳኑ ታቦት ጠባቂ ናቸው!” አልኩ ለራሴ። ለረጅም ጊዜ መገተሬን አይተው ተጠራጥረው ይሆናል አልኩና፡

“አባታችን ይባርኩኝ” አልኩ።

“እግዚአብሔር ይባርክህ፤ እግዚአብሔር ይፍታሕ” አሉና በመስቀል

አላለሙኝ። ቀጥለውም፡-

"የእኔ ልጅ ደኅና ነህ?" አሉኝ።

"ደኅና ነኝ አባታችን። ብቻ በዚህ ቦታ መገኘቴ ተዓምር ሆኖብኝ ነው መሰለኝ" አልኳቸው እየተንተባተብኩ።

"እውነት አለህ የኔ ልጅ" አሉና ፈገግ ብለው አዩኝ።

በዐይኔ ሙሉ በሙሉ ላያቸው አልደፈርኩምና አቀረቀርኩ።

"ግዳሙም ማኅበሩም ደኅና ነው?" አሉኝ እንደዋዛ።

"ድንገት ቀና አልኩኝና የትኛው ገዳም?" አልኩ።

"የመጣህበት ነው እንጂ" አሉና "አባ ኪዳነ ማርያም ደኅና ናቸው?" አሉኝ አስከትለው።

"የፈጣሪ ያለህ!" አልኩና አእምሮዬ መሥራት ሲጀምር አባ ኪዳነ ማርያም ለሁለት ሰዎች መልእክት እንደላኩኝ ገባኝ።

ለአባ ወልደ አረጋዊ "ከሠርጉ እንዳይቀሩ አደራዎትን" የሚል

አባ ወልደ አረጋዊ እኒህ ሊሆኑ አይችሉም። ምክንያቱም እኒህ ሰው እስከ ሥጋ ዘመን ፍጻሜያቸው ድረስ ከዚህ የብረት አጥር ላይወጡ፣ ከቃል-ኪዳኑ ታቦት ላይርቁ የሕይወት ዘመን ብፅዐት ያላቸው ናቸው፤ ስለዚህ ወደ ሆነ ቦታ እንዲሄዱ መልእክት ሊላክላቸው አይችልም። እናም ሊሆኑ የሚችሉት አባ ተክለ ጽዮን ናቸው አልኩና፡-

"አባታችን! አባ ተክለ ጽዮን እርስዎ ነዎት?" አልኳቸው።

ፈገግ ብለው በዝምታ አዩኝ።

ከዚህ በኋላ እርሳቸው መሆናቸውን ለማመን ሌላ ተጨማሪ መልስ አላስፈለገኝም። ግን ደግሞ ጥያቄው እኔን ለመፈተን መሆን አለበት አልኩና ስለገዳሙም ሆነ ስለ አባ ኪዳነ ማርያም ደኅንነት ለመናገር መሞከር ዝም ብሎ መቀባጠር እንደሆነ ገባኝ። ምክንያቱም እነርሱ በየዕለቱ የሚገናኙበት ምሥጢራዊ መስመር እንዳላቸው ግልጽ ነውና። ልናገርስ ብል እነርሱ ያውቁኝ እንደሆነ እንጂ እኔ የታባቴ አውቄያቸው።

"አባታችን!" አልኩና ቦርሳዬን አውርጄ አስቤበት ሳይሆን በአጋጣሚ ቦርሳዬ ውስጥ የተቀመጠውንና እንድሰጥ የታዘዝኩትን በላስቲክ የተጠቀለለ ዕጣን አቀበልኳቸው።

ተቀብለው ወደ አፍንጫቸው ጠጋ አድርገው አሸተቱትና፡-

"ከማኅበረ ሥላሴ ገዳም የበረሓ ዱር የተለቀመ ዕጣን መዐዛው ግሩም ነው። በእግዚአብሔር ፊትም የተወደደ የጸሎት መሥዋዕት ነው" አሉና ወደ ደረታቸው ጠጋ አደረጉት። ሁኔታው ግን ከዕጣኑ ይልቅ በአካል ለማየት የሚናፍቋቸውን የመናንያን ወንድሞቻቸውን ፍቅር ስለአስታወሳቸው ይመስላል።

"እግዚአብሔር ይባርክህ፣ በመንገድህም ይምራህ" አሉና ጸሎት አድርገው በመስቀል አሳልመውኝ የወንድሞቻቸውን ስጦታ ይዘው ወደ ቃል-ኪዳኑ ታቦት ማደሪያ ገብተው ተሠወሩ።

እኔ በዚህ መካከል እንደ ባዶ ቀፎ ወይም ቱቦ ነኝ። እርምጃዬንና ማረፊያዬን ሁሉ እንደተቆጣጠሩት ስረዳ ወደ መሬት ሰግጄ ቀና አልኩና "ፈጣሪዬ ሆይ! የድፍረት ኀጢአቴን ይቅር በለኝ። ይህን ሁሉ ነገር ለበጎ አድርግልኝ" አልኩኝ።

የአክሱም ጽዮን ግቢ በምሽት ድባብ እየተዋጠ ነው። በአግራሞትና በተደሞ ቅዱሱን ግቢ በቀስታ እየተራመድኩ አቋርጬ ወደ ማረፊያዬ ‹የሃ ሆቴል› አመራሁ።

# ምዕሁፍ ለምንጉ

በጠዋት ቀደም ብዬ ተነሣሁና የኮንትራት ባጃጅ ተከራይቼ ከአክሱም ከተማ በስተምሥራቅ አቅጣጫ አራት ኪሎ ሜትር አካባቢ ወደሚገኘው ጥንታዊው የአባ ጰንጠሌዎን ገዳም አመራሁ።

አባ ጰንጠሌዎን በ7ኛው ክፈለ ዘመን አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት ተሥዓቱ ቅዱሳን አንዱ ሲሆኑ ይህ ገዳምም በእርሳቸው እንደተመሠረተ ይታመናል። የገዳሙ ቤተ ክርስቲያን ከአንድ ትልቅ ኮረብታ ጫፍ ላይ የተሠራ ሲሆን የኮረብታው ወይም የተራራው አናት ሙሉ በሙሉ በቤተ-መቅደሱ ተሸፍኗል። ቤተ መቅደሱ አራት ማእዘን ቅርፅ ያለው ሲሆን ግድግዳው ሙሉ በሙሉ በሚያምር የድንጋይ ግንብ የታነጸ ሆኖ የጣራው ቅርጽ ሰቀላ የሚባለው ዐይነት ነው። ከኮረብታው ግርጌ የሚገኙትን ቆርቆሮ ቤቶች ዐልፎ ቀጥ ያለ ደረጃ በመውጣት ወደ አባ ጰንጠሌዎን ገዳም ቤተ ክርስቲያን መግባት ይቻላል። ለወንዶች ብቻ የተፈቀደው ይህ ቤተ ክርስቲያን ሁለት ክፍል ያለው ሲሆን ከመቅደሱ ውጪ ያለው ቅኔ ማሕሌቱና ቅድስቱ አንድ ላይ የተቀላቀለ ሰፊ ክፍል

ነው። የቅኔ ማሕሌቱ ምሥራቃዊ በር ሲከፈት ከሁለት ሜትር በኋላ የገደለ ጫፍ ነው። እዚህች ኮርብታ ላይ ሆኖ ሲመለከቱ ደግሞ በአሻጋሪ የአክሱም አውሮፕላን ማረፊያ ተንጣሎ ይታያል።

ከቤተ ክርስቲያኑ ስደርስ የኪዳን ጸሎት አልቆ ስለነበር አንዳንድ አባቶች የግል ጸሎት እያደረሱ ነበር። ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ስዘልቅ አንድ አጠር ያሉ ሽበታም አዛውንት መነኩሴ ከቅኔ ማሕሌቱ በስተደቡብ አቅጣጫ ባለ ወንበር ላይ ተቀምጠው የንባብ መነጽር አድርገው የጸሎት መጽሐፍ ይደግማሉ።

የቤተ-መቅደሱን በር ተንበርክኬ ተሳለምኩና ቀና ብዬ ወደ እርሳቸው ዘወር ስል ከመነጽራቸው ውጭ በላይኛው ጠርዝ ትኩር ብለው አዩኝና መልሰው ወደ ጸሎታቸው አቀረቀሩ። ልክ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም አባ ኪዳነ-ማርያም ይዘዋት እንዳየኋት ያለች ከዱር እንጨት የተሠራች ከዘራ ከጐናቸው ግድግዳውን ተደግፋ ቆማ አየኋት። "አባ ወልደ አረጋዊ እኒህ መሆን አለባቸው" አልኩ ለራሴና ጸሎታቸውን እስኪጨርሱ ቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ትኩረቴን የሚስብ የተለየ ዕፅዋት ካለ ብዬ ለመቃኘት ወጣሁ።

ወደ ገደሉ እንዳልንሸራተት ተጠንቅቄ ዛፉንም ቁጥቋጦውንም አስተዋልኩት። ሁሉንም የማውቃቸው በመሆኑ የተለየ ትኩርቴን የሚስብ ነገር አጣሁ። ተመልሼ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ወስጥ ገባሁና በሰሜን አቅጣጫ ያለውን ግድግዳ ተደግፌ ኩርምት ብዬ ተቀመጥኩ።

ትንሽ ቆይቶ አንድ ወጣት ዲያቆን ነጠላውን አደግድጐ የቤተ-መቅደሱን በር ሦስት ጊዜ ከተሳለመ በኋላ ወደ ውስጥ ገብቶ አንድ ትልቅ የብራና መጽሐፍ ይዞ ወጣና ከአባ ፊት ለፊት በአትሮንስ ዘርግቶ መጽሐፉን ከፍቶ እልባት ካደረገበት በኋላ አባ እስኪጨርሱ ድረስ እንደኔ ኩርምት ብሎ ቁጭ አለ።

ወደ ሦስት ሰዓት አካባቢ አባ ጸሎታቸውን ጨርሰው አቡነ ዘበሰማያትን ደግመው ዲያቆኑን በመስቀላቸው ሲያሳልሙት አኔም ምንጥቅ ብዬ ተነሥቼ ተሳለምኩ። ዲያቆኑ መጽሐፉን በአንድ እግሩ ቆሞ ሌላኛውን እግሩን እጥፍ አድርጐ ከሌላኛው እግሩ አስደግፎ ማንበብ ጀመረ። ንባቡ በግእዝ ቢሆንም ‹ስንክሳር› የተባለው በየዕለቱ ቅዱሳንንና ሰማዕታትን የተወለዱበትን ወይም የዐረፉበትን ወይም ከፈጣሪ ቃል ኪዳን የተቀበሉበትን ቀን ተከትሎ ከብራቸውን፣ ተጋድሎአቸውንና ቃል-ኪዳናቸውን የሚዘክረው መጽሐፍ መሆኑን መረዳት አላቃተኝም።

አባ መጽሐፉ ሲነበብ ፊገግ ሌላ ጊዜ ደግሞ በአድናቆት ፊታቸውን ወደ ላይና ወደ ታች በማወዛወዝ ያዳምጣሉ። ይህ ሁሉ ሲሆን ዐይናቸውን ጨፍነው አገጫቸውን በቀኝ እጃቸው ተደግፈው ነው። ዲያቆኑ የዕለቱን ንባብ ሲጨርስ መጽሐፉን አጥፎ አባን አሳለመና እኔን ለማሳለም ወደ እኔ ሲመጣ ቀልጠፍ ብዬ ተሳለምኩና በቀስታ፡- “ይቅርታ የእኔ ወንድም አባ ወልደ አረጋዊ እኒህ ናቸው?” አልኩት። ቃል ሳይናገር ራሱን በአዎንታ ነቀነቀልኝ።

አባ ተነሥተው ቁመው ጸሎት አደረጉና ከዘራቸውን ተደግፈው በእኔ በኩል ዐልፈው በስተ ሰሜን በኩል ባለው ዋናው መውጫ በር ሊወጡ ሲመጡ ከእግራቸው ሥር ልስማቸው ውድቅ ስል በፍጥነት ወደ ኋላ አፈገፈጉና “አይገባም የእኔ ልጅ” ብለው ትክሻዬን ይዘው አስነሡኝና፡-

“እንግዳ ትመስላለህ ከወዴት መጣህ የእኔ ልጅ?” አሉኝ።

“አዎን አባቴ እንግዳ ነኝ” አልኳቸው።

“ከወዴት መጣህ?” አሉኝ።

“አሁን ከየት እንደመጣሁ አጥተውት ነው?” እያልኩ በልቤ

“ከባሕር ዳር ነው። እርግጥ አሁን የመጣሁት...” ብዬ ዝም ስል

“እንኳን በደኅና መጣህ” ብለው እጄን ያዙኝና በቀስታ የኮረብታውን ደረጃዎች መውረድ ጀመርን።

ደረጃውን ጨርሰን ከደልዳላው ስንደርስ ወደ ቀኝ ታጠፍንና ከአንድ ዛፍ ሥር በግን በቁጥቋጦ የተከበበች ጠፍጣፋ ድንጋይ ላይ ሄደው ዐረፍ አሉ።

“አባታችን ለእርስዎ መልእክት ነበረኝ” አልኳቸው።

ለመልእክቱ ብዙም ጉጉት ሳያሳዩ፡-

“እንኳን መጣህ የእኔ ልጅ! እንኳን ይህን የተቀደሰ ቦታ ለመርገጥ አበቃህ” አሉ።

በልቤ “ወድጄን መሰለዎት!” እያልኩ “አሜን አባታችን!” አልኳቸው።

“ይህ ቦታ፣ አሁን ያለህበት ሥፍራ አንድ ድንቅ ታሪክ ተጠናቆ ሌላ ግሩም ታሪክ የተጀመረበት ሥፍራ ነው” አሉ።

“እንዴት ማለት?” አልኩ በጉጉት ጆሮዬን አቁሜ።

“ዐፄ ካሌብ የሚባሉ የኢትዮጵያ ንጉሥ በየመን የሚገኙ ክርስቲያኖች በአረማውያን ግፍና መከራ እንደበዛባቸው ሲሰሙ ነጋሪት አስጎስመው፣ ጦር አስከትተው፣ ቀይ ባሕርን አቋርጠው ዘመቱ። ጠላቶቻቸውን አጥፍተው፣ ክርስቲያኖችን ታድገው፣ ለክርስትና ሃይማኖት ያላቸውን ተቆርቋሪነት በተግባር አረጋገጡ። ክርስቲያኖችን አረጋግተውና ድላቸውን አረጋግጠው ሲያበቁ ወታደሮቻቸውን ሰብስበው እንዲህ አሉ፡-

‹ልጆቼ ጦርነቱን በድል አሸንፈናል፣ ክርስቲያን ወገኖቻችንንም ታድገናል። እስከ አሁን ድረስ ትእዛዜን እንዳከበራችሁ ሁሉ

ዘራም ትእዛዜን አስተላልፍላችኋለሁ። ሁላችሁም ወደ ሀገራችን ስትመለሱ የቻላችሁትን ያክል ዐፈር ይዛችሁ እንድትሄዱ ይሁን› ብለው አስታወቁ" አሉ።

"እንዴ ለምን? ኢትዮጵያ ዐፈር ጠፍቶ ነው?" አልኩ።

አባ ፈገግ አሉና "ወታደሮቹም ያሰቡት እንዳንተው ነበር። ለማንኛውም ግሚሱ ወታደር ‹ከሀገራችን ርቀን፣ በየብስና በባሕር መንከራተታችን ሳያንሰን ደግሞ እንዴት ዐፈር ተሸክመ እንባላለን?› ብለው በቁጣ ባዷቸውን ሲመጡ ሌሎቹ ደግሞ ‹ምንስ ቢሆን የንጉሥ ትእዛዝ አይደል?› ብለው ለትእዛዙ ማክበሪያ ያክል ትንሽ ትንሽ በመሀረብ እየቋጠሩ ይዘው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ" አሉ።

"ከዚያስ" አልኳቸው በጉጉት።

"ዐፄ ካሌብ ወደ ሀገራቸው መጥተው ቤተሰባቸውን፣ ሕዝባቸውንና ሹማምንቶቻቸውን ከአረጋጉ በኋላ አብሯቸው የዘመተውን ወታደር በሙሉ ከዚህ ስፍራ ሰብስበው ‹ወገኖቼ ቃሌን አክብራችሁ፣ ሀገራችሁንና ሃይማኖታችሁን ብላችሁ፣ በየብስ በባሕር ስለተንከራተታችሁ ፈጣሪ ሰማያዊውን ዋጋ እርሱ ይክፈላችሁ። አሁንም ለአደረጋችሁት መልካም ሥራ ባይመጥንም ለመተዳደሪያ ይሆናችሁ ዘንድ በየመን ሳለን ያዙ ያልኳችሁ ዐፈር ንጹሕ ወርቅ ይሁንላችሁ። በእርሱ አርሳችሁ፣ ነግዳችሁ ልጅ አሳድጉ፣ እንግዳ ተቀበሉ› ብለው መረቁ" አሉ።

"እንዴ ከዚያስ?" አልኩ አፌን ከፍቼ።

"ከዚያማ ዐፈር የያዘው ሁሉ መሀረቡን ሲፈታ ዐፄ ካሌብ እንደተናገሩት ወርቅ ሆኖ ተገኘ። እናም አስገራሚው የዚህ ዓለም የሰው ልጅ ዕጣ ፈንታ የተገለጸበት አባባል በሊቃውንቱ አንደበት ተነገረ" አሉ።

“ምን ተብሎ?” አልኩኝ ፊታቸውን ትኩር ብዬ እያየሁ።

“‹ዘአጎዘ ሐዘነ ወዘኢአጎዘ ሐዘነ› ብለው ተናገሩ” አሉኝ።

“ምን ማለት ነው ?” ስላቸው ፊገግ አሉና

“የያዘም አዘነ ያልያዘም አዘነ ማለት ነው” አሉኝ።

“አልገባኝም አባታችን” አልኳቸው

“አየህ የእኔ ልጅ! በዚህ ጊዜ በሁሉም ሰው ዘንድ ሐዘን ተፈጠረ። ዐፈር ያልያዘውም ምነው ይገፍ ቢሆን ኖሮ ብሎ ሲያዝን፤ የያዘው ደግሞ እስኪምናለበት በርከት አድርጌ ብዘግን ኖሮ ብሎ ነዋ!” አሉኝ።

“ገባኝ ልክ ነው! ዘመኑን የሚገልጽ ግሩም ኢትዮጵያዊ ፍልስፍና ነው” ስላቸው በእጃቸው ወደ ከተማው እያመለከቱ “ዛሬም ያው ነው። የሌለው ሲያለቅስ ያለውም ያጉረመርማል፤ ጫማ የለኝም የሚለው እግር ከሌለው ጋር እኩል ሲያዝን፤ የአንገት ማስገቢያ የምትሆን ጐጆ አጥቶ የሚጨነቀው ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ለመሥራት ከሚዳክረው ጋር ሐዘኑ እኩል ነው።በቃ በዚህ ዓለም....” ብለው ትክዝ ሲሉ ከአፋቸው ነጠቅ አድርጌ

“እናቱ ወንዝ የወረደችበትና እናቱ የሞተችበት እኩል እንደተባለው” አልኳቸው።

አባ ቀጠሉ፡-

“እናም ዐፄ ካሌብ በዚህ ሁኔታ ሠራዊታቸውን ካሠናበቱ በኋላ ዙፋናቸውንና በትረ መንግሥታቸውን ለልጃቸው ለዐፄ ገብረ መስቀል አውርሰው እዚች ድንጋይ ላይ” የተቀመጡበትን ድንጋይ እያሳዩ “ልብሰ-መንግሥታቸውን አውልቀው ጸጉራቸውን ተላጭተው የምንኩስና ቆባቸውን ጭነው ወደ ምናኔው ዓለም ገቡ” አሉኝ።

"ባጣም ይደንቃል!" ስል

"እና በዚህ የተነሳ ይህች ስፍራ ‹መካነ ጎርመት› ትባላለች!" አሉኝ።

ወዲያው አእምሮዬ ውስጥ ብልጭ አለብኝና

"እንዴ!" ብዬ ‹መካነ ጎርመት› የሚለውን ቃል ደገምኩና "ዕፀ-ጎርመት የምትባለውስ?" ስላቸው ፈገግ ብለው ከድንጋዩ ላይ ያጠላችውን ዕፅ ቀና ብለው ተመለከቱ። በስሜት ተነሣሁና እጃቸውን ሳብ አድርጌ ሳም ሳም አደረኩት።

በስውር ከተጻፈልኝ ብራና ላይ በሁለተኛው ተራ ቁጥር የተጻፈው እንዲህ የሚል ነበር።

‹ዕፀ ጎርመት ዘገዳመ ጸንጠሌዎን ጻድቅ›

ደስታዬን አጣጥሜ ወደ ልቡናዬ ተመለስኩና፡-

"አባታችን እዚህ የመጣሁት እኮ ይህቺን ዕፅ ፍለጋ ነው" አልኳቸው።

ፈገግ ብለው ዝም ብለው ሲያዩኝ ቆዩና "መቼ ወደ ባሕር ዳር መመለስ አሰብክ?" አሉኝ።

"አባታችን ዕድሜ ለእርስዎ እንጂ ከዚህ የመጣሁበትም በቀላሉ ተጣክቶልኛል። ምናልባት ላስታ ውስጥ አንድ ቦታ መድረስ ይኖርብኛል እንጂ በቶሎ ለመመለስ ነው ዕቅዴ" አልኳቸው።

ትንሽ ዝም ብለው ቆዩና፡-

"በጌምድር አንድ የምሄድበት ጉዳይ ነበረኝ" አሉ ማዶ ማዶ እያዩ።

ቀበል አደረኩና፡-

"አባታችን! አባ ኪዳነ ማርያም ከማኅበረ ሥላሴ ገዳም ‹ለሠርጉ

እንዳይቀሩ አደራዎትን፣ ብለዎታል አልኳቸው" ሌላ ተደራቢ መርሐ ግብር ድንገት እንዳይዙ ብዬ።

"አባታችን ደኅና ናቸው?" አሉኝ ።

"ያገኘኋቸው ለአንዲት ሰዓት ብቻ ነው። ግን ደኅና ይመስሉኛል" አልኳቸው። ትኩር ብለው እያዩኝ ዝም ሲሉ ጨነቀኝና፡-

"አባታችን በመንገድ ላይ አንድ ሁለት ቀን መቆየቴ የማያስቸግረዎት ከሆነ በጌምድር ለምን ከእኔ ጋር አንሄድም?" አልኳቸው።

"መኪና ይዘኻል አይደል?"

"አዎን!" አልኳቸው።

"የማስቸግርህ እንዳይሆን እንጂ ማለፊያ ነው" አሉኝ።

"በፍጹም! ይልቁንስ እኔ እንዳላስቸግርዎት እንጂ።"

"እንተማ ምን ብለህ ታስቸግረኛለህ?"

"እንዳልኩዎት ስመለስ ላስታ ውስጥ ከአንድ ጥንታዊ ደብር መድረስ አለብኝ እና እንዳይጉላሉ ብዬ ነው" አልኳቸው።

"እርሱማ እኔስ ቅዱሱን ደብር ብሳለም ምን አለበት?" አሉኝ።

"አባታችን እንግዲያውስ ይሄ ለእኔ ክብር ነው። ብቻዬን ከምጓዝም አብረውኝ ቢሆኑ መልካም ነው" አልኳቸው በደስታ።

"ማለፊያ ነው እንግዲያውስ የዛሬን እንደርና ነገ አብረን እንሂድ" አሉኝ።

"አዎን የእኔም ሐሳብ እንደዛው ነው" አልኩኝና "ነገ በጠዋት ከዚህ ተነሥተን ‹በዓቢይ ዓዲ› አድርገን ‹አበርገሌን› አቋርጠን ዋግ ስቆጣ ከተማ እናድራለን። ከዚያ እንቀጥላለን" አልኳቸው።

"ማለፊያ ነው" አሉ።

"እንግዲያውስ በጠዋት ከዚህ መጥቼ ልውሰድዎት?" ስላቸው።

"ግዴለም አክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በሩ ላይ እቆይሃለው" አሉኝና ተነሥተው ጸሎት አድረገው ሲያበቁ ወደማረፊያቸው ሊወሰዱኝ ሲሉ፡-

" ከዛፏ አንዲት ዘለላ ልቁረጥ እንጂ?" ስላቸው

"በፊት እህል ቅመስ። ስትሄድ ትቆርጣለህ" አሉኝ በፈገግታ።

እሺ ብዬ ወደ መኖሪያ ቤታቸው ወሰዱኝ። ከቤተ ክርስቲያኑ በስተሰሜን አቅጣጫ የተሠራ አራት ክፍሎች ያሉት ትልቅ ቤት ነው። ጠዋት ስንክሳር ባነበበው ዲያቆን አስተናጋጅነት ምሳዬን ተጋበዝኩና ከአባ ጋር ስለ ሥራዬ ስለ ኑሮዬ እየጠየቁኝ እየነገርኳቸው ቆይቼ፤

"እንግዲህ ልሂድ አባ፤ ያው ጠዋት እንገናኛለን" ብዬ ተነሣሁ።

"አትቆይም ትንሽ?" አሉኝ።

"ነገ በጠዋት መሄድ እንድንችል መኪናዬን ጋራዥ ስለተውኳት ልሂድና ልከታተል" አልኩ።

"ግዴለም ደኅና፤ ይሁን" አሉና ተነሥተው ሊሸኙኝ ተከተሉኝ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ሐሳቤ ሁሉ ያለው ከዕፁ ላይ ነው። አባ አንድ እጄን ይዘው በሌላኛው እጃቸው ከዘራቸውን ተደግፈው ጠዋት ተቀምጠው ሲያወሩኝ ወደነበረበት ስፍራ አመራን።

ስንደርስ ግን በድንጋጤ ይሁን በአግራሞት የማየውን ማመን አቅቶኝ ተንገዳግጄ ልወድቅ ምንም አልቀረኝም ነበር።

ጠዋት ጥላው ከድንጋዩ ላይ ዐርፎ ያየሁት ዛፍ (ዕፀ ጎርመት) በቦታው አልነበረም።

"አባታችን የት ሄደ? ምንድን ነው ነገሩ አልኳቸው?" እየተንተባተብኩ።

"የትም አልሄደም" አሉ በእርጋታ።

"ታዲያ መች ይታየኛል?" አልኩ። በቅዠት ውስጥ ያለሁ መሰለኝ።

"እውቃለሁ" አሉ።

"እንዴት ነው የምሆነው? ለምን ቅድም የምቆርጠውን ቆይ አሉኝ?" አልኩ በምሬት።

"አይዞህ የኔ ልጅ እንደታዘዝከው ትወስዳለህ። ብቻ ይህን ድንቅ ነገር እንድታይ ብዬ ነው" አሉና "አትጨነቅ ጠዋት ይገልህ እመጣለሁ" አሉ እራሴን እያሻሹ።

ወዲያው ተረጋጋሁና "ግን እንዴት ይሆናል?" አልኳቸው በመገረም

"አምን! ሁልጊዜ ፀሐይ በአናት ስትሆን ዕፁ አይታይም" አሉ።

"ለምን?" አልኩኝ።

"ያንማ አንተ ተመራማሪ አይደለህ? ወደፊት ተመራምረህ ድረስበት እንጂ" አሉና ፈገግ ብለው "በል ሳይቀትር ሂድ ጠዋት እንገናኛለን" አሉና አሳልመውኝ እንድሄድ ሲገፉፉኝ በአድናቆት አንደተመሰጥኩ፤ ግራም እንደተጋባሁ ግቢውን ለቅቄ ወደ አክሱም ከተማ ተመለስኩ።

ከሆቴል ደርሼ ዕረፍት ላደርግ ብሞክር ያየሁት ነገር ሰላም የሚሰጠኝ አልሆነም። ይህ አይነት ክስተት እንዴት ሊፈጠር እንደሚችል ከሳይንስ አንጻር መልስ ለማምጣት ከአእምሮዬ ጋር ፍትጊያ ገጠምኩ። የተለያዩ መላምቶች ቢመጡልኝም ለጊዜው የሚያረካኝ መልስ ማግኘት አልቻልኩም። ስለዚህ ቁጭ ብዬ መልስ ለማላገኝለት ጥያቄ አእምሮዬን ከምበጠብጥ መኪናዬን አውጥቼ የአርኪዮሎጂ ቁፋሮ ቦታዎችን ለመጎብኘት ወደ አታኽልቲ ጋራዥ አመራሁ። ከጋራዡ ስደርስ አታኽልቲ የአንድ መኪና የፊት ኮፈን ከፍቶ ከረዳቱ ጋር የሆነ ነገር እያጠባበቁ አገኘኋቸው።

ሲያዩኝ በፈገግታ

"እንዴት ነህ? ከተማ አካሱም ተመቸህ?" አለኝ አታኽልቲ።

"አዎን በጣም ተመችታኛለች" አልኩት ፈገግ ብዬ።

"መኪናህም በደንብ ተጠግናለች። አይትጨነቅ" አለኝ።

"አመሰግናለሁ! ስንት ልክፈል?" አልኩት።

"በቃ አያስፈልግም"

"እንዴ! የድካምህን ዋጋማ መክፈል አለብኝ" አልኩ።

"ዋይ! አንተ ማርያም ጽዮን ልትሳለም የመጣህ አይደለም እንዴ?"

"እርሱማ ነው?"

"ዋይ! አታ እኔስ ክርስቲያን አይደለሁ እንዴ?"

"እርሱማ ነህ፤ በአግባቡ መሥራትህ በራሱ እኮ መልካም ነገር ነው እና እባክህ" አልኩት።

"ዋይ!" አለ ነገሩን አቅልሎ እንዳየው የሚያሳስብ ምልክት በእጁ እያሳዬ።

“ስማ አታ ፍትሕዊ መኪናዋን ወደ ውጭ አውጣለት” አለው በትግርኛ።

ወደ እርሱ ተጠግቼ እጆቼን ዘርግቼ አቅፌ ላመሰግነው ስራመድ አየና፡-

“ዋይ አታ ወዲ! ቆሻሻ ቱታ አይታይህም እንዴ!” አለ ወደ ኋላ እየሸሸ።

የሚገርመው ንግግሩ ሁሉ ቁጣ የተሞላ ይመስላል። ደግነትና ቁጣ ተደባልቆ ሲነገር የሆነ ልብ የሚሞላ ፍቅርና ቅንነትን ያሳያል። እናም ለራሴ፡- “የትግራይን ሕዝብ ፍቅር ታላፊ ጊዜ በፊጠረው ውሸንብር ሳትዘናጋ እርሱን እንደ ጥሩ ጠላ ገፈት እፍ እያልክ ከሥር መጠጣት ይገባሃል” አልኩት።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

ከአባ ወልደ አረጋዊ ጋር በተቀጣጠርነው መሠረት ከጠዋቱ 12:00 ሲሆን ከአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን በር ላይ ሲጠብቁኝ አገኘኋቸው። ቢጫ የመነኩሴ ቀሚስና ከላይ እንደዚሁ ከሱፍ ክር የተሠራ ቢጫ ጋቢ መሳይ ነገር ለብሰዋል። አንዲት አነስ ያለች ቦርሣና መደገፊያ ከዘራ ከመያዛቸው ውጭ ባዶአቸውን ናቸው ማለት ይቀላል።

አባ ጸሎት ካደረጉ በኋላ ወደ አድዋ የሚሄደውን መንገድ ተከትለን የአክሱም ከተማን ለቀን ጉዟችንን ጀመርን። አክሱምን እየራቅን ወደ አደዋ በተጠጋን ቁጥር ታሪካዊዎቹን የአድዋ ተራራሮች በጀግንነት እንደተከፈሱ በሩቁ ማየት ጀመርኩ። ከመንገዱ ዳር አንድ ግማሽ አካሉ ዐፈር ደለል ውስጥ የተቀበረና የተቃጠለ የታንክ ቅሪት አየሁና አባን እንዲህ አልኳቸው፡-

“ይህ አካባቢ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን በአንድነት ወራሪውን የጣልያንን ሠራዊት ፊት ለፊት በሀገር ፍቅርና በነጻነት ስሜት የገጠሙበት ቦታ ነው። ኢትዮጵያዊያን ነጻነታቸውን በቀላሉ አሳልፈው የማይሰጡ ጀግኖች የመሆናቸውን ሐቅ ፊት ለፊት ለጣሊያንና ለባዕዳን የነገሩበት ታሪካዊ ምድር ነው”።

“በ1980 ደግሞ ታሪክ መልኩን ቀይሮ እዚሁ አካባቢ ላይ የአንድ እናት ልጆች የሆኑት የሕወሃት እና የደርግ ሠራዊት ተፋልመውበታል። በጦርነቱ ሕወሃት የደርግን ሠራዊት 801ኛ ኮር ሙሉ በሙሉ የደመሰሰበትና ከሁለቱም ወገን በርካታ ኢትዮጵያውያን የተሰውበትና ብዙ ሀብት የወደመበት ሆኖ አልፏል። ይህ የእርስ በርስ ጦርነት ከወርቃማ ታሪካችን ውስጥ አንዱ አሳዛኝ ገጽታ ይመስለኛል። ምናለ የአድዋ ተራሮች ባዕዳንን እንደተዋጋንባቸውና አንፀባራቂ ድል እንደተጎናፀፍንባቸው የብልጽግና ስፍራ ብቻ ሆነው ኖረው ቢሆን!” አልኳቸው።

አባ ፈገግ ብለው፡ “እውነትክን የኔ ልጅ። የእርስ በእርስ ጦርነት አስቀያሚነቱ የሚመነጨው የድሉም ሆነ የሽንፈቱ ፍሬ መራራ መሆኑ ነው” አሉና

“ድል ቀንቶህ ለጊዜው ደስ ቢልህም የገደልከው ወንድምህን ነውና፤ በሞቱ ያለአባት የቀሩትን ልጆች፣ ያለባል የቀረችውን መበለት ሚስቱን፣ ያለ ጧሪ የቀሩትን ወላጆቹን የማስተዳደር ሐላፊነትን መሸከም የኋላ ኋላ ያንተ ይሆናል። ሰው መሆንክን እስካልረሳህ ድረስ ይህ ሐላፊነት ደግሞ በጦርነቱ ያገኘኸውን ድል የበለጠ መራራ ያደርግብሃል።”

“የእርስ በእርስ ጦርነት መራራ ሀገራዊ መዘዝ ከማምጣቱ በላይ ለአንዳንድ ግለሰቦች በተለይ ለእንስቶች ውስጣዊ ሕመምና የሥነ ልቦና ጠበሳ ጥሎ ያልፋል” አሉ።

"እንዴት? አልኳቸው። የበለጠ ከእርሳቸው ለማወቅ በመጓጓት እንጂ ቢያንስ አደይ አብረኸት በዐይነ ኅሊናዬ አይጠፉምና ነገሩ ጠፍቶኝ አልነበረም።

"ለምሳሌ" አሉ በእርጋታ፡-

"የላስታው ገዥ የነበሩት ንጉሥ ተክለ ጊዮርጊስ ሚስት የደጃች ካሳ (ዐፄ ዮሐንስ) እኅት ነበሩ። በሥልጣን ሽኩቻ ባላቸውና ወንድማቸው ለጦር ተሰላለፉ፤ በጦርነቱ ባላቸው በወንድማቸው ተሸንፈው እጅና እግራቸው ተቆራርጦ ዐይናቸው ተጎልጉሎ ተገደሉ።"

"አየህ! በአንድ ዐልጋ የሚተኙትን ባለቤታቸውን በአንድ ማሕፀን የተኙት ወንድማቸው ሲገድሉባቸው፤ የሸንፈትንና የድል ጽዋን መጠጣት የእኒህ ልዕልት ግዴታ ሆነ። እናም እንዲህ አሉ፡

"ተናግሬ ነበር እኔስ አስቀድሜ

ሚቹ ባሌ ቢሆን ገዳዩ ወንድሜ"

በወቅቱ አልቃሾችም ተቀብለው፡-

"ገዳዩ ወንድም'ሽ

የሞተውም ባልሽ

ሐዘንሽ ቅጥ አጣ

ከቤትሽ አልወጣ"

ብለው ሙሾ አውርደውላቸዋል ይባላል።

"የደጃች ካሳ (የዐፄ ቴዎድሮስ) ሚስት እትጌ ተዋበች በቴዎድሮስ የሥልጣን ጉዞ ውስጥ ባላቸውን ወግነው አባታቸውን ትንሹን ራስ ዐሊን ባላቸው እንዲወጉ መፍቀድ ወይም መርዳት ነበረባቸው።

ድሉ የባል ሆኖ ሲመጣ የአባትንም የሽንፈት ጽዋ መጠጣት ግድ ይል ነበር"።

"ከዚሁ ከቴዎድሮስ ታሪክ ሳንወጣ እቴጌ ጥሩ ወርቅ ደም ለማድረቅና ሕዝብን ለማቀራረብ ሲባል የአባታቸውን የራስ ውቤን ገዳይ አግብተው ተወዳጅ ልጃቸውን ልዑል ዓለማየሁን መውለድ ነበረባቸው። በርግጥ የራስ ውቤን ዘር ከዙፋን ላለመንቀል የተደረገ ፖለቲካዊ በጎነት ቢሆንም ወጣቷን ጥሩወርቅን የመሥዋዕት በግ ማድረጉን ማሰብ ታሪኩን መራራ ያደርገዋል" አሉ። ለስለስ ብለው ስለሚተርኩ ጉጉት ያጭራሉ።

"ንግሥት ዘውዲቱ የምኒልክ ዐልጋ እንዲረጋጋና ማዕከላዊውን መንግሥት ለማጽናት በሚል ፖለቲካ ከሚወዱት ባላቸው ከራስ ጉግሣ መለያየት ነበረባቸው። የምኒልክ ዐልጋ ከሸዋ ወጥቶ በሆነ ምክንያት ወደ ሰሜን በጌምድር እንዳይሄድ ሲባል ‹ከእንግዲህ ንግሥት በጸሎትና በጾም ስለሕዝባቸውና ሀገራቸው ማሰብ ስለሚኖርባቸው ባል አይፈልጉም› ተብለው ከሚወዷቸው ባላቸው ተለዩ። ይህም አልበቃ ብሎ ይህን ግፍ አልቀበልም በማለታቸው እንደ ዐማፂ የተቆጠሩትን ባላቸውን በጦር እንዲደመሰሱ በርእሰ ብሔርነታቸው ከባለሙሉ ባለሥልጣን እንደራሴያቸው ከራስ ተፈሪ ጋር ተመካክረው ጦር ማዝመት ነበረባቸው። ደግነቱ በእርሳቸው መንግሥት ጦር የተዘመተባቸው ባለቤታቸውን ሞት መርዶ ሳይሰሙ እርሳቸውም በዚያው ቀን አመሻሽ ላይ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸው ነው"።

"እቴጌ መነን ሸዋንና ወሎን እንዲሁም ሁለቱን ባላንጣዎች ልጅ ኢያሱንና የሐረሩን መስፍን ተፈሪን ለማስማማት ሲባል በተጀመረ ጋብቻ የእናታቸውን ተወዳጅ ወንድም ልጅ ኢያሱን በሰንሰለት አስሮ ድራሹን ያጠፋውን ሰው አግብተው እቴጌ ተብለው መኖር ነበረባቸው። አየህ! የእነዚህ ሴቶች መከራ። የሥልጣን ሽኩቻና የእርስ በእርስ ጦርነት መዘዙ ብዙ ጠባሳው ሰፊ ነው" አሉ።

"አምን ልክ ነው። አሁን አሁን እኮ ግን ይህ ችግር እየተቀረፈ መጥቷል። ሴቶች ለፖለቲካና ለሥልጣን ሲባል ጋብቻ አይመሠርቱም" አልኩኝ።

"ነው እንጂ። የአሁን ዘመን ፖለቲከኞች በመንደር በመንደራቸው ብቻ ስለሚያገቡ እውነት አልክ" አሉና ማዶ ማዶ ማየት ጀመሩ።

በአንድ ወቅት ከዶ/ር ክብረ በዓል ጋር ስንነጋገር እርሱ በሰፊውና በቁጭት የሚናገርለትን ሐሳብ በአጭሩ ሲገልጹት ሰሰማ ድንገት ክት ብዬ ሣቅሁ። ነገሩን አጥብቤ በቅንጭፉ እንደተመለከትኩትም ገባኝ።

ዶ/ር ክብረ በዓል "የቀድሞዎቹ ሰዎች የፖለቲካና የስልጣን ሽኩቻ ችግር ከሚፈቱባቸው መንገዶች የተወሰኑት የሚናቁ አልነበሩም" ይላል። አንድ ቀን በሀገራችን ውስጥ ዐልፎ ዐልፎ ስለሚታየው ግጭት አንስተን ስናወራ እነዲህ አለ፡-

"የአሁን ዘመን ፖለቲከኞች እኮ ከመንደራቸው ውጭ ለፍቅርም ይሁን ለፖለቲካ ዓላማ ማግባት አይችሉም"።

"ለምን? ማን ከልክሏቸው?" አልኩት

"አንድ የኦሀዴድ ባለሥልጣን ሚስቱ የታወቀች ዐማራ ብትሆን ካድሬው ሁሉ ‹እንዴት ነፍጠኛ አገባ?› ብሎ ሲታመስ፣ የደቡብ ባለሥልጣን ትግሬ ቢያገባ ‹አዛኟ እኮ እርሷ ነች፡ ደጎንነት እኮ የተከለበት ናት› ተብሎ ሲወራ አይታይህም። አንድ የብአዴን አባል ኤርትራዊት ወይም የትግሬ ሴት ቢያገባ ወይም አንድ የሕወሃት አባል ኤርትራዊት ቢያገባ ወይም አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ በዚህ ስሌት ጋብቻ ቢመሠርት የትኛው ፓርቲ ውስጥ ያለሓሜት ገብቶ መታገል ይቻላል? ሳናውቀው እኮ የሕዝባችንን የመገናኛ ድልድይ ሙሉ በሙሉ ማፍረስ ባይቻል አንኳን አናግተነዋል። የበፊቶቹስ ግለሰብን የመሥዋዕት በግ ቢያደርጉም ሕዝብን ለማስተሳሰር የላቀ

የፖለቲካ ጥበብ ተጥቀመዋል ማለት ይቻል ይሆናል። የአሁኑ ግን የችግር መፍቺያ ማስተሥርያ ሥርዓቱም መሥዋእቱም ያለ አይመስልም፤ ወይም በደንብ እየሠራ አይደለም?" ነበር ያለኝ።

ከአባ ወልደ አረጋዊ ጋር አእምሮን በሚሞግቱና ዐልፎ ዐልፎ መንፈስን በሚያሸፍቱ ውይይቶቻችን ከፍና ዝቅ ሰል ውዬ ወደ ዐሥር ሰዓት አካባቢ ‹አበርገሌን› ዐልፊን ‹የጥራሪን› ወንዝን ተሻግረን ዋግኽምራ ሰቆጣ ከተማ ደረስን።

የዋግ ተራሮችና ሸንተረሮች ሰውና ድርቅ ተጋግዘው ቢያጎሳቁሏቸውም አሁንም የሰውን ዐይን ለመሳብና ቀልብ ለመግዛት የሚሆን ዐፅመ-ውበት አላጡም። እንዲያውም በሥነ-ምህዳር ሳይንስ እሳቤ ለሚያያቸው ሰው ወድቆ የተሰበረውን ትልቁን የአክሱም ሐውልት ትርክት ያስታውሳሉ።

የአክሱም ሸማግሌዎች እንደሚያወጉት ዮዲት ጉዲት የተባለች ንግሥት ከሁሉም ትልቁ የነበረውን ሐውልት ተሰብሮ እንዲወድቅ ካደረገች በኋላ ከወደቀው በቁመትም በወርድም የሚያንሱትንና አሁን እንደቆሙ ያሉትን ቀጥለው ሊጥሏቸው ሲሉ፡-

"እነርሱን ተዋቸው" አለቻቸው።

ጭፍሮቿም "ንግሥት ሆይ ለምን?" ቢሏት።

"አክሱማዊያን እነዚህን ትንንሽ የቆሙ ሐውልቶች እያዩ ‹መሬት ላይ ወድቆ የተሰባበረው ቆሞ ቢሆን ኖሮ ይሄኔ እንዴት ያምር ነበር› ብለው ዘላለም በቁጭት ሲንገበገቡ እንዲኖሩ ነው" አለች ይላሉ።

እናም የዋግ ተራሮችና ጠቅላላ ሸንተረሩ የተፈጥሮ ጸጋው በአግባቡ ተጠብቆ ቢሆን "አቤት ውበትና ግርማ ሞገስ" በማለት ማንገብገቡ አይቀርም።

ለቆጣ ከተማ እንደገባን፡-

"አባታችን ለማረፊያ የሚፈቅዱት ቦታ ይኖር ይሆን?" አልኳቸው

"የኔ ልጅ ወይብላ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውሰደኝ" አሉ።

ወይብላ ማርያም ቤተ ክርሰቲያን ሰቆጣ ከተማ ውስጥ ከዱሮው ከተማ መካከል ላይ የተገነባችና ዙሪያዋን በተፈጥሮ ዕፅዋት የተከበበች ባለ ግርማ ሞገስ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ናት። ወደዚያው ወሰድኳቸውና ከመኪናው ወርደው፡-

"በል እንግዲህ በጠዋት ከዚሁ እጠብቅሃለሁ" አሉ።

"እንዴት አባታችን? እዚህ አካባቢ ምግብ ቤት ፈልገን እህል ውኃ እንቅመስ እንጂ!" አልኳቸው

"ግዴለም ለእኔ አታስብ። አንተ በጊዜ ማረፊያ ፈልግና እንደዋልክ ስለሆነ እህል ቅመስ" አሉኝና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር አመሩ።

መከራከር አልቻልኩም። "ከማን ጋ ነው የሚያርፉት? ምን ይቀምሳሉ?" ብል መልስ አላገኝም። በአንድ ሀገር ብንኖርም፣ በአንድ መንግሥት ብንተዳደርም፣ በአንድ ቋንቋ ብንናገርም እኔና እነዚህ መናንያን በተለያዩ ዓለማት እንደምንኖር እየገባኝ መጥቷል። እነርሱ እኔንና ድርጊቴን ቢያውቁም እኔ ግን እነርሱን ለማወቅ ገና ብዙ ይቀረኛል። በትንሹ የሞከርኳትም ያመጣችብኝ ውጣ ውረድ የጋለው የመተማ መሬት የለመጠጠው እግሬ እስካሁን አልረሳውም።

አልቤርጐ ከያዝኩና ምግብ ከበላሁ በኋላ ለመናፈስ በከተማው መኻል አስፓልት በእግሬ መንሸራሸር ፈለኩ። በስተምዕራብ በኩል ጀንበር የወርቅ ጋሻ መስላ ግማሽ ጨረሮቿን እየገፋች ግማሹን እየጎተተች በተራሮቹ ልትሸሸግ ታዘግማለች። መኻል አስፓልት መንሸራሸሩን ትቼ ወደ ተራሮቹ ብሄድ ጀንበርን አገኛት ይመስል

ሂድ ሂድ የሚለኝ የሆነ ስሜት መጣ። ያቆመኩትን መኪና አስነሣሁና በስተምዕራብ አቅጣጫ ወደ ዝቋላ ወረዳ የሚወስደውን መንገድ ተከትዬ ነዳሁ።

ከከተማው ሆኜ የሰማይ አድማስ መጋጠሚያ የመሰለኝ ጋራ ስደርስ ጀንበር በጣም እርቃ ማለቂያ ከሌላቸው የዋግ ሌሎች ተራሮች ጀርባ ሆኗ አየኋት። ድብብቆሽ የምትጫወት ዐይናፋር ልጅ ትመስላለች። ‹እሰኪ ከዚህ ደግሞ ና" የምትል ትመስላለች። በሞኝነቱ ፈገግ ብዬ ፊቴን ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ሳዞር የሰቆጣ ከተማ ቁልጭ ብላ ታየችኝ። ዙሪያዋን ከከበቡዋት ጋራዎች መካከል ረባዳ መሬት ላይ የተዘረጋችው ሰቆጣ ከተማ በአካባቢው ማንም የማይጠብቃት ፍንድቅ ያለች ድንብላል ከተማ ናት።

"ይነኻግር ሳቂጣ ሸጊዬን!"

እያሉ ዋጎች በዘፈናቸውም በጫዋታቸውም አፋቸው ቁርጥ እስኪል ድረስ ፍቅራቸውን የሚገልጹላት ውብ ከተማ ናት። እሷም በደጉም በክፉውም ዘመን ለልጆቿ ተስፋ ሆና ኖራለች። ይህን ደግነቷንም የትም ቦታ ቢሆኑም በተስፋ ያነሱታል፡

"ቢሆንም ይሆናል ባይሆን ምንተዳዬ

ማሲንቆዬን ይዤ ወደ ሳቂጣዬ" በማለት።

ሰቆጣ ከተማ ከጥንቱ የሲራራ ነጋዴ የጉዞ መስመሮች መካከል ቁልፍ የነበረች ጥንታዊት ከተማ ብትሆንም የእርስ በርስ ጦርነትና ድርቅ ክፉኛ አጐሳቁለው ተስፋዋን ለመንጠቅ ቢሞክሩም ተስፋ ያልቆረጠች ሕይወት ያላት ከተማ ናት።

ዋግኽምራና አካባቢው ከዚህ ቀደም ለምርምርና ለሌሎች ሥራዎች እመጣ ስለነበር ለእኔ እንግዳ አይደለም። የሕዝቡን ባህል፣ እምነት፣ ሥነ ልቡና ጠጋ ብሎ ላስተዋለ፡

ድህነት ለጋስነትንና ፍቅርን ለማጥፋት ያልተሳካለት ቢታ፣
ኃላቀር አኗኗር ውበትን ማደበዘዝ ያልቻለበት ስፍራ፣
ማጣት ደስታን ማሸነፍ ያለቻለበት አገር ቢኖር ዋግኽምራ ነው"
ማለቱ አይቀርም።

ማስታወሻዬን አወጣሁና፡-

"ዋግ ሆይ! የተራሮችሽ ግርማ፣ የሸንተረሮችሽ መስህብ፣
ከልጆችሽ ውበትና ደግነት ጋር ተዳምሮ የአሸዋ ክምር
ፊታ የሚያደርገውን ሙቀትሽን፣ ምግብም መድኀኒትም
ከሆነው የማር ወለላሽ፣ ልብን ከሚያሸፍተው ዜማሽ ጋር
ተዳምሮ፤ ሠራተኞች ለዕረፍት የሚመርጡሽ፣ በላጸጎች
ስልትና ጥበብን የሚጠበቡብሽ፣ ስፖርተኞች አቅማቸውን
የሚፈትኑብሽ ስፍራ ትሆኛለሽ። ድህነት የጋረደውን
ውበትሽን፣ ኃለቀርነት የከለለውን አቅምሽን ፍንትው
የሚያደርግ፣ አሸዋን ወደ መስታወት፣ በረሓን ወደ ገነት፣
የከርሰሽን ውድ ማዕድን ወደ ፋብሪካ፣ ዜማሽን ወደ ሀብት
የሚለውጥ ልብና ትጋት ያገኘሽ ጊዜ የኢትዮጵያ ዱባይ
ትሆኛለሽ። እሰከዚያው ግን እመኚኝ! አንቺ ማርና ወተት
የሚዘንብብሽ የተሰፋ ምድር እንጂ የእህል አውድማ
ለመሆን ጸጋሽ አይደለምና በከንቱ በኬሚካል ማዳበሪያ
አንጀትሽን አታቃጥይ፣ ፊትሽንም ማዲያት አታልብሺ"
በማለት ጻፍኩ።

በጠዋት ወደ ወይብላ ማርያም ሄጄ ተሳለምኩና ወደ መኪናዬ
ሳመራ አባ ከአንድ ሌላ መነኩሴ ጋር ወደ እኔ አቅጣጫ መጡና
ትክሻ ለትክሻ ተሳስመው ከተሰነባበቱ በኋላ እኔ ዘንድ ሲደርሱ፡-

"እንዴት አደርክ የእኔ ልጅ?" አሉኝ።

"እግዚአብሔር ይመስገን" አልኩና ተሣልሜ ሳበቃ፡-

"ደኅና ማረፊያ አገኙ?" አልኳቸው ለመጠየቅ ያክል ።

"ግሩም እንጂ። እመቤቴ ሳለች ምን ቸግሮኝ" አሉ ።

የሰቆጣ ከተማን ለቀን አንድ ዐሥራ አምስት ኪሎ ሜትር ያክል እንደተጓዝን ለጥ ያለ ሜዳ ላይ ደረስን። እንደዚህ ያለ ሜዳ ዋግ ውስጥ ብርቅ ነው። "ወለህ" ይባላል። እዚህ ሜዳ ላይ ወጣቱ ደጀኔ ኃይሉ ጣሊያንን ፊት ለፊት ገጥመው አርገብግበውበት ነበር።

"አባ መረብ ኃይሌ ኃይሌ አባ ይባስ
አጨደው ከመረው ወቃው እንደ ገብስ
ወለህ ከሜዳው ላይ ገብቶ ሲቀድስ
ቄሱ ታፈረ ነው ዲያቆኑ ሞገስ"

ተብሎ የተሸለለበት ሜዳ ነው።

የቼክ ሪፐብሊክ ተወላጅ የሆነውና ወዶ ዘማች የነበረው አዶልፍ ፓርለሳክ ‹ሃበሻስካ አዴሳ› በሚል ርእስ በጻፈው የታሪክ ማስታወሻ (‹የሀበሻ ጀብዱ› ተብሎ የተተረጎመ መጽሐፉ) ላይ እንዳሰፈረው፡- ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ሠራዊታቸው በማይጨው ግንባር ጠላትን ገጥመው ድል አልቀናቸው ሲል ኮረም አካባቢ በሚገኝ ዋሻ ከመኳንንቶቻቸውና ከጦር አዛገሮቻቸው ጋር ምክክር አደረጉ። በውይይቱ መሠረት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በዚህ ግንባር ከመቆየት ይልቅ ወደ መኻል ሀገር ተጉዘው ጉዳዩ ከባሰም ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ‹ጎሬ› የመንግሥታቸውን መቀመጫ አዛውረው ኃይል እንዲያጠናክሩና ጠንካራ ግንባር እንዲፈጥሩ፤ ይህ ጉዟቸው

ፋታ እንዲያገኝና አዲስ የሚከፍቱት ግንባር ይጠናከር ዘንድ ጊዜ ለመግዛት ሲባል ደግሞ ጣሊያንን አሁን ባለበት ለመግታትና ለማዘግዬት ደጃች ኃይሉ በሰቆጣ በኩል የጣሊያንን ጦር እንዲመክቱ ታዘዙ።

አንቶኒ ይህን ሁኔታ ሲገልጽ "ወጣቱ ኃይሉ የንጉሡን ትእዛዝ በጀግንነትና በወኔ እየፎከረ ተቀብሎ ወደ ሰቆጣ ሲያመራ ወጣትነቱን አይቼ አንጀቴ ተላወሰ" ብሏል።

ደጃች ኃይሉ በጦርነቱ ባሳዩት ጀግንነት በጣሊያን ዘንድ ከፍተኛ መፈራትን አትርፈው ስለነበር በጦር ሜዳ ሞተው እንኳን ጣሊያን ባለማመኑ አንገታቸውን ቆርጦ እስከመውሰድ ደርሶ ነበር።

በጣሊያን ወረራ ወቅት ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ጀግኖች ወጣቶች ነበሩ። በላይ ዘለቀ ከጎጃም ገና አፍላ ጎረምሳ ነበር። ጃጋማ ኬሎ ከሸዋ ገና አንድ ፍሬ ወጣት ነበር። እነዚህ ሁሉ ጀግኖች የወጣትነት ሕይወታቸውን ለውድ ሀገራቸው ያልሠሠቱ ነበሩ። ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ ተጠራርተው ስንቶቹ ጀግኖች የደምና የአጥንት መሥዋዕትነት ዋጋ የከፈሉበትን ሜዳና ተራራ ባየሁ ቁጥር ስንቱን አስታውሼ በስንቱ ተደምሜ በስንቱ ሚዛንስ ራሴን መዝኜና አቅልዬ እችለዋለሁ። ያው ገጣሚው እንዳለው

"እኔ ለስንታችሁ ዋ ብዬ ልሙት

ያውላችሁ ልቤ ተከፋፈሉት"

ከማለት ውጭ ምን ይባላል?

እንደርሱ ያለ ሜዳ ዋግና ላስታን እስክጨርስ ድረስ ላላገኝ ‹ወስዘ
ሜዳውን› እስክ አኩሪ ታሪኩ ተሰናብቸው ፈታኙን የዋግ የተራራ
መንገድ ተያያዝኩት። ዐልፎ ዐልፎ ከእንቅብ አምልጠ መሬት
ላይ የተደፋ ቆሎ የሚመስለ ከተሞችን ዐልፈን በዱሮው የእግር
ጉዞ ዘመን የመንገደኞችን ጅማት አኮማትሮ የብዙዎችን መቅኔ
የሚያፈስ አስቸጋሪ ተራራ በመሆኑ ስሙ ‹ቅልጥም መስበሪያ›
የተባለው አካባቢ ደረስን። እድሜ ለመንገድ፣ እድሜ መንገድ
መሥራትን ለሚያስብ ጭንቅላት እንጂ የቅልጥም መስበሪያን
ያለፈ አስቸጋሪ ታሪኩን በላንድ ክሩዘር ተሳልቀንበት ‹ሸር› ብለን
አለፍነው። አራት ሰዓት አካባቢ ወደ ላሊበላ የሚወስደውን መንገድ
ትቼ በግራ በኩል ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ተገንጥሎ የሚሄድ የቢኮ
መንገድ ተከትዬ ነዳሁ። ወደ ሦስተኛውና የመጨረሻው ዕፅ ማግኛ
ስፍራ። ይምርሐነ ክርስቶስ!

# ምዕራፍ ዐሥር

ረፋዱ ላይ ከታሪካዊውና አስደናቂው ይምርሐነ ክርስቶስ ደብር ደረስን። መኪናዬን ከአንድ የወይራ ዛፍ ሥር አቆምኩና ከአባ ወልደ አረጋዊ ጋር ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አመራን። ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ለመዝለቅ ከመኪናው መንገድ ማብቂያ ጀምሮ ቀጥ ያለ ዳገት በስሚንቶ በተሠሩ ረጅም ደረጃዎች መውጣት ግድ ይላል።

የይምርሐነ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከሰፊ ዋሻ ውስጥ ራሱን ችሎ በጌጠኛ ድንጋዮች የተገነባ ቤተ ክርስቲያን ነው። ዋሻው በምዕራብ በኩል በሰፊው የተከፈተ ሲሆን በጎንና በጀርባ በዐለታማ ቋጥኝ የተዘጋ ነው። በስተምዕራብ አቅጫጣ የሚገኘው የዋሻው መግቢያ ከሥሩ ገደል ሲሆን ከዋሻው ውስጥ ሆኖ ሲታይ ፎቅ ላይ የሆኑ ያክል ይሰማል። ከዋሻው ውስጥ ሆኖ ለሚያይ በስተቀኝ በቀጭኑ ፏፏቴ የምትሠራ ጅረት ወደ ታች ወርዳ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሸለቆ ሠርታ ትፈሳለች። የዋሻው አናት በተፈጥሮ ደን የተሸፈነ ሲሆን በሳተላይት ከተነሳው ፎቶግራፍ ላይ ስለካው የደኑ ስፋት ወደ 25 ሄክታር የሚጠጋ ነው። ዋሻው ቤተ ክርስቲያኑን

ከውስጥ አድርጐ ፊት ለፊቱ በግንብ የታጠረ ሲሆን ሕንጻ ቤተ
ክርስቲያኑን በበቂ መጠን መዞር የሚያስችል ከፍታና ክፍተት
አለው።

ከቤተክርስቲያኑ ስንደርስ በዛ ያሉ ለጠበል የመጡ ሰዎች
ተቀምጠው ጸሎት እያደረሱ ደረስን።

"አባታችን እኔ እንግዲህ ከላይ ከደኑ ወጥቼ የታዘዝኩትን ዕፅ
ለመፈለግ ልሄድ ነው" አልኳቸው።

"መልካም ነው" አሉኝ።

"ያው እስክመለስ መጠበቅዎት ነው" አልኳቸው።

"ታዲያ ምን ችግር አለ። ያሻህን ሰዓት ብትዘገይም በዚህ በተቀደሰ
ሥፍራ መቆየት ለእኔ መልካም ነው" አሉ።

"እሺ እንግዲያውስ" አልኩና ከቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ ጨለም ባለው
በስተሰሜን ምሥራቅ በኩል ሄጄ ጸሎት ቢጤ አደረስኩና በፍጥነት
በስተደቡብ ምሥራቅ ታጥፌ ወደ ዋሻው አናት ወደ ደኑ አመራሁ።

ከዚህ ታላቅ ደብር እንዳመጣ የታዘዝኩት ዕፅ "ዕፅ ተክህኖ" ይባላል።
የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባሳተመውና የኢትዮጵያን ዕፅዋት ዝርዝር
በያዘው መጽሐፍ ውስጥ ስለተካተተ በስሙ አንጻር በተገለጸው
መሠረት ደኑ ውስጥ ባየው መለየት እንደምችል እርግጠኛ ነበርኩ።

ፈተናው ግን አንድን ዕፅ 25 ሄ/ር ስፋት ባለው የተፈጥሮ ደን
ውስጥ እንዴት አድርጐ ፈልጐ ማግኘት ይቻላል የሚለው ነው።
የተለመደውን ሳይንሳዊ የብዝኃ ሕይወት ፍለጋና አሰሳ ስልት
መጠቀምን አሰብኩ። በሃምሳ ሜትር ርቀት የሚዘረጉ ቀጥተኛና
ትይዩ የሀሳብ መሥመሮችን በማሥመር በእያንዳንዱ መሥመር

ላይ ቀጥ ብሎ በመንዝ ግራና ቀኝ እያሰሱ መሄድ ነው። በዚህ ስልት ከ90 በመቶው በላይ በደኑ ውስጥ የሚገኙ ዕፅዋትን ማዳረስ ይቻላል ተብሎ ይታመናል።

በዚህ መሠረት በአብዛኛው በሀበሻ ጽድና በሌሎች ሀገር በቀል ዕፅዋቶች የተሞላውን ደን ከሰሜን አቅጣጫ በኩል ጀምሮ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ የተዘረጉ የሐሳብ መሥመሮችን በያዝኩት ጂፒኤስ እየታገዝኩ እንደ ዝሀ ዘጊ እየተመላለስኩ ፍለጋዬን ጀመርኩ። የደኑን ሦስት አራተኛውን ክፍል አስሼ ስጨርስ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ተኩል ሆኗል። ይሁን እንጂ "ዕፀ ተክሀኖ" የሚባል ዕፅ ምልክቱም አልነበረም።

ድካምና ርሃብ ወደ ተስፋ መቁረጥ እያንደረደሩኝ ቢሆንም በደንና ብዝኃ ሕይወት ጥናት ልምድ መሠረት አንዳንድ ዝርያዎች በተፈጥሯቸው ችፍግ ብለው በአንድ ጥግ ብቻ ሊበቅሉ ይችላሉ። እንደነዚህ ዐይነት ዕፅዋት ‹ልዩ (Unique)› ይባላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ዝርያቸው ተመናምኖ አንድ ግለ-ተክል ወይም በጣት የሚቆጠሩ ብቻ ሊገኙ ይችላሉ። እነዚህ ደግሞ ‹ብርቅዬ (Rare)› ይባላሉ። ስለሆነም የግድ የደኑ ስፋት እስከሚያልቅ መቀጠል ነበረብኝና ቀጠልኩ። ይሁን እንጂ በታላቁ ደብር ይምርሐነ-ክርስቶስ የጽድ ደን ውስጥ እንደጠበኩትና

*"ዕፀ-ተክሀኖ ውስጠ አፀደ ደብሩ ለይምርሐነ ክርስቶስ*

*ወመዐዛሁ ሰናይ"*

ተብሎ እንደተጻፈልኝ ላገኘው ባለመቻሌ እጅግ ተማረርኩ።

ወዲያው ግን፡

"...በፍለጋው በመድከምም ሆነ በመሰላቸት በዚያው መቅረትም አልተፈቀደልህም። ወደ ቅዱሱ ቦታ ለመመለስ በዘገየህ ቁጥር የኋለኛው ዘመንህ እንደምንጣፍ ወደ አንተ እየተጠቀለለ ይቀርባል"

የሚለው ትእዛዝ ትዝ አለኝና ማማረሩ እንደማያዋጣኝ ስረዳ "አሁን ዐሥር ሰዓት ሊሆን ነው። በጣም ደክሞኛል ርቦኛልም። ያለኝ አማራጭ ላሊበላ ከተማ ሂጄ አድሬ እንደገና በማግስቱ በሌላ ሰልት መሞከር ይሻላል" ብዬ የዛለ ሰውነቴን እየጎተትኩ ከዋሻው አናት ወደታች በጥግ በኩል ወረድኩ።

አባ ወልደ አረጋዊ ከዋሻው አጥር ስር ቁጭ ብለው መጽሐፍ ያነባሉ። ጠበልተኞች ከዚህም ከዚያም ግማሾቹ ጋደም ብለው ግማሾቹ ተቀምጠው በዝግታ ያወራሉ።

ወደ አባ ጠጋ አልኩና "አባታችን አልተሳካልኝም እንሂድ" አልኳቸው ተስፋ በቆረጠ ስሜት።

"መጣሁ ትንሽ" አሉኝ።

ወደ ውጭ ወጣሁና በስተምዕራብ በኩል ቁልቁል ጅረቱንና የመጣንበትን የስሚንቶ ደረጃ በመሰላቸት ሳይ ቆይቼ ዘወር ስል ከዋሻው ግንብ ጥግ ትንሽ ራቅ ብሎ ሁለት እናቶች የተነጠፈ ሰሌን ላይ ቁጭ ብለው ‹የመገበሪያ ስንዴ› ይለቅማሉ። ከአንደኛዋ እናት የግራ ጆሯቸው ላይ የሆነ እርጥብ ቀንበጥ ተሰክቶ ሳይ ሰውነቴ ትርትር አለ። ይታዘቡኛል ሳልል እየተንደረደርኩ ጠጋ ብዬ ሳስተውል የምፈልገው ዕፅ ግንጣይ እንደሆነ ተረዳሁ። ሳላስበው "የአምላክ ያለህ!" አልኩ። አፍጥጬ ማየቴ ሳያንስ የአምላክን ስም ስጠራ የተደናገሩት እናት

"ምነው የእኔ ልጅ ደኅና አይደለህም?" አሉኝ።

"ሙይ የኔ እናት ይቅርታ ደኅና ነኝ" አልኩና "እባክዎት አንድ ነገር ላስቸግርዎት" አልኳቸው።

"ምንድን ነው የኔ ልጅ?" አሉ መገረማቸው ጨምሮ።

"ጀሮዎት ላይ ያለውን ዕፅ ከየት ነው ያገኙት?" አልኳቸው።

"ሙይ ይሄንን ነው!" አሉና በእጃቸው ከጆሯቸው ላይ አወረዱት።

"አምን እናቴ በጣም እፈልገዋለሁ" አልኳቸው በሚያስተዛዝን ፊትና ቅላፄ።

"በእርሱ ታችኝ፤ በጠዋት እንጨት ልሰብር ወርጄ ነው ያገኘሁት። ከታችኝ ከሸለቆው ጥግ ተርፏል" አሉና "ብቻ..." ብለው የሆነ ነገር ሊነግሩኝ ሲሉ አላስጨረስኳቸውም።

በተቃራኒው አቅጣጫ ስለፋ መዋሌ ቆጨኝና እየተንደረደርኩ ወደ ሸለቆው ስወርድ ሳላስበው የረገጥኩት ድንጋይ ተፈንግሎ ወደ ሰማይ ጉኜ መሬት ላይ ተዘረርኩና ከቁጥጥር ውጭ ሚዛኔን ስቼ እንደ ሙቀጫ እየተንከባለልኩ ቁልቁል ወረድኩ። በቃ እተርፋለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም። ረጅም ርቀት ተንከባልዬ ሳበቃ ከአንድ ከሸለቆው ጥግ ካለ የደደሆ ቁጥቋጦ ሥር ሄጀ ተወሸቅኩ።

በቃ ድካም ርሃብ ሕመም ተጋግዘው በእጅጉ እንደተጎሳቆልኩ ተሰማኝና "ወይ መከራዬ!" ብዬ ለደቂቃዎች እዛው እንደተጋደምኩ ቆየሁ።

እንደምንም ብዬ ተቀመጥኩና የአካል ክፍሎቼን መቁጠር ጀመርኩ። የተሰበረ ወይም የወለቀ ነገር የለም። ዐይኔ አልፈሰሰም፣ ጥርሴ አልረገፈም፣ አጥንቴም አልተሰበረም። ደም ግን ከፊቴም ከእጄም ከእግሬም በጣም ይፈሳል። የሚፈሰውን ደሜን አይቼ እንደገና

ጥልቅ ምሬትና ማጉረምረም ውስጥ ልገባ ስል ዶ/ር ማግዳሊና ድንገት ትዝ አለችኝ።

በአንድ ተራራማ የቤተክርስቲያን ደን ተዳፋት ላይ ወድቃና ተንከባላ ቁስሏን እያሻሸች ስናገኛት የምሬት ሣቅ እየሣቀች፡- "I love Ecology" ነበር ያለች ። እኔም ድንገት ስሜቴ ተቀየረና እየሠራሁት ባለሁት እብደት ከት ብዬ ሣቅሁኝ።

እንደተቀመጥኩ አካባቢውን ስቃኝ የምፈልገው ዕፅ ምልክቱ ጨርሶ የለም። የበለጠ ብሰጭትና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆኜ በተቀመጥኩበት አንገቴን አቀረቀርኩ። ድንገት የሰው ኩቴ የሰማው መሰለኝና ዘወር ስል አባ ወልደ አረጋዊ ናቸው።

ተጋግጦና ተፋፍጦ ደም በደም የሆነውን ፊቴንና እጄን ሲያዩ ፈገግ አሉና፡-

"ዘእንበለ ድካም ኢይትረከብ ጸጋ" አሉ። ያለድካም ጸጋ አይገኝም ማለታቸው ነው።

"አይ አባታችን እርግማኑ ይቅርልኝ እንጂ ጸጋ አገኛለሁ ብዬ እንኳን ተስፋ አላደርግም" አልኳቸው።

"እንዱ ሲቀር ወይም ሲወገድ በሌላው መተካቱ ግድ ነው" አሉ።

ወዲያው ጸሎት አደረጉና ከቀሚስ ኪሳቸው ውስጥ በትንሽ ጠርሙስ የያዙትን ጸበል አወጡና ወደ ሸለቆው አካበቢ ረጩት።

ዐይኔ እያየ የሆነ ነገር እንደ መጋረጃ ተጠቅልሎ እንደ እባብ ሸረር ብሎ ጠፋና ከተቀመጥኩበት በቅርብ ርቀት ከሸለቆው ዳር በብዛት ለምልሞ አየሁት፤ ‹ዕፀ ተክሀኖን›።

"ምን ጉድ ነው?" አልኩ አፌን ከፍቼ።

አባ ፈገግ አሉና "አየህ የኔ ልጅ ለሰው ልጅ ደኅንነት እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ዕፆችን አጋንንት አንዲህ ይሰውሩታል" አሉኝ።

በፍርሀት ይሁን በአድናቆት በተቀመጥኩበት ደርቄ ቀረሁ።

"እንዴት ይሆናል? ይህ እንዴት ይታመናል? እንዴት ግዘፍ የነሳ ተክል በዐይኔ ፊት ይሰወራል?" በዚህ ዐይነት በየአብያተ ክርስቲያኑና ገዳማቱ እየዞርን አጠናነው መዘግብነው የምንለው በከፊል ነበራ?"። ከጥያቄ ላይ ጥያቄ እየተነባበረ አእምሮዬን ይነርተው ጀመር።

ፈዝዤ መቅረቴን የተረዱት አባ "በል እኮ ያዝና እንሂድ አንጂ" አሉኝ።

ተስፈንጥሬ ተነሣሁና ደሜን እያንዣረገዣርኩ ሄጄ አንዱን ተክል እቅፍ አድርጌ ሽታውን ማግ ማግ አደረኩት። መዐዛው ግሩም ነው! ውስጤን የሆነ ፍስሐ ሲሰማው ይታወቀኛል። እንደ ንብ ከዚህ ከዚያም እየሄድኩ ሳሽት ቆየሁና ከለመለመው ቀንበጥ ቆርጬ ያዝኩ። በተጨማሪም አንዷን ቡቃያ ከነዐፈረ-ሥሯ ለመውሰድ አስቤ ልነቅል ስል አባ የአይሆንም ምልክት በእጃቸው አሳዩኝ።

"ለምን?" አልኳቸው።

"ውጊያውን አትችለውም" አሉ፤ አልተከራከርኩም።

እየተንከባለልኩ የወረድኩትን ጋራ እንደ ዝንጀሮ እየቧጠጥን ወጥተን ወደ መኪናችን አመራን። በየመሐሉ ግን "እንግዲህ ከዐይኔ ፊት ዕፅ ከተሰወረ ሌላውንማ..." እያልኩ ያለፊ ጥርጣሬዬን ወደ መተው ተቃረብኩ።

"እኔ እምለው" አልኩ ለራሴ "አባ ወልደ አረጋዊ አብረውን
ባይመጡ ኖሮ ይህን ዕፅ እንዴት አድርጌ ላገኘው ኑሯል? ምነው
እነርሱስ ይህን እያወቁ እንዴት ይህን ዕፅ እንዳመጣ ያዙኛል?
ዕድሜ ልኬን ስዳክር እንድኖር ፈርደውብኝ ነበር ማለት ነውን?"
ወዲያው ደግሞ "ፈጣሪ ሳይደግስ አይጣላም አለ የሀገሬ ሰው" ብዬ
ቅሬታዬን በአድናቆት ቀየርኩ።

ከመኪናችን ስንደርስ የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ መስጫ
ቦርሳዬን አውጥቼ ራሴን እንደነገሩ አከምኩና ወደ ላሊበላ ከተማ
ጉዟችንን ቀጠልን። ላሊበላ ከተማ ስንደርስ ምሽቱ እየተቃረበ
ነበር። መኻል ከተማው አካባቢ ስንጠጋ፡-

"አባታችን የት ነው የሚያርፉት?" አልኳቸው እንደልማዴ።

"ቤተ-መድኃኔዓለም ውሰደኝ" አሉ።

ቤተ-መድኀኔዓለም ከዐሥራ አንዱ የላሊበላ ውቅር አቢያተ
ክርስቲያን መካከል ትልቁ ሲሆን ስለነዚህ አብያተ ክርስቲያን
ታሪክና የኪነ-ሕንጻ ውበት እንኳን በዚህ ድካሜና የሚጠዘጥዝ
ቁስል እየተሰማኝ ቀርቶ ተረጋግቼ ብጽፍላቸውም ያልተባው ብዕሬ
እነርሱን የሚመጥን ቃላት እንደማይተፋ አውቃለሁ።

"አሁን የሚያስፈልገኝ የተፋፋገና የተጋጋጠ ገላዬንና የነበዘውን
አእምሮዬን የሚያሳርፍ ፍል ውኃ ውስጥ መነከር ወይም ‹መኝት›
ነው" አልኩና አባን ቤተ መድኃኔዓለም አድርሼ ወደ ‹ሮሃ ሆቴል›
አመራሁ።

በማግስቱ እንደተለመደው በጠዋት ተነሥተን ደብረ-ሮሃ ላሊበላ
ከተማን ለቀን የላስታ ተራሮችን ወደ ኋላችን እየተውን ወደ ደጋ
መቄት አቀናን። በመካከል ልጠይቃቸው ወይስ ልተወው እያልኩ
ስፈራ ስቸር ቆይቼ፡-

"አባታችን" አልኳቸው።

"አቤት የእኔ ልጅ!" አሉ።

"እንዲያው አንድ ነገር ልጠይቀዎት ነበር?" አልኳቸው።

"ምናለ ታዲያ?" አሉ።

"በቀደም እንደነገርኩዎት በታዘዝኩት መሠረት በብዙ ድካም ዕያቹን ፊልጌ አግኝቻቸዋለሁ። ግን አእምሮዬ እነዚህ ሦስቱ ዕያች ለምን ይሆን የተፈለጉት? እኔንስ ለምን በዚህ ሁሉ ድካም ፊልጌ እንዳመጣ አዘዙኝ? እያለ ዕረፍት ነሳኝ" አልኳቸው።

"የኔ ልጅ ያንማ እኔ ምን አውቃለሁ ብለህ ነው፤ የላኩህ ያውቃሉ እንጂ" አሉ።

በሐሳቤ " ይሄስ አመላችሁ ነው" አልኩና ፈገግ ብዬ ደግሞ አሁንም ለራሴ።

"እኛ ስለማናውቀው ነገር ሳንጠየቅ የባጥ የቆጡን እንቀባጥራለን፣ ጅራቱን ብቻ ይዘን ስለአናቱ ጭምር እንተረትራለን፤ እናንተ የምታውቁትን ተጠይቃችሁ እንኳን መለሳም አመላችሁ ነው" እያልኩ በልቤ ሳጉረመርም ከንፈሬም ተንቀሳቅሶ ስለነበር።

"ምን አልክ ልጄ?" አሉኝ።

"አይ እኔማ ማጎበረ ሥላሴ ገዳም ሂጀም የእርስዎን ስም አንሥተው መልእክት ስለላኩኝ በዚህ ጉዞዬ ምሥጢር ውስጥ እርስዎም እንዳሉበት ስለተሰማኝ ነው። ይሁንና አላስቸግረዎትም" አልኳቸው።

ዝም ብለው ቆዩና፡-

"ስማ የኔ ልጅ! ብዙ ልዩ ጠባይና ኃይል ያላቸው ዕያች ይኖራሉ።

ዕፀ ሰሎሞን ወይም ዕፀ ዘዌ ወይም ዕፀ ሳቤቅ ወይም ዕፀ ሥላሴ ወይም ዕፀ ሕይዎት ወይም ዕፀ መሰውር ሌላም ሌላም የሚባሉ ይኖሩ ይሆናል። ጥበብ የሚገልጽ ዕፅ ቢሆን እንኳ ጥበብ ደስታና እርካታ የሚሰጥ በድካምና በዕውቀት ላይ ተመሥረቶ ሲገኝ እንጂ በገጸ በረከተና በአቋራጭ ሲገኝ አይደለም። ዕፀ-ሕይወትን አግኝተህ አሁን የምትኖርበትን ጫጫታና ጥድፊያ የተሞላበት ሕይወት ይዘህ ለዘለዓለም መኖር የምትሻ አይመስለኝም። ዘለዓለም መኖር ከፈለክ በሰላም በፍቅር ነው። እርሱ ደግሞ በዕፅ ሳይሆን በመልካም ሥራና በእምነት የሚገኝ ነው። ዕፅዋትን ሁሉ ከልዩ ባህሪያቸውና ኃይላቸው ጋር የፈጠራቸውን ፈጣሪን ማመን ከሁሉ ይበልጣልና" አሉ። በዝምታ ትንሽ ቆዩና፡-

"እናም የእኔ ልጅ መልካም የሚሆነው የታዘዝከውን እንደፈጸምክ ሁሉ ቀሪውንም ከእነርሱ ሁሉንም በሂደት ለመረዳት በትዕግስት መጠበቁ ይመስለኛል" ብለው ወደ አርምሟቸው ተመለሱ።

"አሁን ያለህን ሕይዎት ይዘህ ለዘለዓለም መኖር የምትፈልግ አይመስለኝም" ያሉትን ደግሜ ለራሴ ነገርኩትና የሆነ ገጠመኜን አስታውሼ ፈገግ አልኩ።

ቀድሞ እሠራበት ከነበረ ድርጅት ሠራተኞችን ጠዋትና ማታ ወደ ሥራ ቦታ ለማመላለስ ተወዳድሮ ያሸነፈ አንድ ባለመኪና ወጣት ነበረ። መኪናው አሮጌ ችኳንታ አውቶብስ ስለነበረች ሩቅ መሥመር ለመጓዝ ወጭዋ ከባድ ስለሆነበት በአነስተኛ ዋጋ ለሠራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥልን ተዋዋልነው። አውቶብሷን እንዳመሏ ራሱ እየጠጋገነና ራሱ እያሸከረከረ የሚተዳደር ወጣት ነው። ጠባዩ መልካም በመሆኑ ከሠራተኞቹ ጋር ተግባብቶ እስከ መቀላለድ ደርሶ ነበር። አንድ ጊዜ እምነቱ ክርስትና ሆኖ ለየት ያለ እንደሆነ፣ በእምነቱ መሠረትም አሁን ባለበት ሁኔታ ሞት ሳይደፍረው ለዘለዓለም እንደሚኖር ተናገረ። ከእርሱ እምነት ውጭ ያሉ ሰዎች በሞት የሚወሰዱ ቢሆንም እርሱ ግን ከሞት ነጻ

አንደወጣ በሙሉ ልብ ተናገረ። ሌላኛው ልጅ ታዲያ ሃይማኖታዊ ክርክሩን ትቶ በጣም አስቂኝ አስተያየት ሰነዘረ።

"አዲስ ጐማ እንኳን ሠርቶ መቀየር የማይችል መኪና ይዘህ፣ ዐሥር ሺሎ ሜትር ለመጓዝ ሁለት ሦስት ጊዜ አቧራ ላይ እየተንከባለልክ፣ እየጠገንክ፣ እያንኳተትክ የምትነዳውን መኪና ይዘህ በዚህ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ኑሮ እየዳከርክ ዘለዓለም ለመኖር ስታስብ እንዲያው ትንሽ አይዘገንንህም?" አለው። ተሳፋሪው ሁሉ አንዴ በሣቅ አውካካ። ለነገሩ አባ ወልደ አረጋዊም ያሉኝ ይህንኑ ነበር።

መቄት ከደጋው ላይ ስንደርስ አባ ከጥልቅ ዝምታቸው ተመልሰው "እ.." አሉ ዒማቸውን እያፍተለተሉ። የሆነ ነገር ሊያወሩኝ እንደሆነ ገባኝና ፊቴን በግማሽ ወደርሳቸው ዘወር አደረኩኝ።

"እ...በ1830 ዓ.ም ጆርጅ ዊልኸለም ሸምፐር የተባለ ጀርመናዊ በምፅዋ በኩል አድርጐ ወደ ትግራይ አድዋ ዘለቀ። ይህ ሰው የሥነ ዕፅዋት ባለሙያ ሲሆን ቀደም ሲል በአልጀሪያና ግብጽ ተዘዋውሮ ዕፅዋት በመሰብሰብ ይታወቅ ነበር። ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ በመረብና በተከዜ ሸለቆ፣ በአድዋና በላስታ እንዲሁም በሰሜን ተራሮች እየተዘዋወረ የመሬቱን አቀማመጥ፣ የአየር ንብረቱን (Meteorology)፣ የማዕድናቱንና (Mineralogy) የዐለቶችን ዐይነት (Geology) እንዲሁም አዝርዕቱን ሲመለከት በእጅጉ ተደነቀ። እንግዳ ተቀባዮቹ ኢትዮጵያውያንም ይህን ሰው በራቸውን ከፍተው ተቀበሉት" አሉና፡-

"ባይገርምህ በወቅቱ የሰሜንና የትግራይ ገዥ የነበሩት ደጃች ውቤ ሸምፐርን ከእንግድነት አሳልፈው ባለሟል ያደርጉታል። የኢትዬጵያ ንጉሠ ነገሥት የመሆን ዓላማ ነበራቸውና ሸምፐር በቱርጅማንነትም በአማካሪነትም የውጭ ግንኙነታቸውን እንዲያከናውንላቸው በማሰብ ነበር። ሸምፐርም የዚችን ሀገር አጋና ሀብት ወዲያው የተረዳው በመሆኑ ወዳጅነቱን አጠናከረ። እናም

የደጃች ውቤ ዘመድ የሚሆኑትንና ከአድዋ የመኳንንት የሚወለዱትን ወ/ሮ መርሲትን አግብቶ የእንጦጮና አካባ ገዥ ሆኖ ተሾመ" ሲሉ

"እንዴ!" አልኩኝ በመገረም ።

አባም ዝም ብለው ቀጠሉ ።

"አሳዛኙ ትዝብት ግን ሽምፐር እንዲህ ባለ አኳኋን የተከፈተለት ዕድል ተጠቅሞ በአካባቢው የሚገኙትን ዕፅዋት ዝርዝር መረ ከናሙና ጋር አድርጐ በምሥጢር ፈረንሳይ ፓሪስ ለሚገኘ ጃርዲን ደስ ፕላንቲስ (Jardin des Plantes)፣ ጀርመን ሙኒክ ለሚገኘው ቦታንስቺስ ሙዚዬም (Botanisches Museum)፣ ለእንግሊዝ ደግሞ ሎንዶን ኪው ለሚገኘው ሮያል ቦታኒካል ሶሳይቲ (Royal Botanical Society) እና ለሌሎችም እየላከ ሀብት ይሰበስብ ነበር" አሉ።

"የፈጣሪ ያለህ!" እላለሁ በልቤ ።

"እንዳልኩህ ደጃች ውቤ ዓላማቸው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መሆን ስለነበር ለዚሁ ዝግጅት ቅብዐ መንግሥት የሚፈጽሙበት ቤተ ክርስቲያን ማሠራት ነበረባቸው። በዚሁ መሠረት ሽምፐር ከእንጦጮ ወደ ሰሜን ደረስጌ መጥቶ የደረስጌ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን እንዲያስገነባ ሓላፊነት ይሰጠዋል። ሽምፐር ደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያንን እያስገነባ አሁንም የዕፅዋትና የመልክአ ምድር ጥናቱን ወደ አውሮፓ ማጋዙን ቀጥሏል።"

"የደረስጌ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አሠርቶ ካስጨረሰ በኋላ ውስጧን በልዩ ኢትዮጵያዊ ሥነ ሥዕል እንዲዋብ አስደረገ። የደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሥዕሎች አይተሃቸው እንደሆነ ዕፅዋት፣ አበቦችና ሐረጐች ይበዙባቸዋል። ይህ እንግዲህ የእርሱ የሙያ ተፅዕኖ ነው። በዚህ ሁኔታ ከ2400 በላይ የዕፅዋት ናሙናዎችን በመላክ የአውሮፓ ቤተ መዘክሮችን ሲያበለጽግ

እርሱም የአሳሽነት ዝናው በአውሮፓ ሲናኝ በኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ከአውሮፓ በሚላክለት ገንዘብና እንጥፍ በሀገረ ገዥነቱ በሚያገኘው ሀብት ባለጸጋ ሆኖ ከቤተ መንግሥት ባለሟልነት ጋር የተንደላቀቀ ኑሮ መኖር ቀጠለ"።

" ይገርማል! እ...ሽ" አልኩ።

"አውሮፓዊ ወገኖቹም ላበረከተላቸው ጉልህ ሳይንሳዊ መረጃ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ዕፅዋት በተለይ መድኃኒትነት ያላቸውን በስሙ ሰይመውለታል። ለምሳሌ ታዋቂውን ጥገኛ የኮሶ ትል መድኃኒት ‹እንቆቆን› ብትወስድ ሲሉኝ ወዲያው ሽምዳጅ አእምሮዬ ‹*Embelia schiperi*› *(ኢምቤሊያ ሽምፐሪ)* ሲል አስተጋባ። ሳይንሳዊ መጠሪያቸው ሽምፐር የሚል ስም የያዙ የበርካታ አስማተ ዕፅዋት ከመቅጽበት በአእምሮዬ ይግተለተል ጀመር። እንቆቆ፣ ደድሆ፣ ቃጫና፣ ፍሬጮ፣ መረንዝ .... እያልኩ ስቆጥር "ዋው!" አልኩ በመደነቅ።

አባ አረጋዊ ቀጠሉና፡-

"በእርግጥ ደጃች ውቤ ለአገሪያቸው ክብርና ነጻነትም ደረስጌ ማርያም አካባቢ ያገኘውን የሚዳ አበባ ዝርያ ‹ውቤ› የሚለውን ስም (በእርሱ አጠራር ‹ዩቤ›) ከላቲን ጋር አስተሳስሮ *Ubyaea* (ዩቢያ) ብሎ የእርሱን ስም ጨምሮ *Ubyaea schimperi* ብሎ 22 ግንቦት 1830 (30 May30 1838) የሚል ቃል ጨምሮ ለሎንዶኑ ኪው ቤተ መዘክር ልኮታል። እስከ አሁን ድረስ ናሙናው በዚሁ በሎንዶኑ ኪው ቤተ መዘክር ውስጥ ከዚሁ ስሙ ጋር በክብር ይገኛል" አሉ።

በመኻል ብዙ ሳስብ ቆየሁና "አባታችን *Ubyaea schimperi* (ዩቢያ ሽምፐሪ) የሚባል የኢትዮጵያ ዕፅዋት ዝርያ ቢያንስ በስም ደረጃ ሰምቸው አላውቅም" አልኳቸው በመገረም።

"አየህ የኔ ልጅ!" አሉ

"የሚያሳዝነው... ያለ ሀገሪቱ ፈቃድና ጥቅም የዕፅዋት ዝርፊያ መካሄዱ ብቻ ሳይሆን ትምክህተኞቹ አውሮፓውያን ናሙናውን ከተቀበሉ በኋላ በርካታ በእርሱ ስም የሰየማቸውን ዕፅዋት ስም ሲያጸድቁ *Ubyaea schimperi* የሚለውን የደጃች ውቤ መታሰቢያ ስም ግን ለምደባ አይመችም በሚል ሰበብ የደጃች ውቤን መታሰቢያ ብቻ ቆርጠው Haplocarpha schimperi (ሃፕሎካርፓ ሽምፐሪ) በሚል ስለተቀየረ ነው" ሲሉኝ

"ምን?" አልኩና በንዴት የመኪናውን መሪ ለቀኩትና መኪናው ሚዛኑን ሊስት ሲል ተረጋግቼ ከመንገድ ዳር አውጥቼ አቆምኩት።

"አዎን! Haplocarpha schimperi ይህንማ አውቀዋለሁ ‹ገተን ወይም ነጭሎ› (Ethiopian Daisy) የሚባል ባለቢጫ አበባ የሜዳ ዕፅዋት ነው አልኩና እንዴት እንዲህ ይደረጋል? እንዴት ሳይንስ ውሰጥ ትምክህት ይገባል? መቀየር ቢያስፈልግ ብዙ የተሰየመለት የእርሱ ስም ተቀይሮ በእርሳቸው መተካት ነበረበት አንጂ እንዴት?" አልኩ በምሬት። በቃ ብው! አልኩ።

"በእርግጥ በሚያስተዳድሩት ሀገር፡ በአደጉበት ሜዳ የበቀለን ዕፅ ያውም በእርሳቸው መልካም ፈቃድ የተገኘን ከ2400 ዕፅዋት ውስጥ አንዱን ብቻ በስማቸው መሰይም የሚያንስ እንጂ የሚበዛ አልነበረም። ነገር ግን በምዕራቡ ዓለም ይሉኝታና ውለታ ቦታ የለውም" አሉና፡-

"የኔ ልጅ በዚህ ግን አትደነቅ፣ አትበሳጭም። በዚህ ሥጋዊ ዓለም ማንም ወርቃማ ታሪክ ይዘህ፣ አስደናቂ ቅርስ ኖሮህ፣ አኩሪ ባህልና ወግ ተጎናጽፈህ፣ ጥንታዊ የተሰናሰለ ሃይማኖት ተጫምተህ በእኩልነት ከጎኑ እንድትሰለፍ አይፈልግም። ምናልባት በተራብን ጊዜ ስማቸው በተጻፈበት ከረጢት የተሞላ ስንዴ እንዳንሞት እንዳንድን ይመጸውቱን ይሆናል። እርስ በርሳችን በተኳረፍን ጊዜ

ለአንዳችን ክላሽ ለሌላችን ቦንብ ይለግሱን ይሆናል። ከወንድም ጋር ተጣልተህ ተቃዋሚ ስትሆን በራችውን ገርበብ አድርገው የሚከፍቱልህና የተገባ ቢሆንም ለሥራ፡ ለትምህርትና ለጥበብ ገበያ ሲሆን ግን በራቸው የተከረቸመ መሆኑን አስተውል። እናም አንገታችንን ቀና አድርገን፡ ከድህነት ማጥ ወጥተን፡ ወደ ብልጽግና ማማ ለመውጣት፡ ወደ ቀደመ ክብራችን ለመመለስ ከራሳችን በስተቀር ማንም አያግዘንም። ልብ በል! ‹ለምን አያግዙንም? ለምን የእኛን ክብር አይፈልጉም?› እያልን ማላዘንም የለብንም። ዓለሙ እንዲሁ ነውና! አንገትክን ካቀረቀርክ፡ ዓለም ስምህን ከታሪክ መዝግብ ይፍቀዋል። ከአንተ ሀገር በተገኘ የዘረመል (ጂን) ሀብት ጎተራቸውን ቢሞሉም የአንተን ባዶ ስልቻና የተራበ ሆድህን እያሳዩ መሳለቂያ ያደርጉሃል እንጂ ያለፈ ውለታህን አስታውሶ የሚያግዝህ የለም! እናም የእኛ ክብርና ተስፋ በእጃችን ነው የኔ ልጅ!። ራሳችንን ስናከብር ሌሎች ያከብሩናል” አለኝና “ይልቁንስ ስሜታዊነቱን ተወውና ታሪኩን ልጨርስልህ” ሲለኝ

“እርስዎ ግን ይህን ሁሉ እንዴት አወቁ?” አልኩ ሳይንሱንም ታሪኩንም ከእርሳቸው በማልጠብቀው ሁኔታ ሲገልጹት ተገርሜ።

“የኔ ልጅ! ለምን የኔ ማወቅ ይህን ያክል ያስገርምሃል? ይልቁንም የምነግርህን ነገር አድምጥና የራስክን ድርሻ ተወጣ” አለ ኮስተር ቆጣ ብለው።

“አባቴ ይቅር በለኝ! ዝም ብዬ ነው እምቀባጥር፡ እባክዎትን ታሪኩን ይጨርሱልኝ” አልኩ በልምምጥ።

“እንዳልኩህ ደጃች ውቤ ቤተ ክርስቲያን ቢያሳንጹም ጳጳስ ከግብጽ ቢያስመጡም እንዳሰቡት ሳይሆን ቀርቶ በደጃች ካሳ ተሸንፈው ሸምጥር በተቆጣጣሪነት ባስገነባት ደረስጌ ማርያም ደጃች ካሳ ‹ሀሄ ቴዎድሮስ› ተብለው ነገሡበት። ሸምጥር የደጃች ውቤ ባለሟል በመሆኑ ብቻ ሳይሆን በስውር ያለመንግሥት ፈቃድ የሀገር

ሀብት ወደ አውሮፓ እንደሚልክ ቴዎድሮስ መረጃው ስለነበራቸው ፊት ነሱት። ከእንጥጮ ገዥነቱም ተነሣ። እንደልቡ ተዘዋውሮ ዕፅዋቱን መሰብሰብም ችግር ሆነበት። በዚህ ሁኔታ ክብሩም ተቀነሰ፣ ገቢውም እየተሟጠጠ በሰዎች ርዳታ ከባለቤቱና ከልጆቹ ጋር አድዋ መኖር ጀመረ። ይሁን እንጂ እንደበፊቱም ባይሆን የዐለት ናሙና እና ዕፅዋትን መሰብሰቡንና ካርታ እየሠራ ወደ አውሮፓ በሚስዮናውያን አማካኝነት መላኩን አላቋረጠም ነበር። ይህም ድርጊቱ በዐፄ ቴዎድሮስ ዘንድ የሚታወቅ ነበር"።

"በደብረ ታቦር ጋፋት በቁም እሥረኝነት ተይዘው መድፍ እንዲሠሩ ከታዘዙት አውሮፓዊያን ሚስዮናዊያን መካከል አንደኛው የሽምፐርን ልጅ ወ/ሪት ጣይቱ ሽምፐር ትባል የነበረችውን ያጫል። ይሁን እንጂ ጋብቻው በቤተሰብ ፈቃድ ቢያገኝም ሙሽራው የቁም እሥረኛ በመሆኑ ሽምፐር ሙሽሪት ልጁን ይዞ ከአድዋ ወደ ጋፋት መጓዝ ነበረበት። ጋፋት ደርሶ ሙሽሪትን ለሙሽራው አስረክቦ ከሚስዮናውያኑ ጋር የደሥታ ጊዜ እያሳለፈ እንዳለ ዐፄ ቴዎድሮስ ጋፋት ሲሄዱ ያገኙታል"።

"እ...ሽ" አልኩ በጉጉት ወንበሩ ላይ እየተንቆራጠጥኩ።

"ቀደም ሲል ያደረገውን ስለሚያውቁና አሁን ደግሞ ከቁም እሥረኞቻቸው ጋር ሲያገኙት፤ ‹ከመጣሽ ማርያም ታምጣሽ ብለው ወደ መቅደላ በግዞት ላኩት" አሉና

"ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ግዞት ሲልኩት የተናገሩት ኃይለ-ቃላት ግ ሽምፐርን እጅግ ኅሊናውን እንደጎዳውና እንዲጸጸት እንዳደረገ ተናግሯል" ሲሉ

"ምን ብለውት ይሆን?" አልኳቸው በጉጉት።

አባም ፈገግ ብለው፡-

" ‹አንተ እሥሥት! ደጃች ውቤን ያክል ትልቅ ሰው አምነውህ፣ የተከበረችውን ወይዘሮ እኅታቸውን ድረውልህ፣ አገረ ገዥ አድርገውህ ሲያበቃ አንተ ግን የዚችን ቅድስት ሀገር ሀብት በድብቅ እየዘረፍክ ወደ ወገኖችህ ትልክ ነበር። ይህን ያክል ተንደላቀህ ለኖርክባት ለዚህች ሀገር ግን ምንም የፈየድከው የለም። የሰበሰብከው ዕፅ ጥቅሙን አንኳን የነገርከው ሰው የለም። ድሮስ እናንተ ምናችሁ ይታመናል! እግዚአብሔር የሥራህን ይስጥህ። እኔ በሕይዎት እስካለሁ ድረስ ግን ድጋሚ እንድትዘርፍ አልፈቅድልህም› ብለውት ነበር።"

"በዚህ የተነሣ በእሥር መቅደላ ቆይቶ በእንግሊዞቹ ነጻ ቢወጣም ሞራሉ ተነክቶ ወደ አድዋ ተመለሰ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ የመጀመሪያ ሚስቱ ስትሞትበት ሌላ አግብቶ ቀሪ ዘመኑን በድህነት አሳልፎ ብዙ ልጆችን ወልዶ አርባ ዓመት በኖረባት ሀገር ምንም እንኳን ሀገሪቱን ቢወዳትና ቢደነቅባትም እንደ ፍቅሩ ሳይታመንላት በአድዋ ከተማ በ1860 ሞቶ ተቀበረ" ብለው በረጅሙ ተነፈሱና፡-

"እናም የኔ ልጅ... አንተ እንደ አስቸጋሪ ትእዛዝ የቆጠርከውን ጉዞ እነ ጀምስ ብሩስ፣ እነ ጆርጅ ዊሊኸልም ሽምፐርና ሌሎችም ከብዙ ዓመታት በፊት በፈቃደኝነት፣ በጀብደኝነትና በድፍረት የተጓዙበት፣ ብዙ ውጣ ውረድ ያለፉበት ነበር። እናም አዲስ ነገር፣ ውስብስብ ጉዞ፣ ከባድ ፈተና እንደተጋፈጥክ ሳትቆጥር የታዘዝከውን ጨርስና ድርሻህን ተወጣ" አሉኝ ፈርጠም ብለው።

ለራሴ በሚመስል አነጋገር፡- "ምን ድርሻ አለኝ? እኔ ምን አቅም አለኝ? በቃ ትምህርቴ የይድረስ ይድረስ፣ ዕውቀቴ ግልብ፣ ልምዴም በጥድፊያ የተሞላ ያልሰከነ ነው" አልኩና፡-

"እኔ የምለዎት አባታችን፤ አይቀየሙኝና እንዲያው እርስዎ እንዴት ይህን ሁሉ ደረሰቡት?" አልኳቸው በማስተዛዘን።

በመኪናው መስኮት ማዶ ማዶ እያዩ ከቆዩ በኋላ፡-

"ወጣት በነበርኩበት 1960ዎቹ ውስጥ የቅስና ማዕረግ እንዲተቀበልኩ ለከፍተኛ የሥነ-መለኮት ትመህርት ወዴ ግሪክ ሀገር ተልኬ ነበር። የመመረቂያ ጥናቴም በጥንቱ የኢትዮጵያ አብነት ትምህርት ቤቶች በሚሰጠው የሥነ-ዕዕዋት ጥበብ ዙሪያ ነበር። ታዲያ በዚሁ ሰበብ በአንድ ወቅት ለንደን ‹ኪው› ከሚገኘው ቤተ መዘክር ለዲግሪ ማሟያዬ የሚሆን ማጣቀሻ ጹሑፍ በመፈለግ ሂደት ከላያ የነገርኩህን ታሪክ ለመረዳት ቻልኩ። ሽምጥር የዕዕዋት ናሙና ብቻ ሳይሆን የዐለት፡ የማዕድናት ናሙናና ካርታም ጭምር ይልክ ነበር። እነዚህን መረጃዎች በጽሞና ሳጠና የሕይወቴን አቅጣጫ የሚያስቀይር አንድ ካርታ አገኘሁ" አሉ።

ዝም ብዬ ዐይን ዐይናቸውን በጉጉት ማዬት ያዝኩ።

"ሽምጥር አስደናቂ ዕዕዋትን ያገኘበትን ቦታና ልዩ የማዕድን ክምችት የሚገኝበትን ሥፍራ በልዩ ምልክት ካርታ ሠርቶላቸዋል። ከዚህ ውስጥ የአንድ ተራራ አናት የሚያመለክተው ካርታ ላይ ‹Biet Bendelion› ብሎ ምሥጢራዊ ቁጥሮችን አስቀምጠበታል።"

"በጥልቀት ሳጠናው ‹Beta Pantalewon› ወይም ‹ቤተ ጳንጠሌዎን› ለማለት እንደሆነ ተረዳሁ። ካርታውን የበለጠ ሳጠናው ከሌሎች ቦታዎች ጋር በልዩ ጥበብ ያስተሳሰረው ሲሆን ከዚህ ሁሉ ጀርባ ያለውን ምሥጢር በግልጽ ስረዳ ቀሪ ዘመኔን በአባ ጳንጠሌዎን ገዳም ማሳለፍ እንዳለብኝ ወሰንኩ። እናም ላለፉት 33 ዓመታት በዚሁ ገዳም ቆየሁ" አሉና በረጅሙ ተነፈሱ።

"የፈጣሪ ያለህ!" አልኩ።

አባ ጳንጠሌዎን ገዳም እንዳመጣት የታዘገበትና በአባ ፈቃድ የየኋት ስውር ዕዕ ጉዳይ ከዚሁ ምሥጢር ጋር የተያያዘ መሆኑን ብረዳም ተጨማሪ ጥያቄ ለመጠየቅ አቅም አጣሁ። በቃ ሁሉም ነገር ከአቅሜ በላይ እየሆነ መሰለኝ። ያቆምኩትን መኪና አሥነስቼ በዝምታ ጉዞዬን ቀጠልኩ። ጎሊናዬ አንዴ በአድናቆት፣ ሌላ ጊዜ በቁጭት፣ ሌላ ጊዜ በራሴ ቁንዕል ዕውቀት እየተፋጨ እንደ ጸናጽል ይንሿሿብኛል።

ከምሳ ሰዓት በፊት ደጋውን መቂትንና ጋይንትን ዐልፈን ደብረ ታቦር ከተማ ተቃረብን።

"አባታችን! ደብረ ታቦር ከተማ እየደረስን ነው። የጉዞ መዳረሻዎትን አልነገሩኝም። ሊነግሩኝ ፈቃድዎ ከሆነና መኪና የሚያስገባ ከሆነ እዛው ድረስ ልሸኝዎት?" አልኳቸው።

"ተባረክ የኔ ልጅ! እንኳን ደብረ ታቦር አደረስከኝ እንጂ ከዚያ በኋላ የሌላ ሰው ፈንታ ነው" አሉኝ።

"ታዲያ ለጊዜው ደብረ ታቦር የት ነው የሚያርፉት?" አልኳቸው ።

"ቆየኝ አንድ ጊዜ" አሉና ከቦርሳቸው የሆነ ማስታወሻ አወጡና አይተው፡-

"እናቲቱ ማርያም ከምትባል ቤተ ክርስቲያን ነው የምትጥለኝ" አሉ።

ደብረ ታቦር ከተማው መግቢያ ላይ ወደ ቀኝ ታጥፌ ከፊለጉት ቦታ አደረስኳቸውና ከመኪናው ሁላችንም ወረድን።

"አባታችን አባክሞት ትንሽ ፍራንክ ለአንዳንድ ወጪ ልስጠሞት" አልኳቸው ።

"አያስፈልገኝም። የምፈልገውንማ እኮ አደረክልኝ። ተባረክ የኔ ልጅ" አሉ ።

"ታዲያ የመጡበትን ሲጨርሱ ለምን በባሕር ዳር በኩል መጥተው ቤተሰቤን ቢባርኩልኝ ምን አለ?" አልኳቸው ።

"እሰቲ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ" አሉ ።

"እንዴ! አለበለዚያ እኮ ደግሜ አላገኝዎትም ማለት ነው?" አልኳቸው ቅር እያለኝ ።

ፈርጠም ብለው "እንግናኛለን አንጂ የኔ ልጅ!" አሉና ጸሎት አድርገው አሳልመው ትክሻዬን ስመው ሸኙኝ።

# ጥንተ ሓገር
## ኣሳ ኮርጎሪ ዘንዶ ያመጣሕ

# ምዕራፍ ዐሥራ ኣንድ

ወደ ከተማው መሐል ሂጄ የለመድኩት ቦታ ‹ጎብረት ሆቴል ምሳ በላሁና የእንግዳ ማረፊያው አካባቢ ሆኜ ቡና ለጠጣ ስዘጋጅ ሺፈራው ቁጭ ብሎ አገኘሁት። ረጅም ጊዜ ተለያይተን የቆየን ይመስል ተቃቅፈን ሰላምታ ተሰጣጣንና፡-

"እንዴት ነው ነገሩ ወደ መተማ ሂድን ብላችሁ ደብረ ታቦር ተገኘህሳ?" አለኝ።

"አንተስ ጭልጋ አይከል ብለህ እንዴት እዚህ ተገኘህ" አልኩት በተራዬ ።

"እኔማ ከዚህም የግንባታ ፕሮጀክት ስላለኝ የጭልጋውን ችግር ከፈታሁ በኋላ በዚሁ መጥቼ ቃኘቼ ልሂድ ብዬ ነው" አለኝ።

"የጭልጋው ችግር በቀላሉ ተፈታልህ እንዴ?" አልኩት።

"ገንዘብና ኔትወርክ ካለ ምን ችግር አለ። ብቻ አንተና ዶ/ር ክብረ በዓል ይሄ ስለማይጥማችሁ የኔን ጉዳይ ተምውና ይልቁንስ አንት እንዴት ከዚህ ተገኘህ?" አለኝ።

"ኧረ ባክህ እንዲህ በቀላሉ የሚነገር አይደለም" አልኩት።

"መቼም አንተና ክብረ በዓል ነገሮችን ፊታ አድርጋችሁ መናገር አይሆንላችሁም። እኔ እኮ በየጋራና ሸንተረሩ፣ በአብያተ ክርስቲያኑና ገዳማቱ እየዞራችሁ ምን እንደምትሠሩ ራሱ አይገባኝም" አለ በቀልድ መልክ።

"ምን እናድርግ ብለህ ነው የሙያ ልክፍት ይሆናል እንጂ" አልኩት

"አሁን በቀደም መተማ ሄድን አላችሁ፤ አሁን ደግሞ ደብረ ታቦር ተገኘህ። ክብረ በዓል ደግሞ ይኼኔ በአንዱ በረሓ ይሆናል" አለና "ምናለበት አንድ ነገር ላይ ዐረፍ ብላችሁ why don't you make money ለምን ገንዘብ የሚያስገኝ ነገር ላይ አትሰሩም" አለ በፈገግታ።

ሳቅ አልኩና "እንኳን ዶ/ር ክብረ በዓል እዚህ አልኖረልህ" አልኩት።

እርሱም ሳቀና "ይለቅስ ረጅምም ቢሆን ቡና እየጠጣን አውራልኝ። የሆነ ምሥጢራዊ ነገር እየፈለጋችሁ እንደሆነ ይሰማኛል" አለ።

"ኧረ ምንም ምሥጢር የለም" አልኩት ኮስተር ብዬ።

"ስማ ሲሳይ! ክብረ በዓል በየጊዜው የሚገስጸኝ ነገር የውሃ ጠብታ በጊዜ ብዛት ዐለትን እንደምትቦረቡር ሁሉ አሁን አሁን እኔንና ሕይወቴን እንድመረምር እያስገደደኝ ነው። አንተም የሳይንስ ሰው ብትሆንም ለመንፈሳዊ ሕይወት ያለህን ዝንባሌ አከብራለሁ አሁን ለመንገር የከበደህ ለገንዘብ ብቻ የምኖር ፍጹም ሥ እንደሆንኩ ስለምታውቅ ነው፤ እውነት ነውና አልፈርደብህም" ምርር ብሎ።

"እረ ባክህ ተው እንደሱ አትበል" አልኩት እንደዚህ ሲሆን አይቸው ስለማላውቅ።

"ይቅርልህ ሲሳይ! አሁን አሁን ግን ሕይዎት እየሰለቸኝ መጥቷል። ገንዘብ ሕይዎቴን እያራቆተው እንደሆነ ይሰማኛል። ሁሉ ነገር ነፋስን እንደ መከተል እየሆነብኝ ነው። ሁልጊዜ ችግርን ከእኔ በማሸሽ እንጂ በመፍታት ኑሬ አላውቅም። ችግሩን እኔው እየፈጠርኩ ከእኔ አርቄ ለሌሎች እያሸከምኩ በነጻነት የምኖር የመሰለኝ ሁሉ ስህተት ሆኖ በጎሊና ባርነት እንደምኖር እየገባኝ መጥቷል። በገንዘብ ክምር ውስጥ የምኖር የገበር አይጥ የሆንኩ ያክል እየተሰማኝ ነው። እና እባክህ ሽፍጥ፣ የጉቦ ቅሌትና ሥሥት የሌለበትን የነጻነት ጉዟችሁን ተርክልኝ። እባክህ የት ሄዳችሁ፣ አሁን ደግሞ ለምን ከዚህ እንደመጣህ ነግረኝ" አለኝ።

"ይሄ ሰው ዛሬ ምን ነካሁ" ብዬ ሁሉንም ለመንገር ወሰንኩና "እኔ ምን ቸገረኝ ለመስማት ትዕግስቱ ካለህ ልንገርህ" አልኩት።

እግሩን ዘረጋና አንድ እጁን ግንባሩ ላይ አድርጎ ለማዳመጥ መዘጋጀቱን አሳየኝ።

"ታሪኩ ረጅም ነው" አልኩና "ለመስማት ይኸን ያክል ከጓጓህ ግን ብነግርህ ደስ ይለኛል" አልኩና በረጅሙ ተንፍሼ ሳበቃ ትረካዬን ጀመርኩለት።

"በፈረንጆቹ የበጋው ወራት ፈረንሳይ ውስጥ በሜድትራኒያን ባሕር ዳርቻ በተመሠረተችውና በበርካታ ዩኒቨርሲቲዎቿና የምርምር ተቋማቶቿ ከምትታወቀው ሞንቴፕለየር ከተማ በሚካደው የብዝሓ ሕይዎት ጥናታዊ ጉባዔ ላይ ለመሳተፍና በዚያውም የምርምር ሥራዬን ለማቅረብ ተጋብገዬ ሄጄ ነበር።

የመክፈቻው ዕለት ዕረፍት ሰዓት ላይ ፕሮፌሰር ሃሮልድ ጋር ተገናኘንና ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋወጥን። ፕሮፌሰር ሃሮልድ ቀደም ብዬ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሥራ መጥተው የተዋወኳቸው የሥነምህዳር በተለይም የደረት ተሳቢዎችና ነፍሳት ሊቅ (Herpthologist and Entomologist) ናቸው። የእባብ መርዝ ማርከሽ መድኀኒት ቀምመው ለዓለም ያበረከቱ ሲሆን በተለይም በአንድ ገጠመኛቸው ዝናቸው በዓለም የናኘ ነው።

በአውስትራሊያ ባሕር ጠረፍ ተማሪዎቻቸውን ይዘው በአንድ ባሕር ውስጥ የሚኖር አደገኛ መርዛማ እባብ ዝርያ ላይ የተግባር ገለጻ እያደረጉ ባለበት ቅጽበት በርካታ ልምድ የነበራቸው ሃሮልድ በድንገት በእጃቸው የያዙት እባብ ይነድፋቸዋል። በገዳይነቱ የሚታወቀው ይህ እባብ እንደነደፋቸው በአፋጣኝ ሆስፒታል መድረስ ያለባቸው ቢሆንም በባሕር ጠረፍ ላይ በመሆናቸው ከሞት ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥ ግዴታ ሆነ።

ፕሮፌሰር ሃሮልድ ወዲያውኑ ለተደናገጡት ተማሪዎቻቸው እንዲህ አሉ፡-

"በፊጠርኩት ስህተት መሞቴ አይቀሬ ነው። ይሁንና ከዚህ ስህተቴ በሌላ አጋጣሚ የማይገኝ የሳይንስ ሙከራ እንዲሆን መርዙ ከመግደሉ በፊት በእኔ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ተረጋግታችሁ ደረጃ በደረጃ መዝግቡ። እንዲህ ያለ በሰው ልጅ ላይ የሚደረግ የሳይንስ ሙከራ ድጋሚ ስለማታገኙ" አሉ። ተማሪዎቹም የፕሮፌሰራቸውን ትእዛዝ ተቀብለው ምልክቱን መመዝገብ ጀመሩ።

በአጋጣሚ በአውሮፕላን የአንቡላንስ አገልግሎት የሚሰጡ ሐኪሞች በአካባቢው ሲበሩ ታዩና በደቂቃዎች ልዩነት ሃሮልድ ተረፉ። የሚደንቀው በእርሳቸው ላይ በአግባቡ ተማሪዎቻቸው የመዘገቡት ምልክት ታላቅ የሳይንስ የምርምር ውጤት ሆኖ ተመዘገበ።

ፕሮፌሰር ሃሮልድ ለሙያቸው በዚህ መልክ የመነኑ አርዓያነት የነበራቸው ምሁር ናቸው።

ዛሬ እራት አብረን እንድንበላ እፈልጋለሁ። የምጠይቅህ ጉዳይ አለኝ" አሉ።

"ይደስታ" አልኳቸው። ማታ አንድ ሰዓት ላይ ካረፍንበት ሆቴል እንግዳ መቀበያው ዘንድ ለመገናኘት ተስማምተን ተለያየን።

በምዕራባውያን ባህል እራት ወይም ምሳ አብረን እንብላ የሚል ግብዣ ሲቀርብ በጠየቂው ወቤ ግብዣው የሚፈጸም ይሆናል ማለት ላይሆን ይችላል። በግልጽ የእራት ወይም የምሳ ወቤ እኔ እሸፍናለሁ ወይም እገዛለሁ ካልተባለ በስተቀር ወቤ የሚሸፈነው ለየራስ ነው። በአንጻሩ በእኛ ሀገር ምሳ ልጋብዝህ ብለህ ወስደኸው ከፍዩው ሲመጣ እኔ ካልከፈልኩ ብሎ ሊከራከርህ ይችላል። ይህን የመሰለ ልዩነት ስለማውቅ ራሴን አዘጋጅቼ ወደ ቀጠሮው ቦታ አመራሁ። መሐል ከተማ አካባቢ ከሚገኙት የቱሪስት ደረጃ ካላቸው ምግብ ቤቶች መካከል ‹ላ ዲሊጀንስ› (La Diligence) ወደተባለው ገብተን እንደየምርጫችን እራት ከአንድ ጠርሙስ የፈረንሳይ ወይን ጋር አዘዝን። ሬስቶራንቱ በተጠረቡ ድንጋዮች የታነጸ ሲሆን መተላለፊያዎቹና ክፍሎቹ በቀስተደመና አምሳል ከጣራው ጋር በተሠሩ መከፋፈያዎችና ከዚሁ ጋር አብረው በሚሄዱ የግድግዳና ጣራ መብራቶች የተጌጠ እጅግ ማራኪ ነው።

የተለመዱ ማሟሟቂያ ወሬዎችን ስናወራ ቆይተን እራታችንን ጨርሰን ገበታ ከተነሣ በኋላ ፕ/ር ሃሮልድ ዐይን ዐይኔን በትኩረት እያዩ፡-

"የዚያን ቤተ ክርስቲያን ደን ምሥጢር ደረስክበት ወይ?" አሉ።

"አይ ጊዜ ስላልነበረኝ ድጋሚ አልሄድኩም" አልኩ እንደማፈር ብዬ።

"ይህን ለማመን ይከብደኛል" አሉና "ምሥጢሩን ልትሸሽገኝ ፈልገህ ካልሆነ በስተቀር ተመልሼ አልሄድኩም ብትለኝ አልቀበልህም" ብለው በረጅሙ ተነፈሱ።

"ልሸሽግዎት ፈልጌ አይደለም። ከምሬ ነው አዝናለሁ አልሄድኩም" አልኩኝ። በጣም እንደተሳሳትኩ ገባኝ።

"በሀገርህ በወንዝህ ያለን ትልቅ ምሥጢር ዘለህ ወደ ኣውሮፓ ለዕውቀትና ለሳይንስ መምጣትህ አስገራሚ ነው። ይቅርታ አድርግልኝና ትዝብትም ነው" አሉና

"ለሀገርህ ክብር ያለህ፣ ለምስጢሮቿም የምትጓጓ፣ ለችግሮቿም የምትተጋ ሰው አድርጌ ገምቼህ ነበር። አሁን ሳስበው ላንተ የነበረኝ ግምት ስሕተት ነበር ማለት ነው" ብለው እንደ መርግ የከበደ፣ እንደ ጎራዴ የሰላ ትችታቸውን አወረዱብኝና የወይን ብርጭቆቸውን ወደ አፋቸው አስጠግተው የምግብ ቤቱን ጣራ ይቃኙ ጀመር።

እንዲህ ዐይነት ዕይታ የሚመጣው አብሮህ ከተቀመጠው ሰው ጋር በሐሳብ ስትለያይ ወይም በቃ አለ አይደል የማይረባ ሰው ሲሆንብህ የሚፈጠር ስሜት መሆኑ ገባኝና፡-

"እይ እኔ እኮ ብዙም ሳይንሳዊ ጥቅም አይኖረውም ብዬ ነው" አልኳቸው በግብዝነት።

"ሳይንሳዊ ጥቅም አለመኖሩን የምታረጋግጠው ቀርበህ ስትፈትሸው ነው። ሳይንሳዊ ጥቅም ባይኖረው እንኳን ማኅበራዊና ባህላዊ እሴት ይኖረው ይሆናል። ያም ባይሆን የሥነ-ጥበብና የፍልስፍና መነሻ ሊሆን ይችላል" አሉ።

"እየህ ሲሳይ! ሀገር የሚያድገው በእኔና በአንተ የሰነ- ምህዳር ሙያ ወይም በተፈጥሮ ሳይንስ ብቻ ሳይሆን በማኅበራዊ ሳይንስ፣ በባህል፣

ሰሥነ ጥበብና በምስጢራዊ እሳቤዎችና ኩነቶች /Myth/ ጭምር ነው"።

ታላቋ ብሪታኒያ በአይዛክ ኒውተን፣ በቻርልስ ዳርዊን ወይም በዊነስተን ቸርችል ብቻ አይደለም ስሟ የሚታወቀው። በዊሊያም ሸክስፒር፣ በቻርሊ ቻፕሊን፣ በሃሪ ፓተርና በመሳሰሉት ጭምር ነው" አሉና

"ሃሪ ፖተርን ታውቀዋለህ አይደል?" አሉ።

በልቤ "ወይ አበሳዬ!" እያለኩ "አዎን" አልኳቸው።

"ሃሪ ፖተር በአካል በዚህ ዓለም የኖረ ወይም የተመላለሰ አይደለም። ምጡቅ አእምሮ የፈጠረው በምናብ ዓለም ያለ ገጸ-ባሕርይ ነው። ሃሪ ፖተር ሰፊ ባህልና ታሪክ፣ ውብ መልክአ ምድርና የትውልዶች ተረትና ወግ የፈጠረው በምናብ ዓለም ያለ ዝነኛ እንግሊዛዊ ነው። ልብ በል! በምናብ ዓለም ያለው ሃሪ ፖተር በአካል ካሉትና ከነበሩት እንግሊዛውያን እኩል ለእንግሊዝ የሀብትና የዝና ምንጭ ሆኗታል።"

"የደራሲ ጀ ኬ ሮውሊንግ ፈጠራ የሆነው ሃሪ ፖተር መጽሐፍ በ2013 ብቻ 400 ሚሊዮን ቅጅ ተሽጧል። በ73 ቋንቋ ተተርጉሟል። የንግድ ምልክት በመሆን ለእንግሊዝ ከ13 ቢሊዮን ዶላር በላይ አስገኝቶላታል ።"

"በጣም ይገርማል!" አልኩ። ይህ ሁሉ ማብራሪያ የእኔን የስንፍና መጠን አግዝፎ ለማሳየት እንደሆነ ገብቶኛል።

"ተመልከት! እንኳን ብዙ ሳይንቲስቶችንና ተማራማሪዎችን ግራ ያጋባ ምሥጢርና እንቆቅልሽ በገሃድ አግኝተህ ቀርቶ እንስት ነብሯ ጀዋኒ ሮውሊንግ በምናቧ በፈጠረችው እንቆቅልሽና ምስጢራዊ ዓለም የእንግሊዝ መኩሪያ መሆን ችላለች።"

"እናም ምናልባት የአእምሮ ከፍታን ሊሰጥህ የሚችል ምሥጢራዊ አጋጣሚ ማሳለፍህን ስነግርህ ተመራማሪ ነኝ ከሚል ከእንዳንተ ያለ የሳይንስ ሰው ከይቅርታ ጋር ውድቀት መሆኑን በወዳጅነቴ ልነግርህ እፈልጋለሁ" አሉኝ ጠንከር ብለው።

እኔም በንዝህላልነቴ እጅጉን ኃፍረትና ቁጭት ተሰማኝ። "አባቴን የማያውቅ አያቱን ጠየቀ" የተባለው ተረት በእኔ እንደደረሰ አመንኩ።

ከፕ/ር ሃሮልድ ጋር ከተለያየን በኋላ ሆቴል መኝታ ክፍሌ ገብቼ ለመተኛት ብሞክር እንቅልፍ እንቢ አለኝ። እንዲሁ በጎሊና ወቀሳ መደሻ ስወቀር አደርኩ።

በማግስቱ ከሰዓት በኋላ ያለውን መርሐ ግብር ጨርሰን ከኮንፈረንሱ አዳራሽ ስንወጣ ጠሩኝና ካፌ ሂደን ቡና አዝዘን ቁጭ አልን ።

"ስማ ሲሳይ! እኔ ነገ ወደ አውስትራሊያ መሄድ አለብኝ ። አንተ ኮንፈረሱን ትጨርሳለህ መሰለኝ?" አሉ።

"ሌላ ምን ቁምነገር አለኝ፤ በየአገሩ እየዞሩ ኮንፈረንስና ወርክሾፕ ላይ በነጭ ጉርድ ሸሚዝ ክራባት አስሮ መቀላወጥ ነው እንጂ" አልኩና በልቤ "አምን ሁለት ቀን ይቀራል:: ጨርሼ ነው የምሄድ" አልኳቸው።

"ትናንት ያነሣሁልህን ጉዳይ በድጋሚ ላሳስብህ ነው። እስከመጨረሻው ድረስ ተጉዘህ የዚያን ደን ምሥጢር እንድትፈታው አሳስብሃለሁ። ምናልባት ምሥጢሩን ለመፍታት ከላይ ታች መውጣትና መውረድ ሊኖር ይችላልና ለሎጅስቲክ ወጪ መሸፈኛ እንዲሆንህ ሶስት ሺህ ዩሮ ስለወዳጅነታችን ይኸውልህ። የቀረውን አንተ ራስህ ለመሸፈን አታንስም አሉና" የታሸገ ፖስታ አውጥተው ጠረንጴዛው ላይ አድርገው ወደ እኔ ገፉት።

"ፕሮፌሰር በጣም አመሰግናለሁ። ይሁንና የቸገረኝ ወደ ውስጥ የማየት ሞራል ብቃት እንጂ ገንዘብ አልነበረም። ይህን ሞራል ስለሰጡኝ አመሰግናለሁ፣ ለገንዘቡ ብዙ አያስቡ በሀገሬ ወንዞችና ተራሮች፣ ሜዳዎችና ሸለቆዎች ያለውን ምሥጢር ለመዳሰስ የሚያስችል የገንዘብ አቅም እንኳ አላጣም" አልኳቸውና ፖስታውን መልሼ ወደ እርሳቸው ገፋሁት።

ብዙ ካግደረደሩኝ በኋላ በአቋሜ መጽናቴን ሲያዩ ፖስታውን አንሥተው ኪሳቸው ውስጥ እየከተቱ፡- "እንግዲህ ምክሬንና አስተያየቴን በወዳጅነት መንፈስ ተቀብለህ ከዳር እንደምታደርሰው ተስፋ አደርጋለሁ" አሉ።

"አያስቡ ቃሌን እጠብቃለሁ" አልኳቸውና ተሰናብቻቸው ወደ ሆቴሌ አመራሁ" አልኩት በረጅሙ ተንፍሼ።

"ምን ጉዳይ አጋጥሟችሁ ኖሮ እንዲህ የወቀሱህ?" አለኝ ሺፈራው በጉጉት።

"አዎን እርሱን ልነግረህ ነው" አለኩት።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

"ሁሉም የጥናት ቡድኑ አባላት በተሰጠው ማሳሰቢያ መሠረት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ደብረ ታቦር ከተማ ካረፍንበት ጎብረት ሆቴል፣ መሰብሰቢያ ክፍል ተገኝተዋል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ለዘመናት ተጠብቀው በቆዩት ቅርስ የተፈጥሮ ደኖች ላይ ለምናደርገው ሥነ ምህዳራዊ ጥናት ከተለያዩ ሀገሮችና ዩኒቨርሲቲዎች የጋበዝናቸው ልምድ ያላቸው ተመራማሪዎች ተገኝተዋል።

የምርምር ፕሮጀክቱን የምናስተባብረው እኔና አሜሪካዊቷ ዶ/ር ጃኔት ነን። የሎጅስቲክና ከሚመለከታቸው አካላት ሕጋዊ ፈቃድ ማግኘታችንን በማረጋገጣችን የመስክ ሥራችንን ለመጀመር የተግባር መርሐ-ግብርና የሥራ ድልድል ለማድረግ ነበር ውይይቱ የተዘጋጀው።

ሁሉም ሰው መነኑን ካረጋገጠች በኋላ ቆፍጣናዋ እና ሠር
የማይደክማት ዶ/ር ጃኔት ሁሉም ነገር የተዘጋጀ በመሆኑ በነጋ
ዕለት ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ወደ መስክ የምንንቀሳቀስ መሆኑ
ከገለጸች በኋላ ገርገር የተግባር ድልድል መስጠት ጀመረች።

"ኢትዮጵያ ውስጥ ከምንቆይባቸው ሁለት ሳምንታት ውስጥ ዐሥ
ሁለት ቀናት በመስክ ሥራ የምናሳልፍ ሲሆን በዐሥር አባያ
ክርስቲያንና ገዳማት ደኖች ውስጥ መረጃ መሰብሰብ ይኖርብናል
አለች።

በዚህ መሠረት አሜሪካዊው የጅኦግራፊና ጅኦይኤስ ባለሙ
የሆነው ዶ/ር ክርስቶፎር የደኖቹን የመሬት አቀማመጥ በጂፒኤ
(GPS) በተወሰደውና በሳተላይት ከተነሣው ፎቶግራፍ ጋ
በማመሳከር የደኑን ስፋት መለካትንና የዛፎችን የዐይነትና
የመጠን ስብጥር ለሚያጠናው ቡድን የአቅጣጫ ድጋፍ እንዲሰጥ
እኔና የሥነ-ሕይወት ባለሙያ የሆነችውና ከካናዳ የመጣችው
ዶ/ር ማግዳሊና በሦስት አቅጣጫ የሚዘረጉ የሐሳብ መሥመሮችን
በመከተል የዕፅዋቱን ዐይነት፡ ቁመትና ውፍረት እንዲሁም የደኑን
የብቅለት ደረጃ ከሁለት ኢትዮጵያውያን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች
ጋር እንድናጠና፤ ዶ/ር ጃኔት ከሁለት አሜሪካውያን የድህረ ምረቃ
ተማሪዎች ጋር እኛ በምንመርጣቸው እናት ዛፎች አካባቢ የዐፈር
ናሙና መውሰድና ከተመረጡት ዛፎች የላይኛውና የመጨረሻው
ቅርንጫፍ ላይ ቅጠል በመውሰድ ለንጥረ ነገር ውደት ጥናት
የሚሆኑ ናሙናዎችን መሰብሰብ፤ አንጋፋው የደረት ተሳቢዎችና
ነፍሳት ሳይንስ ሊቅ (Herpetologist and Entomologist) ፕሮፌሰር
ሃሮልድ ደግሞ ከነዶ/ር ጃኔት በኋላ አሁንም የእኛን መስመር
ተከትለው የደኑን ጤንነት ለማወቅ ይቻል ዘንድ ጥቃቅን ነፍሳትን
በተለይም የጉንዳኖችን ማንነትና ስርጭት እንዲያጠኑ ከአንድ
የድህረ-ምረቃ ተማሪ ጋር ተመደቡ።

በዚህ ምደባ መሠረት እያንዳንዳችን መያዝ ያለብንን መሣሪያዎች አዘጋጅተን እንድናድር ተስማሙን ወደ ማረፊያችን አመራን።

በማግስቱ በሦስት ላንድክሩዘር መኪኖች ተሣፍረን ከደብረ ታቦር ከተማ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ ተነሥተን መጀመሪያ ለመሥራት ወደ መረጥነው የቤተ ክርስቲያን ደን (በእኛ አጠራር ሳይት 01) አመራን። በዕለቱ ማታ የተወያየንባቸውን የአሠራር ስልቶች በተግባር ከልሰን በፍጥነት ለመሥራት ወደሚያስችለን ስልት ቀይረን በሚቀጥለት ቀናት በቅልጥፍና መሥራት ቀጠልን።

ሥራው አድካሚ ቢሆንም አሰልቺ ግን አልነበረም። ደን ውስጥ ሆነህ የምትሠራው ሥራ በተፈጥሮ መመሰጥና መደነቅ ስለሚታገዝ ሥራው አይሰለችም። በተለይ የእኔና ዶ/ር ማግዳሊና ሥራ በኮምፓስና በጂፒኤስ ከቤተ ክርስቲያን ህንፃ በመነሣት ወደ ውጭ በሦስት አቅጣጫ የምናሠምረውን የሐሳብ መሥመር ተከትለን ግራና ቀኝ ሁለት ሜትር ስፋት ውስጥ የሚገቡትን ዕፅዋቶች መለየትና መለካት ነው። የሐሳብ መሥመሩ ቀጥ መጠበቅ ስላለበት ለመተላጠፍ ፕሮቶኮሉ አይፈቅድም። እሾህ የሞላበት ትብትባ፣ ቋጥኝ ወይም ሀፈረ ገደል፣ አንዳንዴም የአሰፈሪ እንስሳት መራቢያ ወይም መኖሪያ ሊያጋጥም ቢችልም በቀጥታ ከመጓዝ ማሸብረክ የጥናቱን ሳይንሳዊ ዋጋ ይቀንሰዋል። እናም ይህን ለመጠበቅ የምናደርገው ጥረት በተለይ የአጋም፣ የቆንጥር፣ የቀጋና የጉመሮ እሾህ ልብሳችንን ዕልፎ አካላችንን ይሸነትረው ነበር።

ዶ/ር ማግዳሊና በጣም ወፍራም ሆና አጭር ናት። ያን ውፍረት ይዛ ተራራ ስትወጣና ስትወርድ በቁጥቋጦ ሥር ስትንከባለል ማየት በጣም ያስደንቃል። ከዚህ በላይ በጣም ፍልቅልቅና ደስተኛ ናት። ከእርሷ ጋር መሥራት በቃ መሣቅ ነው። ዛፎችን እንደ ሰው ታወራቸዋለች። በጣም ዘር የተሸከመ ትልቅ ዛፍ ስናገኝ "Hi Big Mama" (ትልቋ እናት፣ እንዴት ነሽ) ትልና ታቅፈዋለች። የአበባ

ዕፅዋቶችን ስታይ ለተራክቦ መዘጋጀታቸውን ስለሚገልጽ "You are so beautiful. Good luck lady" ትላለች። የአንድ ቤተክርስቲያን ደን እጅግ ተራራማና ተዳፋታማ በሆነ ቦታ የበቀለ ስለነበር ዶ/ር ማግዳሊና ሳታስበው ተንሸራታ ወደቀችና ረጅም ርቀት እንደበርሚል እየተንከባለለች ወረደች። በቃ ትተርፋለች የሚል ግምት አልነበረንም። እየወደቅን እየተነሣን በፍጥነት ስንደርስ ቁጭ ብላ እየሣቀች አገኘናት። የእጆቿን ልብስ ሰብስባ የተጋጋጠውን ክንዷን እያሸች "I love Ecology" አለች።

እያንዳንዱን የጥናቱን ሂደት ወደ ቀልድ በፍጥነት ትቀይረዋለች። የዕፅዋቱን ዐይነት ለመለየት የቅጠሉን ቅርፅና ከቅርንጫፉ ጋር የተያያዘበትንና አወቃቀሩን፡ እንዲሁም የቅርንጫፍ አዘረጋጉና ከግንዱ ጋር የተጣበቁበት መንገድ፡ የቅርፊቱ ዐይነትና ቅርፊቱ ሲቀረፋ የሚወጣው ፈሳሽ መልኩና ጠረኑ፡ ዕፅዋቱን የየትኛው ወገን እንደሆነ ለመለየት ያስችላል። ከዚያም ቀጥታ ስሙን ለማግኘት ከቤተሰብ (family) እስከ መሠረተ ዝርያ (Genus) ለመለየት ያስችላል። በመጨረሻም ቀጥታ የዝርያውን ስም በያዝነው ማመሳከሪያ መጽሐፍ እየታገዝን እንደርስበታለን። በዚህ ካልተሳካ ወደ ቤተ-መዘክር ወስዶ ለማመሳከር ናሙና እናዘጋጃለን።

በዚህ መሠረት አንድ ትልቅ ዛፍ ለመለየት በአደረግነው መላምት እንዲህ አልኳት "ዛፉ ሆማ/ኮማ (Prunus africana) ከሆነ ቅርፊቱን ስቀረፋው የሰባ የዐሣማ ሥጋ መምሰል አለበት። ካልሆነ ሌላ ዛፍ ነው ማለት ነው" አልኩና በሰንጢ ስቀረፋው እውነትም ስብ የተቀላቀለበት ትኩስ ሥጋ ይመስላል።

"Wow!" አለችና "It looks like an American Ass" አለች። ሁለታችንም መሬት ወድቀን እየተንፈራፈርን ሣቅን።

ዘዚህ መልክ ዝርያቸው ከምድረ ገጽ ለመጥፋት የተቃረቡትን ሰምሮ በርካታ የሀገር በቀል ዕፅዋቶችን ማግኘት የመንፈስ ደስታ ይሰጣል። እነዚህ ሁሉ ዕፅዋቶች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ደኖች ባይኖሩ አገልግሎታቸውና ጥቅማቸው ይቅርና መኖራቸውም ላይታወቅ እጣ ፈንታቸው ሙሉ በሙሉ ገጸ ምድር መጥፋት እንደነበር ለማወቅ አይቸግርም። አሁንም አንዳንዶቹ ሊጠፉ መቃረባቸውን ማሰብ ደግሞ በሌላ በኩል ዕረፍት ይነሳል።

ለማንኛውም የስምንት አብያተ ክርስቲያንና ገዳማት ደኖችን በአቀድነው መሠረት አጥንተን እንደተለመደው ወደ ሳይት 09 የቤተ ክርስቲያን ደን አመራን። የቀሩን ሁለት ቀናት ብቻ ናቸው። ስለዚህ ሥራችን በተያዘለት መርሐ-ግብር እየተጓዘ ነበር።

ዘጠነኛው የቤተ ክርስቲያን ደን (ሳይት 09) ከደብረ ታቦር ከተማ በ78 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከአካባቢው ደርሰን ስሙን ጠይቀን በአረጋገጥነው መሠረት የምንፈልገው ቦታ መድረሳችንን አወቅን። ይህ የቤተ ክርስቲያን ደን በአንድ ትልቅ ተራራ ላይ የበቀለ ሲሆን ከርቀት ዐይንን ይማርካል። ከተራራው አናት ወረድ ብሎ የቤተ ክርስቲያኑ ጉልላት ሙሉ በሙሉ ከቆርቆሮ የተሠራው ጣራው ደግሞ ግማሽ የሚታይ ሲሆን ዙሪያውን ከተሸፈነበት ዕፅዋት፡ ከተራራው ቅርፅ ጋር ተዳምሮ ልዩ ግርማን ተላብሷል።

ደኑን ከቤተ ክርስቲያኑ ጉልላት ጋር በርቀት ሳየው ገዙም ብሎ የሚያስፈራ ስሜት ተሰማኝ። በርካታ የአብያተ ክርስቲያንና ገዳማት ደኖችን የመጎብኘት ዕድል የነበረኝ ቢሆንም እንዲህ ዐይነት የፍርሀት ስሜት ሲሰማኝ ግን የመጀመሪያዬ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰማኝን ፍርሀቴን ግን ለባልደረቦቼ ማጋባት ስላልፈለኩ እንደተለመደው እየተቀላለድን ወደ ደኑ ተጠጋን።

ከረባዳው መሬት ስንደርስ እኛ በተጠጋንበት አቅጣጫ ደስ የሚል በሣር የተሸፈነ ሜዳ አለው። በተለምዶ ‹ማርገጃ› የሚባለው መሆኑ ነው።

መኪኖቻችንን አንድ ጥግ አቁመን እንደተለመደው የፊቃድ ወረቀታችንን አሳይተንና ሕጋዊ መሆናችንን አሳውቀን ሥራችንን ለመጀመር የቤተ ክርስቲያኑን አስተዳደሪ አስጠራን። መልካም ኦጋጣሚ ሆኖልን አስተዳዳሪው በአቅራቢያው አውድማ ጥሬው እህል እየወቁ ነበርና እንግዶች መምጣታቸውን ሲሰሙ የሥራ ልብሳቸውን እንደለበሱ ከተፍ አሉ።

የእግዚአብሔር ሰላምታ ከአቀረብኩ እና በመስቀላቸው ከተባረክሁ በኋላ፡-

"የቤተ ክርስቲያናችሁን ደን ለማጥናት ነው የመጣን። ከመንግሥትም ከሀገረ ስብከቱም የፊቃድ ደብዳቤ ይዘናል" አልኩና ሁለቱን ደብዳቤዎች አውጥቼ ሰጠኋቸው።

በእርጋታ ደብዳቤዎቹን ካነበቡ በኋላ ግራ በተጋባ ስሜት "ምንድን ነው የምታጠኑት?" አሉን::

"የዕፅዋቱን ዝርያ፡ ያለበትን ሁኔታ፡ ችግርም ካለባቸው ለመለየት እና ወደፊት ተጠብቀው እንዲቆዩ የሚያስፈልግ ነገር ካለም ለሚመለከተው አካል ሳይንሳዊ መፍትሔ ለመጠቆም ነው" አልኩኝ።

"ነገሩስ ደኅና ነው" አሉና "ታዲያ እንዴት ነው የምታጠኑት?" አሉ

"ያው ፊቃድ ከሰጣችሁን ውስጥ ገብተን በሦስት አቅጣጫ እየተዘዋወርን ነው" አልኳቸው። ቄራሽ የመረበሽ ስሜት አየሁባቸው።

"ዕፅዋቱን ማወቅ ከሆነ እኛ እዚሁ ተወልደን ነው ያደግነ። እናም አንድ በአንድ እናውቃቸዋለን። እኛ እየነገርናችሁ ብትመዘግቡት አይሻልም?" አሉ።

መልአከ ሰላም እንደሱ አይደለም ጥናቱ የሚካሄደው። ስማቸውን ብቻ ሳይሆን ሌላ ብዙ ተጨማሪ መረጃዎችንና ልኬታዎችን እንወስዳለን። አይዞዎት እኔም ክርስቲያን ነኝ። ቅርስና ንዋየ ቅድሳት መጥፋት አስግቶዎት ከሆነ በቀን ነው የምንሠራው። ደግሞም ወደ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑም አንጠጋም። እርስዎም አንድ አብሮን የሚሆን ወኪል ሊመድቡ ይችላሉ። እነዚህ አብረውኝ ያሉትም የማምናቸው የሳይንስ ሰዎች ናቸው እና ስጋት አይግባዎት" ብዬ ለማረጋጋት ሞከርኩ።

"እይ በዚህ ዐይነት ጉዳይ እናንተን በመጠርጠር እንኳን አይደለም። እ..." አሉ።

"ለማንኛውም ደብዳቤ ስለያዛችሁ መተባበር ግዴታችን ነው" አሉና "በሉ አትቁሙ እንሂድ" ብለው ሁላችንንም በመጋበዝ ዐይነት በእጃቸው ምልክት አሳይተው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አመሩ።

መፈቀዱን ለሥራ ባልደረቦቼ ነግሬ በፍጥነት የጥናት መሣሪያዎቻችንን በጀርባችን አዝለን ተከተልናቸው። ቀጥ ባለ ዳገት ግራና ቀኝ ቅርንጫፎቻቸው በገጠሙ ዕድሜ ጠገብ ዛፎች ሥር በሚያልፍ መንገድ ለ15 ደቂቃ ያክል ተጉዘን ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ካለበት ስፍራ ደረስን።

ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ለገጠር አካባቢ ትልቅ የሚባል ሲሆን በስሚንቶ የተለሰነ ግድግዳና በድንጋይና በስሚንቶ የተሠ ዙሪያውን የሚከቡ ደረጃዎች አሉት። ጣራው ከቆርቆሮ የተሠሪ ዙሪያውን የሚንሿሿ ተንጠልጣይ ከቆርቆሮ የተሠሩ ጌ አሉት። በነፋስ ሲወዛወዙ ልዩ ሙዚቃዊ ቃና አላቸው። ጉል

ከዛፎቹ ለቆ የሚታይ ሲሆን የሰሜን እንቁላል የሚመስሉ ጌጣጌጦቹ ላይ ያለበት ትልቅ መስቀል አለው። የበርና መስኩቶቹ መቃንና ጉበን ከሰፋፊ የጽድ እንጨት የተሠሩ ሆነው ተከፋችቹ ግን ከብረት ተሠርተው ቀለም ተቀብተዋል።

ከቤተ ክርስቲያኑ በስተሰሜን ምሥራቅ በኩል በ50 ሜትር ርቀት ላይ ከጽድ የተሠራ ባለ አንድ ደርብ ጣራው ቆርቆሮ የሆነና በቆርቆሮ የተጋረደ በረንዳ ያለው ቤት አለ። በቤተ ክርስቲያኑና በደኑ መካከል አረንጓዴ ሣር የበቀለበት ሰፋ ያለ ሜዳ ሲኖር በደኑ በኩል በዕድሜ ጠገብ የድንጋይ ካብ ዙሪያውን ተከቧል። ከቤተ ክርስቲያኑ ጥግ ሆኖ አሻግሮ ሲታይ ዙሪያውን እጅግ የሚያምሩ ዕድሜ ጠገብ ግዙፍ የሀገር በቀል ዕፅዋት እንጂ ሌላ ነገር አይታይም። ወደ ላይ ደግሞ የጠራ የበጋ ሰማይ ብቻ።

ዶ/ር ክርስቶፈር በሳተላይት የተነሣውን የቤተ ክርስቲያኑን ደን ፎቶግራፍ ከመሬቱ አቀማመጥ ጋር ካገናዘበ በኋላ ከቤተ ክርስቲያኑ በመነሣት ወደ ውጭ የሚወጡትን የሐሳብ መሥመሮች ለይቶልን ለመንቀሳቀስ ዝግጁ ስንሆን አብረውን ወደ ቆመት አስተዳዳሪ ዞር አልኩና፡-

"መልአከ ሰላም አሁን እንግዲህ ከድንጋዩ ካብ በመነሣት በሦስት አቅጣጫ ተራ በተራ ወደ ውጭ እየተንገዘገዝን ሥራችንን እናከናውናለን" አልኳቸው።

ግራ በመጋባት ስሜት ሁነው "በየት በየት በኩል ነው የምትሄዱት?" አሉ።

በስተሰሜን 0°፡ በስተደቡብ ምሥራቅ 120° እና በደቡብ ምዕራብ 240° ባለው አቅጣጫ በእጄ እያመለከትኩ ገለጽኩላቸው።

ደንገጥ ብለው በስተሰሜን ያለውን በእጃቸው ሜዳማ እያመለከቱ "በዚያ በኩል ያለውን ብትተውትስ?" አሉ።

"አይ የሳይንሱ መመራያ ስለሚያስገድደን ማለቴ ሌላ ቦታም የሠራንበት ስለሆነ እዚህ መቀየር አንችልም። ምነው በዚያ በኩል ብንሄድ ምን ችግር አለ?" አልኳቸው።

"አይ..... ችግር እንኳን የለም እንዲያው..... ቢቀርባችሁ ብዬ ነው" አለ. እየተንተባተቡ:: ብቻ ሁለንገራቸው በጣም የመደናገጥና ያለመመቸት ይመስላል።

መሣርመው እኔ ደግሞ ከውጭ የጀመረኝ የመረበሽ ስሜት ብሏል።

ስለሠራን ይሆናል)አለችና በቁሚ ዘፍ ብላ መሬት ላይ ተቀመጠች

"I am not sure" አልኩና መሬት ላይ ሽርተት ብዬ ጋደም አል
ዶ/ር ማግዳሊና ወደ እኛ መጥቶ አቅጣጫችን እንዲያረጋግጥ
ክርስቶፈርን በሬድዮ ጠራችው። በአቅራቢያው ነበርና ወዲ
ከተፍ አለ።

"በየት ነው የወጣችሁት?" አለን።

"የወጣንበትን መስመር ርቀት ለመለካትና እያን
የምንመዘግበው ዕዕዋት የት እንደሚገኝ ለማመላከት የምንጠቀ
ባለ 50 ሜትር ገመድ ከደኑ ውስጥ ወደ ውጭ ወደ ተዘ
አመለከትነው። ሄደ ሜትሩ ላይ ቆመና እርሱ ቀድሞ
ከደረገበት ቦታ ጋር አስተያየው።

"No way! You Guys devated from the line way far" (ሊሆን አ
ከመስመሩ በጣም ርቃችኋል) አለ።

"ምን ያክል ራቅን?" አልነው። እስከ 10 ዲግሪ ወደ ግ
ወደ ቀኝ ማዘንበል ጥቅጥቅ ባለ ደን ያለ ነገር ስለ
ባለመደነቅ።

"ወደ ሰሜን ምዕራብ በ30° ዲግሪ ርቃችኋል። እንዲያው
ማለት ይቀላል" አለ በመገረም።

"ሊሆን አይችልም" አልን በአንድ ላይ እንደተማከርን

"እምን ሆኗል ኑና ተመልከቱ" አለን። በፍጥነት ሄደን
ቀጥታ ከሳተላይት የተነሣውን የደኑን ፎቶግራፍ ከ
አንጻር የወጣንበትንና መውጣት የነበረብንን አቅጣጫ
በጣም እንደተሳሳትን አመንን። ወዲያው በፍጥነ
ላሉት ሁለት ቡድኖች የተሳሳተ አቅጣጫ ስለመ
አቋርጠው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲመለሱ ነገር

በስንት መረበሽና ጭንቀ[illegible] ...ንደገና መድገም
እንዳለብን ሳስብ ጭራሽ ተሸበርኩ። ለማንኛውም ሳይንስና
ስሕተት አብረው የሚኖሩ አንዱ ለአንዱ ሞረድ ስለሆኑ እንደገና
ለመሥራት ሞራላችንን አነሣስተን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ዳገት
መውጣት ጀመርን። አሁን ሰዓቱ ከቀኑ 8:30 ሆኗል።

ከቤተ ክርስቲያኑ ደርሰን ከቀሩት የቡድኑ አካላት ጋር ሁነን
ኮምፓሳችንና ጅፒኤሱን ፈትሸን ምንም የተለየ ብልሽት ባይኖርም
ሌላ ቀይረን እንደገና መነሻ ነጥባችንን ደጋግመን አይተን 0°
ሰሜን አቅጣጫ ይዘን መሥራት ቀጠልን።

እውነት ለመናገር እኔና ዶ/ር ማግዳሊናም ሆነን ሌሎቹ ረዳቶቻችን
ደስ የማይል ስሜት ውስጥ እንዳለን ግልጽ ነበር። እኔ ዛፎቹን
ስለካም ሆነ ስጽፍ እጆቼ ይንቀጠቀጣሉ። "ምንድን ነው? በደሜ
ውስጥ የስኳር መጠን ተዛባ እንዴ" ብዬ አሰብኩ። ይኸኛው
መስመር ደግሞ ከፍ ያለ ተዳፋት ያለው እንደሆነ ተረዳን። ስለዚህ
መስመራችን ተሻሽሏል ብለን ተዕናናን። ልክ ከቀኑ 9:40 ላይ
ኑን ጨርሰን ዳር ስንዘልቅ እፎይ አልኩ። ለዶ/ር ክርሰቶፈር
ንደተለመደው በሬዲዮ አሳወቅን።

/ር ክርስቶፈር ሸንቀጥ ያለ፡ ለግላጋ ቁመት ያለውና ወርቃማ
ጫ ጸጉሩ ከግንባሩ የተደፋ የ45 ዓመት ጎልማሳ ነው። ከፊቱ
ኤም ፈገግታ የማይጠፋ ትሑትና ንግግሩ እጅግ የተረጋጋ ነው።
ሱ ራሱ የተዋጣለት የመልክአ ምድር ሳይንቲስት ቢሆንም በዚህ
ድን ሥራ ውስጥ ራሱን እንደ አጋዥ እንጂ ዋና ተመራማሪ
ርጐ የማይቆጥር አብሮ ለመሥራት የሚመች ሰው ነው።

ን ከሞላ ጎደል በትክክል እንደመጣችሁ ተስፋ አደርጋለሁ"
ጅፒኤሱን አውጥቶ ከሳተላይት ጋር ማገናኘትና ምስል
ዘብ ጀመረ። ትንሽ ቆይቶ ወደኛ የድመት ዐይን ቀለም
ው የዋህ ዐይኖቹ ትኩር ብሎ እየተመለከተ፡-

"ዛሬ ምንድን ነው የነካችሁ?" አለን

"አሁንም ተሳሳትን እንዴ?" አለች ዶ/ር ማግዳሊና እጇን ካፏ ላይ ጭና።

እኔ ደግሞ "ኤጭ ምን ዐይነት ዕዳ ነው" በሚል ስሜት ማዶ ማዶ ማየት ጀመርኩ ።

"አዎን በጣም ተሳስታችኋል። ጭራሽ ከቅድሙ በተቃራኒ በ35 ዲግሪ ወደ ሰሜን ምሥራቅ ታጥፋችኋል" አለና ለዶ/ር ጃኔትና ለፕ/ር ሃሮልድ እንዲያቆሙና ወደ ታች መጥተው እንድንነጋገር ጠራቸው።

ኮተታቸውን ተሸክመው እያለከለኩ ከእኛ ጋ እንደደረሱ ዶ/ር ጃኔት በፈገግታ፡-

"እናንተ ልጆች ዛሬ ምንድን ነው የነካችሁ?" አለች ።

ዶ/ር ማግዳሊና ቀበል አድርጋ፡-

"እየውልሽ ጃኔት እንደተለመደው በጥራት እንደሠራን ላረጋግጥልሽ እወዳለሁ። ስገምት የሆነ የተለየ እንግዳ ነገር ያለ ይመስለኛል" አለች በአግራሞት ደኑን እያመለከተች።

እኔም ቀበል አድርጌ "እኔ በኮምፓስ፡ ማግዳሊና በጅፒኤስ ሁለታችንም ፊትና ኋላ ሁነን በተለየ ሁኔታ በተለይ ሁለተኛው ዙር ላይ በደንብ አቅጣጫችንን ደጋግመን እንዳረጋገጥን ነው የማስታውሰው" አልኩ።

ዶ/ር ክርስቶፈር በተለመደው እርጋታው "ሁለት ሰው በሁለት መሣሪያ ተጠቅሞ ይህን ያክል ስህሕተት ሊሠራ አይችልም። ለማንኛውም ስሕተት ስንደጋግም ከምንውል የሠሩትን አንዱን መረጃ ወስደን ብንቀጥል የሚሻል ይመስለኛል" አለ።

ምንም ዐይነት የፕሮቶኮል መዛነፍና ጥቃቅን ስሕተቶችንም ቢሆን እያወቀች መቀበል የማትፈቅደው ዶ/ር ጃኔት ኮስተር ብላ፡-

"እንደዚያ እንኳን አናደርግም። እኔ የሚመስለኝ ማግዳሊናና ሲሳይ ላለፉት ስምንት ቀናት በሜና ውስጥ በማሳለፋቸው ከድካም የመነጨ ይመስለኛል። እናም ለዛሬው እዚህ ላይ አቁመን ነገ በጠዋት ስሕተታችንን አርመን እንቀጥላለን" አለች።

አንጋፋው ፕ/ር ሃሮልድ እኔንና ዶ/ር ማግዳሊናን ግራና ቀኝ አቅፈው፡-

"I think somebody seeped too much beer yesterday" (ትናንት ብዙ ቢራ ተጠጥቷል ማለት ነው) አሉ። እየተሣሣቅን ወደ መኪኖቻችን አመራን።

የዕለቱ የከሸፈ መርሐ ግብራችን በእኔና በዶ/ር ማግዳሊና መዛል ተመካኝቶ ወደ ማረፊያችን ተመለስን። እኔ ግን የሰጠነው ምክንያት አልተዋጠልኝም ነበርና መኪና ውስጥ ሆኜ ብዙ ሐሳብ ይመላለስብኝ ጀመር።

ጠዋት ሥራ ከመጀመራችን በፊት መልአከ ሰላም በተለየ ሁኔታ ይህንን አቅጣጫ እንድንተወው ለዘብ ብለው በሜንቀት መጠየቃቸው ትዝ አለኝ። እኔና እርሳቸው የተነጋገርነውን ሌሎቹ የሥራ ባልደረቦቼ አልተጋሩትም። እኔም ክብደት ሰጥቼ አልተረጐምኩላቸውም ነበር። አሁንም ለእነርሱ ለማካፈል አልደፈርኩም። እስኪ ምናልባት ነገ የሚለወጥ ነገር ካለ ብዬ በራሴ መብሰልሰል ቀጠልኩ።

"ለምን ይህንን አቅጣጫ እንዳንጠቀም መልአከ ሰላም ፈለጉ?"

"ለምንድን ነው የመረበሽ ስሜት የሳየኝ?

"እንዴት እኛስ ልንሳሳት ቻልን?"

ለምንድን ነው ባልተለመደ ሁኔታ ውስጤስ ይረበሽ የነበረው?" የሚሉ ጥያቄዎች በመንገድም፣ ማታ ራት ላይም፣ ሌሊትም በጣም ሲረብሹኝ አደሩ።

በማግስቱ በጠዋት ተነሥተን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አመራን። ትናንት መኪኖቹን ከአቆምንበት ቦታ ስንደርስ ወርደን እንደተለመደው ኮተታችንን ተሸክመን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ለመውጣት ከደኑ ጫፍ ስንደርስ መልአከ ሰላም ከቤተ ክርስቲያኑ ቆይተው ሲወርዱ ተገናኘን። ሰላምታ ከሰጡንና በመስቀል እኔንና ሌሎቹን ኢትዮጵያውያንን ከባረኩን በኋላ፡

"አልጨረሳችሁም እንዴ?" አሉ ለዘብ ብለው።

"አይ ትንሽ ሥራ ቀርታን ነው" አልኳቸው ለማረጋጋት ብዬ ።

"ትናንት እትሂዱ ባልኳችሁ አቅጣጫ ሄዳችሁ?" አሉ ።

ካነሱትስ ብዬ "አዎን አባታችን። ምንም አማራጭ ስለሌለን ሞክረናል። እንዳሰብነው ግን አልተሳካልንም" አልኳቸው።

"ምነው ምን ተፈጠረ?" አሉ ደንገጥ ብለው።

"የተፈጠረ ችግር እንኳን የለም ብቻ እንዳሰብነው አልሠራንም" አልኩና፡-

"መልአከ ሰላም በዚያ በኩል እንዳንሄድ የፈለጉበት ምክንያት ምንድን ነው?" አልኳቸው።

ሌሎቹ ፈንጠር ብለው ቆመዋል። ለቤተ ክርሲታያ' ካህናትና መነኮሳት ከፍተኛ ክብር ስላላቸው እኔ ምልክት እስካልሰጠሁ ድረስ ራቅ ብለው በእርጋታ መጠበቅ የፕሮቶኮላችን አንዱ አካል ነው።

መልአከ ሰላም እንደመንተባተብ ብለው "ኸረ ምንም ችግር የለም እንዲያው ለአንተም ለእንግዶችህም ጥሩ አይደለም ብዬ ነው እንጂ አሉና።

"ለማንኛውም ሕጋዊ ሰዎች በመሆናችሁና ሀገረ ስብከቱም ትእዛዝ ሰላስተላለፈ ብዙ አናስቸግራችሁም ቀልጠፍ ብላችሁ የምትፈልጉትን ፈጽሙ" አሉ።

ትንሽ ጠጋ አልኩና፡-

"መልአከ ሰላም እርግጥ ሕጋዊ ደብዳቤ ይዘናል። ግን የእርስዎም መልካም ፈቃድ ወሳኝ ነው እና ምናልባት እኛ የሳይንስ ሰዎች ነን የምናምነው በምናየውና በምንጨብጠው ነገር ስለሆነ የእርስዎን ምክር እየጣስን እንደሆነ ይሰማኛል። እንዲያው ችግር ይገጥመን ይሆን?" አልኳቸው። ፍርሀቴ አሁን መጠኑን እያለፈ እንደሆነ ስለተገነዘብኩ።

"አይ እንግዶች ስለሆናችሁና ቀና ዓላማ ስለያዛችሁ ችግር እንኳን አይገጥማችሁም ብቻ ..."

"ብቻ ምን? ..." አልኳቸው።

"የመጣችሁበት ላይሳካላችሁ ይችላል ብዬ ነው እንጂ" አሉና፤ "በሉ አትቁሙ ሂዱ" ብለው በእጅ ምልክት ለሁሉም አሳዩ።

ቅር እያለኝ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ለመውጣት ዳገቱን ተያያዝነው። ከቤተ ክርስቲያኑ ሰንደርስ በፍጥነት ተሳለምኩና ወደ ዕቃ ጠባቂው መነኩሴ ሄድኩ።

"እንደምን አደሩ አባ" አልኳቸው።

"እግዚአብሔር ይመስገን የእኔ ልጅ እንደምን አደርክ" ብለው መስቀላቸውን ዘረጉልኝ። ትልቅ የብራና መጽሐፍ ገልጠው

እያነበቡ ነበር።

"ትናንት የመጣነው ደኑን የምናጠናው ነን" አልኳቸው።

"እምን ለይቼሃለሁ። አልጨረሳችሁም ነበር?" አሉ።

"ዛሬ እንጨርሳለን" አልኳቸው።

"ደኅና ነው በል አትቁም" አሉኝ።

"እሺ አባታችን" ብዬ የእኛ በአካባቢው መኖር ምንም ጭንቀት እንዳልፈጠረባቸው ከእርጋታቸው በመረዳቴ እየገረመኝ ወደ ሥራ ባልደረቦቼ ስመለስ በየት እንደምንጀምር እየተነጋገሩ ደረስኩ።

ዶ/ር ክርስቶፈር "ትናንት 120 ዲግሪን ብቻ ስለሠራን በአዲስ መንፈስ 240 ዲግሪን እንሥራ። እነ ሲሳይም መሣሪያዎቻችን ትክክል መሆናቸውን በዚያውም ያረጋግጣሉ። ከዚያ ቀጥለን ወደዚህ አስቸጋሪ መስመር እንምጣ" አለ በእጁ 0 ዲግሪ ስሜን እያመለከተ። ሁላችንም ተስማምተን በ240 ዲግሪ አቅጣጫ ሥራችንን ጀመርን። 380 ሜትር ርቀት ቀና የሆነ ሥራ ሠርተን ደኑን ጨርሰን ገላጣው ስፍራ ላይ ደረስን። ይኸኛው መስመር በጣም ደስ ይላል። ወቅቱ ዕፅዋቱ ግማሹ ያበቡበት ግማሹ ያፈሩበት ስለሆነ መዐዛው ግሩም ነው። በርካታ አዳዲስ ዕፅዋት በማግኘታችንም ተደሰትን።

ዶ/ር ክርስቶፈር መጥቶ አቅጣጫችንን ካገናዘበ በኋላ በ5 ዲግሪ ብቻ መዛነፉን ነግሮ፡-

"ዛሬ በደንብ ሠራችሁ። We are back!" አለ በድል ስሜት እጆቹን ወደ ላይ ዘርግቶ እያወዛወዘ። ይህንኑ ለዶ/ር ጄኔትና ለፕ/ር ሃሮልድ ቡድን በሬዲዮ ገልጸን ወደ አስቸጋሪው መስመር ለመሄድ እንደገና ዝግጅት መውጣት ጀመርን።

ከቤተ ክርስቲያኑ ደርሰን ትንሽ ዕረፍት ካደረግንና እነ ጃኔት መጨረሳቸውን ከአረጋገጥን በኋላ ሥራ ለመጀመር ወደ ድንጋዩ ካብ ተጠጋን። የድንጋዩን ካብ ዘለን በስተውጭ በኩል ቁመን ኮምፓሱንና ጂፒኤሱን አስተካከልን።

ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ረዳቶቻችን የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ የባዮሎጂ 3ኛ ዓመት ተማሪዎች ናቸው። አንደኛው መልካሙ ይባላል ስምን መልአክ ያወጠዋል እንዲሉ ገጹ ያማረ አእምሮው ብሩህ የሆነ ወጣት ነው። የእርሱ ሥራ 50 ሜትር ርዝመት ያለውን ሜትር በምንሰጠው አቅጣጫ በመጎተት መስመር መፍጠር ነው። ሌላኛው ወጣት አዳሙ ይባላል። ዝምተኛ ግን ንቁ ወጣት ነው። የእርሱ ሥራ ደግሞ የሜትሩን የመጀመሪያ ጫፍ ከመነሻ ነጥባችን ላይ ወጥሮ በመያዝ እስክንጨረስ ድረስ መጠበቅ ነው።

በዚህ ሁኔታ አዳሙ ሜትሩን ከካቡ ጥግ ለግቶ ሲይዝ መልካሙ ደግሞ በሰጠነው 0 ዲግሪ አቅጣጫ ሜትሩን እየተረተረ ሄደ። እኔና ማግዳሊና እንተደለመደው ዕፅዋቱን መመዝገብና መለካት ያዝን። ወዲያው ግን እንደትናንቱ ልቤ ይሸበር ጀመር። ወደ ፊት በተራመድን ቁጥር ወደ ኋላ የሚገፋኝ ኃይል ያለ ይመስል አቅም ያንሰኝ ጀመር። የዛፎቹ ቁመት እየጨመረ እጅግ የሚከብድ ድባብ እየተፈጠረ እንደመጣ ይሰማኛል። ብቻ ስሜቴን ግን ማጋራት አልፈለኩም።

ሃምሳ ሜትሩን ጨርሰን እንደገና ወደ ፊት ለመዘርጋት አቅጣጫችንን ለማየት እኔ ኮምፓስ ማግዳሊና ደግሞ ጂፒኤስ አወጣን። በመኸል መልካሙ በግምት ሜትሩን እየጎተተ ወረደ።

ዶር ማግዳሊና ድንገት "ኡፍ አለች" በመበሳጨት መልክ።
ምነው?" አልኳት።
ግሉኮላይት ሽፋን ጠፋ። ጅፒኤሱ አይመልስም" አለች።
ችግር የለም በኮምፓሱ እንጠቀማለን" አልኩና ኮምፓሱን መዳፌ
ላይ አድርጌ ለማየት ስሞክር የአቅጣጫ አመልካቹ ቀስት ወይም
መርፌ ግራ ቀኝ ይርገበገባል። ብዙ ጠበኩት አሁንም ግራና ቀኝ
ይዋልላል። በተለመደው ጊዜ የተያዘበት ክንዴ ከረጋ ቀስቱ ግራና
ቀኝ ተንቀሳቅሶ መጨረሻ አንድ ቦታ ላይ ይረጋል። በዚህ ጊዜ
ግራና ቀኝ በመንቀሳቀስ ቀስቱንና የሚፈለገውን የዲግሪውን ቁጥር
ማናናት ነው።

አሁን ግን ቀጥ ብዬ ቁሜም የኮምፓሱ ቀስት ግራና ቀኝ እየተወዛወዘ
መረጋት አልቻለም። ምን አልባት እጄ እየተንቀጠቀጠ ይሆናል
አልኩና ለዶ/ር ማግዳሊና ሰጠኋት።

ትንሽ ቆይታ "ይሄ ኮምፓስ ምንድን ነው የሆነው?" አለች። "በጣም
ይወዛወዛል የሆነ ማግኔት እንደሚሥበው ዐይነት" አለች።

"እኔም እኮ እንደዚያ ሆኖብኝ ነው" አልኳትና ኮምፓሱን ተቀብ
እንደገና ስሞክር አሁንም ለውጥ የለም።

በመሻሉ የፍርሀትና የአድናቆት በሚመስል ቃና ዶ/ር ማግዳሊና

"ሲሳይ!" አለችኝ።

"አቤት" ብዬ ፊቴን ወደ እርሷ ሳዞር ፊት ለፊት ወደ ታች እ
ዘርግታ፡-

"Oh my God, I think that tree is moving!" (አ አምላኬ! ያ
ይንቀሳቀሳል) አለች።

"Yaa every tree moves with the wind" (አዎን ማንኛውም ዛፍ በነ
ይነቀሳቀሳል) አልኳት ለማቃለል ብዬ። እንደ እውነቱ ከሆነ እኔ
በከፍተኛ ፍርሀት ውስጥ ነበርኩ።

"No, no I mean it is moving not swinging" (አይደልም አይደል
መወዛወዝ ሳይሆን ይንቀሳቀሳል ነው ያልኩህ) አለች ኮስተር ብ

"What?!" (ምን?!) አልኩ።

"በእርግጥ አይቸዋለሁ! አንድ ጊዜ ወደግራ ሌላ ጊዜ ወደ

መቼም የፍርሀቴ መጠን በአንድ ጊዜ እጥፍ ሁኗል። ትንሽ እንደሄድኩ ዙሪያውን ሰቃኝ አጣሁት። ጮክ ብዬ እንዳልጣራ ፈራሁ። ከአሁን አሁን መብረቅ ወረደብኝ ወይም ጦር ተሰካብኝ እያልኩ ዶ/ር ማግዳሊና ሲንቀሳቀስ አየሁት ካለችው ‹ሎል› ከሚባለው ዛፍ ደረስኩ።

በቀስታ ወደ ዛፉ እየተጠጋሁ ሽምቅቅ ብዬ ዙሪያውን ቃኘሁት። ዙሪያውን ቃኝቼ ወደ ዛፉ ሰጠጋ መልካሙ ከዛፉ ሥር እግሩ መሬት ላይ ተዘርግቶ ከወገቡ በላይ ቀጥ ብሎ አንገቱን ወደ ጎን ዘንበል አድርጐ ተቀምጧል። ዐይኖቹ ተከድነዋል።

"የፈጣሪ ያለህ! የሰው ልጅ አስቀሰፍኩ" አልኩና በርከክ ብዬ አንገቱን ቀና ሳደርገው፤ ልክ ከእንቅልፉ እንደሚነቃ እንደመባነን ብሎ ተስፈንጥሮ ተነሥቶ ቆመ።

"ምንድን ነው የሆንከው መልካሙ?" አልኩት ።

"እኔ እንጃ" አለና ለማስታወስ ቀኝ እጁን ግንባሩ ላይ አደረገ።

"ለማንኛውም ይህን አካባቢ እንልቀቅ" አልኩትና በፍጥነት ወደ ላይ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሄድን።

"አሁን አስታወስኩ ጋሽ ሲሳይ" አለ እየተርበተበተ።

"ምንድን ነው የሆንከው?" አልኩት ።

"ሜትሩን እየጎተትኩ ያንን ትልቅ ዛፍ እንዳለፍኩ አንድ ረጅም ሽበት የወረሳቸው መነኩሴ ከፊቴ ቆሙና ድንገት በያዙት ምርኩዝ ትከሻዬን ሲነኩኝ ግንዱን ተደግፌ ሸርተት ብዬ እንደወደኩ አስታውሳለሁ" አለኝ።

"እውነትክን ነው?" አልኩት።

"እንዴ እርግጠኛ ነኝ" አለ እየተሸበረ።

"በል በቃ ዝም በል" አልኩት ቀስ ብዬ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ስንደርስ እነ ዶ/ር ጃኔት ሥራቸውን ጨርሰው ሲመጡ እኩል ሆነ።

ዶ/ር ጃኔት ፈገግ ብላ፡-

"እንዴት ነው እስካሁን አልጀመራችሁም እንዴ?" አለች ለማረፍ በጀርባዋ ያዘለችውን ሻንጣ እያወረደች።

"ባክሽ ይህ መሥመር የሚሳካ አይደለም። በዚህ በኩል የተለየ ኃይልና ምሥጢር አለ" አለች ዶ/ር ማግዳሊና በድንጋጤ እጆቿን እያወራጨች ።

"እንዴት?" አለች ዶ/ር ጃኔት ኮስተር ብላ።

ኮምፓሱም ጅፒኤሱም አለመሥራቱንና አንድ ትልቅ ዛፍ ቦታ ሲቀያይር ማየቷን በፍጥነት ተናገረች።

"I don't believe this" (ይህን አላምንም) አለች ዶ/ር ጃኔት ፈገግ ብላ።

"አውቃለሁ። እኔም ቢነገረኝ አላምንም ነበር፤ ግን የሆነው ሁሉ ሆኗል። በዚህ እርግጠኛ ነኝ" አለች ዶ/ር ማግዳሊና።

ሞገደኛዋ ዶ/ር ጃኔት "ማረጋገጥ እፈልጋለሁ" አለችና ብድግ አለች።

"እኔ ሁለተኛ አልሄድም። እናንተ መሄድ ትችላላችሁ" አለች ዶ/ር ማግዳሊና ኮስተር ብላ።

ዶ/ር ጃኔት ኮምፓስ ይዛ ለመሄድ ስትነሣ ፕ/ር ሃሮልድና ተማሪዎቹም ተከተሉ። አማራጭ አልነበረኝም እኔም እንደፈረደብኝ ተከተልኩ።

እንደ እውነቱ ከሆነ በዚህ ሰዓት የምፈልገው በተቻለ ፍጥነት ቤተ ክርስቲያኑን ለቆ መውጣትና ከአካባቢው መራቅ ነበር።

ተከታትለን ትንሽ እንደሄድን ኮምፓሱ የተርገበገበበት ቦታ ስንደርስ፡-

"እዚህ ላይ ነው የተመለስነው" አልኳት።

"መልካም" አለችና ኮምፓሱን አውጥታ እያየች ቆየችና "ይህ ሊሆን አይችልም!" አለች።

ፕ/ር ሃሮልድ ጠጋ ብለው ሲያዩ እኔም ተንጠራርቼ ሳይ ከቅድሙ በባሰ የኮምፓሱ ቀስት ዙሪያውን እንደሰዓት ሴኮንድ ቆጣሪ ይዞራል።

"This place is weared! I think we better leave now" (ይህ ቦታ ግራ የሚያጋባ ነው። አሁኑኑ ለቀን መሄድ ያለብን ይመስለኛል) አሉ ፕ/ር ሃሮልድ።

"Yaa we should leave now because tomorrow we have to fly to US" (ልክ ነው! ነገ ወደ ሀገራችን መብረር ስላለብን አሁኑኑ ከዚህ መውጣት ይገባናል) አለች። ዶ/ር ጃኔት በአንድ ጊዜ ከእኛ ላይ የሰፈረው የፍርሀት ስሜት ውስጧ እንደገባ ንግግሯ ያሳብቃል።

"እፎይ!" አልኩ።

ኮሽታ ሳናሰማ በሽንፈትና በፍርሀት ስሜት ቤተ ክርስቲያኑን ለቀን ቁልቁል በደኑ ውስጥ ባለው ዋናው መንገድ ወርደን ሜዳው ላይ መኪኖቻችንን ከአቆምንበት ስንደርስ ዶ/ር ክርስቶፈርን በሬዲዮ ጠራነውና መጣ። የሆነውን ሁሉ ስንነግረው እጁን ከአፉ ላይ ጭኖ በዝምታ ሲገረም ከቆየ በኋላ፡-

"እንዲህ ዐይነት ሁኔታና ክስተት ሊፈጠር የሚችለው በሁለት ምክንያቶች ነው" አለ። ሁላችንም ወደ እርሱ በንቃት ትኩረታችንን አደረግን።

"የመጀመሪያው በአካባቢው ከፍተኛ የብረት ማዕድን ክምችት ካለ የኮምፓሱን ቀስት ወይም መርፌ በከፍተኛ መግነጢሳዊ ኃይል በመሳብ ሊያሽከረክረው ወይም ሊያርገበግበው ይችላል፤"

"ሁለተኛው ደግሞ የዩራኒየም ክምችት ካለም ከመግነጢሳዊ ኃይል ውጭ የሆነ ጨረር በመልቀቅ ሊያዛባው ይችላል። ስለዚህ ዮሩ የምርምር ነጥብ ሊሆን ይችላል" አለና በልበ ሙሉነት ገለጸ።

"እና?" አለች ዶ/ር ማግዳሊና ወፍራም ወገቧን በሁለት እጆቿ ይዛ።

"እናማ... ተመልሰን ሂደን የዐፈር ናሙና እናምጣና የበለጠ እናጥናው" አለ ዶ/ር ክርስቶፈር በቅንነትና በጉጉት።

ዶ/ር ማግዳሊና ኮስተር አለችና "ማንኛችንም ከዚህ በኋላ ወደዚህ ደን መመለስ የለብንም። ለኮምፓሱ እሺ ያንተ መላምት ትክክል ሊሆን ይችላል። እንዴት ዛፉ ይንቀሳቀሳል?" አለች።

"ዛፉ ስለመንቀሳቀሱ እንኳ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ምናልባት ኢሉዥን ሊሆን ይችላል" አለ ዶ/ር ክርስቶፈር በተለመደው እርጋታው።

ያን ጊዜ ዶ/ር ማግዳሊና በንዴት ብው አለች።

በዚህ መኻል ፕ/ር ሃሮልድ ጣልቃ ገቡና፡-

"በአጠቃላይ ቆይታችን ዐሥር የቤተ ክርስቲያን ደን ለመሥራት አቅደን ስምንት ሠርተናል። ይህም 80% ነው። ሰፋ ያለ ሥነ ምህዳር መሸፈን የሚያስችሉ ወሳይ ቦታዎችን ማካተት ችለናል።

ይህም ሥራችን በጣም በቂና ውጤታማ እንደሆነ ያሳያል። በነገው ዕለት ወደ አዲስ አበባ ከዚያም ወደ አሜሪካ መመለስ ስለሚኖርብን ተጨማሪ ፈተና መጋፈጥ አያስፈልግም" አሉና ቀጥለው፡-

"እ.. በዚህ ሥፍራ ያጋጠመን ጉዳይ ጥልቅ ምርምር የሚጠይቅ አስደናቂ ክስተት ነው። በሌላ ጊዜ በተረጋጋ መንፈስ ሲሳይ ተመልሶ መጥቶ የተለያዩ መላምቶችን አስቀምጦ ጉዳዩን በጽሞና ይመርምረው። በእኔ ግምት ሲሳይ ለዚህ ሥራ ብቁ ነው። ድጋፍ ካስፈለገም ካለንበት ሁነን ልንደግፈው እንችላለን። ለአሁኑ ግን ሥራችንን በብሥጭት ሳይሆን በስኬት መንፈስ እንደምድመው" አሉ።

ሁላችንም ተስማማንና ወደ መኪኖቻችን አመራን። ይህ ከሆነ ከአንድ ዓመት ተኩል በኋላ ነበር ከፕሮፌሰር ሃሮልድ ጋር ፈረንሳይ ሞንቴፕሊየር ሳገኛቸው ድጋሜ ቦታው ባለመሄዴና ባለማጥናቴ የወቀሳ መዐት ያወረዱብኝ" አልኩት።

ሺፈራው በተመስጦ የነገርኩትን ታሪክ በአእምሮው ውስጥ እንደሚያብላላ ሆኖ በዝምታ ከቆዬ በኋላ "ይቅርታ አድርግልኝና እውነትም ወቀሳ ይገባሃል" አለኝ ፈገግ ብሎ በወዳጅነት ገጽታ። "እሽ ከዚያስ?" አለኝ አሁንም በገጉት።

እኔም የቀረበልኝን ቡና እየጠጣሁ በዝምታ አሻግሬ ሳይ ቆየሁና ትረካዬን ቀጠልኩ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

ከአሜሪካውያን የምርምር ተባባሪዎቼ ጋር ከተለያየን ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ ከፈረንሳይ ከመጣሁ ከሁለት ሳምንት በኋላ ለፕ/ር ሃሮልድና ለራሴም ቃል በገባሁት መሠረት ወደ ሞገደኛው ደን ሳይት 09 ለመሄድ በጠዋት ተነሣሁ።

ወደዚህ ጥንታዊ የቤተክርስቲያን ደን ለመሄድ ከባሕር ዳር በሁለት አቅጣጫ መሄድ ይቻላል። ይሁንና ረዘም ቢልም ለስላሳው መንገድ በደብረ ታቦር በኩል በመዞር በመሆኑ በዚሁ በኩል ለመሄድ ወሰንኩ።

የመጀመሪያው ሥራዬ አድርጌ የወሰድኩት ዶ/ር ክርስቶፈር የሰጠውን መላምት ለማረጋገጥ የዐፈርና የድንጋይ ናሙና ወስጄ የብረትና የዩራኒየም ክምችት መኖሩን መፈተሽ ነው። ዐፈሩ የተለመደው ዐይነት ቢሆን ከዚያ ዐልፎ ምን ምርመራ ማድረግ እንዳለብኝ አጠቃላይ ምሥጢሩንም እንዴት መፍታት እንደምችል ግም ሐሳብ የለኝም። ብቻ ግን እስከመጨረሻው ተኩ ሥጢሩን ለመረዳት እንደወሰንኩ ግን ልቡናዬ ተግንዝቧል።

በመካከለኛ ፍጥነት እየነዳሁ ከባሕር ዳር ከተነሣሁ ከ3፡30 በኋላ ሞገደኛውን ደን ከቤተክርስቲያኑ ግማሽ ጣራና ጉልላት ጋር በርቀት ከማይበት ቦታ ደረስኩ። ገና ከእይታዬ እንደገባ ሰውነቴ ስንጥቅ አለ፤ መረበሽ ጀመርኩ። መኪናውን ወደ ዳር አቁሚ ወረድኩና፡-

"ምንድን ነው የሆንኩት?" አልኩኝ። "እኔም ክርስቲያን ነኝ። ምሥጢር ለማወቅ እንጂ ለማጥፋት እየሄድኩ አይደለም። ታዲያ ለምን እረበሻለሁ?" አልኩና ራሴን ለማረጋጋት ሞከርኩ።

መኪናውን አስነስቼ እየነዳሁ ሳይሆን እያንኳተትኩ ማለት ይቀላል ለመጠጋት ሞከርኩ። በግምት አንድ ሁለት ኪሎ ሜትር ሲቀር ከአንድ አርሶ አደር ቤት ጥግ አስፈቀድኩና መኪናዬን አቁሚ እንዲጠብቁልኝ ነግሬ መስክ ስወጣ የማትለየኝን ሻንጣዬን በጀርባዬ አዝዬ ወደ ደኑ ተጠጋሁ።

ደን እወዳለሁ፤ ለዛፎች ከፍተኛ ፍቅር አለኝ። በተለይ የአብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ደኖች ካላቸው ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ክብር ጋር ተዳምሮ ልዩ ድባብና ሞገስ አላቸው። ሁልጊዜም ወደነዚህ ደኖች የመሄድ አጋጣሚ ባገኘሁ ቁጥር መንፈሴ ይታደሳል። ያንን ስሜት ለማምጣት ሞከርኩ። የሚሳካልኝ ግን አልሆነም። ልቤ ድንግጥ ድንግጥ እያለ ዳገቱን ጉልበቴን እየደገፍኩ ወጣሁና ቤተ ክርስቲያኑ ስደርስ ባለፈው የተዋወኳቸው ዕቃ ጠባቂ መነኩሴ ከተለመደው ቦታቸው አየኋቸው።

"እው! እርሳቸው መኖራቸው ጥሩ ነው" አልኩና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ተጠግቼ በግንባሬ ተደፍቼ ተሣለምኩና "አቤቱ በምሕረትህ ጠብቀኝ" አልኩ። ወዲያው በራሴ ተገረምኩ። "ምሥጢር ለማወቅ መጓጓትና ደግሞ በፍርሀት መናጥ ምን ይሉታል?" አልኩና ወደ አባ ሄጀ፡-

"እንደምን አደሩ አባ" አልኩኝና እጆቼን ደረቴ ላይ አመሳቅዬ ለመሣለም ጠጋ አልኩኝ።

"እንደምን አደርክ የእኔ ልጅ" አሉና ሥራቸውን አቁመው ከደረታቸው አካባቢ በልዩ የቆዳ ማጎደር ውስጥ የተሸጠውን መስቀላቸውን ሳብ አድርገው አሣለሙኝና፡-

"እዚህ ላይ ዐረፍ በል" አሉኝ ጠፍጣፋ ድንጋይ እያመለከቱ።

ከጐናቸው የጋመ ከሰል የተሞላ ምድጃ አለ፤ በጉማጅ ዕንጨት ላይ የተሰካ የበሬ ቀንድ በእሳት እያጋሉ ዋንጫ በመሥራት ላይ ናቸው።

"ከወዴት መጣህ የኔ ልጅ?" አሉ።

"እረስተውኝ ነው እንጂ ባለፈው ከፈረንጆች ጋር ደኑን ለማጥናት የመጣሁት ነኝ" አልኳቸው።

ቀና ብለው አዩና "አይ የኔ ነገር ዘንግቸህ አይደል" አሉና ቀጥለውም፡-

"ደኅና ናችሁ" አሉና "ታዲያ እንግዶችህ የት አሉ?" ብለው አካባቢውን ለማየት ሞከሩ።

"አይ ዛሬ እንኳን ብቻዬን ነው የመጣሁት። እነርሱ ሥራቸውን ጨርሰው ከሄዱ ቆዩ" አልኳቸው።

"የት ነው ሀገራቸው?"

"አሜሪካን ነው።"

"አንተም እዛው ኗሪ ነህ?"

"አይደለም። እኔ እንኳን ባሕር ዳር ነው የምኖረው። ያው ሥራ አገናኝቶን ነው እንጂ።"

"እምን መቹስ በዚህ ዓለም ያለ ያዳም ልጅ ሁሉ መገናኛው ባዜ ነው" አሉ።

እኔን እያዋሩ ሥራቸውን ግን አልቦዘኑም። ዕንጨቱን ይዘው እያዚዚሩ ቀንዱን አሳት ያስለበልቡና እንደገና ቀንዱን መሬት ላይ ተክለው እንጨቱ የበለጠ ወደ ቀንዱ ውስጥ እንዲገባ መታ መታ ያደርጉታል። በዚህ ጊዜ ቀንዱ ቀስ በቀስ ይለጠጣል።

"አባ ስምዖት ማን ይባላል?" አልኳቸው።

ፈገግ ብለው ወደእኔ ዞር አሉና " አባ መዝገበ ሥላሴ" አሉ።

ቁመታቸው ያልረዘመ ያላጠረ ልከኛ ሲሆን ጸጉራቸው ጥቁሩ እየጠፋ ነጩ እያደላ ይመስላል። ፊታቸው ቀይ ሲሆን ረጅም ደስ የሚል ፂም አላቸው። ግንባራቸውና ዐይናቸው አካባቢ ቆዳቸው መጨማደድ መጀመሩ በፊጠራቸው መሥመሮች ይታወቃል። ከጺም እንደምንም ያመለጡት ከንፈሮቻቸው ሲገለጡ የዋህነታቸውን የሚገልጹ ዘርዘር ያሉ ጥርሶች አሏቸው። ዐይኖቻቸው ሞጮሙጨዋል ግን አሁንም ንቃት ይታይባቸዋል።

"ስንት ዓመት እዚህ ቤተ ክርስቲያን አገለገሉ?" አልኳቸው።

ቀና ብለው እንደማሰብ አሉና እንግዲህማ "ወደ ሀያ ስምንት ዓመት ሊሆን አይደል?" አሉ።

"በጣም ይገርማል ሃያ ስምንት ዓመት አንድ ቦታ መቀመጥ!" አልኩ ለራሴ በሚመስል ሁኔታ።

"ጊዜ እኮ ሲቆጠር ነው እንጂ ሲኖሩት አይታወቅም" አሉ።

"እርሱስ እውነት ነው" አልኩና "በምን ይተዳደራሉ?" ሌላ ጥያቄ አከልኩ።

"የቤተክርስቲያኑ ዕቃ ጠባቂ በመሆኔ ደመወዝ ሀገሬው ይከፍለኛል።"

"በዕቃ ጠባቂነት የሚከፈለዎት ለኑሮው ይበቃዎታል?"

"ይበቃል እንጂ፣ እንደምታየው የእጅ ጥበብም አለኝ። ዋንጫ፣ መለኪያ ፣ ዕፀ መስቀል፣ መቁጠሪያም እሠራለሁ እና ያ ሲጨማመር ብዙ ነው። ደሞስ ለአንድ መነኩሴ ከዚህ በላይ ምን ያስፈልጋል ብለህ ነው?"

"እርሱስ እውነት ነው" አልኩና "ቀንድ ከየት ነው የሚያገኙት?" ስል ሌላ ጥያቄ አስከተልኩ።

"የንስሓ ልጆቼ ፍሪዳ ሲታረድ፣ ከብት ሲሞትም አስበው ያመጡልኛል። የሩቁ ሰው ደግሞ ቀንዱን እራሱ አምጥቶ ዋንጫ እንድሠራለት ይጠይቀኛል፣ የእጅ ዋጋም ይከፍለኛል ።"

"ጠቅላላ ስንት ብር ያገኛሉ ልል አልኩና እዚህ ቅዱስ ቦታ የብር መጠን ምን ያደርጋል?" ብዬ ራሴን ገሠጽኩት። "ደመወዝ ስንት ይከፍላሉ?፣ ትርፍ ስንት ይገኘዋል? ቢዝነሱ ያዋጣል ወይ?" የሚሉት ጥያቄዎች እዚህ ቦታቸው አይደለም ። ያው ለምዶብኝ ነው አንጂ!

"አብሮዎት የሚያድር ጥበቃውን የሚያግዘዎት ሌላ ሰው አለ?" አልኳቸው።

"ኸረ የለም። ምን ያስፈልጋል ብለህ ነው?"

"እዚህ ግርማው በሚከብድ ደን በተከበበ ቤተ ክርስቲያን ብቻን ውሎ ብቻን ማደር አያስፈራም? "

"ሳለ መድኃኔዓለም ምን ያስፈራኛል? ደሞስ መቼ ብቻዬን ሆንኩ?"

"አይ ቅድም እኮ ሌላ ሰው የለም ስላሉኝ ነው እንጂ"

"እውን ሌላ ከውጭ የተመደበ ጠባቂ ሰው የለም። እንደዚያ ሰልህ ግን ብቻዬን ነኝ ማለት አይደለም።"

"እንዴት?" አልኳቸው ሰላልገባኝ።

"የባለፈው ጥናታችሁ እንዴት ሆነ?" አሉኝ። ሆን ብለው ውይይታችን ወደ ሌላ ርእስ እንዲቀየር ማድረጋቸውን ተረዳሁና

"እ... ጥናታችን ጥሩ ነው። የአንዳንዶቹ ቤተ ክርስቲያን ደኖች አስቸኳይ እንክብካቤና ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል። በተረፈ በርካታ ዕፅዋትና እንስሳት ተጠልለው የሚኖሩባቸው ቦታዎች መሆናቸውን ተረድተናል" አልኳቸው።

"ታዲያ ምን ልታደርጉ አስባችኋል?"

"እኛ ተመራማሪዎች ነን። አጥንተን መፍትሔ ነው የምንለውን ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ነው። ከዚያ ያለፈ ብዙ አቅም የለንም"።

"ይሆናል። ብቻ እኛም አካባቢ ሴቱ ወንዱ እየተጠየቀ ይሞላል፣ ሕዝቡ ይመዘገባል፣ ከብቶቹ መሬቱ ጥናት እየተባለ ይለካል፣ መፍትሔ ግን ብዙ የለም" አሉ አባ።

"እውነት ነው ጥናት አስፈላጊ ቢሆንም ተጠንቶ መፍትሔ ካልመጣ ትርጉም የለውም" አልኩኝ። ለራሴ ደግሞ "እርግጥ አሁን አሁን ጥናት እንጀራ እየሆነ ስለመጣ መፍትሔው ጋ መታገል የሚፈልግ የለም። ችግር ካለ ጥናት ያስፈልጋል። ጥናት ደግሞ ሞያና እንጀራ ሆ'ል። ታዲያ ይህን ለስላሳ እንጀራ መፍትሔ በሚል ፈንገስ ማን ያሻግታል!" በሚል ተሳልቆ ራሴን ወጋሁት።

"የእኛን፣ የዚህን ደብርስ እንዴት አገኛችሁት?" አሉ።

የዐፈር ናሙና ምርምሬን ውጤት ሳላይና ሌላ ሳይንሳዊ መላምቶችን ሳልጨርስ ሥራችንን ባልታወቀ ምክንያት አቋረጥነው ማለት አልፈለኩም። ምክንያቱም የምሥጢሩ ተካፋይ እርሳቸውም ጭምር ስለሆኑ አሁን ያለወቅቱ ማንሣት ሳይንሳዊ ትንታኔ ለመስጠት አያስፈልግም ብዬ ስለአመንኩ ነበር።

"ባጠቃላይ ደኑ ከውጭም ከውስጥም ሲታይ በደኅና ሁኔታ ያለ ነው። እንደሌሎች ልቅ የእንስሳት ግጦሽም አላጋጠመንም። ያም ሆኖ ብዙ ማወቅ ያለብን ነገር ይኖራል" አልኳቸው።

"ምንድን ነው ማወቅ የምትፈልጉት" አሉ እንደዋዛ።

"እ... ለምሳሌ የዐፈሩን ሁኔታና የመሳሰሉትን" አልኳቸው።

"ለዚህ ነው አንተ የመጣህ?" አሉ ።

"አዎን አባታችን። ባለፈው ቸኩለን የዐፈር ናሙና አልወሰድንም ነበር እና አርሱን ለመውሰድ ነው የመጣሁት" አልኩ።

"ማለፊያ ነው። ታዲያ በየት በኩል ነው የምትወስደው?"

"ቀልጠፍ አልኩና በዚህ በምዕራብ በኩል ወይም በስተደቡብ ሊሆን ይችላል" አልኩ። እኔ ግን የምፈልገው በስተስሜን አቅጣጫ ቢሆንም ያንን አይፈቅዱ ይሆናል ብዬ ነው።

"በል እንግዲያ ሥራ አይደል ሂድ እንጂ" አሉ።

"እሺ አባ መጣሁ" ብዬ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሄድኩ።

የድንጋዩን ካብ ዘልዬ በውጭ ከሆንኩ በኋላ ስለማይታይ ጎንበስ ብዬ ካቡን እየታከከሁ ወደ ስሜን አቅጣጫ አመራሁ። ቀደም ሲል ከዶ/ር ማግዳሊና ጋር የስሜኑን መሥመር ለመሥራት ከጀመርንበት ቦታ ስደርስ ፊቴን ወደ ሰሜን አቅጣጫ አዞርኩና ወደፊት ተራመድኩ።

ከአባ መዝገበ ሥላሴ ጋር በቆየሁባቸው ደቂቃዎች ተረጋግቼ እንደነበር ትዝ ያለኝ አሁን እንደገና ልቤ መሸበር ሲጀምር ነው። ባለፊው ከተመለስንበት ቦታ ስደርስ ኮምፓስ አውጥቼ ለማየት ሞከርኩ። ኮምፓሱ እንደ ባለፊው አልተርገበገበም ወይም አልተሽከረከረም።

"ሊሠራ ነው እንዴ?" አልኩኝና በመዳፌ ላይ አስቀምጬ ወደ ኋላዬ ዞርኩ። ኮምፓሱ የሚሠራ ከሆነ 180 ዲግሪ መዞር ስላለበት ለማረጋገጥ ነው። ዐይኔን ማመን አቃተው። ኮምፓሱ መርገብገብም፣ መሽከርከርም ትቶ ባለበት ደርቆ እንደቆመ ተረዳሁ።

"የፈጣሪ ያለህ! አሁን እኔን በቁሜ ሳያደርቀኝ በፍጥነት የዐፈር ናሙና መውሰድ አለብኝ" አልኩና ሻንጣዬን አውርጄ የእጅ ጓንት ካደረኩ በኋላ የተከማቸውን የቅጠል ብስባሽ ሙልጭ አድርጌ ጠረኩና ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ጫፉ በተሳለ የዐፈር ናሙና ማውጫ ቱቦ (Augur) 50 ሳ/ሜ ጥልቀት ድረስ ያለ ዐፈር አውጥቼ በፕላስቲክ ከረጢት በፍጥነት መክተት ጀመርኩ።

ብቻ ልቤ ድው ድው ይላል። ከአቅራቢያ ካለ ረጅም ዛፍ ላይ ድንገት፡-

"ጀፍ.. ጀፍ.. " የሚል ድምፅና የሚንቀሳቀስ አካል ስሰማ ደንግጬ በጀርባዬ ተዘረርኩ።

"ካካ ካካ ... አህ አህ... አህ" የሚል ድምፅ ስሰማ ከድንጋጤዬ ተመለስኩ። ጠማዎች ነበሩ። "ተንኮለኞች!" አልኩና እየተርበተበትኩ

ሁለት ቦታ ላይ የዐፈር ናሙና ወሰድኩ። አንድ አራት የሚሆኑ ድንጋዮችም በከረጢቶች ከተትኩና በፍጥነት ከአካባቢው ለቀቅኩ።ከዚያም ወደ ምዕራብ ሄድኩና የድንጋዩን ካብ ዘልዬ ወደ አባ ዘንድ ሄድኩኝ።

"መጣሀ?" አሉኝ ።

"አዎን አባ። ይኸው ይዤ መጣሁ" ብዬ አንዱን የፕላስቲክ ከረጢት አሳየኋቸው።

"የት ነው የምትመረምረው?" አሉ ።

"አዲስ አበባ ነው" አልኳቸውና "እ.. አባ አሁን መሄድ አለብኝ (አቤት ችኮላዬ!)። ያው እዚህ ቦታ መመላለሴ ግን የሚቀር አይመስለኝም" አልኳቸው።

"ምነው በደኅና?" አሉ ።

"እንዴ ቤተ ክርስቲያኑን ለመሳለም እርስዎንም ለመጠየቅ ብመላለስ ምን አለበት?" አልኳቸው እንደመሣቅ ብዬ።

"አይ፤ ያው ሥራህን የጨረስክ መስሎኝ ነው እንጂ እኔማ ምን ገደኝ" አሉ ትንሽ የገፉኝ መሰላቸውና፡- "እኔማ እንኳንስ ለመጠየቅ መምጣት ይቅርና እዚሁ እኔ ጋር መጥተህ ብትኖርስ ምን ገደኝ " አሉ ለማረጋጋት።

"አይ አውቃለሁ አባታችን" አልኩና "ይልቁንስ ስመጣ ከከተማ የሚፈልጉት ነገር ካለ ላምጣልዎት?" አልኳቸው

"ተባረክ የኔ ልጅ። ግን ምንም የምፈልገው የለም ብቻ ..." አሉ ሊጠይቁት የፈለጉት ነገር እንዳለ ስለገመትኩ፡-

"ብቻ ምን? ይንገሩኝ ግዴለም" አልኳቸው።

"ማንበቢያ መነጥር ነበረኝ እና በቀኝ በኩል ያለው ብረቱ ተሰብሮ ተቸገርኩ" አሉ ።

"እስኪ ልየው?" አልኳቸው ።

ተነሥተው ወደ ላይኛው ደርብ ወጡና ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ላይ በመዋሉ ፍሬሙ የዛገ፣ መስታዎቱ የደበዘዘ፣ ወደ ጆሮ የሚሄደው የቀኝ ፍሬም የተሰበረ መነጽር ይዘው ተመለሱ።

"እይይ... አባ ይኸማ ባይሰበርም እኮ አርጅቷል" አልኳቸው ተቀብዬ እያየሁ።

"መሰበሩ ነው እንጂ ማርጀቱ እንኳን ብዙም አልጎዳም ነበር" አሉ ።

"ታዲያ ይሄን ይገርው ልሂድ ወይስ ቁጥሩን ያስታውሱታል?" አልኳቸው ።

"ይሄማ ለጊዜውስ በምን እጠቀማለሁ?" አሉና "ቆይ እስቲ ስመረመርና መነጥሩን ስገዛ የተሰጠኝ ወረቀት ይኖራል" አሉና ድጋሜ ወደ ደርቡ ወጡ።

ትንሽ ቆይተው የመነጽር ማዘዣ ወረቀት ይዘው መጡ። ተቀብዬ አየሁና፡-

"አሃ ፕላስ ቱ ነው (+2)" አልኩ።

"አዎን ፕላስ ቱ ነው" አሉ። በማስታወሻዬ መዝግቤ፡-

"በሉ እንግዲህ አባታችን በቅርብ እመለሳለሁ" አልኩና በመስቀላቸው ተባርኬ ቁልቁለቱን በደኑ ውስጥ መውረድ ስጀምር አባ መዝገበ ሥላሴ የተናገሯቸው ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ከአእምሮዬ ውስጥ እንደ ኳስ ይነጥሩ ጀመር።

"አዎን ሌላ ከውጭ የተመደበ ጠባቂ ሰው የለም። እንደዚያ ስልህ ግን ብቻዬን ነኝ ማለት አይደለም" ያሉትና የመነጽሩን የንባብ ሃይል መጠን ፕላስ ቱ የሚለውን በእንግሊዝኛ ስናገር "አዎን ፕላስ ቱ ነው" የሚሉት ነበሩ።

"ለማንኛውም ለጊዜው የደኑ እንቆቅልሽ ይበቃኛል። ሌላ እንቆቅልሽ የምደርብበት አቅም ያለኝ አይመስለኝም" አልኩና ፈጠን ብዬ እየተራመድኩ ደኑን ጨርሼ መኪና ወደ አቆምኩበት መንደር ሳመራ ከቤተ ክርስቲኑ ደን በስተሰሜን ትንሽ ሸለቆ ተሻግሮ ከብት የሚጠብቁ ልጆችን ተመለከትኩ።

ሂጄ በአካባቢው ስለደኑ ምሥጢር የሚነገር ወሬ ካለ ለማውጣጣት የሆነ ነገር ገፋፋኝ። ወደ ምሥራቅ የነበረውን መንገዴን ትቼ ወደ ሰሜን ልጆቹ ወደ አሉበት ሸለቆውን ተሻግሬ ሄድኩና አጠገባቸው ሰደርስ፡-

"ልጆች እንዴት ዋላችሁ" አልኩ።

"ዛየርመስጌ ደኅና!" አሉ አንዱ በአንዱ እየተሸሸጉና እየተሸኮረመሙ። ስድስት ልጆች ናቸው ዕድሜአቸው ከ7-14 ይሆናል።

"ምን እየሠራችሁ ነው?" አልኳቸው።

"ከብት እየጠበቅነ" አለ ከመካከላቸው አንዱ።

"ጎበዞች" አልኩና "አትማሩም እንዴ?" ስል የተለመደ የባይተዋር ከተሜ ጥያቄ አቀረብኩ።

"እንማራለን እንጂ" አሉ።

"ታዲያ አሁን እዚህ ምን ትሠራላችሁ?"

"በሸፍት ስለሆነ።"

"አሃ !" አልኩና ከሰዓት በኋላ ትሄዳላችሁ ማለት ነው" አልኩ።

"አዎድ" አሉ።

ወደጥያቄዬ ከመግባቴ በፊት ዘና እንዲሉ ብዬ ፎቶ ግራፍ እነሣኋቸውና ምስላቸውን በስክሪኑ አሳየኋቸው። በጣም ደስ አላቸው።

"እረረ..ይ።"

"እረ ጉባይ!"

"እይ.. እትናን" እያሉ ይሣሣቁ ጀመር።

እያንዳንዱ ልጅ ማየት የሚፈልገው የራሱን ምስል ስለሆነ ጐላ እያደረኩ ለሁሉም አሳየኋቸሁ። በጣም ደስ ያላቸው ይመስላል። የራሳቸውን ምስል ሲያዩ ይገረማሉ ይደሰታሉ። የሰው ልጅ አእምሮው ጤነኛ ከሆነ እንደራሱ የሚወደው የለም። የራሳችንን ምስል እንደማየት የሚያስደስተን ነገር የለም። መጠኑ ሲያልፍ ግን ትልቅ ቢል ቦርድ አሠርቶ ፎቶ በመስቀል፣ ሐውልት አስቀርጾ በአደባባይ በማቆም ሰዎች ሁሉ ይመልከቱኝ ወደ ሚል በሽታ ከፍ ሊል ይችላል።

እየተሸኮረመሙና እየተሣሣቁ ዘና ማለታቸውን አየሁና "ልጆች?" አልኳቸው። ሁሉም ወደ እኔ ዘወር ሲሉ፡-

"እዚህ ቤተ ክርስቲያን ደን ውስጥ ከብት ታስገባላችሁ እንዴ?" አልኳቸው።

"አሪ! ከብት አይገባም" አሉ።

"አጋም፣ ቀጋ ለመልቀምም አትገቡም?" አልኳቸው።

"እረ አይገባም" አለ አንደኛው ልጅ።

"ለምን?"

"እኛ አናውቅም ብቻ አይገባም" አለ ሌላኛው ትክሻውን ወደ ላይ ከፍና ዝቅ እያደረገ።

ከዚያ ሌላኛው ልጅ፡-

"አያ ደጎች ስላሉበት ነው" አለ።

"ምን? እነማን ናቸው ደጎች?" ብዬ ለማጣራት ስሞክር

"ወይ ዕድልህ አንተ ቀባጣሪ ወንፊት" ሲል አንደኛው ልጅ

"ቆይ ለአጊጌያ ባልናገር" አለ ሌላኛውና ሁሉም ተረባረቡበትና ልጁ በጣም ደነገጠ።

"ለምን እንደሱ ትሉታላችሁ። እኔ እኮ ሁሉንም አውቀዋለሁ" አልኳቸውና ለማረጋጋት ከኪሴ አወጣሁና ለሁሉም አንዳንድ ብር ሰጠኋቸው።

ሁሉም ብሩን በእሽታ ተቀብለው እያገላበጡ ሲያዩ፡-

"እኔ እምላችሁ" አልኩና ወደ እኔ ሲመለከቱ፡-

"ማነው ከእናንተ ውስጥ ጐበዝ ልጅ ተጨማሪ ብር የምሰጠው አብሮኝ በዚህ በኩል ከደኑ ገብቶ ደጎቹ ያሉበትን የሚያሳየኝ?" ስላቸው ሁሉም በድንጋጤ ክው ሲሉ አየኋቸው። ከዚያ ተለቅ ያለው ልጅ መጣና ብሩን ከእግሬ ሥር ጥሎ ራመድ ሲል ሁሉም የሰጠኋቸውን ብር ጥለውልኝ ከእሩጫ በማያንስ እርምጃ እየተገላመጡ ትተውኝ ወደ መንደሩ አቅጣጫ ሄዱ።

ነገሩን እንዳበላሸሁትና ትልቅ ችግር እንደፈጠርኩ ስለገባ
ወሬው ወደ መንደር ከመዛመቱ በፊት በፍጥነት ወደ መኪና
ተራመድኩ።እንደደረስኩ መኪናውን ሲያዩልኝ የነበሩትን እና
አመሰግኜ መኪናውን አሥነስቼ በፍጥነት እየነዳሁ ከአካባቢው
ራቅሁ። ከዋናው የመኪና መንገድ ስገባ "እፎይ" አልኩ። በአንድ
ወቅት የሠራሁት ቀሽም ስሕተት ታወሰኝና ፈገግ አልኩ።

ከስድስት ዓመት በፊት ይመስለኛል ወደ አንድ ሰፊ የተፈጥሮ ደን
ወዳለው ደብር ለጥናት ሄጄ ነበር። ቤተ ክርስቲያኑ ከወረዳው ከተማ
በአምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ነው። እስከ ወረዳው
ከተማ በሕዝብ ትራንስፖርት ሄድኩና ማረፊያዬን ካመቻቸሁ በኋላ
ከቀኑ ወደ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ቢያንስ ለሁለት ሰዓታት መሥራት
እችላለሁ አልኩና ሁሌም እንደማደርገው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ
የሆነ ልጅ እንዲያግዘኝ ቀጠርኩ። ልጁ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ
ሲሆን ዕድሜው ወደ ዐሥራ አምስት ዓመት ይጠጋል። ሥራው
ሜትር ወጥሮ መያዝ፣ ዕቃ ማቀበል፣ አንዳንድ ጊዜም እኔ ዛፍ ላይ
ስወጣ የምነግረውን ማስታወሻዬ ላይ መጻፍ ነው።

ሁለት ቀን አብሮኝ ሲሠራ በክፍያ ተስማምተን ለሥራ የሚያስፈልጉ
መሣሪያዎችን ተከፋፍለን ተሸክመን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አመራን።
ከተማዋን ለቀን እንደወጣን በርካታ ሕዝብ ከቤተ ክርስቲያኑ ወደ
ከተማው ሲመለስ አገኘን።

"ምን አለ ዛሬ አልኩት?"

"አንድ በከተማው የታወቁ ሰው ሞተው ከቀብር እየተመለሱ ነው"
አለኝ።

የባጥ የቆጡን እያወራን እኔ ከፊት እርሱ ከኋላ ሁነን ተጉዘን ከቤተ
ክርስቲያኑ ለመድረስ አንድ ሁለት ኪሎ ሜትር ሲቀረን፡-

"ጋሽ! ምንድን ነው ደኑ ወስጥ የምታጠናው?" አለኝ።

ምን እንዳቀበለኝ አላውቅም ብቻ ቀልድ የፈጠርኩ መስሎኝ፡-

ሞተው ቤተ ክርስቲያን የተቀበሩ ሰዎችን መመርመር ነው። እየውልህ ዛሬ የምንሠራው ከቤተ ክርስቲያኑ እንደደረስን ሰው ወደሚቀበርበት አካባቢ እንሄድና ዛሬ የተቀበሩትን ሰውዬ ቆፍረን እናወጣለን። ከዚያ በእርግጥ አሁንም እንደሞቱ እንደሆነ እናያለን። ሙሉ በሙሉ ሞተው ከሆነ ደግሞ በምን ምክንያት እንደሞቱ እንመረምራለን። አትፈራም አይደል?" አልኩት

ዝም... መልስ የለም...

"አያስፈራም እኮ። የሞተ ሰው ከዚህ በፊት አይተህ ታውቃለህ?"

መልስ የለም...

"ፈራህ እንዴ?" አልኩና ዘወር ብዬ ባይ ከአጠገቤ የለም።

ሻንጣዬን ጥሎልኝ በፍጥነት ወደ ከተማ እግሬ አውጭኝ እያለ እንደሆነ ተመለከትኩ። በግዴለሽነት የፈጠርኩት መራራ ቀልድ እንዳስበረገገውና ከተማ ሲደርስ ደግሞ "አንድ ወዘ ልውጥ ሰው መቃብር ሊቆፍር መጥቷል" ብሎ ቢያወራ ሊደርስብኝ የሚችለው ችግር ወዲያው ታሰበኝና ደነገጥኩ።

በፍጥነት ጥሎልኝ የሄደውን ሻንጣ አንሥቼ ከከተማው ከመድረሱና ከማውራቱ በፊት ልጁን መያዝና ቀልዴን መሆኑን ማስረዳት ነበረብኝ። ሳንባዬ ጉሮሮዬ ላይ የተወተፈ እስኪ መስለኝ ባለ በሌለ ኃይሌ መሮጥ ጀመርኩ። አባራሪና ተባራሪ ሆነን በስንት ልመና ከተማው መግቢያው ላይ አቁሜ ቀልዴን እንደሆነ እየማልኩና እየተገዘትኩ ነግሬ በስንት ልመና አሳመንኩት። በዕለቱ ልሠራው ያሰበኩት ተሰርዞ ሥራዬን በማግስቱ እንደሠራው አስታወስኩና ዛሬ ደግሞ ተመሳሳይ ስሕተት መሥራቴ ተሰምቶኝ "ኤዲያ!" አልኩ ለራሴ ።"

# ምዕራፍ ዐሥራ ኸራት

"ከሞገደኛው የቤተ ክርስቲያን ደን ተመልሼ ባሕር ዳር በጊዜ ገባሁ። መንገድ ላይ እያለሁ ወደ አዲስ አበባ የአውሮፕላን ትኬት ለማግኘት በጸሐፊዬ በኩል አስመዘገብኩ።

ማታ ባለቤቴን፡-

"ነገ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ አስቢያለሁ" አልኳት።

"አንተ በቃ እንደ ዘላን ብድግ እያልክ መሄድ ሥራህ ሆነ ማለት ነው? ዛሬ ደግሞ ምን ተገኘ?" አለችኝ ።

"በጣም ወሳኝ የሆነ የዐፈር ናሙና ለማስመርመር ነው" አልኳት ።

"ሊሆን ይችላል። ግን ዛሬ ከመስክ ነው የመጣህ። ለምን እያረፍክ አትሠራም?" አለች ለዘብ ብላ ።

"ያልተነካ ግልግል ያውቃል› አሉ። እኔ እንደሆነ የዚያን ቢጉ ከርስቲያን ደን ምሥጢር ሳላውቅ ከእንግዲህ ዕረፍትም እንቅልፍም እንደማይኖረኝ አውቃለሁ" አልኩ በልቤ። ዝርዝሩን ብነግራት ደግሞ አደጋውን በመፍራት ተመልሼ ወደዚያ ደን እንዳልሄድ ልተከላከለኝ ትችላለች ብዬ ላለመንገር ወሰንኩና፡-

"አይ በአውሮፕላን አዲስ አበባ ለመሄድ ምን ዕረፍት ያስፈልጋል? ብቻ የምርምር ሥራው አሰቸኳይ ስለሆነ ነው" አልኩ።

ጠባቤንም ሥራዬንም የለመደችው ስለሆነ "በል እንደፈቀደሀ" ብላ ዝም አለች።

በጠዋት ተነሣሁና የዐፈርና የድንጋይ ናሙናዎቹን ከሁለት ከፈልኩና ከአፈሩም ከድንጋዩም ለመጠባበቂያ አንድ አንድ አስቀርቼ አንድ የዐፈርና አንድ የድንጋይ ናሙና በፕላስቲክ ቁጥሬ ሻንጣዬ ውስጥ ከተትኩና ላፕቶፔንና ትንሽ ቅያር ልብስ ይዤ ወደ ባሕርዳር አውሮፕላን ጣቢያ ሄድኩ።

አውሮፕላን ጣቢያው እንደተቀመጥን ከአዲስ አበባ ወደ ባሕር ዳር የሚመጣው አውሮፕላን በአንድ ሰዓት እንደሚዘገይ አስታወቁ። "ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው" እንደተባለው በንዴት ብግን አልኩ።

"ሰው ሲቸኩልማ አላቸው ነገር" አልኩ። "እንዲያው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ካለ ነገሩ ሰዓት አያከብርም በተለይ የአገር ውስጥ በረራ!" ብዬ ተነጫነጭኩ።

ለእኛ ቀድሞ በተነገረን ሰዓት ሳይሆን እነርሱ በተመቻቸው ሰዓት አውሮፕላኑ መጣና ተሳፍረን አዲስ አበባ ቦሌ 4፡50 ላይ ደረስን። እየተጣደፍኩ ወጣሁና ኮንትራት ታክሲ ይዤ አሥመራ መንገድ ወደ ሚገኘው የኢትዮጵያ ጂኦሎጅካል ሰርቬይ ኢንስቲትዩት አመራሁ።

አርሰ በርስ መከባበርና በሕግ መመራት የማያውቀው የአዲስ አበባ ትራፊክ እንደተለመደው ተሳስሮ ቁሟል። "ጨንራዬን ለብዙ ጉዳይ ስለምፈልገው ከአሁኑ ልጨ የትም አልደርስም" አልኩና ተረጋጋሁ። ስንንኳተት ውለን ከቀኑ 6:00 አካባቢ ኢንስቲትዩቱ በር ደረስን። ባለታክሲውን ከፍዬና አመሰግኜ ሻንጣዬን ይዤ ወደ አጥሩ ዋና በር ተጠጋሁና ልገባ ስል።

"ወንድም ሰዓት ደርሷል" አለኝ።

"6:30 አይደለም እንዴ የሥራ መውጫው?" አልኩት በትሕትና

"እኮ!"

"ታዲያ አሁን እኮ ገና 6:00 ነው" አልኩት።

"በቃ ምን ቀረው፡ አሁን መውጫቸው ነው። ከሰዓት ተመለስ" አለኝ ቆጣ ብሎ ወደ መቀመጫው እየሄደ።

"አይ እኛና ሰዓት!" አልኩ በሆዴ።

በእኛ ሀገር የሥራ መግቢያ 2:30 መውጫ 6:30 ይባላል እንጂ ሥራ መጀመሪያ 3:00 የሥራ መውጫ ደግሞ 6:00 ነው። ለምን ቢባል ጠዋት ሥራ ለመጀመር መዘጋጃ ጊዜ ያስፈልጋል። ወንበር ለማስተካከል፣ ኮምፒውተር ለማስነሣት፣ ከብዙ የማይሠሩ ቁልፎች መካከል ለይቶ የጠረንጴዛ ኪስና ቁም ሳጥን ለመክፈት፣ ከዚያ ደግሞ የዕለቱን ወሬ ለመቀዳዳት ነው። ለመውጫስ ቢሉ ደግሞ ለእርሱም መዘጋጃ ያስፈልገዋል። የመንግሥት ቢሮ ዝም ብሎ ጥሎ ይወጣል እንዴ! ዝግጅት ያስፈልገዋል እንጂ!

እውነት ለመናገር በእኛ ሀገር የሥራ መግቢያና መውጫ ጊዜ
ከ3-6 ከሰዓት ደግሞ ከ8-11 ነው። በዚህ መካከል ባሉት ሰዓት
በአግባቡ የሚሠራ ካለ እርሱ የተመሰገነ ነው። ብቻ የሥራ ሰዓት
በሀገራችን ሞቶ ከተከተተ ዘመኑ አይታወቅም ወይ መጀመሪያም
አልተፈጠረ ይሆናል? ለነገሩ እንኳን ተራ ሠራተኛ መንግሥት ራሱ
ሥራ ለመጀመርና ለመጨረስ ብዙ ዝግጅት ይፈልግ የለምን?
መጀመሪያ መወዳደር፣ ከዚያ መመረጥ፣ ከዚያ መዋቀር፣ ከዚያ
መሸሸም፣ ከዚያ ቢሮና መኪና መመዳደብ፣ ከዚያ ማቀድ፣ ከዚያ
በዕቅድ መወያየት፣ ከዚያ ከሚሠራው ሥራ በታች ላይ የመሠረት
ድንጋይ ማስቀመጥ፣ ከዚያ ባጋጠመ ችግሮች ላይ መወያየት፣
ዝግጅት ይቀጥላል...

እርግጥ ሕይወት በራሷ በዝግጅት የተሞላች ናት። መጀመሪያ
መወለድ፣ ከዚያ ለማደግ መታገል፣ ከዚያ መማር፣ ከዚያ አግብቶ
ትዳር ለመመሥረት መዘጋጀት፣ ቤት ሠርቶ ልጆችን ለማሳደግ
መዘጋጀት፣ ከዚያ ለጡረታ መዘጋጀት፣ ከዚያ ዕድር ውስጥ
ተመዝግቦ ለመሞት መዘጋጀት ነው። አበቃ!

እንዲህ ራሳችንንም መንግሥትንም በጥርሴም በጥፍሬም ስቦ
በር ላይ ተገትሬ መቅረቴ ታውቀኝና "ሆሆ!" ብዬ የምግብ ፍላጎት
ባይኖረኝም የምሳ ሰዓት ነውና በአካባቢው ምሳ ፍለጋ ሄድኩ።

ለስምንት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ተመልሼ ከአጥሩ በር ደረስኩና ወደ
ውስጥ ልዘልቅ ስል፡-

"ወዴት ነው?" አለኝ ጥበቃው።

"ቅድም መጥቼ ሰዓት ደርሷል ብላችሁኝ ተመልሼ ስለነበር፣ አሁን
ድጋሚ መምጣቴ ነው" አልኩ ።

"እኮ ወዴት ነው የምትሄድ?" አለ ።

"ላቦራቶሪው ዘንድ ነው።"

ሥንድን ነው ጉዳይህ?" አለ። በቃ ልዩ ፖሊሳዊ ሥልጣን ያለው ይመስላል አነጋገሩ።

እኔም "እስኪ ይለፍልህ" አልኩና "የዐፈር ናሙና ለማስመርመር ነው" አልኩ።

"ምን ዐፈር ነው?" አለ አሁንም እንደተኮሳተረ።

"መሬት ዐፈር" አልኩ እንደመሣቅ ብዬ። "‹የመቃብር ዐፈር› ብለው እኮ ሌሊቱን በሙሉ ሲባባ ያድራል" አልኩ በልቤ።

"ለምን ሥራ ነው?" ቀጠለ። እዚህ ላይ ትዕግስቴ አለቀ።

"የኔ ወንድም የአንተ ሥራ ሕጋዊና ሰላማዊ ሰው መሆኔን መታወቂያዬን አይተህ ፈትሸህ ማስገባት ብቻ ነው። ሌላው ጥያቄ ውስጥ ያሉት ባለሙያዎች ሥራ ነውና የማይመለከትህ ውስጥ እየገባህ አይመስልህም?" አልኩት ኮስተር ብዬ።

"እሺ መታወቂያ አምጣ?" አለ።

መታወቂያየን አውጥቼ ስሰጠው እንደ ነገሩ ተመለከተና ጠጋ ብሎ ጎኔን ቸብ ቸብ አድርጐ "እሺ ግባ" አለ።

ከኤድስ ቀጥሎ ለአፍሪካውያን ትልቁ በሽታ ሥልጣን ነው። በቃ በተቻለህ መጠንና አጋጣሚ ሁሉ በሌላው ላይ መሠልጠን። የምትኮፈስበትና የምትጀነንበት ሰው መፈለግ፡ ማጉላለትና ማንገራገር። እንዲያው ይህን በሽታ ያስለከፈን ማን ይሆን?!

ቀስቱ በሚያመለክተው መሠረት ወደ ላቦራቶሪው ገባሁ። ትልቅ የእንግዳ መቀበያ ዴስክ ጀርባ በርከት ያሉ ጋዋን የለበሱ ባለሙያዎች ውር ውር ይላሉ። ወደ ዴስኩ ጠጋ ብዬ ሳማትር አንዲት ረዘም ወፈር ያለች ራሷን ጅንስ ሱሪ ውስጥ የከተተች ሴት ጠጋ አለችና፡-

"ምንድን ነበር?" አለችኝ። ከፊቷ እስከ ንግግሯ ትሕትና የሚባል የሌለው የደረቀ ጥያቄ ነበር።

"የዐፈረና ድንጋይ ናሙና ለማስመርመር ነበር" አልኩ በሁኔታዋ እየተገረምኩ፡-

"ተመልሳ ሄደችና ጠረጴዛ ላይ አንድ ወረቀት ላጥ አድርጋ አምጥታ ዴስኩ ላይ ወደ እኔ ገፋ አድርጋ "ይሄን ፎርም ሙላና አምጣ" አለች ኮስተር ብላ።

"መድኃኔዓለም ሰላሙን ይላክልሽ" አልኩና በልቤ ፎርሙን እያነበብኩ መመላት ጀመርኩ።

ለነገሩ ፎርሙ ስምና አድራሻ፣ ናሙናው የተሰበሰበበት ቦታና የሚፈለገው የምርመራ ዐይነትና የመሣሉትን ነበር። ናሙና የተሰበሰበበትን ቦታ የጅኢፒኤስ ነጥብ ከሚጠይቀው ላይ ሆን ብዬ በ50 ኪሎ ሜትር ራቅ አድርጌ ሞላሁና የሚፈለገው የምርመራ ዐይነት ላይ የብረት ማዕድን ክምችት መጠንና ሌሎች ያልተለመዱ ራዲዮ አክቲቭ ንጥረ ነገሮችን እንዲያጠቃልል አድርጌ ሞላሁና ፈርሜ ሰጠኋት።

ተመልሳ ሄደችና ጠረንጴዛ ላይ ቁጭ ብላ ኮምፒውተር ላይ የሆነ ነገር ስትሞላ ቆይታ ሌላ ተጨማሪ ወረቀት አትማ ይዛ መጣችና "ሂድና ከፍለህ ና!" አለችኝ።

"የት ነው እምከፍል?" አልኩ።

"ካሸሯ ጋ ነዋ!" አለች እየተቆጣች።

"ማለቴ የካሸሯ ቢሮ የት ነው?" አልኩ።

እጁን አመናጭቃ አቅጣጫውን አሳየችኝ።

ከሸሪ ጋር ደረስኩና በመስታወት መስኮት በኩል ወረቀቱን አቀበልኳት። ወረቀቱን ተቀብላ ከአነበበች ብኋላ፡-

"አሁን ሲስተም ስለተበላሸ እዛጋ ዐረፍ ብለህ ቆይ" አለች።

"ባለው! ዛሬ አማልክት በሙሉ ከእኔ ጋር ጦርነት ጀምረዋል ማለት ነው" ብዬ ሄጀ ቁጭ አልኩ። ለነገሩ ብዙዎቻችን ሲስተም ተበላሽ ሲባል የሚመጣልን ግዑዙና በሽቦ የተጠላለፉት መሣሪያዎች ይመስሉናል። በእኔ ግምት ግን የተበላሸው ይህንን የሚያደራጀውና የሚያስተባብረው የሰው አስተሳሰብ ነው። ከግማሽ ሰዓት መቀመጥ በኋላ ካሸሪ በእጇ ጠቀሰችኝና ወደ መስታወቱ ስጠጋ ክፍያ እንድፈጽም ነገረችኝ። በፍጥነት ከፈልኩና ደረሰኙን ይዤ ወደ ላቦራቶሪው ተመለስኩ።

ከዴስኩ ጋ ተደግፌ መቆሜን ስታይ እየተግላወደች መጣችና ደረሰኙን ካየች በኋላ፡-

"ናሙናውን አምጣው!" አለች።

ቀልጠፍ ብዬ ሁለቱን የናሙና ከረጢቶች ዴስኩ ላይ አስቀመጥኩ። ምንም ዐይነት መለያ ምልክት ወይም ጽሑፍ ሳታደርግ አነሣችና ማዶ ጥግ ላይ በአንድ ትልቅ ጠረንጴዛ ላይ ከተደረደሩ ሌሎች ናሙናዎች ጋር አስቀመጠችው።

"በጣም ደነገጥኩ፤ ታዘብኩም።"

ወዲያው ተመልሳ መጣችና "ከሦስት ቀን በኋላ ብቅ በል" አለችኝ በተለመደው ፍልጥ ንግግሯ።

"እባክሽ የእኔ እጎት ውጤቱን በጉጉት ነው የምጠብቀው እና...." አልኳት በልምምጥ።

"እንዴ! ዛሬ መጥተህ ዛሬ እንዲሠራልህ ትፈልጋለህ እንዴ? የማነው እባካችሁ" አለች።

"ምናለበት ስለቸኮልኩ እኮ ነው" አልኩ።

"ምም ያ የኔ ችግር አይደለም" ብላኝ ትታኝ ሄደች።

"በዚህ ሁኔታ ተሠርቶ ውጤቱም አያስተማምንም። ዝም ብዬ ለዶ/ር ጃኔት በደኤችኤል በፖስታ ብልከው ይሻላል" አልኩና ገንዘቡም ከስሮ ቢሆን ናሙናውን ለመውሰድ ወሰንኩና ከውስጥ እስክትመለስልኝ መጠበቅ ያዝኩ።

በመኻል ከመጀመሪያው ጀምራ በርቀት ስትከታተለን የነበረች ሌላኛዋ ሠራተኛ ጠጋ አለችና ።

"ምን ሆነህ ነው? አልጨረስክም እንዴ?" አለችኝ በትሕትና።

"ምን እጨርሳለሁ። በአግባቡ እንኳን አታናግሩም። ሌላው ቢቀር የሳይንስ ናሙና ያለምንም መለያ ወስዳ ከሌላው ጋር ስትደባልቀው ቅር አላላትም። እና የከፈልኩት ገንዘብም ይክሰር ናሙናውን እባክሽ መልሺልኝና ውጭ ልኬ አስመረምረዋለሁ" አልኳት በምሬት።

"አይ ያን ያክል አትማረር፡ ይኼ ያጋጥማል። በግለሰቦች የተነሣ በመሥሪያ ቤቱ ላይ እምነት ማጣት የለብህም" አለች።

"ያው መሥሪያ ቤት የሚገለጸው እኮ በሠራተኞች ነው፤ ምን ላድረግ?" አልኳት።

"ይገባኛል። ለማንኛውም ነገ አምስት ሰዓት ላይ ተመለስ። እኔ አሠርቼ እጠብቅሃለሁ" አለችና ናሙናዎቹን እያየሁ መርጣ ልዩ ምልክት አድርጋ ወደ ውስጥ ይዛው ገባች።

ጥይት ጉድ!" አልኩ።

ብዙ ከጥራ ጋር፣ ስንዴ ከእንክርዳድ ጋር፣ ደግ ከክፉ ጋር፣ ታታሪ ከሠነፍ ጋር ተደባልቆ መሳ ለመሳ የሚኖርብሽ ዓለም፤ ጨርሰን እንዳንጠላም፤ ጨርሰን እንዳንወድም፣ ጨርሰን እንዳንወቅስም፣ ጨርሰን እንዳናመሰግንም ጉራማይሌ ዓለም ስሚታችንንም ጉራማይሌ አደረገችው" አልኩና በተስፋ ላቦራቶሪውን ለቅቄ ወጣሁ።

ከማስቱ የቀጠሮው ሰዓት እስኪደርስ አላስችልህ ቢለኝ ጠዋት 3፡00 አካባቢ ካረፍኩበት ‹ከፍል ውኃ› ሆቴል ተነሣሁና ወደ መገናኛ አመራሁ። ለቸኮለ ነው እንጂ እንደኔ የቀጠሮው ሰዓት አልደርስ ላለው ሰው የአዲስ አበባ ትራፊክ ፍቱን መድኅኒት ነው። መደበኛ ታክሲ በመጠበቅ፣ ተሣፍሮ በተዘጋጋ መንገድ በዝግታ መንኳተት፣ ሹፌር ሲሰዳደብና ቤተ አራዊት ውስጥ እንደታሳሩ ጉሬላዎች ሲናጭ በአግራሞት እያዩ ለመጓዝና ጊዜ ለመግደል ጥሩ ነው።

ብቻ ለአምስት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ኢንስቲትዩቱ በር ላይ ደረስኩና እንደተለመደው መታወቂያዬን አሳይቼ ወደ ላቦራቶሪው አቀናሁ። መቼም ጉጉቴ መጠን የለውም።

"አሁን ከፍተኛ የብረት ክምችት ወይም ዩራኒየም መኖሩ ቢታወቅ ምንድን ነው የማደርገው? የተቀደሰ ቦታ የማዕድን ማውጫ ይሆናል ተብሎ መቼም አይታሰብም" እያልኩ ወደ ዴስኩ ጠጋ አልኩና ትናንት በአግባቡ ያስተናገደችኝን ሠራተኛ በዐይኔ መፈለግ ያዝኩ።

"የለችም ወይ ጣጣ" አልኩ።

ፈዝገፍ እንደቆምኩ ወደ ውስጥ የሚያስገባው በር ተከፈተና ወረቀት በእጁ ይዛ ስትወጣ አየኋት።

"ስውነቱ ስንጥቅ አለ" ምን ትነግረኝ ይሆን በሚል።

"መጥተሃል እንዴ! ይቅርታ ውስጥ ስለነበርኩ ነው። ለማንኛውም ተሠርቶልሀል ጠብቀኝ" አለችና ተመልሳ ወደ ውስጥ ገባች። ትንሽ ቆይታ እንድ ቀጠን ብሎ ረዘም ያለ ጠይም ወጣት ጋር መጣች

"ውጤቱን እራሱ ይገልጽልሃል የሠራው እርሱ ነው አለችኝና" ሄደች።

"ሲሳይ አንተ ነህ" አለኝ ።

"አዎን እኔ ነኝ። እንዴት ነው ውጤቱ?" አልኩ ።

"እ... ደጋግሜ ለማየት ሞክሬያለሁ። የብረትም ሆነ የሌላ ማዕድን ክምችት የለውም። ያው ኖርማል የጫካ ዐፈር ነው። ብዙ ካርበንና ናይትሮጂን አለው። ድንጋዮቹም ከቀለጠ ዐለት የሚፈጠረው ኢግኒዮስ ሮክ የምንላቸው ዐይነት ናቸው። እና ይህ ነው የምልህ የተለየ ነገር የለውም" አለኝ።

"እርግጠኛ ነህ ማለቴ ብዙ ብረት ወይም ራዲዮ አክቲቭ ንጥረ ነገር ይኖረዋል ብለን ገምተን ነበር" አልኩት።

"ልትገምቱ ትችላላችሁ። የማረጋግጥልህ ግን ዐፈሩ የተለየ የማዕድን ክምችት ያለው ሳይሆን ለም የጫካ ዐፈር ነው" አለ ፈርጠም ብሎ።

"በለው!" አልኩ ።

"እሺ ይኸውነው ወንድሜ" አለና ወረቀቱን ሰጠኝ።

"በጣም አመሰግናለሁ ስለትብብራችሁ" አልኩና ቀናዋን ልጅም በርቀት አንገቴን ጎንበስ ቀና እያደረኩ ምስጋናዬን ገልጬ ወደ ውጭ ወጣሁ።

የዶ/ር ክርስቶፈር መላምት ዜሮ ገባ ማለት ነው። ዶ/ር ማግዳሊና ትክክል ነበረች ማለት ነው።

"ታዲያ የጂፒኤስ ሞገድ የሚዘጋ፣ የኮምፓስ መርፌን ሲፈልግ የሚያሽከረክር ሲፈልግ የሚያቆም፣ ዶ/ር ማግዳሊና እንዳለችው ዛፍን የሚያንቀሳቅስ፣ ወጣቱን መልካሙን ዛፍ ሥር የሚያስተኛ፣ የእኔን ልብ ደግሞ በፍርሀትና በሽብር የሚንጥ ምን ኃይል ነው?" የሚል የማልመልሰው ጥያቄ ለራሴ አቀረብኩ።

የኢንስቲትዩቱን አጥር በስተውጭ በኩል ተደግፌ በጥልቀት ማሰብ ጀመርኩ። አንዳንድ ነገሮችንም ወደ ኋላ እያስታወስኩ መገጣጠምና ሥዕል መፍጠር ቀጠልኩ።

"ሲጀመር መልአከ ሰላም ለምን በዚያ በኩል እንዳናልፍ ጠየቁ?"

መልካሙ "የሆኑ መነኩሴ በበትር ትክሻዬን ሲነኩኝ ወደቅሁኝ" ያለው ደግሞ ትዝ አለኝ እውነቱን ከሆነ ለምን በአካባቢው አላየኋቸውም?

አባ መዝገበ ሥላሴ ደግሞ "ብቻዬን ነኝ ማለት አይደለም" ያሉት ደግሞ መጣ። ብቻቸውን ካልሆኑ ታዲያ እነማን አብረዋቸው እየኖሩ ነው?

ከእረኞቹ መካከል "ደጐቹ" ያለው ልጅ ደግሞ ትዝ አለኝ። "በቤተ ክርስቲያን ደጎች የሚባሉት እነማን ናቸው? ውስጥ ካሉስ ያን ያክል ስንዳክር እንዴት ሳናያቸው ቀረን? አይታዩም ማለት ነው? ሰው ሆነው እንዴት ነው የማይታዩት? አቅጣጫችንን ያሳተን የተፈጥሮ የብረት ክምችት ወይም ሌላ ማዕድን ካልሆነ የእነርሱ ኃይል ነው ማለት ነው?"

"ለመሆኑ እውነት እዚያ ደን ውስጥ የሆነ ግዘፍ የነሣ አካል ካለ

ለምን አይታይም?" አልኩና ደጋግሜ ባስብም ጣቢ የሚልልኝ ፍንጭ አጣሁ።

የእኔ ሙያና የሳይንስ ግንዛቤ ብዙ ርቀት ሊወስደኝ እንደሚይችል ተረዳሁ። እናም አሁንም በጥልቀት ሳስብ ስለ መከሰትና አለመታየት (visbility/invisiblity) የመሣሉትን በአጠቃላይ የሥነ ዕይታ (የኦፕቲክስ) ዕውቀት ያለው የማውቀው የፊዚክስ ባለሙያ ለማስታወስ ሞከርኩ።

"እንዴ!" አልኩ። ኖርዌይ ከሚገኝ ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዲግሪውን እየሠራ ያለና በቅርቡ የጥናት ሥራውን ለመሥራት መጥቶ ያገኘሁትና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጓደኛዬ የሆነው እምሩ ትዝ አለኝ። በአጋጣሚ ስልክ ተለዋውጠን ስለነበረ ተንቀሳቃሽ ስልኩ ላይ ደወልኩ። ስልኩን አንስቶ "ሀሎ" ሲለኝ በለስ እንደቀናኝ ታወቀኝና በደስታ፡-

"ታዲያስ ራስ እምሩ እንዴት ነህ? ሲሳይ ነኝ" አልኩት። ሁሌም ስንጠራው ራስ እምሩ እያልን ነው።

"እረ ሲስ፡ ዛሬ ከየት ተገኘህ? እንዴት ነህ?" አለኝ። የሞቀ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ፡-

"እባክህ ላስቸግርህ ነው። አንድ ጉዳይ ላይ ሙያዊ ማብራሪያ እንድትሰጠኝ ፊልጌ ነበር?" አልኩት።

"የኢኮሎጂ ሰዎች ደግሞ ከፊዚክስ የሚፈልጉት ነገር ምን ተገኘ?" አለኝ ።

"ኢኮሎጂ እኮ የብዙ ሳይንስ ዘርፍ ጥርቅም ነው" አልኩት ።

"ይሆናል። ለማንኛውም የኮንሰልታንሲ ክፍያ ይኖራል" አለና ቀለደ።

ግለጽርሱ አታስብ ከቫት በፊት የኮንደሚኒየም መግዣ እከፍልሃለሁ"
አልኩት።

ስንሣሣቅ ቆይተን ከቀኑ ዐሥር ሰዓት ላይ አራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲው በሩ ላይ እንደሚጠብቀኝ ተቀጣጥረን ተለያየን። ቀጠሮ አክባሪ እንደሆነ ስለማውቅ ዐሥር ደቂቃ ቀደም ብዬ አራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲው በር ላይ ቆሜ ጠበኩት። ካሪና-ኢ መኪናውን ይዞ ከተፍ አለ። መኪና ውስጥ ገብቼ አብረን ወደ ቢሮው ዘለቅን። ከቢሮው እንደገባን፡-

"ብፒኤችዲ ፕሮጀክቴ ላቦራቶሪ እያደራጀሁ ነው። መጀመሪያ ባስጐበኝህ?" አለኝ። ተከትዬው ወደ አንድ ሰፊ ክፍል ገባሁ። በአውሮፓና አሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ያየኋቸው አንዳንድ መሣሪያዎች ሳይቀሩ ተደርድረዋል።

"ዋው በጣም ደስ ይላል። ግን እንዲያው መሬት ጠብ የሚል ገጠር ቤት የሚገባ የሳይንስ መላ ምናለ ብታመጡ?" አልኩት።

ሣቅ አለና "አንድ ጓደኛዬ ምን አለ መሰለህ?"

"ሳይንስ ባለ ክንፍና እግር ሆና አውሮፓ ተወልዳ፣ አሜሪካ አደገች። ወደ አፍሪካና ኢትዮጵያ ስትመጣ ግን እግሯን ጥላ ክንፎቿን ብቻ ይዛ ስለመጣች ይኸው መሬት ሳትነካ አየር ላይ ስትንሳፈፍ ትኖራለች" አለ ።

"ትክክል ብሏል" አልኩት እየሣቅኩ ።

እንዲህ እየተተራረብን ላቦራቶሪውን ጎብኝቼ ስጨርስ፡-

"በእውነት በጣም ትልቅ ጥረት ነው። ተማሪዎቻችሁን ብዙ የሚያግዝ ይመስለኛል" አልኩት።

"አዎን ለመምህራንም ብዙ ነገር ያቀላል። እያሳየህ ማስተማርና

ገም ብሎ በቲዎሪ መናገር ብዙ ልዩነት አለው" አለኝ።

ተያይዘን ከቢሮው ግባንና ወንበር ስቤ ቁጭ ስል እሱ ደግሞ ባሩን ዘግቶ ከፊት ለፊቴ ቁጭ አለ።

"ምንድን ነው እንዳብራራልህ የፈለከው?" አለኝ። በአጠቃላይ አጠር አድርጌ የገመገኝን ገለጽኩለትና ይሆናል ብለን የገመትነው መላምትም አለመሥራቱን የዐፈርና ድንጋይ ምርመራውን ውጤት ገልጬ ነገርኩትና፡-

"እኛ የማናያቸው ነገር ግን እነርሱ ሊያዩን የሚችሉ ሰዎች ወይም ሌላ ግዙፍ የነሱ አካላት ሊኖሩ የሚችሉበት አጋጣሚ ይኖራል ወይ? ካለስ ከሳይንስ አንጻር እንዴት ይገለጻል?" የሚል ጥያቄ አቀረብኩ።

ትንሽ እንደማሰብና ፈገግ እንደማለት ብሎ፡-

"በዚህ ዓለም የማየትና የመታየት ነገር የሚከናወነው በብረሃን ጨረር አማካኝነት ነው። በአንድ ግዙፍ የነሣ ነገር ላይ የብርሃን ጨረር ሲያርፍና ሲንፀባረቅ በሚፈጠር ኩነት ነው። እንደምታውቀው የብርሃን ጨረር የሰባት ቀለማት ውሕድ ሲሆን ይህ ጨረር ግዙፍ የነሣ አካል ላይ ሲያርፍ የዚያን አካል ቀለም የያዘ ነፀብራቅ ይፈጠራል ቀሪውን ደግሞ ውጦ ያስቀረዋል።

አካሉ ሁሉንም የቀለም ዐይነቶች በአንድ ጊዜ ካንፀባረቀ አካሉ ነጭ ሆኖ ይታየናል። አረንጓዴ ቀለም ያለው ደግሞ አረንጓዴውን የብርሃን ክፋይ ብቻ ለይቶ ያንፀባርቃል። እንደዚህ እያለ ሙሉ በሙሉ ከማንፀባረቅ ጀምሮ እስከ ሙሉ በሙሉ ውጦ ማስቀረት ይሄዳል። ሙሉ ለሙሉ ውጦ የሚያስቀር አካል ጥቁር መልክ ያለው ሆኖ ይታየናል (በሳይንስ አገላለጽ ቀለም አልባ ይባላል)። ለማንኛውም አንድን ግዙፍ የነሣ አካል በሰው ዐይን ለማየት በመጀመሪያ ብርሃን ያስፈልጋል፡ ቀጥሎ ብርሃኑ ግዙፍ የነሣው

አካል ላይ ማረፍና መንፀባረቅ ወይም መዋጥ (Reflected or Absorbed) ይኖርበታል።" አለ የሁለት እጆቹን ጣቶች ከመሰለቻቸው ጋር በማገናኘት እያወዛወዘ።

"ይሁንና አንዳንድ ጊዜ ብርሃንም ኖሮ ግዘፍ የነሣው አካል የብርሃን ጨረር እንዳያርፍበት ሊያደርግ የሚችል ኃይል ወይም ሁኔታ ሊኖር ይችላል። በዚህ ጊዜ መሰወር ወይም በእንግሊዘኛ ክሎኪንግ (Cloaking) ይፈጠራል። በሌላ አጋጣሚ ደግሞ ግዘፍ የነሣው አካል ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ጨረሩን በመዋጥ ወይም በማንጸባረቅ ፋንታ ሙሉ በሙሉ ጨረሩን የማሳለፍ (Transparent) ባሕርይ ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ በጣም ንጹሕ የሆነ የግድግዳ ወይም የመስኮት መስታዎት የብርሃን ጨረርን ሙሉ በሙሉ ያሳልፋል። በዚህ ጊዜም አለመታየት (Invisibility) ሊከሰት ይችላል። አንዳንዴ ከንጹሕ መስታዎት በር ጋር የምንጋጨው በዚህ ምክንያት ነው" ብሎ በረጅሙ ሲተነፍስ።

"የብርሃን ጨረር እንዳያርፍበት ማድረግ የሚያስችል ኃይል ወይም ዘዴ ወይም ሁኔታ (Defelecting Ability or Cloaking) እንዴት ይፈጠራል ወይስ የሚታወቅ ዘዴ አለ?" ስል ጠየኩ።

"ለጊዜው በቤተ ሙከራ ደረጃ በአደጉት ሀገራት አንዳንድ መሣሪያዎች እንደተፈለሰፉ እሰማለሁ። ከዚህ በተረፈ በቲዮሪ ደረጃ እንጂ በተግባር የማውቀው ነገር የለኝም" አለና። "የሆነው ሆኖ እኛ ያልደረስንበት የጨረርን አቅጣጫ የሚያስት አቅም (Cloaking Power) ያለው ነገር በአካባቢያችን ሊኖር ይችላል። ከዚህ በላይ በተፈጥሮ ሊከሰት የሚችልን ምሥጢር ለማብራራት አቸገራለሁ። አላውቅም ብል ይቀላል" አለኝ።

"ወይ ጣጣ!" አልኩ።

"እ.. ምንአልባት..." ሲል ጆሮዎቼ ቀጥ አሉ።

"ከሰው የማየት ገደብ ውጭ የሆነ ሞገዶችን ሊያሳይ የሚችል የዕይታ መሣሪያ ወይም መነጽር ብታገኝ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የማየት ዕድል ሊኖርህ ይችላል። ምክንያቱም ከሰው ከሆነ መሰወር የፈለጉት የሚጠቀሙት ጥበብ የሰውን የዕይታ ሞገድ ገደብ ግምት ውስጥ አስገብተው ሊሆን ይችላል።ሁለተኛው አመራጭ በብርሃን ጨረር ሳይሆን በድምጽ ሞገድ በሚጠቀም ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ለማየት መሞከርም ይቻላል። ችግሩ ግን እኛ እንደምናስበው የጥበብ ወይም የቴክኒክ ጉዳይ ካልሆነ ግን ልፋትህ ከንቱ ይሆናል" አለኝ

"እንዴት?" አልኩት።

"የተሰወሩት በተዓምራት ከሆነ ሳይንሱ ብዙ መፍትሄ አያመጣልህም ዝም ብለህ ከመቀበል በቀር" አለኝ።

"እንደዚህ ዐይነት ተዓምራት ሊኖሩ ይችላሉ ብለህ ትገምታለህ? ታምናለህ?" አልኩት።

"ቢያንስ ከሳይንስ ውጭና በላይ የሆኑ ጉዳዮችና ምሥጢሮች በዓለም ላይ እንዳሉ አውቃለሁ። በእግዚአብሔርም አምናለሁና አዎን ተዓምራት ሊኖሩ ይችላሉ" አለኝ።

"ግን እንደዚህ ዐይነት መሣሪያ በቅርብ እዴት አገኛለሁ?" አልኩት ።

"በሀገር ውስጥ የሚገኝ አይመስለኝም። ምናልባት ምናልባት ከተገኘም ከደኅንነትና የመከላከያ ተቋማት ነው። ያውም በከፍተኛ ምሥጢር" አለ ተስፋ የሌለው መሆኑን ለመጠቆም ከንፈሩን እየለጠጠ።

ከመጣሁበት ውጭ ያሉ ቤተሰባዊ ጉዳዮችን ስናወራ ቆይተን አመሰግኜው ወደ ማረፊያ ሆቴሌ አመራሁ። ውይይታችንን እንደገና አንድ በአንድ እያነሣሁ እየጣልኩ ማሰላሰል ቀጠልኩ። የሆነ ቦታ

ላይ ጓደኛዬ እምሩ ባላደርገው ሊያጸጽተኝ ወይም እንዲህ ቢሆን ኖሮ ብዬ የምቆጭበት መላምት እንደነገረኝ አቃጨለብኝ።

"ከሰው የማየት ገደብ ውጭ የሆኑ ሞገዶችን ሊያሳይ የሚችል ወይም የድምጽ ሞገድ በመጠቀም ዕይታን የሚያመጣ ማሣሪያ ወይም መነጽር ብታገኝ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የማየት ዕድል ሊኖርህ ይችላል" ያለኝ ነው።

በተለይ ከብርሃን ሞገድ ውጭ የድምጽ ሞገድ በመጠቀም ወደ ዕይታ መቀየር የሚለው አስደሳች ሐሳብ ነው። በተግባር ለሕክምና አግልግሎት የሚውለው አልትራ ሳውንድ የሚባለው መሣሪያ በዚህ መርሕ የተፈለሰፈ ነው። እጅግ የረቀቁ የድምጽ ሞገዶችን በመልቀቅ ተጋጭተው ሲመለሱ የተጋጨበትን አካል ቅርጽ ተከትለው የሞገድ ፍጥነታቸው ይቀየራል። ይህን ልዩነት ኮምፒተሩ ወደ ምስል ይቀይረዋል። በኢኮሎጂ ሙያዬም የሌሊት ወፎች በዚህ መርሕ በድቅድቅ ጨለማ መንቀሳቀስ እንደሚችሉ አውቃለሁ። በእንቅስቃሴአቸው ሁሉ የማያቋርጥ ድምጽ ያወጣሉ። ድምጻቸው በአካባቢው ካለ አካል ጋር ተጋጭቶ የገደል ማሚቶ ሲፈጠር እርቀቱንና ቅርፁን ይረዳሉ። በዚህ መልክ የጨለማ እንስሳት ሁነው ያለምንም ችግር ምግባቸውን አድነው ይመገባሉ።ይህ በርግጥም የሚያጓጓ አማራጭ ነው። ጥበብን በጥበብ የመብለጥ ነገር ነው። ችግሩ እንደዚህ ዐይነት መሣሪያ በሀገር ውስጥ በቀላሉ ማግኘት የማይቻል መሆኑ ነው። ከውጭ ካልሆነ በስተቀር።

ወዲያው ፕሮፌሰር ሃሮልድ ትዝ አሉኝ። በወቅቱ ከአውስትራሊያ ወደ አሜሪካ ሄደው እዛው እንዳሉ ስለማውቅ ለምን አላማክራቸውም አልኩ። ሰዓቴን ሳይ ከምሽቱ 1:00 አካባቢ ነው። ባለን የሰዓት ልዩነት መሠረት አሁን እርሳቸው ካሉበት ኖርዝ ካሮላይና ስቴት ዩኒቨርሲቲ ዘንድ ከቀኑ 6:00 አካባቢ ይሆናል። እናም ቢሮ እንደሚሆኑ ገመትኩና ኮምፒውተሬን ስከፍት skype ላይ አየኋቸው። ዕድለኛ ነኝ መስመር ላይ ናቸው። ጊዜ አላጠፋሁም

ደወልኩና ተገናኘን። ከተለመደው ሰላምታ በኋላ ሳይት እንደሄድኩ ነገርኳቸው።



"Excellent and what did you find?" (ግሩም ነው! እና ምን አገኘህ) አሉኝ በጉጉት ወደ ኮምቲውተሩ ሰክሪን እየተጠጉ።

"ምንም የተጨበጠ ነገር የለም" አልኩና ይባስ ብሎ የኮምፓሴን የአቅጣጫ መርፌ ከመስታውቱ ጋር አጣብቆ እንዳቆመው ነገርኳቸው።

"Incredible" (አስደናቂ ነው!) አሉ ።

"ዶ/ር ክርስቶፈር እንዳሰበው የዐፈርና ድንጋይ ናሙና አምጥቼ እንዳስመረመርኩና ምንም የተለየ የብረት ወይም ሌላ ንጥረ ነገር ከምችት እንዳልተገኘ ነገርኳቸው።"

"ያ ቦታ አንዳች ከባድ ምሥጢር ይኖረዋል አላልኩህም?" አሉ ፈገግ ብለው።

"አዎን ልክ ነኽት። እኔም አግራሞቴና ፍርሀቴ እየጨመረ መጥቷል" አልኳቸው።

"እውነት ነው። ግን መፍራት አያስፈልግም ተመራማሪ አይፈራም" ብለው አደፋፈሩኝና "ታዲያ ምን አሰብክ?" አሉ ቀጥለው።

"ከዚያ ደን ውስጥ እኛ የማናየው ወይም የማናያቸው ሰዎች ወይም ሌላ ፍጥረታት ሊኖሩ ይችላሉ።ከሰው ዕይታ ሊሰወሩ የሚችሉበት ጥበብ ይኖራቸዋል ብዬም ገምቻለሁ። እናም እነርሱን ለማየት አንድ ዕድል አለ" አልኩና ከእምሩ ጋር የተወያየንበትን ነገርኳቸው።

"Interesting! Now we are thinking a classic research" (አንጊ ነው! አሁን መሠረታዊ ምርምር እያሰብን ነው ማለት ነው) አሉ እንደመቀለድ ብለው። ከዚያም

"ታዲያ ምን ልርዳህ?" አሉ።

"እንዲያው የሚቻል ከሆነ ከእናንተ ዩኒቨርሲቲ ወይም ገበያ ላይ ካለ ይህንን መሣሪያ/መነጽር የማገኝበትን መንገድ ቢያመቻቹልኝ ብዬ ነው" አልኳቸው።

"Oh I see" (ገባኝ) አሉና ነጭ ፂማቸውን በግራ እጃቸው እየዳበሱ አንገታቸውን ከፍና ዝቅ እያደረጉ ማዶ ማዶ እያዩ የሆነ ነገር ለማስታወስ ይሞክሩ ጀመር።

"እንድ የፊዚክስ ፕሮፌሰር ጓደኛ አለኝ። በአጋጣሚ የምርምር ሥራው የሚያተኩረው በሥነ-ዕይታ ሳይንስ (Optics) ላይ ነው። እና ከእርሱ ዘንድ አንዳች ነገር አናጣም። ዛሬ ለማግኘት እሞክራለሁ። ስለዚህ ነገ ጠዋት እንገናኝ" አሉ።

"በጣም አመሰግናለሁ! ፕሮፌሰር እጠብቃለሁ" አልኳቸው።

"ምንም አይደለም የጋራ ፍላጐታችን ነው" አሉኝና ተሠነባበትን።

እንዲሁ እንቅልፍ ሳይወስደኝ ስገላበጥ አደርኩና በጠዋት ተነሣሁ። ይሁን እንጂ ፕሮፌሰሩ የቀጠሩኝ በእነርሱ ጠዋት ሲሆን ስለነበር ይህ ማለት ደግሞ በእኛ ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ይሆናል ማለት ነው። ባለኝ ሰፊ ጊዜ ቁጭ ብዬ በሐሳብ ከምናጥ ለምን ተጨማሪ መረጃ አልፈልግም አልኩና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነትና መንበረ ፓትርያርክ ቤተ መጽሐፍት አመራሁ።

ቤተ መጽሐፍቱ ከቤተ መዘክር ጋር ተያይዞ የተሠራ ነው። ጥንታዊቷንና ባለብዙ ቅርስና መጽሐፍት ባለቤት የሆነችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ይመጥናል ባይባልም ማራኪ ግርማ አለው። ያልጠበኩትና የስደነቀኝ ነገር ቢኖር የካቶሊክና የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያን የነገረ መለኮት

ማስተማሪያ መጻሕፍት ሳይቀሩ በሥርዐት በባለመስታውት ሽለፍ ላይ ተደርድረው ማየቴ ነው። ማንበብ የፈለኩት ምንኩስናና ምናኔ እንዲሁም የገዳማዊ ሕይወትን በተመለከተ የተጻፉ መጽሐፍትን ነው። በዐማርኛ ተጽፈው ከተደረደሩት መጽሐፍት መካከል ከምፈልገው ጉዳይ ጋር ተቀራራቢ ርእስ ያላቸውን ሦስት መጽሐፍት መርጬ ጥግ ላይ ከሚገኝ ማንበቢያ ጠረንጴዛ ላይ ተቀመጥኩ።

በተለይ አንደኛው መጽሐፍ እኔ የምፈልገውን ጉዳይ በዝርዝርና በስፋት ይዟል። ጠቅለል ብሎ ሲቀርብ፡-

"የእግዚአብሔር ወዳጆች ቅዱሳን በአንድ ጊዜ የፍጹምነትና የቅድስና ደረጃ ላይ አይደርሱም። ይልቁንም የተወለደ ሕፃን ቀስ በቀስ ከመዳህ ወደ መቆም፣ ከመቆም ወደ መራመድ፣ ከዚያም ወደ መሮጥና መዝለል እንደሚሸጋገር ሁሉ ቅዱሳንም ከወጣኒነት ጀምረው በጸጋ እግዚአብሔር እያደጉ ወደ ፍጹምነት ይደርሳሉ። በዚህ መሠረት ቅዱሳን ደረጃ በደረጃ የሚደርሱባቸው ዐሥር መዓርጋት አሉ። እነዚህም ሦስቱ በንጽሐ ሥጋ የሚገኙ፣ አራቱ በንጽሐ ነፍስ፣ ሦስቱ ዶግሞ በንጽሐ ልቡና የሚገኙ ናቸው" ይልና በዝርዝር እንደሚከተለው ይገልጻቸዋል፡-

"በንጽሐ ሥጋ የሚገኙት ሦስቱ መዓርጋት፡-

> ጽማዌ፡- ዝም ጸጥ ማለት፣ መናገርና መቀባጠርን መተው ማለት ነው። ሙሉ ሐሳባቸውን ወደ ፈጣሪያቸው ለማድረግ ሥራውንም ለማዘከር ይችሉ ዘንድ የዚህን ዓለም ጣጣ ከማሰብና ከማውራት መላ ሕዋሳታቸውን ይከለክሉታል።
>
> ልባዌ፡- ልብ ማድረግ፣ ማስተዋል፣ በጥልቀት ነገሮችን መረዳት ማለት ነው።

ጣዕመ ዝማሬ፡- ሳይሰለቹና ሳይቸኩሉ ምሥጢርና ትርጓሜውን እያወጡና እያወረዱ በንቁ ጎሊና ማመስገንና መጸለይ ነው።

በንጽሐ ነፍስ የሚገኙ አራቱ መዓርጋት ፡-

አንብዕ፡- እንባን ከዐይናቸው እንደ ሰን ውኃ ሳያቋርጥ ማፍሰስ ነው። ይህም ማለት ሰውነታቸው በሐዘን ሳይከፋ በሥጋዊ ሐሴትም ሳይሞላ ሳይሰቀቁ ከዐይናቸው የሚያፈልቁት እንደ ሰን ውኃ የሚፈስ እንደ ነሐሴ ዝናብ የሚመነጭ ከአርምሞና ከተደሞ የሚመጣ ነው።

ኩነኔ፡- በመዓርጋት ሂደት ኩነኔ ማለት ሥጋን ለነፍስ ማስገዛት ማለት ነው። ቅዱሳን ከኩነኔ መዓርግ ላይ ሲደርሱ ፈቃደ ሥጋቸው ፈጽሞ ለነፍሳቸው ይገዛል። ሥጋ የነፍስ መሣሪያ ይሆናል። ነፍስ ሥጋን የወደደችውን ታሠራለች። መስገድ፣ መጸም፣ መጸለይ ሁሉ ቀላልና ጠባያዊ እስኪሆኑ ይደርሳሉ።

ፍቅር፡- እግዚአብሔር ከመፍጠር ያልናቀውን ፍጥረት ሁሉንም አስተካክሎ መውደድ ማለት ነው። ጎጥና ጻድቅ፣ አማኒና መናፍቅ እንዲሁም ወዳጅና ጠላት ብሎ መለያየት ሳይኖር ማንኛውንም ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል በክብር የተፈጠረ ስለ ሆነ ብቻ መውደድ ነው።

ሐሴት፡- ካሉበት ቦታ ሆኖ ካሰቡት መድረስ ነው። ይኸውም ከአንድ ቦታ ሆነው እንደ እግረ ፀሐይ ካሰቡት ቦታ ይደርሳሉ በሌላው ቦታ የሚሠራውን ያውቃሉ። ለምሳሌ ነቢዩ ኤልሳዕ በኢየሩሳሌም ሆኖ የሶርያው ንጉስ ወልደ አዴር እልፍኙን ዘግቶ ከባለሟሎቹ ጋር የመከረውን ምክር ማንም ሰው ሳይነግረው ያውቅበት ነበር ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደሰፈረው ማለት ነው።

በንጽሐ ልቡና የሚገኙ ሦስቱ መዓርጋት ደግሞ፡-

ንፃሬ መላእክት፡- በዓዐደ ሥጋ ሆነው መላእክ
በየከተማቸውና በየቦታቸው ያያሉ። በሦስቱ ዓለ
መላእክት በኢዮር፣ በራማና በኤረር ያሉ ቅዱ
መላእክትን በየነገዳቸውና በየአለቃቸው እንዲሁም በየከፍ
ቦታቸው ሆነው "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ" እያሉ ፈጣሪያቸው
ሲያመሰግኑ ያያሉ።

ተሰጥሞ ብርሃን፡- ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር የባሕርያ
ገንዘብ በሆነው በሚያስደንቀው ብርሃን ውስጥ መዋኘት
ነው። ይህም እነርሱ በዚህ ብርሃን ውስጥ እያሉ ሌላ ለዚህ
መዓርግ ያልበቃ ሊያየው የማይችለው ብርሃን ነው። ጨለማ
የማይሰለጥንበት አንደዚህ ዓለም ብርሃን የማያቃጥል፣
ጨረሩ ዐይን የማይበዘብዝ፣ ነፍስን ከሥጋ መለየት
የሚያስችል ደስታ እስኪሰማ ድረስ ግሩም መዐዛ ያለው
ነው።

ከዊነ እሳት፡- የመጨረሻው መዓርግ ሲሆን እዚህ ደረጃ
የደረሱ ቅዱሳን ሰውነታቸው ለእጋንንት የሚያቃጥልና
የማይቀረብ ይሆናል።

እነዚህን አጠቃለው የያዙ የልብ ንጽሕናን ገንዘብ አድርገዋልና
ለነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ ይበቃሉ። ልበ ንጹሓን ብፁዓን ናቸው
እግዚአብሔርን ያዩታልና ተብሎ እንደተጻፈ" ብሎ በእያንዳንዱ
መዓርግ ሥር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እየተቀመጠ ሰፊ ማብራሪያ
ተጽፏል።

በተለይ ተሰጥሞ ብርሃን የሚለው መዓርግ እኔ ከገጠመኝ ጋር
የሚመሳሰል በመሆኑ በእጅጉ ተፈተንኩ።

ከላይ ያነበብኳቸውን ታሪኮች ከልጅነቴ ጀምሮ በቤተክርስቲያን

አካባቢ እየሰማሁ ያደኳቸው ናቸው። ስለምንኩስና፣ ስለበቁ አባቶችና እናቶች፣ ስለተሰውሩ ቅዱሳን ብዙ ሰምቻለሁ። እንዲያውም ‹አረጊት ኪዳነ ምሕረት› በምትባል ጥንታዊጽ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ‹ደንችና ስውራን› አንደሚኖሩ፣ ጠበል በዕቃ ተደርጎ ጸሎት ሲደረግበት እንደሚፈላ እናቱ በልጅነቱ እንደነገረችው የቅርብ ጓደኛዬ እንዳጫወተኝ ሁሉ አስታውሳለሁ። አስገራሚው ነገር ግን ስሰማው ኖርኩ እንጂ ድርጊቱ ሲፈጸም ወይም ተፈጽሞ ሲገኝ ለመቀበል የሚችል እምነት ግን እንዳልነበረኝ የተረዳሁት ግን በዚህ ወቅት ነው።

የቤተ ክርስቲያኗን አስተምህሮ እቀበላለሁ። እንደ አስተምህሮዋም አምናለሁ ብዬ አስባለሁ። ለቤተ ክርስቲያኗም ፍቅርና አክብሮት ያለኝ ይመስለኛል። አሁን ግን “ዝርዝር ነገር ሲመጣ እንዴት ሊሆን ይችላል?” የሚለው ጥያቄ በውስጤ ድንገት እንደ እንጉዳይ በቀለ። የሒሳብ ባለሙያዎች “ሰይጣኑ ያለው ከዝርዝሩ ነው” የሚሉት ታወሰኝና ፈገግ አልኩ።

“ወይ ጉድ! ሰው ለካ እራሱን ሙሉ ለሙሉ ለማወቅ ብዙ ጊዜ ይፈጅበታል ማለት ነው” አልኩና “የማከብራትን ቤተ ክርስቲያን አስትምህሮዋን ሙሉ በሙሉ መቀበል የማልችል ከሆነ ታዲያ እኔ ምን ዐይነት አማኝ ነኝ ማለት ነው?” አልኩና ለራሴ ጠየኩ።

“በከፊል የሚያምን መናፍቅ ይባላል” አለኝ ሌላኛው አእምሮዬ

“በስመ አብ ... መናፍቅ እንኳን አይደለሁም። በቃ ደካማ አማኝ ነኝ” ብዬ ለራሴ የተሻለ የመሰለኝን ስያሜ ሰጠሁት።

“ልዩነቱ ምንድን ነው?” አለኝ አሁንም ሌላኛው የአእምሮዬ ክፍል።

“መናፍቅ አውቆ የሚያጣምምና ለክሕደቱ ምክንያት የሚፈልግ ሲሆን ደካማ አማኝ ግን ምክንያት የሌለው ማመን አለመቻል ብቻ ነው።” አለ መልስ ሰጪ የአእምሮዬ ክፍል በተራው።

"እስኪ ይሁንልህ!" አልኩና ለራሴ የሚከተሉትን ስንኞች ቋጠርኩ፡

አንድ የማላውቀው ሰው አብሮኝ እየኖረ፣

ስበላ እየበላ ስተኛ እሚተኛ ከእኔ የሰመረ፣

ማንነቱን ላውቀው በብዙ ተግቼ፣

ከደብር ከገዳም ሱባኤ ገብቼ፣

ምሥጢሩ ተገልጾ እሱነቱን ሳውቀው፣

የኔው የራሴ ገጽ የራሴ ሰብእና ሆነና አረፈው።

ያም ሆኖ ከመጻሕፍቱ ያገኘሁትና በመስክ ያጋጠመኝ ነገሮች ተዳምረው ዐለታማውን ልቤን ሊያላሉት አልቻሉም። እናም ልቤ ወደ ሳይንሱ አደላና ፕሮፌሰር ሃሮልድ ትዝ አሉኝ።

ቤተ መጻሕፍቱ ውስጥ በተቀመጥኩበት ሳላውቀው ከቀኑ 6:20 ሆኗል። መጻሕፍቱን ከአገኘሁበት ቦታ መልሼ ወደ አረፍኩበት ሆቴል አመራሁ። የምግብ ፍላጐት ስላለነበረኝ ምሳ እንደነገሩ ቀማምሼ ኮምፒውተሩን አስነስቼ መሥመር ላይ መጠበቅ ጀመርኩ። ሠላሳ ደቂቃ ያህክል እንደጠበኩ ፕ/ር ሃሮልድ ወደ በይነ መረብ መግባታቸውንና መሥመር ላይ መሆናቸውን የሚያመለክተው አረንጓዴ መብራት በስማቸው ትይዩ ኮምፒውተሬ ላይ ሲበራ ተመለከትኩ።

የልቤ ምቱ ጨመረ። ከደቂቃዎች በኋላ የቪዲዮ ጥሪ ኮምፒውተሬ ላይ ተሰማ። አንጋፋው ፕሮፌሰር ስክሪኑ ላይ የጆሮ ማዳማጫቸውን ሰክተው ገጭ አሉ። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ፡-

"ዕደለኛ ነህ። ጓደኛዬ ሊረዳን ዝግጁ ነው" አሉ።

"እውነትዎትን ነው? እንዴት?"

"የገለጽከውን ዐይነት ኦፕቲካል መሣሪያ አለው ።"

"ግሩም! እናስ?"

"እናማ መሣሪያውን በእኔ ኃላፊነት ሊያውሰን ፈቃደኛ ሆኗል።"

"በጣም ግሩም" አልኩና ደስታዬን ተቆጣጥሬ፡-

"ታዲያ እንዴት ላገኘው እችላለሁ?" አልኳቸው።

"እሱንም ጉዳይ አስቤበታለሁ። በፖስታ ቤት በኩል መላክ የማይታሰብ ነው" አሉ።

"እና ምን ይሻላል?" አልኩ ወዲያው ደስታዬ ቀዝቅዞ ፈንቀት ተላብሼ።

"የእኔም የጓደኛዬም ጓደኛ የሆነ ፕሮፌሰር ለዕረፍት ወደ ኢትዮጵያ ይመጣል። የሚቆየው ለዐሥር ቀናት ብቻ ነው። እርሱ ያመጣልሀና በፍጥነት ቦታው ወስደህ ሥራህን ጨርሰህ ትመልስለትና እሱ ይዞልን ይመጣል" አሉ ።

"ዋው! ፕሮፌሰር በጣም በጣም አመሰግናለሁ። ሌላ ምን ማለት እችላለሁ" አልኩ ።

"ምንም አይደለም። ብቻ ውድ መሣሪያ ስለሆነ በጥንቃቄ እንድትይዘው። እንደደረሰህ በskype ተገናኝተን ጓደኛዬ አጠቃቀሙን ያብራራልሃል" አሉኝ ።

"ለጥንቃቄው አያስቡ መሣሪያው ምን ያክል ውድ ሊሆን እንደሚችል እረዳለሁና" አልኳቸውና፡-

"ታዲያ ጓደኞችሁ ወደ ኢትዮጵያ መቼ ሊመጡ አስበዋል?"

"በሚቀጥሉት ዐሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ይመጣል" አሉኝ ።

በመጨረሻ ቱሪስቱ ፕሮፌሰር ሲመጡ ደውለው እንዲያገኙኝ ስልክ ቁጥር ሰጥቼ ኮምፒውተሩን ዘጋሁ። ሳላስበው ክፍሌ ውስጥ በድል ስሜት አንድ ሁለቴ ዘለልኩ።

በማግስቱ ወደ ባሕር ዳር ተመለስኩና ለዶ/ር ክብረ በዓል ስለሁኔታው ላማክረው ወሰኜ ቀጠሮ አስያዝኩት። ሁሌም ከበድ ያሉና ሙያዊ ጉዳዮች ሲያጋጥሙኝ የማማክረው ሰው ሳስብ በቅድሚያ የሚመጣልኝ ዶ/ር ክብረ በዓል ነው" አልኩት።

"እሺ... እባክህ ቀጥል" አለ ሺፈራው። መቼም አትኩሮቱ ዘላለለም እንዲያወሩ ይገፋፋል። በልቤ ደግሞ "ዛሬ ይኼ ሰው ለእንደዚህ ዐይነት ታሪክ ይህን ሁሉ ትዕግስትና አትኩሮት ከየት አመጣው" እያለኩ እገረማለሁ።

"ጣና ሆቴል› ውስጥ በጣና ሐይቅ ዳርቻ በሚገኘው መናፈሻ በቀጠሮችን መሠረት ከቀኑ ዐሥር ሰዓት ላይ ከዶ/ር ክብረ በዓል ጋር ተገናኘን።

"እሺ ወንድም ሲሳይ እንዴት ነህ?" አለኝ።

"ደኅና ነኝ ማለት እንኳን አልችልም። አንድ የሚያስጨንቀኝ ጉዳይ ገጥሞኛል" አልኩት።

ከሙያ ብስለቱ በተጨማሪ ዶ/ር ክብረ በዓል በእኔ መለኪያ ከፍ ያለ የሞራል ሰው ነው ብዬ ስለማምን ልሠራ ያሰብኩት ነገር ተገቢ መሆኑን ላማክረው ስለፈለኩ ነው የዛሬው ቀጠሮአችን።

እንደተለመደው በእርጋታ "ምን የሚያስጨንቅ ነገር ገጠመህ?" አለኝ ።

ከመጀመሪያው ጀምሮ ከምርምር ባልደረቦቼ ጋር የገጠመንንና እኔም ብቻዬን የሞከርኩትን አሁን ደግሞ ላደርግ ያሰብኩትን ከዘረዘርኩለት በኋላ፡-

"እንዲያው ዘመናዊ መሣሪያ ተጠቅሞ አንድ ለዘመናት ተከብሮና ተፈርቶ የኖረን የአንድ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን አጸድ ምሥጢር ለማወቅ መሞከር ከሞራል አንጻር እንዴት ታየዋለህ ብዬ ነው?" አልኩት ።

በዝምታ ሩቅ እያየ ከቆዬ በኋላ፡-

"ምሥጢሩን ሳታውቀው ቢቀርብህስ?" አለኝ

"ዶ/ር ክብረ በዓል እሱ እንኳን የማይታሰብ ነው። ባሰብኩት ቁጥር ፍርሀት የሚያርደኝ ቢሆንም ምሥጢሩን ሳላውቀው ለመቅረት ግን የምችል አይመስለኝም። እንዲያውም አሁን አሁን ስለ እርሱ አለማሰብ ተስኖኛል። በዚያ ላይ ለማከብራቸው ሰው ቃል ገብቻለሁ" አልኩት።

"እኔ እምልህ! እስከአሁን የተጠቀማችኋቸው መሣሪያዎች ካልሠሩ ይኼ አሁን የምትጠብቀው መሣሪያስ ለመሥራቱ ምን ያክል እርግጠኛ ነህ?" አለ ፊገግ ብሎ፡-

"ይኼ እንኳን በብዙ ምክንያቶች ውጤታማ ሊያደርገኝ ይችላል። መሣሪያው የሚረዳኝ አለመታየትን ወደ መታየት በማምጣት ነውና። ስለዚህ ማንኛውም ድርጊት በስውርም ቢሆን ሲከናወን ማየት እችላለሁና" አልኩት በመተማመን ስሜት።

"እናያለን እስኪ!" አለና "ታዲያ ምኑ ነው ያስጨነቀህ?" አለኝ ።

"ምን መሰለህ! ቦታው የተቀደሰ የሃይማኖት ቦታ ነው። እኔም ክብር የምሰጠው ነው። እና እንዲያው በመሣሪያ ለመፈተሽ መሞከሬ የድፍረት ጎጠአት ይሆን ወይ ብዬ ነው?" አልኩና "እንዲያው

በዚህ የተነሣ መቅሰፍት ይወርድብኝ ይሆን?" አልኩት ፍርሀቴን በግልጽ አውጥቼ።

"መላምትህ ግን ምንድን ነው?" አለኝ ።

"እኔማ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ቤተ መጻሕፍት ካነበብኩትም፣ በአካባቢው ያሉ እረኞችም የነገሩኝ እንዳለ ሆኖ ከልጅነቴ የሰማሁትም ቢሆን እንዲህ ይገጥመኛል ብዬ አስቤ ስለማላውቅ ለማመን ከበደኝ። እናም አንዳች ጥበብ ይኖራል ብዬ ነው" አልኩት።

"አሃ! ማወቅ የፈለከው በሃይማኖቱ ከሚሰጠው ምክንያት ውጪ አንዳች የሆነ የሳይንስ ወይም የፊዚክስ ጥበብ ይሆናል ብለህ የገመትከውን ዕውቀት ነው?" አለ።

"አዎን" አልኩት እንደ ማፈር ብዬ።

በዝምታ ከቆዬ በኋላ፡-

"በመሠረቱ ቦታው የእምነት ቦታ ነው። የሚሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር ኃይል ሆኗል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው ብዬ አላስብም። ይሁንና አንተ ይህንን ማመን አለመቻልህ አያስገርምም። ይህ የጀመርከው ፍለጋም መረዳትንና ዕውቀትን በመሻት እንጂ በክሕደት መንፈስ ለማጥፋትና ለማዋረድ ባለመሆኑ የሞራል ችግር አለው ብዬ አላምንም። ምክንያቱም ስለ እግዚአብሔር ፈጣሪነት፣ መጋቢነትና ሁሉን ቻይነት ወይም ከሃሊነት የሚታወቅበት መንገድ አንዱ በቅንነት የሚሠራ ምርምር በመሆኑ ነው።" አለና ጸሙን ሲያፍተለትል ቆይቶ፡-

"ይሁንና የእምነት ቦታ ነውና ባለማመን መቅረብ ለጊዜው ወደ ብርቱ ቅጣት ያስገባሃል ብዬ ባልገምትም የሆነ ዋጋ ግን ሊያስከፍል ይችላል" አለኝ።

"እርሱን ዋጋ ለመክፈል ልቡናዬ የፈቀደ ይመስለኛል" አልኩት ፈርጠም ብዬ ።

"እንዳንዴም ዋጋው በማመን ይለወጥና መልካም የመሆን ዕድልም ይኖረዋል" አለኝ ።

"እንደ አፍህ ያድርግልኝ" አልኩት። ‹አያ በሬ ሆይ ሣሩን አየህና ገደሉን ሳታይ› እንደተባለው የሚያስከትልብኝን መዘዝ ከቁብ ሳልቆጥር እኔም በድፍረት ልገባበት ልቤን አጨከንኩት።

"እና መቼ ልትሄድ አሰብክ?" አለኝ ።

"መሣሪያው እንደደረሰኝ እሄዳለሁ" አልኩት ።

"እኔም ደብረ ታቦር አካባቢ ሥራ ስላለኝ ስትዘጋጅ ንገረኝና መኪና ከምትከራይ እኔ እሸኝሃለሁ" አለኝ ።

"አ በጣም ጥሩ" አልኩትና በዚሁ ከዶ/ር ክብረ በዓል ጋር ተለያየን።

# ምዕራፍ ዐሥራ ኣምስት

"ከፕሮፌሰር ሃሮልድ ጋር በSkype በተገናኘን በ13ኛው ቀን መጣሪያውን እንደላኩትና ከሁለት ቀናት በኋላ ባሕር ዳር መረከብ እንደምችል ነገሩኝ። ደስታዬ መጠን አልነበረውም። እንዳሉትም በሁለተኛው ቀን ፕሮፌሰር ፓዎል የሚባሉ አሜሪካዊ ካረፉበት ሆቴል ሄጄ እንድቀበላቸው ስልክ ደወሉልኝ። ከዐሥር ቀናት በኋላ እንደሚመለሱና መጣሪያውን መልሶ መውሰድ እንዳለባቸው ስለነገሯቸው አንድ ቀን ቀደም ብዬ እንዳመጣላቸው ተስማምተን መጣሪያውን ተቀብዬ እርሳቸውንም አመሰግኜ ወደ ቢሮዬ በረርኩ።

የሰዓት ልዩነቱን ጠብቄ ወደ ፕሮፌሰር ሃሮልድ በ Skype ደወልኩ። ከሠላሳ ደቂቃ በኋላ ድጋሜ እንድንገናኝ አሳስበውኝ የመጣሪያውን ባለቤት ጓደኛቸውን ፕሮፌሰር ኮሊንን እንደሚያገናኙኝ ተነጋገርን።

ኮሊን የፊዚክስ ፕሮፌሰር ሲሆኑ በተለይ በሥነ-ዕይታ (Optics) ላይ አንጋፋ ተመራማሪ እንደሆኑ ከፕ/ር ሃሮልድ ተረድቻለሁ። በኮምፒውተር ስክሪን ላይ ሲታዩ የሃምሳ ዓመት አካባቢ የሚሆኑ ሙሉ ጸማም ናቸው። የራሳቸው ጸጉር የዐይናቸው ቅንድብ ድረስ

የተደፋ ነው። ትውውቃችንን በግርድፉ ጨርሰን መሣሪያው እንዴት እንደሚሠራ ገለጻቸውን ጀመሩ።

"መሣሪያው በቀይ ሳጥን ውስጥ የተገጠመ ሲሆን በገመድ ከዋናው መሣሪያ ጋር የተያያዘ መነጽር መሣይ አለው። የድምፅ ሞገድ ማሰራጫና መቀበያ አንቴናውን ወደ ላይ መምዘዝ አትርሳ። ቀጥሎ መሣሪያው ጨረር እንዲያመነጭ የምትጨቁን ቀይ ቁልፍ አለች፡ እርሷ ከተጨቆነች ከሴኮንዶች በኋላ አረንጓዴ መብራት ይታያል። ይሄኔ መሣሪያው እየሠራ መሆኑን እወቅ። ከዚያም መነጽሩን ከዐይን ላይ አድርጐ ማቅረቢያና ማራቂያ እጀታውን እያዘዋወሩ ማየት ነው። ይህ መሣሪያ ልዩ የብርሃንና የድምፅ ሞገዶችን በመልቀቅ በተልምዶ በሰው ዐይን የማይታዩ ነገሮችን ማየት የሚስችል በመሆኑ የምትፈልገውን የሚሳይህ ይሆናል። ስለሆነም አንዳንዴ በተለምዶ ከምናውቀውና ከግምት ውጭ የሆኑ አስፈሪ ፍጥረታትን ማዬት ሊጋጥም ስለሚችል የሥነ ልቡና ዝግጅት ማደረግ ተገቢ ነው። በተረፈ አሁን ያለው ባትሪ ስምንት ሰዓት ሊያሠራ ይችላልና በቂ ይመስለኛል። መልካም ዕድል!" አሉኝ።

እኔም ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቅርቤ ተሰነባብተን ከተለያየን በኋላ ወዲያው ለዶ/ር ክብረ በዓል ደወልኩና፡-

"መሣሪያው ስለመጣልኝ እባክህ ነገ መሄድ እንችላለን?" አልኩት። ቀደም ብዬ ስለዚሁ ጉዳይ ስላማከርኩት ለጉዳዩ እንግዳ አልነበረም።

"ኦ እንኳን ደስ አለህ! አንዴ ጠብቀኝ መልሼ እደውላለሁ" አለኝ።

የኪራይ መኪና ስለሆነ የምንጠቀመው እሱኑ ለማረጋገጥ ይሆናል ብዬ መጠበቅ ያዝኩ። ትንሽ ቆይቶ ደወለልኝ። ስልኩን አንስቼ "እንዴት ነው?" አልኩት።

"ወንድም ሲሳይ ነገ መሄድ አንችልም ከነገ ወዲያ ነው" አለኝ።

እኔ ግን ጉጉቴ ስለናረ ዝም ብዬ በማግስቱ ጠዋት ተነሥቼ መሄድ ፈለጌ ነበር። ነገር ግን ያው እኔም መኪና ልከራይ ብል ዞሮ ዞሮ አንድ ቀን መጠበቅ ይኖርብኛል እያልኩ ስልኩን ሳልዘጋው በዝምታ መዋጤን ሲረዳ፡-

"በፍጥነት መሄድ እንደምትፈልግ አላጣሁትም። ለማንኛውም ነገን ብቻ ታገሥ" አለኝ።

ሃያ ኪሎ ሜትር ዐልፎ ስለሆነ የአቅጣጫ መምታታት ችግር አልነበረብንም።

"አቤት ሲሳይ በጣም የምትገርም ሰው ነህ" አለኝ መንገድ ላይ፡-

"እንዴት?" አልኩት።

"ብቻ የምትፈልገው ነገር ሲኖርህ፤ በተለይ የተደበቀህ ወይም ካንተ የተሰወረ ነገር ያለ ሲመስልህ ያንን ለማወቅ ያለህ ጉጉት በጣም ይገርመኛል" አለ።

"አዎን! ብቻ በሽታ ሳይሆን አይቀርም" አልኩት።

"ግን እንደዚህ ጉጉትህ የምትፈልገውን ስታገኝ ወይም ስታውቅ ምን ይሰማኻል?" አለኝ።

"የሚገርምህ ሁልጊዜ ሂደቱ እንጂ ውጤቱን ሳገኝ ብዙ አያስደስተኝም፤ እናም አንዱን ጨርሼ ውጤቱን ሳላጣጥመው ሌላ ወከባ ሌላ መቃተት ውስጥ እገባለሁ" አልኩት።

"የምዕራቡ ዓለም ባህልና አስተሳሰብ በአያሌው የተጫነህ ይመስላል" አለኝ።

"እኔ እንጃ፤ ውስጤ የምዕራባዊነት ወይም የኢትዮጵያዊነት መንፈስና አስተሳሰብ እንዳለብኝ መለየት እቸገራለሁ። የተደበላለቀብኝ ይመስለኛል" አልኩትና።

"እንተስ?" አልኩት።

"እኔ እንኳን ከድብልቅልቅ አስተሳሰብ በጊዜ ወጥቼ ሕይወትን ፈልጌ ወደ አንድ መሥመር እየመጣሁ መሆኔ ይታወቀኛል" አለ።

"የሕይወት ጥግህና ፍልስፍናህ ወደ የትኛው ሆነልህ?" አልኩት።

ይህን ጥያቄ ብዙ ጊዜ ልጠይቀው እፈልግ ስለነበር በአጋጣሚ ስለተነሣልኝ ደስ አለኝና መልሱን በጉጉት ጠበቅሁ።

"እ... አሁን ብዙ ሐሳብና ጉጉት ላይ ነህ። የጀመርከውን እንቆቅልሽ መፍታት ላይ አተኩር። የእኔን ሌላ ጊዜ እነግርሃለሁ" አለኝ።

እንዲህ እየተነጋገርን ለሁለት ሰዓታት ያክል እንደተጓዝን የምፈልግበት ቦታ ለመድረስ እንደተቃረብኩ ተረዳሁና፡-

"እኔ እምልህ ዶ/ር ክብረ በዓል ለምን አብረኸኝ አትሄድም?" አልኩት፡

"ሆ! የሰው ምርምር ሥራ ውሰጥ ዘሎ ይገባል እንዴ? በኋላ የምርምሩ ግኝት ተጋሪ ነኝ ብዬ ብቅ ያልኩ እንደሆነ ይጨንቅሃል" አለኝ።

"አትቀልድ እባክህ! የሆነ የፍርሀት ስሜት እንደገና እየጀመረኝ ነው እና ለምን አንሄድም?" አልኩት።

"የምን ፍርሀት ነው። ተመራማሪ አይደለህም እንዴ? ለማንኛውም ከእኔ ጋር አብረን የምንሄደው ምሥጢሩን ከፈታኸው በኋላ ነው" አለና ልክ ከዋናው መንገድ ተገንጥዬ የምገባበት የቀበሌ መንገድ ላይ ሲደርስ በዚህ ነው አይደል?" አለኝ ።

"አምን እንዴት አወቅህ?" አልኩት ተገርሜ።

"አይ ያው እየደረስኩ ነው ስላልከኝ በግምት ነው" አለና "ምን ያክል ቀን የምትቆይ ይመስልሃል?" አለኝ።

"ምን አውቄ። እኔማ ዛሬ ሞክሬ ከቻልኩ ዛሬውኑ ካለበለዚያ ነገ ጠዋት ነው" አልኩት።

"ለማንኛውም ከዚያም በላይ ብትቆይም እዚሁ አካባቢ እጠብቅሃለሁ። እንዲያውም ብዙ አርሶ አደሮችን የማነጋገር ዕድል አገኛለሁ" አለኝ።

መኪናው መጨረሻ ሊደርስበት ከሚቻለው ቦታ ስንደርስ ኮተቴን
በፊቴም በጀርባዬም የቀረውን በእጄ አንጠልጥዬ ተሰነባብተን
ወደ መንደሩ አመራሁ። መጀመሪያ ማግኘት የፈለኩት የደብሩን
አለቃ መልአከ ሰላምን ነበርና ወደ መኖሪያ ቤታቸው ሄድኩ።
ስጠይቅ ወደ ደብረ ታቦር ለሥራ ጉዳይ መሄዳቸውን ተረዳሁ።
አለመኖራቸውን ስሰማ አልተከፋሁም። እንዲያው በአካባቢው
መቆየት ቢያስፈልገኝ እርሳቸው እስኪመጡ ለመጠበቅ መሆኑን
ለመናገር በቂ ምክንያት ይሆናል ብዬ ደስ አለኝ።

በቀጥታ ወደ ሞገደኛው ደን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ለመውጣት ዳገቱን
ተያያዝኩት። የሚገርመው ልክ ከደኑ ውስጥ ስገባ እንደተለመደው
ልቤ የፍርሀት ከበሮውን ይደልቅ ጀመር። ሌላኛው ስሜቴ ደግሞ
‹አሁን የምሥጢር መፍቻ መሣሪያ ይዘኻል። በአጭር ጊዜ ውስጥ
እንቆቅልሹን ትፈታለህ› እያለ ያደፋፍረኛል። መሣሪያው በቀይ
ሳጥን ውስጥ የተገጠመ በመሆኑ ትኩረት እንዳይስብ በቦርሳዬ
ውስጥ ከትቼ በጀርባዬ አዝየዋለሁ። ዳገቱን ጨርሼ ቤተ ክርስቲያኑ
ስደርስ በቀጥታ ወደ ሰሜኑ በር ሄጄ በግንባሬ ተደፍቼ ተሳለምኩ።

“አምላኬ ሆይ ይቅር በለኝ” አልኩኝ። መልሼ ደግሞ “እንዴ እኔ
እኮ ለማወቅ ነው፡ ምን አጠፋሁና ነው” አልኩና እንደገና፡-

“አምላኬ ሆይ ምሥጢሩን እንዳውቅ እርዳኝ” አልኩ። የተሻለ
ጸሎት ያደረኩ መሰለኝ።

ተነሥቼ ሰሜን ምሥራቅ አቅጣጫ ወዳለው ወደ አባ መዝገበ
ሥላሴ መኖሪያ ሄድኩ። እንደተለመደው በሥራ ተጠምደዋል። ዛሬ
ግን ከከብቶች ቀንድ ዋንጫ መሥራት ሳይሆን ቀጫጭን የዕፅዋት
ለበቅ መሳይ ይዘው በሰንጠ. ቅርፅ እያወጡ ነው። ከእግራቸው ጥግ
በእጅ የምትሽከረከር የዕንጨት ማለስለሻ ሞረድ ተቀምጣለች።
አቀርቅረው መቁጠሪያ እየሠሩ ነው።

"አባ እንዴት ሰነበቱ?" አልኩኝ ወደ እርሳቸው ጎንበስ ብዬ። ቀና ብለው አዩኝና ከአሰተዋሉ በኋላ፡-

"ኸረባኝ! እንዴት ነህ የእኔ ልጅ" አሉኝ በፊገግታ።

ጎንበስ ብዬ ጫማቸውን ልስም ስል ቀልጠፍ ብለው አገጩን ያዙና ጉንጮቼን ሳሙኝ። ከዚያም መሰቀላቸውን አውጥተው አሳለሙኝና፡-

"ዐረፍ በል እስቲ፡ ይኼ ሁላ ጓዝ ምንድን ነው?" አሉ።

"ለሥራ የሚያገለግሉኝ ቁሳቁስ ናቸው" አልኩኝ። በልቤ "የያዝኩትን መሣሪያ ቢያውቁና ለምን እንዳመጣሁት ቢረዱ በያዙት መሰቀል ግንባሬን ብለው ያባርሩኝ ይሆን?" የሚል ፍርሀት ግን ይሰማኛል።

"ኸረ ግሩም! እንዲህ በቶሎ የምትመጣ አልመሰለኝም ነበር" አሉ።

"አዎን እኔም አላሰብኩትም ነበር። ግን ባለፈው ሳልወስደው የቀረሁት መውሰድ የነበረብኝ አንድ ናሙና ነበርና ያው መጣሁ" አልኩ።

"እ.... ይሆናል እንጂ" አሉና ስለለመደባቸው ወደ ሥራቸው አቀረቀሩ።

"ወይ ድብብቆሽ!" አልኩ ለራሴ።

"አባ ባለፈው በተነጋገርነው መሠረት መነጽሩን አምጥቼለዎታለሁ። እንዲያው ምናልባት እይታዎ ቀንሶ ከሆነ ብዬ ከፍ ያለ ቁጥርም አምጥቻለሁ" አልኩና በቦርሳ የተቀመጡትን ሁለቱን መነጽሮች ጠጓቸው። ቀና ብለው ፊገግ አሉና ፡-

"ተባረክ ልጄ ቁምነገረኛ ነህና" አሉና ቦርሳውን ከፍተው አንደኛውን መነጽር ወደ ዐይናቸው አስጠግተው ከጎናቸው የነበረን የተደጐሰ አነስተኛ መጽሐፍ ገልጠው ማንበብ ጀመሩ።

"ደኅና ነው" አሉ።

"እስኪ ሁለተኛውን ደግሞ ይሞክሩት?" አልኳቸው።

የመጀመሪያውን መነጽር በጥንቃቄ ቦርሳው ውስጥ ከትተው ሁለተኛውን አወጡና ዐይናቸው ላይ አድርገው መጽሐፉን ተመለከቱ።

" አሃ! ይሄ ደግሞ በጣም ያጎላል" አሉ።

"አዎን! እንግዲህ የሚመችዎትን ይምረጡ፡ አንደኛው መጠባበቂያ ይሆንዎታል" አልኳቸው።

"ተባረክ ልጄ እንግዲህ እንደልቤ አነባለሁ" አሉ። ደስ እንዳላቸው ፊታቸው ላይ ይታወቃል። ደስ እንዳላቸው ስረዳም ልባቸው ተከፈተልኝ ብዬ እኔም ደስ አለኝ።

መልሼ ግን ለራሴ፡-

"እንኳን ከብርጭቆ የተሠራ ማንበቢያ መነጽር ይቅርና የወጣትነት ዐይን እራሱን በአልማዝ ሳህን አድርገህ ብታቀርብላቸው ከስጦታ የተነሣ የሚፈጠር አዲስ ነገር የለም" አልኩና ከልቤ ደስታ ላይ ውኃ ቸለስኩበት።

"አባታችን፤ ባለቤቴ ደግሞ ይህን ልካልዎታለች። ቡራኬዎ ይድረሰኝ ብላለች" አልኩኝ በአንድ ቦርሳ የያዝኳቸውን ቁሳቁሶች ወደ እርሳቸው እያቀረብኩኝ።

“አይ ልጄ፡ እኔ ይህ ሁሉ ምን ያደርግልኛል? የሚቸግረኝ ነገር የለ። የቸገረኝንማ መነጥሩን ነግሬሃለሁ” አሉ።

“አባታችን ስጦታ ነው። ስጦታን ደግሞ መርቆ መቀበል እንጂ ምን ያደርግልኛል ይባላል?” አልኳቸው በትሕትና።

“አይ ልጄ እንዲያው ያለችግራችሁ ተቸገራችሁ ብዬ ነው እንጂ” አሉና “ተባረኩ ልጆቼ” ብለው የእኔንም የባለቤቴንም የክርስትና ስም ጠይቀውኝ ነግሬያቸው ጸሎት አደረጉና እንደገና መስቀል አሳለሙኝ። ያመጣሁላቸውንም ዕቃ ወደ ፎቁ ወስደው አስቀምጠው ተመለሱና ወደ ሥራቸው አቀረቀሩ ።”

# ምዕራፍ ዐሥራ ሰዳስት

"አባ መዝገበ ሥላሴ ሰው ሲያነጋግሩ ወይም ሲጸልዩ ካልሆነ በስተቀር በሌላ ጊዜ በፍጥነት በሥራቸው ይጠመዳሉ። ታዲያ ለየት የሚያደርጋቸው በሥራ ላይ እያሉ ያለማቋረጥ ያዜማሉ። ብዙ ጊዜ የሚያዜሙት የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ድርሰት የሆነው ሰዓታት የሚባለውን ነው። ሌላ ጊዜ ውዳሴ ማርያምና ሌሎች የማላውቃቸውን የማሕሌት ዜማዎችን ያዜማሉ። ድምጻቸው ቀጠን ያለና የሆነ ጉልበት ያለው ማራኪ ነው።

በደን ግርማ በተከበበው ቤተ ክርስቲያን ከወፎች ዝማሬና ዐልፎ ዐልፎ እንደ ማጀቢያ ከሚደመጠው የጠጣዎች ድምፅ ጋር የአባ ዜማ ልብን ያሸፍታል። በተመስጦ ዝም ብዬ ሳዳምጥ ቆይቼ ድንገት እንደመባነን አልኩና፡-

"አባታችን የመጣሁበትን እረሳሁት እኮ! በስተምዕራብ ልሂድና ናሙና ይገፍ ልምጣ እንጂ" አልኳቸው።

"በል እኮ ሥራ አይደል፤ ሂድ" አሉና ተመልሰው አቀርቅረው ሥራቸውንና ማዜማቸውን ቀጠሉ።

እንደተለመደው ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሄድኩና ጥንታዊውን የድንጋይ ካብ ዘልዬ ወደ ደኑ አንድ ሠላሣ ሜትር አካባቢ ገባ ብዬ በቦርሳ ያነገትኩትን ዘመናዊ የዕይታ መሣሪያ አወጣሁ። ወደ ምሥጢራዊው የሰሜን አቅጣጫ ከመሄዴ በፊት በሰላማዊው የምዕራብ አቅጣጫ መሣሪያውን ለመሞከር ፈለጌ ነው።

ፕሮፌሰር ኮሊን በነገሩኝ መሠረት መሳሪያውን መሬት ላይ አደላድዬ አስቀመጥኩና የድምፅ ሞገድ መልቀቂያና መቀበያውን አንቴና ወደ ላይ መዘገዘኩ፣ የጨረር ማስተላለፊያ የሌንሱን መስኮትም ከፈትኩና የማስነሻ ቁልፉን ተጫንኩ። ቀይ መብራት ሲበራ ልክ የቢምቢ ድምፅ ዐይነት ሲ...ሲ... የሚል ድምፅ ያሰማ ጀመር። የድምፅ ሞገድ እየለቀቀ መሆኑ ነው። ከአንድ ዐሥራ አምስት ሴኮንዶች በኋላ አረንጓዴ መብራት ሲበራ መነጽር መሳዩን ነገር ከዐይኖቼ ላይ አደረኩኝ።

መጀመሪያ ላይ ከተለመደውና ከማውቀው የዛፎች ቅርፅና ቀለም በስተቀር ምንም አዲስ ነገር የለም። ቀስ እያልኩ ማራቂያውንና ማቅረቢያውን እየነካካሁ ስመለከት ግን በራሪ ነፍሳትን ማየት ቻልኩ። መነጽሩን አውልቄ ሳይ አይታዩም። መልሼ ሳደርገው ግን ይታያሉ።

አስደሳች ከመሆናቸው በስተቀር አስፈሪ ወይም አስቀያሚ አልነበሩም። ብቻ ብዙም የሚያስደንቅ ነገር አላየሁም። የሆነ ሆኖ ግን መሣሪያው በትክክል የምፈልገውና የተደበቀውን ምሥጢር ሊገልጽልኝ እንደሚችል ሳስብ ደስታዬ ወሰን አጣ። ትንሽ ቆይቼ ግን፡-

"ማየቱንስ ልይ እሺ፤ ግን በሕይወቴ አደጋ ላለመኖሩስ ምን ዋስትና አለኝ?" አልኩና ፍርሀት መልሶ ወረረኝ።

"በተቀደሰው በዚህ ቦታ ሰዎች ምሕረትን ተስፋ አድርገው ፈጣሪን

ከሚማፀኑበት ስፍራ መቼም መቅሠፍት አይወርድብኝም" አልኩ። መልሶ ጎሊናዬ ደግሞ፡-

"እንዴ ድፍረትህ ገደብ ሲያልፍስ?"

"ድፍረቴ ጉዳት አያመጣ፤ በቃ ተራ ጉጉት ነው" አልኩ በማስተዛዘን። እንዲህ ጎሊናዬን ለሁለት አቧድኜ ሳሚግት ቆየሁና፡-

"ለማንኛውም ከሕደትም ይሁን ጉጉት፣ ድፍረትም ይሁን ስሕተት፣ እንዴ ጀምሬዋለሁ። አሜሪካ ድረስ እንደ ደፋር መሣሪያ አስመጥቼ ሳበቃ አሁን መፍራት ምን ይባላል?" ብዬ መሣሪያውን አንስቼ ወደ ድንጋዩ ካብ ተመለስኩና እንደገና ታጥፌ ወደ ስሜን አቅጣጫ ዞርኩ።

የስሜኑን አቅጣጫ እንደያዝኩ ወደ ፊት ተራመድኩና የዐፈር ናሙና የወሰድኩበት አካባቢ ስደርስ መሣሪያውን አስቀመጥኩ። ትንፋሼን ሰብስቤ በፍጥነት መሣሪያውን ለሥራ ዝግጁ አደረኩ። መጀመሪያ ቀይ መብራት ከዚያ ድምፅ ከዚያ ቀጥሎ አረንጓዴ መብራት ሲበራ የልቤ ምቱ ጨምሮ የሸሚዜ ኪስ ድረስ ብድግ ብድግ ያደርገው ጀመር። እየተንቀጠቀጥኩ መነጽሩን አነሣሁና ፊት ለፊት ለማየት ከዐይኖቼ ላይ አደረኩ።

"ዋው!" አልኩ ሳላስበው። የተባዘተ ጥጥ የሚመስልና በእጅ ቢዳሰሱት እንደ ግድግዳ የሚዳሰስ የመሰለ ጉም/ጭጋግ ደኑን ሞልቶታል። የሚጉለመለመውን ጉም አይቼ ሳልጠግበው፡-

"ግን እንዴት?" አልኩና መነጽሩን አውልቄ በዐይኔ ላይ ምንም የለም። ግራ ተጋባሁና እንደገና መነጽሩን ዐይኔ ላይ አድርጌ ሳይ ደነገጥኩ።

"ለምን?" ድቅድቅ ጨለማ ሆና! በፍጥነት መነጽሩን አውልቄ ወደ መሣሪያው ስመለከት አረንጓዴው መብራት ጠፍቷል።

"አይደረግም!" አልኩና መሣሪያውን ሁሉንም ቁልፎች አጠፋፍቼ እንደገና አስነስቼ ለመሞከር ፈለኩ። የሆነ እልህ የያዘኝ መሰለኝ። እንደተለመደው አንቴናውን መዝዤ የሌንሱን መስኮት ከፍቼ ማስነሻ ቁልፉን ተጫንኩ።

ቀይ መብራት የለ፣ ድምፅ የለ፣ በቃ መሣሪያው ሥራ አቁሟል። መሬት ላይ እንደተንበረከኩ ቀና አልኩና ሁለት እጆቼን ወገቤ ላይ አድርጌ ከንፈሬን ነክሼ ወደ ደኑ አፈጠጥኩ። የገረመኝ ነገር ጭራሽ ፍርሀቴ መጥፋቱ ነው። ድንገት ብድግ አልኩና ወደ ፊት በወኔ ልራመድ ስል... ከኋላዬ ከትከሻዬ ላይ የሆነ ነገር... ነካ አደረገኝ። ዘወር ብዬ ለማየት ስሞክር ሰማይ ምድሩ ዞረብኝና መሬት ላይ ዝልፍልፍ ብዬ ወደቅሁ።

ከቆይታ በኋላ ልክ በሙሉ ዕረፍት ድብን ብሎ ተኝቶ እንደነቃ ሰው ብንን አልኩ። የሥቃይም ሆነ የቅዠት ቆይታ አልነበረም። በቃ ሰላማዊ እንቅልፍ ላይ የቆየሁ ያክል ተሰማኝና ተንጠራርቼ አካባቢዬን ስቃኝ ከአባ መዝገበ ሥላሴ ዕቃ ቤት ከጎናቸው ተጋድሜያለሁ። እርሳቸው ግን አሁንም ከጥዑም ዜማቸው ጋር ሥራቸውን እየሠሩ ነው። የተመካሁበት መሣሪያም ከአነገትኩበት ሻንጣ ጋር ምርኩ ሆኖ ጥግ ላይ ተቀምጧል።

"የፈጣሪ ያለህ!" አልኩ ሳላስበው።

"ነቃህ እንዴ?" አሉ አባ በሙሉ ፈገግታ ወደ እኔ ዘወር ብለው።

"ምንድን ነው የሆንኩት?" አልኳቸው።

"የሆንከውንማ አንተ ታውቃለህ እንጂ ልጄ።"

"እንዴት እርስዎ ዘንድ መጣሁ? ማንስ አመጣኝ?"

ፈገግ ብለው አዩኝና ሥራቸውን ከዜማቸው ጋር ቀጠሉ። "ከማንም ወፈፌ ጋር ምን አዳረቀኝ" ያሉ መሰለኝ።

"ተመስገን! በማስተኛት ማሳለፋቸው ጥሩ ነው። ሌላም ቅጣት ሊኖር ይችል ነበር" አልኩኝ ለራሴ። ከዚህ በኋላ የዚህን ታላቅ ደን ምሥጢር በራሴ ጥበብና ዕውቀት፣ ኃይልና ድፍረት ልመረምረው እንደማልችል አመንኩ። ምሥጢሩን ምሥጢር አድርጌ ትቼው ለመመለስ ግን የሚታሰብ አይሆንም። ለማንኛውም የዚህ ምሥጢር መክፈቻ ቁልፍ ያለው ከአባ መዝገበ ሥላሴ እጅ ብቻ እንደሆነ ተረዳሁ። ቀደም ብዬ እርሳቸውን አለመጠየቄና አለማማከሬ ትልቅ ስሕተት መሆኑ ሲገለጽልኝ የመክፈቻውን ቁልፍ አርቄ እንደቀበርኩት ገባኝና በጣም ተጸጸትኩ።

የሆነው ሆኖ ዐይኔን በጨው አጥቤ ሁሉንም ነገር ግልጽልጽ አድርጌ ነግሬአቸው እርሳቸውን መለማመጥ እንደሚገባኝ አመንኩ። ከተጋደምኩበት ቀና ብዬ ቁጭ አልኩና፡-

"አባ ምን ተዓምርና ምሥጢር ነው ከዚህ ደን ውስጥ ያለው?" አልኳቸው።

"እንዲህ በቀላሉ የምትረዳውና የምትመረምረው ነገር እንዳልሆነ የተረዳህ ይመስለኛል" አሉ።

"አባታችን ስለድፍረቴ ይቅርታ ያድርጉልኝ። ከመጀመሪያው ጀምሮ በሳይንስ አግባብ የምፈታው ተራ የተፈጥሮ ክስተት መስሎኝ ብዙ ሞከርኩ። አሁን ግን ከአቅሜ በላይ እንደሆነ አምኛለሁ" አልኳቸው።

"ከአቅም በላይ የሆኑ ነገሮች ሲያጋጥሙ አምኖ መቀበል ብልኅነት ነው፤ ይሁንና አንተ ግን የዘገየህ ይመስለኛል" አሉ።

"አዎን አባ ከዚህ በኋላ የምሞክረው የሳይንስ መላምት የለኝም። ይሁን እንጂ ምሥጢሩን ሳላውቀው ብቀር ግን ልቡናዬ ሰላም፣ አእምሮዬም ዕረፍት ያጣል" አልኳቸው በልምምጥ መልክ።

"እረዳለሁ። ሁሉም ሰው ምሥጢር የመሰለውን ነገር የማወቅ ጉጉት አለው" አሉ። ሥራቸውን ጨርሰ የማቋረጥ ፍላጐት ያላቸው አይመስልም። ችግሬን የተረዱልኝ መሰለኝና ተስፋ አደረኩ።

"አባ ታዲያ የዚህ ደን ምሥጢር ምንድን ነው?" አልኳቸው።

"ቦታው የተቀደሰ፣ የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ የሆነ የአምልኮ ስፍራ መሆኑን ካመንክ ሌላው ነገር ቢቀርብህ ምን አለ?" አሉ።

"አባታችን ለዚህ የከበረ ምሥጢር ተካፋይ ለመሆን የሚያበቃ እምነትና ንጽሕና እንደሌለኝ አውቃለሁ። ይሁንና እንዲህ በቀላሉ እርግፍ አድርጌ የምተወው አይመስለኝም" አልኩና፡-

ተነሥቼ እግራቸው ሥር ተደፋሁና "አባ በፊጣሪዎት ይሠዎታለሁ ይንገሩኝ" አልኳቸው።

"ኸረ በፊጠረህ ተነሥ፤ ምነው ልጄ ምን አደረኩህ?" አሉ በእጃቸው ጭንቅላቴን ይዘው እንድነሣ እየገፉ።

ተነሣሁና ቁሜ "ለምን ነግረው አያሳርፉኝም" አልኩ በምሬት።

"ልጄ እኔ የቤተ ክርስቲያኑ ዕቃ ቤት ጠባቂ የሆንኩ ተራ መነኩሴ ነኝ። ወደዚህ ምሥጢር ዘልቄ የመናገርና የማስረዳቱ ዕውቀቱም ሥልጣኑም የለኝም" አሉ ፊርጠም ብለው።

"ከመጀመሪያው ጀምሮ ሁሉንም ያውቃሉ። ከወደኩበት አንሥተው ያመጡኝ፣ ምን እንደሆንኩም የሚያውቁ እርስዎ ብቻ ነዎት። ባለመንገርዎም አላዝንብዎትም" አልኳቸው።

እንደተለመደው አቀርቅረው ሥራቸውን ለመጀመር ሲዘጋጁ፡-

"አባ ይወቁት! የዚህን ደን ምሥጢር እስካላወኩ ድረስ ከዚህ ቦታ አልሄድም" አልኳቸውና ተኝቼበት ከነበረው ቦታ ላይ ሄጀ በጀርባዬ ተኛሁ።

"እንዴ ሥራህስ? ኑሮ ትዳርህስ? ልጄ" አሉ ደንገጥ ብለው።

"ብሄድም ሥራውን በአግባቡ ስለማልሠራው፣ ኑሮውንም በሰላም ስለማልኖረው ምንም ለውጥ አያመጣም" አልኳቸው።

"የሀገሬው ሰውም ቢሆን ከዚህ መሰንበትህን የሚፈቅዱ አይመስለኝም" አሉ።

"ከቤተ መንግሥትም ከቤተ ክህነትም እዚህ ደን ውስጥ ምርምር እንዳደርግ ፈቃድ ስላለኝ እርሱ አያሳስበኝም" አልኩና ተገላብጬ በጎኔ እግሬን እጥፍ አድርጌ ተደላድዬ ተኛሁ።

እርሳቸውም ከተለመደው ዜማቸው ጋር ሥራቸውን ቀጠሉ። ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ሥራቸውን አቋርጠው ተነሡና እንደመንጠራራት ብለው የጸሎት መጽሐፋቸውን አንሥተው ወደ ውጭ ወጡና ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ወደ ቤተልሔም ሄዱ። ትንሽ ቆይቼ በቀስታ እርሳቸው ወደ ሄዱበት አቅጣጫ ሄድኩና ምን እንደሚሠሩ ለማየት ሞከርኩ። ከቤተልሔም ጥግ ፊታቸውን ወደ ቤተክርስቲያኑ አዙረው ቆመው ጸሎት በማድረግ ላይ መሆናቸውን ሳይ ቀስ ብዬ ተመለስኩና ከዕቃ ቤቱ በር ላይ ተቀምጬ የዛፎቹን ግርማ ከወፎች ዝማሬ ጋር በተመስጦ መመልከት ያዝኩ።

"ምን ያክል ቀን ነው የምቆየው?" አልኩ ለራሴ። "በቃ ምሥጢሩን መፍታት ካልቻልኩ ለምን ትቼው አልሄድም" ብዬ ሳስብ በፍጹም ልቡናዬ የማይቀበለው መሆኑን ተረዳሁ። "ወይ ፈጣሪዬ" አልኩና በሁለት እጆቼ ራሴን ሸፍኜ ተቀመጥኩ።

ከቆይታ በኋላ የሰው ኮቴ የሰማሁ መሰለኝና ዐይኔን ገልጬ ሳይ አባ ጸሎታቸውን ጨርሰው እየመጡ ነው።

"የእኔ ልጅ እንግዲህ እኔ ዘንድ ላቀርብልህ የምችለው የጣመ የላመ ነገር የለም ያለውን እንሥራና ቅመስ" አሉኝ። እንደ እውነቱ ከሆነ የምግብ ፍላጐቴ ጨርሶ ጠፍቷል።

አባ እሳቱን በደንብ አቀጣጥለው አሮጌ ብረት ድስት ጣዱና እስከ ግማሹ ውኃ ሞሉ። ትንሽ ሲፈላ በርበሬ እና ጨው ጨምረው አማሰሉትና ወደ ላይኛው ክፍላቸው ሂደው የደረቀ እንጀራ / ድርቆሽ/ አመጡ። ውኃው ፈልቶ ሲያጥር ድርቆሹን ጨመሩና ከላዩ ላይ የተደቆሰ ተልባ ነስነስ አድርገው ፍርፍር ሠሩ። ከዚያም ዕድሜ በተጫነው ሰፌድ ገለበጡና እጄን እንድታጠብ ውኃ ሰጡኝ። ጸሎተ ማእድ አድርገው ሲያበቁ፡-

"እንግዲህ ባይጥምህም ብላ። የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ቆሞ የሚሄደው በእህልና ውኃ ነውና" አሉና ትንሽ አንሥተው ቀመሱ። እኔም እጄን ሰድጄ በትንሹ ቀመስኩት። በጣም ይገርማል እጅግ ጣፋጭ ምግብ ነው።

"ምንድን ነው ነገሩ እርቦኛል ማለት ነው? ከቤቴ በቅቤ ወይም በዘይትና በሽንኩርት የሚከሸነው ፍርፍር እንደዚህ የጣመኝ መሆኑን አላስታውስም" አልኩ ለራሴ።

ምሳችንን በዚህ ሁኔታ በልተን የተሠራውን ስላልጨረስነው ለራት አስቀምጠን አባም ወደ ሥራቸው እኔም ወደ ዝምታዬ ተመለስን። ዐሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ አባ ከሥራቸው ተነሡና ሁለት ቢጫ ጀሪካናቸውን ይዘው ውኃ ለመቅዳት ሲዘጋጁ፡-

"አባ የውኃ ምንጩ ያለበትን ቦታ ለምን አያመላክቱኝምና እኔ አልቀዳውም?" አልኳቸው። "ግዴለም የዘወትር ተግባሬ በመሆኑ አይከብደኝም። አንተ ደግሞ እንግዳ ነህ" አሉ ።

"እዚህ ዝም ብዬ ከምቀመጥ ለእኔም መንቀሳቀሻ ይሆነኛል" አልኳቸው።

"ደግ ነው፤ ባይሆን አብረን እንሂድ" አሉ።

ከቤተ ክርስቲያኑ ደን ድንበር በስተሰሜን ምሥራቅ ላይ ከምትፈልቅ ምንጭ እያንዳንዳቸው አምስት አምስት ሊትር በሚይዙ ጀሪካኖች ውኃ ቀድተን ስንጨርስ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ከመመለሳችን በፊት አባ "ካዳገቱ ጥግ ቁጭ ብለህ ቆየኝ፤ መንደር ደርሽ መጣሁ" ብለውኝ ሄዱ።

ምን አልባት የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ መጥተው ከሆነ ወይም ለገበዙ እዚህ መኖሬን ለመንገር ይሆናል ብዬ ገመትኩ። ቢናገሩም ኃላፊነታቸው ስለሆነ ወዲህም ፈቃድ ስላለኝ አላሳሰበኝም። ግምቴ ስሕተት መሆኑን ያወኩት ወደ ዐሥራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ሁለት ልጆች እንጀራና ወጥ ይዘው ሲመጡ ነው። አባ ወደ መንደር የሄዱት ለእኔ የሚሆን ምግብ ከምዕመናን ልጆቻቸው ለመጠየቅ ነበር። በእርሳቸው ግምት የቀኑን ፍርፍር የወደድኩት አልመሰላቸውም።

"አባ ለምን እርስዎም ተቸግረው ሰውም ያስቸግራሉ። እኔ እኮ የቀኑ ምግብ በጣም ጣፍጠኛል" አልኳቸው።

"አይ! የመነኩሴ ምግብ ምኑ ይጥማል ብለህ ነው። ደግሞስ ልጆቼ እኮ ገበሬ ናቸው ምን ይቸግራቸው ብለህ" አሉ።

በዚህ ሁኔታ ማታ እራታችንን እንጀራ በሚጣፍጥ ክክ ወጥ በላን። አመስግነን ስናበቃ አባ ከዕቃ ቤቱ የላይኛው ደርብ ሣር የተጐዘጐዘበት በረንዳ ላይ አንድ አሮጌ ምንጣፍ ዘረጉና እዛ ላይ እንድተኛ አሳዩኝ። የእርሳቸው መኝታ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መግቢያ መንገድና ቤተ ክርስቲያኑን ከሚያሳየው ማእዘን ላይ ነው። ከታች ያለውን ዕቃ ቦታ ካስያዙ በኋላ የዕቃ ቤቱን ቆልፈው ወደ መኝታቸው አመሩ። እኔም ከምንጣፉ ላይ የመኝታ ከረጢቴን

ዘረጋሁ። የፀረ-ተባይ ፍሊት አካባቢውን ከረጨሁ በኋላ ቁጭ ብዬ የሚያደርጉትን ነገር በጥሞና መከታተል ያዝኩ።

አባ እንደኔው መኝታቸውን አረጋግፊው ከአነጠፉ በኋላ ጋቢያቸውን በትእምርተ መስቀል አጣፍተው ለብሰው የዕቃ ቤቱን ግድግዳ ተደግፊው ፊታቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አዙረው ቆመ። ለጸሎት መዘጋጀታቸው ነው። በለሆሳስ ለረጅም ሰዓት ጸሎት ሲያደርሱ ከቆዩ በኋላ መቁጠሪያቸውን አውጥተው በእርጋታ እየቆጠሩ ጸሎታቸውን አሁንም በለሆሳስ ቀጠሉ። ቆይተው ደግሞ በዜማ ይሉት ገቡ። የድምፃቸው ማማር ከእርጋታቸው ጋር ተዳምሮ ‹እኒህ ሰው እንደ ወፍ ለዝማሬ የተፈጠሩ ናቸው› አልኩ። የእርሳቸውን ዜማ መስማት በዚያ ግርማው በሚያስፈራ ጨለማ ልዩ ስሜት ውስጥ ይከታል። ከምሽቱ አራት ሰዓት አካባቢ ጸሎታቸውን ጨርሰው መኝታቸው ላይ ጋደም አሉ። እኔም ለሚታገለኝ እንቅልፍ እጄን ሰጠሁ።

ሌሊት ድንገት ስነቃ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የጎበረት ዜማ ሰማሁ። ሰዓቴን ሳይ ከሌሊቱ 9:30 ሆኗል። ከመኝታቸውጋ ስሄድ አባ መዝገበ ሥላሴ የሉም።

“ወይ የሰው ልጅ ጥንካሬ!” አልኩና በፍጥነት ልብሴን ለባብሼ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሄድኩና በሰሜኑ በር በኩል ገባሁ። ቅድስት ከሚባለው ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን ክፍልና በውጨኛውና ሦስተኛው ክፍል ላይ በምዕራቡ በኩል የሚገኘው ቅኔ ማሕሌት የሚባለው በበርካታ ወንድ መነኮሳት ተሞልቷል።

ሰዓታት የሚባለውን የኢትዮጵያዊውን የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የጸሎት ድርሰት እያስኬዱ ነው። በ14ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ይህ ኢትዮጵያዊ ቅዱስ እንደ ቅዱስ ያሬድ ትምህርት አልገባው ብሎ በሐይቅ እስጢፋኖስ በድንጋይ ወፍጮ ለሰባት ዓመታት እህል እየፈጨ ገዳሙን ካገለገለ በኋላ ወደ ዕውቀትና ጥበብ የመጠቀ ከዐሰራ አራት በላይ (አንዳንድ ሊቃውንት ቁጥሩን እሰከ አርባ

ያደርሱታል) ቅዱሳት መጻሕፍትን የደረሰ ጻድቅ ነው። በተለይ ለዓታት የተባለው የጸሎት ድርሰቱና ዜማው ልዩ ነው። ይህ ድርሰት በጀርመንኛና በእንግሊዝኛ መተርጎሙን አውቃለሁ። ከቤተ ክርስቲያን የጸሎትና የዜማ ክፍሎች በጣም የሚማርከኝ ቢኖር ይኸው ሰዓታት ነው። የዛሬው ሌሊት የምሰማው ጣዕመ ዜማ ግን ቃላት አይገልጹትም። በቃ መካከላቸው ድንግል ማርያም ተቀምጣ እያበረታታቻቸው እነርሱም እያዩአት የሚያዜሙት ይመስላል። እራሴን በእነዚህ መነኮሳት መካከል ሳገኘው ከድንቁርናዬና ከጉድፌ ጋር ተዳምሮ ድንገት እርጎ ላይ ዘው እንዳለ ዝንብ የሆንኩ መሰለኝ።

"ቢሆንም የእኔ ያለቦታዬ መገኘት የእነርሱን ንጽሕና አያጎድፈውም፣ የድንቁርና ዝምታዬም ይህንን ሰማያዊ ዜማ አያደናቅፈውም" አልኩና ከአንድ ጥግ ሄጀ ኩርምት ብዬ ቁጭ አልኩ።

ዜማው አልፎ አልፎ ልቡናዬን ቢያሸፍተውም በአዕምሮዬ ግን፡-

"ይህ ቦታ ደብር እንጂ ገዳም አይደለም። እነዚህ ሁሉ መነኮሳት ከየት መጡ። አካባቢው የአርሶ አደር መኖሪያ እንጂ የአንድነት ገዳም አይደል ታዲያ ከየት መጡ?" እያልኩ በርካታ ጥያቄዎችን ከመላምቶች ጋር መደርደር ያዝኩ።

"ለማንኛውም ጸሎቱ ሲያልቅ ሁሉም ይታወቃል። ከቤተ ክርስቲያኑ ሲወጡ ተከታትዬ ወዴት እንደሚሄዱ፣ አድራሻቸው የት እንደሆነ፣ እነማን እንደሆኑ ሲነጋ በብርሃን እደርስበታለሁ" አልኩና እንደ ዳገት ጅረት ልብን እየሳበ ከሚፈሰው የዜማ ፏፏቴ ራሴን ነከርኩ።

ቃላት ሁልጊዜ የልብን ሐሜትም ሆነ ሐዘን የመግለጽ አቅም የላቸውም። ምናልባት በእያንዳንዱ ሰው አእምሮ ውስጥ ያሉ ቃላት ብዛትና ጥራት ይለያይ ይሆናል። ስለሆነም በእኔ አእምሮ ውስጥ ያሉ ቃላትን ባወጣ ባወርድ የጎብረ ዝማሬውን ጣዕምና የተሰማኝን ሐሜት ሊገልጹልኝ የሚችሉትን አጣሁ።

ምን እንደተፈጠረ ባላውቅም ቁጭ ካልኩበት የነቃሁት ግን አባ መዝገበ ሥላሴ መጥተው በእርጋታ ሲቀሰቅሱኝ ነው። ሁሉ ነገር አልቆ አባ የቤተ ክርስቲያኑን በሮች እየቆላለፉ ነበር። ያ የቅዱሳን ዜማ፣ ያ ጣዕም፣ ነፍሴን ከደመና በላይ ወደ ሰማየ ሰማያት የሚያመጥቃት ሳይሆን እንደ ሕፃን ልጅ አባብሎ እንዳስተኛኝ ሳስብ ድክመቱና ሥጋዊነቴ የተራራ ያክል ገዝፎ ታየኝ። ሌሊት ያየኋቸው መነኮሳት እንዴት እንደመጡ፣ ወዴት እንደሄዱ ሳላያ በእንቅልፍ ሞት ተሸንፌ ያሰብኩትን ሳላሳካ ቀረሁ። እየተደናበርኩ ተነሥቼ ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥቼ ከደረጃው ቁጭ አልኩ። አባ የመጨረሻውን በር በውጭ በኩል ቆልፈው ወደ ዕቃ ቤቱ ሲያመሩ፡-

"አባ" አልኳቸው ከኋላቸው እየተከተልኩ "ሌሊት ያየኋቸው በርካታ መነኮሳት ወዴት ሄዱ" አልኳቸው።

"ወደ ማረፊያቸው ይሆናል እንጂ ልጄ" አሉኝ።

"ወዴት ነው ማረፊያቸው" አልኩ በችኮላ።

"አይ ያንተ ነገር። ቤተ ክርስቲያን የሚመጣውን የሁሉንም ምዕምናንና መነኮሳት ማረፊያ የማውቅ ይመስልሃል?" አሉኝ እየተራመዱ።

"አባታችን ሊነግሩኝ ስላልፈለጉ እንጂ ያውቃሉ። መቼም ይሄ ገዳም አይደል፤ እነዚያ ሁሉ መነኮሳት እዚህ መገኘት በጣም እንግዳ ነገር ነው" አልኳቸው።

"ይሆን ይሆናል" አሉ።

"ይተውት ነገ እንቅልፌን አሸንፌ ሲወጡ ተከታትዬ እነርሱኑ አጠይቃቸዋለሁ" አልኩ አኩርፌ።

"እሱ ማለፊያ ሐሳብ ነው" አሉና ወደ ፎቁ ወጥተው ልብሳቸውን ቀይረው ወደ ምድጃው ሄደው እሳት አያያዙና ውኃ በበራድ ጣዱ። ዕለቱ ሐሙስ በመሆኑ ለእኔ ቁርስ ነገር ለመሥራት ፈልገው እንደሆነ ገምቼ፡-

"አባ ለእኔ ብለው ከሆነ አይድከሙ። አሁን ምንም የምቀምሰው ነገር የለም" አልኩ።

አኩርፌ እንደሆነ ስለገባቸው፡-

"ልጄ የእኔ ሥልጣንና ፈቃድ ባልሆነው ነገር ለምን ትቀየመኛለህ?" አሉ ትክዝ ብለው።

ስሜታዊ መሆኔ ገባኝና እንደምንም ፈገግ ብዬ፡-

"አባ በፍጹም አልቀየመምትም። ተቀይሜም አይደለም። በጠዋት ለምግብ ብዙም ፍላጎት ስሌለኝ ነው በኋላ ከእርስዎ ጋር ቆይቼ እቀምሳለሁ" አልኳቸው።

"በል እንደፈቃድህ" አሉና ትናንት የጀመሩትን የመቁጠሪያ ሥራ ቀጠሉ። እኔም ተጣጥፌ በመተኛቴ የተከማተረውን ጅማቴን ለማፍታታት ፀሐይ ከፈነጠቀችበት ቦታ ሄጀ ተዘረጋሁ።

በዚህ ሁኔታ በሐሳብ ስባዝን ውዬ ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ሲሆን ከአባ ጋር ምሳችንን በላን። ራታችንንም እንዲሁ ከአካባቢው ነዋሪዎች እንደትናንት ሁሉ በሚጣፍጥ የሽሮ ወጥ መጥቶልን በላን። ማታ እንደተለመደው አባ በልዩ ዜማቸው የንዋም ጸሎታቸውን ጀመሩ። እኔ ግን ስትራቴጂ እየቀየስኩ ነበር።

“መቼም እንደትናንቱ ሌሊት ለጸሎት መምጣታቸው አይቀርም። ማድረግ ያለብኝ ከቤተ ክርስቲያኑ ሲወጡ ተከታትዬ በአካባቢው የሚኖሩ መነኮሳት መሆናቸውን ወይንም በዚሁ በደኑ ውስጥ የሚኖሩ ስውራን መሆናቸውን እለያለሁ። ሲወጡ ከሥር ካሥር እየተከተልኩ እስከ መጨረሻው እሄዳለሁ። በርግጥም ስውራን ከሆኑ ከፊቴ በቅፅበት ሲጠፉ ማየት እችላለሁ። በዚህ መሠረት የዚህ ሞገደኛ ደን ምሥጢር ስውራን ቅዱሳን ወይም ሌላ ኃይል መሆኑን አረጋግጣለሁ ማለት ነው” አልኩ።

“ቀጠልኩና በዚህ መካከል ትልቁ ችግሬ እንቅልፌ ነው። ይህንን ድካሜን የሚያባብሰው ደግሞ የቅዱሳኑ ጣዕመ ዜማ ነው። በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን ከገባሁ እንደትናንቱ ዜማቸው አባብሎኝ መተኛቴ የማይቀር ነው። እናም የተሻለው ዘዴ እዚሁ ዕቃ ቤት መኝታዬ ላይ ቆይቼ ወደ ዐሥር ሰዓት ተነሥቼ ከበሩ ላይ መጠበቅ ነው” ብዬ ወሰንኩ።

በርግጥ ይህን ያክል መሬት ላይ እየተንከባለልኩ እያደርኩ ሥራዬን ትቼ ለመጣሁበት ጉዳይ እንቅልፌ እንቅፋት መሆኑን ሳስብ “ምን ዐይነት ድካም ነው?” አልኩ። ሞባይሌን ለዐሥር ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን እንዲቀሰቅሰኝ ማንቂያ ደወል ሞላሁና ጸሎት ቢጤ ለማድረግ ሞከርኩ። በኋላ ሳስበው የእኔን መያዣ መጨበጫ የሌለውን ጸሎት ከማነብነብ የአባን ዜማዊ ጸሎት እየሰማሁ “ፈጣሪ ሆይ! እኔንም አስበኝ ብል ይሻላል” አልኩና ተኝቼ ማዳመጥ ቀጠልኩ። አቤት የአባ ድምፅ! በአካባቢው ከሰፈነው ጸጥታና ጨለማ ጋር ተዳምሮ መቼም ልዩ ነው።

ደስ የሚልና እርግት ያለ ስሜት ውስጤን ሲሞላው ተሰማኝ። ቆየና ደግሞ እንቅልፍ ባሕር ላይ ሲያንሳፍፈኝ ታወቀኝ። ሕልም የለ፣ ቅዠት የለ፣ ድብን ያለ እንቅልፍ እንደወሰደኝ ያወኩት ድንገት ባንኜ ከመኝታዬ ተስፈንጥሬ ስነሣ ነበር።

"የፈጣሪ ያለህ! ፀሐይ ወጥታለች" አልኩና ሰዓቴን ላይ አንድ ሰዓት ከፀሰር ይላል። እየተደናበርኩ ልብሴን ለብሼ ወደ ታች ወረድኩና ወደ ውጭ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ስመለከት አባ መዝገበ ሥላሴ የቤተ ክርስቲያኑን በርና መስኮት ቆልፈው ወደ እኔ አቅጣጫ እየመጡ እንደሆነ አየሁ።

መሬት ላይ ተደፋሁና ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ። "እንዴት ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጌ መጥቼ ሳበቃ እንደ አህያ እሬሳ ወድቄ እድራለሁ? የሞላሁት ማንቂያ ደወልስ ለምን አላነቃኝም? እኔ ራሴስ ቢሆን ለወትሮው ከ11፡30 በኋላ መቼ እንቅልፍ ይወስደኛል?" ብዬ በጣም ተበሳጨሁ።

"ደኅና አደርክ የእኔ ልጅ" አሉኝ አባ ከእኔ ጋር ሲደርሱ።

"ምን ደኅንነት አለኝ አባ" አልኳቸው ።

መስቀላቸውን ካሳለሙኝ በኋላ "ምነው ምን ሆንክ? ምን አገኘህ?" አሉኝ ።

"በቃ እንቅልፍ ጥሎኝ ነና አሁን መንቃቴ ነው" አልኳቸው።

"ይሄ ሥጋ መቼ እንዲህ በቀላሉ ይገዛል ብለህ ነው" አሉኝ።

"እንደዚህ ሆኜ ጭራሽ የሞት ያክል በእንቅልፍ ተሸንፌ አላውቅም ነበር" አልኳቸው።

"ይሆናል፤ ቢሆንም ይህን ያክል የሚያስከፋ ነገር የለውም" አሉ።

"ለምን አልከፋ አባታችን፤ ትናንት ያየኋቸውን ቅዱሳን ማንነታቸውን ንገሩኝ ብለዎት እርስዎም ፈቃደኛ አልሆኑም፤ ዛሬ ተከታትዬ አያቸዋለሁ ስል ደግሞ ይሄው ተኝቼ ቀረሁ" አልኩ በምሬት።

"ያየሃቸው መነኮሳት እኮ ምንም የተለየ ነገር የላቸውም" አሉኝ ።

"እንዴ! ዜማቸው፣ እርጋታቸው እኮ ልዩ ነው። ደግሞስ ያንን ያክል መነኮሳት ከዚህ የገጠር መንደር ይኖራሉ ተብሎ አይታሰብም አይደል? አንዳች ምሥጢር እንዳለው እረዳለሁ እርስዎ ባይነግሩኝም" አልኳቸው።

"እየሀ የእኔ ልጅ ያየሃቸው የተለዩ መነኮሳት ናቸው ብለህ ብታምን ኖሮ አትተኛም ነበር ።"

"ምን ላድረግ አባ? እኔ ምን እንደነካኝ እኮ አላውቅም ።"

"ለማንኛውም ወይ እይታህን ወይ እንቅልፍህን መምረጥ ይኖርብሃል" አሉ ወደ ቤት እየገቡ።

"ምን ማለትዎ ነው?" አልኳቸው ግራ ተጋብቼ ።

"ያየኸው ካስደነቀህ እንቅልፍ ሊያስችግርህ አይችልም፣ እንቅልፍህ የሚበልጥብህ ያየኸውን በሙሉ ልብ ባለመቀበልህ ነው" አሉና "በዚያ ላይ ደግሞ" አሉና ዝም አሉ። የሥራ ልብሳቸውን እየለበሱ ነው።

"በዚያ ላይ ደግሞ ምን ...?" አልኳቸው ።

"ከምታየው ነገር ለሕይወትህ የሚጠቅም ነገር ለመገብዬት ሳይሆን ዝም ብሎ ምሥጢር የማወቅ ጉጉት ብቻ ያለህ ይመስለኛል" አሉ።

"አባታችን እኔ እንጃ ብቻ ተምታትቶብኛል። እንዲያውም የዚህን ቤተ ክርስቲያን ደን ምሥጢር ለማወቅ በሞከርኩ ቁጥር የበለጠ ሕይወቴ እየተምታታብኝ መጣ" አልኳቸው።

ዛሬ የሚሠሩት የቀንድ ዋንጫ በመሆኑ እሳት አቀጣጥለው እያፋፋሙ ነው።

"ለመሆኑ የዚህን ቦታ ምሥጢር ሳታውቀው ቢቀር ምን ይጎድልብሃል?" አሉኝ ።

"አባታችን እውነቱን ልንገርዎት፣ የዚህን ቦታ ምሥጢር ካላወኩ ሕይወቴ ጐደሎ መሆን ብቻ ሳይሆን ባዶ ይሆናል" አልኳቸው።

ቀጠልኩና "እንድ ነገር ፈልጌ ሳጣ፣ ጠብቄ ሲቀር፣ እያንኳኳሁ ሲዘጋብኝ፣ በተለይ ደግሞ የተከለከልኩ ሲመስለኝ ነፍሴ በእልህ ትናጣለች፣ ደስታዬና ሰላሜ ጠፍቶ በመረበሽ እሞላለሁ" አልኳቸው የልቤን አውጥቼ።

"ሁሉን ነገር መፈለግ፣ ሁሉን መሻት፣ ያለገደብ ለመኖር ማሰብ የዚህ ዓለም ጣጣ፣ የድካም ምንጭ ነው" አሉ አባ።

"እየህ ልጄ! የፈለከውን ነገር ብታገኝም የሚቀር መኖሩ እሙን ነው። ምሥጢራትን ሁሉ ያወክ ቢመስልህም በዚህ ዓለም ከአንተ ጎሊና በላይ የተሰወረ ብዙ ነገር ይኖራል" ብለው በረጅሙ ተነፈሱና፡-

"እናም የሚሻለው የምትጠቀምበትን ያክል ብቻ እወቅ፣ የሚያጠግብህን ያክል ብቻ ብላ፣ የሚያረካህን ያክል ብቻ ጠጣ፣ ሁሉን ነገር ማጣት ሰቀቀን ቢሆንም ሁሉን ነገር ማግኘትም ዕዳ ይሆናል። ምንም አለማወቅ ባዶነት ቢሆንም ሁሉን ማወቅ ደግሞ ሸክምም ይሆናል" አሉና ዋንጫውን በእሳት ማጋሉን ቀጠሉ። በውስጤ ግን እኔን በእሳቱ እያጋሉ የሚቀጠቅጡኝ መሰለኝ።

"መዋረድ መጥፎ ቢሆንም፣ መከበርም ሐላፊነት አለው። መከልከል ቅሬታ ቢፈጥርም ሁሉን ማድረግ መቻል ግን ይሰለቻልና እርካታ የለውም" አሉ እንደ ዋዛ።

የሚሉት ነገር እውነት እንደሆነ ባውቅም ልቤ ግን ሸፍቷል። አሁንም የዚህን ቤተ ክርስቲያን ምሥጢር ለማወቅ ይዳክራል።

"አባታችን የሚያዝኑልኝ ከሆነ በትንሹም ቢሆን የዚህን ቤተክርስቲያን ደን ምሥጢር ይንገሩኝ። እንዲሁ እንድሄድ ቢገፋፉኝ ግን ባዶ ጎሊናና ደካማ ሰውነቴን ይገፍ የምሄድ መሆኑን ይወቁት" አልኩና "ለማንኛውም የመጨረሻ ሙከራ ዛሬ ማታና ሌሊት አደርጋለሁ። ካልተሳካልኝ መድኃኒት ይገፍ ሳይሆን የጎሊና በሽታ ተሸክሜ እያዘንኩ እሄድለወታለሁ" ብዬ አማረርኩ።

"ፈገግ ሲሉ" አየኋቸው ።

የተለመደው የሥራ ዜማ ተጀመረ። እኔም ማስታወሻ አውጥቼ መሞነጫጨር ጀመርኩ። በመጣሁበት ጉዳይ ላይ አባ ምንም ዐይነት ፍንጭ እንደማይሰጡኝ ተረዳሁ። ድጋሜ ወደ ደኑ ለመሄድ አስቤ ገና ሐሳቤን ሳልጨርሰው የፍርሀት ስሜት እንዳደረብኝ ስረዳ ከዚህ በላይ መዳፈር እንደሌለብኝ ወሰንኩ። ይሁንና የቀረችኝን አንዲት ሌሊት በአግባቡ ልጠቀምባት ግን ቆርጫለሁ። በምንም ምክንያት በእንቅልፌ ምክንያት አጋጣሚውን እንዳላሳልፍ ተሰልፌያለሁ።

ከአባ ጋር ከተደበቀው የምሥጢር ጉዳይ ወጥተን ስለአስተዳደጋቸውና ስለማንነታቸው በመጠኑም ቢሆን እያጫወቱኝ ውለን ሰባት ሰዓት አካባቢ መኝታዬ ሂጀ ለማረፍ ፈለኩና አባን ነግሬ ወጥቼ ጋደም አልኩ። መቼም የሰላም እንቅልፍ በገፍ ያለበት ቦታ ነውና ወዲያው ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰደኝ፤ የነቃሁት አባ ምሳ እንድንበላ ሲቀሰቅሱኝ ነበር። ጥሩ እንቅልፍ በመተኛቴ ደስ አለኝ። ከወዲሁ የሌሊቱን ሒሳብ ማወራረድ ለወሳኙ ፍልሚያ ይረዳኝ ይሆናል በሚል ተስፋ። ምሳችንን በልተን ስንጨርስ ቢጫ ጀሪካኖቹን ይዤ ‹ውኃ ቀድቼ ልምጣ› ብዬ ወደ ታች ወደ ምንጩ ወረድኩ።

ትንሽ እየተዘዋወርኩ አካባቢውን ከቃኘሁና ሰውነቴንም በደንብ ከአፍታታሁ በኋላ ውኃውን ቀድቼ ዳገቱን መውጣት ስጀምር ጦጣዎች ከሰሞኑ በበለጠ እኔ ወደምመጣበት መንገድ አካባቢ በመምጣት እርስ በርስ እንደሚጣሉ ዐይነት መረባበሽ ጀመሩ። ወደፊት ዳገቱን በወጣሁ ቁጥር ወደ እኔ አቅጣጫ እየተከተሉ ይጨፍሁ ጀመር። ለበርካታ ጊዜያት በበርካታ ደኖች ውስጥ መዋል ብቻ ሳይሆን እያደረኩ የምርምር መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። አንድም ቀን ግን ከአድናቆትና ከደስታ በስተቀር የፍርሀት ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም። አሁን ግን የጠጣዎቹ ድርጊት የሆነ ሽብር ለቀቀብኝ። ሆን ብለው እኔን ለማሸበር የሚሠሩት ቲያትር መሰለኝ። ብቻ ፈጠን ብዬ እያለከለኩ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ስገባ የፍርሀቱ ስሜት ለቀቀኝ።

ውኃውን ይገቼ ወደ ዕቃ ቤቱ ስገባ አባ ተነሥተው ተቀበሉኝና መረቁኝ። በነገራችን ላይ ዋናው የዕቃ ቤቱ በር ምንጊዜም እንደተቆለፈ ነው። አባ ዕቃቸውን የሚያስቀምጡት ከዕቃ ቤቱ ተቀንሶ በተሠራች ክፍል ውስጥ ነው። ማታ ሲመሽ እራት በልተን አመስግነን ወደመኝታ ቦታችን ስናመራ ቀን የገባሁትን ቃል ለመጠበቅ ጫማዬንና ልብሴንም ሳላወልቅ ግድግዳውን ተደግፌ በባትሪ መጀመሪያ ጸሎት አድርሼ ከዚያም መጽሐፍ ማንበብ ጀመርኩ። አባ የተለመደ ጸሎታቸውን ጀምረዋል። ትንሽ ቆይተው ደግሞ በዜማ እንደሚያደርሱ አውቃለሁ። ይህ ዜማቸው እንዳያባብለኝ ጆሮ መስጠት እንደሌለብኝም ወስኛለሁ።

ምሽቱ እየገፋ ሲሄድ የአባ ዜማም ጨለማውን እየሰነጠቀ ወደ እኔ ጆሮ ደርሶ ልቤን ለማሸፈት መሞከሩ አልቀረም። ቢሆንም "እጅ መስጠት የለብኝም" አልኩና ተነሥቼ ከመኝታዬ ላይ ቆምኩ። አባ ጸሎታቸውን ጨርሰው መኝታቸው ላይ ጋደም አሉ። አሁን ድሉ የእኔ እየሆነ ነው። ትንሽ ቆይተው እንቅልፍ እንደወሰዳቸው በአተነፋፈሳቸው ተረዳሁ።

ማንበቡን ትቼ በጸጥታ ሁሉንም ነገር መከታተል ያዝኩ። ከደኑ ውስጥ የሌሊት አራዊቶች ድምፅ ዐልፎ ዐልፎ ይሰማል። በተረፈ ጸጥ እንዳለ ነው። እንቅልፍ ድንገት ቸርው ብሎ እየመጣ ያንገዳግደኛል።

"ወይ ጉድ" አልኩ። በአሁኑ ዘመን ሰው በተለይ በምዕራቡ ዓለም የሚጨነቀው በእንቅልፍ እጦት ነው። ለዚህም ሲባል ከባድና ውድ የእንቅልፍ ማስወሰጃ ክኒንና መርፌ ተፈልስፈዋል። የእንቅልፍ ማጣት እንጂ የእንቅልፍ መብዛት ችግር ሆኖ አልተነሣም። እኔ ግን ይኸው እዚህ በእንቅልፍ ብዛት መከራዬን አያለሁ። በነገራችን ላይ ብዙ ጊዜያት እኔም በእንቅልፍ እጦት ተቸግሬ አውቃለሁ። አሁን ግን ይኸው ከእንቅልፍ ጋር እታገላለሁ።

ሰዓቴን ሳይ ገና ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት ከሃያ ነው። "እቤት ይህን ያክል ጊዜ ነው ለካ በየቀኑ የምንተኛው" አልኩ።

እንዲህ እየወደኩ እየተነሣሁ ከእንቅልፌ ጋር ስታገል አባ መዝገበ ሥላሴ ከእንቅልፋቸው ተነሥተው ከመኝታቸው ላይ ኩርትም ብለው ጸሎት መጀመራቸውን ተረዳሁ። ሰዓቴን ሳይ ለዘጠኝ አምስት ጉዳይ ይላል።

"ግሩም ነው አሁን ወደ ቤተ ክርስቲያኑ መሄጃቸው ሰዓት ተቃርቧል። ከውጭ የሚመጡ ሰዎችም ከየት አቅጣጫ እንደሚመጡ ማየት እችላለሁ" አልኩና የበለጠ ንቃት ጨመርኩ።

የሚገርመው ግን ሰዓቱ እየገፋ ቢሄድም አባ ከመኝታቸው ላይ ሆነው ጸሎታቸውን በለሆሳስ ቀጠሉ እንጂ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ለመሄድ አለመነሣታቸው ነው። ሰዓቴን ደጋግሜ አየሁ ወደ ዐሥር ሰዓት እየተጠጋ ነው። ምንም ዐይነት እንቅስቃሴ ቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ አይሰማም። ሰዓቱ እየገፋ በሄደ ቁጥር ግራ መጋባቴ እየጨመረ መጣ። ከሌሊቱ ለዐሥራ አንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ አካባቢ አንድ ቄስና አንድ ዲያቆን እየተነጋገሩ ወደ አጸዱ ሲገቡ ሰማሁ።

ዘዚያም ዲያቆኑ እኛ ወዳለንበት መጥቶ አባን ተጣራ።

"እንዴት አደርክ ፍሬው? እንካ ቱልፋን" አሉና በደረጃው ወደታች ወረወሩለት። ዲያቆኑ በያዘው ባትሪ ቱልፋን ፈልጎ አነሣና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አመራ። አከታትለው ሌሎች ካህናት እየደረሱ እንደሆነ ተረዳሁ። አባም ለባብሰው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሲሄዱ ተከታትዬ ሄድኩና ውስጥ ገብቼ ሳስተውል ሦስት ቄሶች፣ ሁለት ዲያቆናትና አንድ ትልቅ አባት ብቻ እንዳሉ አየሁ። ከአንድ ቀን በፊት ያየኋቸው መነኮሳት ፈጽሞ እንደሌሉ ተረዳሁ። ያገኘኋትን አንዲት ወርቃማ ዕድል እንቅልፌን መቋቋም አቅቶኝ እንዳሳለፍኳት ሲገባኝ ሐዘኔ በጣም በረታ። የሆነ አልቅስ አልቅስ የሚለኝ ስሜት መጣና እንባዬን ያሳርፈው ጀመር።

የተለመደው የኪዳን ጸሎት ተደርሶ ከዚያ ቅዳሴ ተገባ። ቀስ በቀስ የአካባቢው ሕዝብ ሴቱም ወንዱም መጠራቀም ጀመሩ። የደኑ የኃይል ምሥጢርም ከእነዚያ ቅዱሳን መነኮሳት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ወደማመኑ ተቃረብኩ።

"ምሥጢሩን መፍታት ቀርቶ ዜማቸውንና ገጽታቸውን እንኳን በአግባቡ ብጠግበው ኑሮ?" አልኩ። በእርግጥ ከዚህ ክቡር ምሥጢር ለመካፈል የሞራልም ሆነ የእምነት ብቃት የሌለኝ መሆኑ ግልጽ ነው። የሳይንስና የአመክንዮ ዕውቀት ደረጃዬም ገና ብዙ የሚቀረው እንደሆነ እረዳለሁ። ብቻ ተስፋ በመቁረጥና ሌላ ልሞክረው የምችለው ምን ዘዴ ይኖራል በሚለው መካከል ልቤ ዥዋዥዌ እየተጫወተ ሥርዓተ ቅዳሴው አብቅቶ ሠርወተ ሕዝብ ሲሆን ወደ ማረፊያዬ ሄጀ ዕቃዬን መሸካከፍ ጀመርኩ።

በርካታ እናቶች ለአባ በአገልግልና በሳህን እንጀራ በቅልና በፕላሰቲክ ጀሪካን ደግሞ ጠላ አምጥተው ከሥራ ቦታቸው ላይ ደርድረዋል። አባ መዝገበ ሥላሴ በአካባቢው ምዕመናን ዘንድ በጣም እንደሚወደዱ ለመረዳት አላዳገተኝም። ከቤተ ክርስቲያኑ

ወጥተው ሲመጡ ሁሉም መስቀላቸውን ለመሳለም ወደርሳቸው ይፋጠናሉ።

እርሳቸው ቆም ሂድ እያሉ እያሳለሙ በዚያውም "ያልጅ ተሻለው ወይ?፣ እናትሽ እንዴት ናቸው?፣ ወንድምሽ ደኅና ተመለሰ?፣ ያ የተሠበረው ወይፈን እንዴት ሆነ?፣ ከአባትህ ጋር ተስማማችሁ ወይ?" ይላሉ። የሁሉንም ጓዳ ጐድጓዳ የሚያውቁ፣ ችግርና ብሶት የሚካፈሉ እንደሆነ ይታወቃል።

እናቶች ነጠላቸውን ከአፋቸው ላይ ጭነው መሬት መሬት እያዩ የሆነ ነገር በቀስታ ይነግሯቸዋል። እርሳቸውም "ግዴለም አታስቢ የእኔ ልጅ፤ እኔ ቀስ አድርጌ አወያየዋለሁ" ይላሉ።

አባ እየተራመዱም፣ ቆመውም፣ ተቀምጠውም ሁሉንም እንደየችግሩና ምስጢሩ ሲያነጋግሩና ሲያዕናኑ ከቆዩ በኋላ ወደ እቃ ቤት ገብተው የለበሱትን ጋቢ መኝታቸው ላይ ጥለው ውኃ ቀድተው እጄን እንድታጠብና እህል ውኃ እንድንቀምስ አሳሰቡኝ።

"ዛሬ ያው ቀኑ ቅዳሜ ነው። ወደ ገበያ ወጥቼ የሠራኋቸውን ዋንጫዎችና የጸሎት መቁጠሪያዎች እሸጣለሁ። ከቀናኝም በዚያው አንዳንድ ነገሮችን እሸምታለሁ" አሉ።

"የት ነው ገበያችሁ? እሩቅ ነው?" አልኳቸው ።

"እሩቅ የሚባል እንኳን አይደለም፤ እንዲያው ግፋ ቢል አንድ ሰዓት ቢወስድ ነው" አሉ።

በዚህ ሁኔታ ምሳችንን በልተን ከጨረስን በኋላ እኔም ኮተቴን ሰባስቤ ለጉዞ ዝግጁ ሆንኩ።

አባ ወደ ገበያ የሚወስዷቸውን ምርቶቻቸውን በጥንቃቄ አስረው በማዳበሪያ ከረጢት ከትተው በዱላቸው ሰክተው በትክሻቸው ለመሸከም ሲያዘጋጁ፡-

"አባ!" አልኳቸው።

"አቤት የእኔ ልጅ" አሉ።

"በቃ ጨከኑ ማለት ነው። ምንም ፍንጭ ሳላገኝ እንድመለስ ፈረዱ ማለት ነው?" አልኳቸው።

"ፈገግ ብለው አይ ያንተ ነገር" አሉና መቆጣጠራቸውን ቀጠሉ። ለጉዞ ዝግጁ አደረጉና "መጣሁ" ብለው ወደ ቤተልሔሙ ሂዱና ብዙ ቆይተው መጡ።

"ምነው በደኅናዎት ነው?" አልኳቸው።

"ኸረ ደኅና ነኝ። አንድ የምከውነው ጉዳይ ኑሮኝ ነው" አሉና ዕቃቸውን አውጥተው የዕቃ ቤቱን የውጭ በር ቆለፉና የቋጠሩትን በምርኩዛቸው ላይ ሰክተው ለጉዞ ዝግጁ ሆኑ። እኔም የዕይታ መሣሪያውን በጀርባዬ አዝዬ ሌላውን በሁለት እጀቼ አንጠልጥዬ እርሳቸው እንዲቀድሙ ጠየኳቸው።

"ኃይለ ጊዮርጊስ" አሉኝ በክርስትና ስሜ ። መጀመሪያ እንደመጣሁ አስቡኝ ብዬ ነግሬያቸው ነበር። እስካሁን አንድ ጊዜም ሳያነሡት አሁን በዚህ ስም ሲጠሩኝ ልቤ ድንግጥ አለ።

"ምኞትህና ፍላጐትህ ምን እንደሆነ አውቃለሁ። የተማርከው ትምህርት ብዙ እንድትጠይቅ እንደሚገፋህ እረዳለሁ። የሆነው ሆኖ ማወቅ የምትፈልገው ነገር በእኔም በአንተም ፍላጎትና ዕውቀት የሚሆን አይደለም። ለማንኛውም ፍላጎትህና ጉጉትህ ከክፋት የመነጨ ባለመሆኑ የቦታውን ምሥጢር ለማወቅ ከሚፈቅዱት መልእክት ይገለሃለሁ" አሉ ፈገግ ብለው፡-

"ምንድን ነው አባ?" አልኳቸው መጠን በሌለው ጉጉት ።

"ልነግርህ እኮ ነው አትቸኩል! አሁኑኑ የሚፈጸም ነገር የለም። ገበያው ስንደርስ እነግርሃለሁ። አሁን ሳይረፍድ እንሂድ" አሉ ።

"እሺ አባታችን" አልኩና በደስታ።

"የእሳት ብልጭታ የምትሆን ምልክት እንኳን ባገኝ ምን ያክል ተስፋ እንደሚሆነኝ ልገልጽለዎት አልችልም" አልኳቸውና መንገዳችንን ቀጠልን።

እርሳቸው ከፊት እኔ ከኋላ ሆኜ መጓዝ ጀመርን። የተሸከምኩት የዕይታ መሣሪያ በጣም እየከበደኝ መጣ። ምንም ሰላልጠቀመኝ ነው መሰለኝ ስወስደው ሳይከብደኝ አሁን ስመለስ በጣም ታወቀኝ።

አባ መዝገበ ሥላሴ ሰው ለመሳለም ሲያስቆማቸው ካልሆነ በስተቀር ማዜማቸውን ቀጥለዋል። አንዳንዴ በዜማው ከመመሰጣቸው የተነሣ ወደ ፊት ደርደር ይሉና ጎንበስ ብለው ቀና ይላሉ። ይህንኑ ይደጋግማሉ። ከግማሽ ሰዓት ጉዞ በኋላ ቀጥ ያለ ዳገት መውጣት ጀመርን። ዳገቱን ጨርሰን ብቅ ስንል በቁጥር ትንሽ ቤቶች ያሉባት መሀል ለመሃል አዲስ አስፓልት የተነጠፈላት ከተማ መድረሳችንን አወቅኩ። ከከተማው በስተደቡብ ምሥራቅ በኩል በተፈጥሮ ደን የተከበበ ቤተ ክርስቲያን ይታያል። አባ ወደ ደኑ አቅጣጫ ተጓዙና አንድ ዐሥር ሜትር ገባ ብለው ጓዛቸውን አወረዱና ተሳለሙ። እኔም እንደዚያው አደረኩ።

አባ አጭር ጸሎት አድርገው ዐረፍ እንዳሉ፡-

"ይህች ከተማ ማን ትባላለች?" አልኳቸው።

" ጅባስራ (ጅብ-አስራ)፡ ቤተ ክርስቲያ' ደግሞ ጅብ-አስራ ማርያም ትባላለች" አሉ።

ፈገግ አልኩ። ይህችን ከተማ ስሟ በዘፈን ሲነሣ ቀደም ብዬ አውቃለሁ። ስሟ የገነነ ቢሆንም ከተማዋን ሳያት ግን አነሰችብኝ። አብዛኛው የአገራችን ከተሞች ስማቸው የገነነ ሆኖ በአካል ሲታዩ ለምን እንደሚኮሰምኑ አይገባኝም። ለማንኛውም፦

"እኔ እየተከተልኩ እርሷ እየመራችኝ

መቼም ይብላው ብላ ጅብ-አስራ ቆየችኝ"

ጉባለላት ስሟ በዘፈን የገነነላት ትንሽዬ ከተማ ናት።

ዕረፍት ካደረጉ በኋላ ከተቀመጡበት ተነሡና ከደረት ኪሳቸው ድ የተጣጠፈ የለሰለሰ ብራና አውጥተው፦

ወቅ የምትፈልገው ምሥጢር እንዲገለጽልህ ልብ ብለህ ስማኝ!"
ና፦

"ከዚህ ብራና ላይ ስማቸው የተጻፉ ሦስት ዕፆች አሉ። ከተጠቀሱልህ ቦታዎች ብቻ ሂደህ ይዘህ ተመለስ። ያን ጊዜ ማወቅ የምትፈልገው ምሥጢር ይገለጽልሃል። ዕፆቹን ሳትይዝ ግን ድጋሚ ወደተቀደሰው ቦታ በምንም ምክንያት እንድትመጣ አልተፈቀደልህም!" አሉኝ ፈርጠም ብለው።

ም ከአራት ታጥፎ የታሰረውን ብራና ሰጡኝ።

ድር ዳርቻም ቢሆን ሂጄ ይገፍው እመጣለሁ። እንኳን የተስፋ ሰጡኝ እንጂ ሌላው ዕዳው ገብስ ነው" ብዬ አሰብኩና ፊቴ

ሂድ ብረር ብረር" የሚለኝ መጣ። ደስታዬ ግን ብዙ አልቆየም።

ወደ እኔ ጠጋ ብለው የግራ እጃቸውን ከትከሻዬ ላይ ጭነው እጃቸው አመልካች ጣት እየቀሰሩ፦

"ኃይለ ጊዮርጊስ ልብ በል! ሌላም ትእዛዝ አለ" አሉ።

"ምንድን ነው?" አልኳቸው በመገረም

"በፍለጋው በመድከምም ሆነ በመሰላቸት በዚያው መቅረትም አልተፈቀደልህም። ወደ ቅዱሱ ቦታ ለመመለስ በዘገየህ ቁጥር የጎለኛው ዘመንህ እንደምንጣፍ ወደ አንተ እየተጠቀለለ ይቀርባል" አሉ።

"ምንድን ነው የሚሉኝ?" አልኳቸው በድንጋጤ።

"ይህ ትእዛዝ የፍላጎትህ መልስም ቀኖናህም ጭምር ነው። እግዚአብሔር ይርዳህ" ብለው መስቀላቸውን አሳልመውኝ ቋጠሯቸውን አንሥተው ወደ ገበያው ሲያቀኑ እኔ ባለሁበት ፈዝዤ ቀረሁ።

"እኔ እየተከተልኩ እርሷ እየመራችኝ

መቼም ይብላው ብላ ጅብ አሰራ ቆየችኝ"

የሚለውን ግጥም እንደገና ሳስብ ለእኔ የተገጠመ መሰለኝና የምፀት ፈገግታ ፈገግ አልኩ።

"አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል" አለ ያገሬ ሰው አልኩና መሬት ላይ በቁሜ ዘፍ አልኩ። ወዲያው ሞባይሌን አውጥቼ ለዶ/ር ክብረ በዓል ደወልኩ።

"ሀሎ ወንድም ሲሳይ" ሲለኝ።

"ዶ/ር ክብረ በዓል የት ነህ? ጅባስራ ከምትባል ከተማ ነኝ እባክህ ቶሎ ልትመጣልኝ ትችላለህ?" አልኩት።

"ደኅና አይደለህም እንዴ?" አለኝ ።

"ደጎና ነኝ ብቻ ታክቶኝ ነው" አልኩት።

"ከተማዋን አውቃታለሁ፣ በአጋጣሚ ብዙ ሩቅም አይደለሁም፣ በግማሽ ሰዓት ውሰጥ እደርሳለሁ" አለኝ።

መሬት ላይ በጀርባዬ ተኛሁ። ጭንቅላቴ በዱላ የተመታ ያክል ተናውጧል። የሚደንቀው ግን ብራናውን ገልጬ ለማንበብ አለማሰቤ ነበር። በኋላ ላይ ሳስበው ገልጬ ለማንበብ ብሞክር ኖሮ ግራ መጋባቴ ጨምሮ ወደ እብደት ባመራኝ ነበር።

የዶ/ር ክብረ በዓል ስልክ እስኪያነቃኝ ድረስ የት እንዳለሁ እንኳን እረስቸዋለሁ። መኪናዋን አስፓልት ዳር ቆማ አየኋት። በፍጥነት ተራመድኩና የኋላውን የመኪናውን በር ከፍቼ ዕቃዬን ከአስቀመጥኩ በኋላ ጋቢና ሄጀ ዘፍ አልኩና በሩን በኃይል ዘግቼ ዶ/ር ክብረ በዓልን ሰላም እንኳን ሳልለው፡-

"እባክህ ወደ ባሕር ዳር፣ ወደ ቤቴ፣ በተቻለህ ፍጥነት ንዳው!" አልኩት"። ብዬ ትረካዬን ስጨርስ ሺፈራው ዐይኖቹ በመገረም አፍጥጠው እያዩኝ ነበር።

በዝምታ ከቆየን በኋላ "ይህ ሁሉ ምሥጢር፣ ይህ ሁሉ ድንቅ ነገር በዙሪያችን እያለ የኔ ቢጤዎቹ ባይታወር ሆነን፣ የከበረውን እየናቅን፣ የተሰወረውን እንደሌለ እየቆጠርን፣ በግብዝነት ሕጋዊ በሚመስል የውንብድና ሕይዎት ዘመናችን ማለፉ ያሳዝናል" አለና

"ታዲያ እንድታመጣ የታዘዝከውን ዕፆች ማግኘት ቻልክ?" አለኝ ፤ አሁንም በጉጉት።

"ነገሩ እንዲህ በቀላሉ የሚሳካ አልነበረም" አልኩና ትዕዛዙ በስውር መጻፉን ያንንም ለመረዳት አቡዳቢ ሙዚዬም ፍንጭ እንዳገኘሁ፣ በዚያ ተመሥርቼ መልእክቱን እንዳነበብኩ፣ ወደ መተማ የሄድነውም አንደኛውን ዕፅ ለመፈለግ እንደነበረና አሁን ሁሉንም

አግኝቼ ወደ ቅዱሱ ስፍራ ላመራ እንደሆነ በዝርዝር ተረኩለት።

ድንገት ዘለሞ ተነሣና ወደ እኔ መጥቶ አቅፎ ሳመኝና፡-

"ሲሳይ! በዚህ የተቀደሰ ጉዞህ ከመጀመሪያው ያልነበርኩ ሰው አሁን መጨረሻ ላይ አብሬህ ልሂድ ብዬ አላስቸግርህም። ደግሞስ አንደ እኔ ዐይነት ሰው እንዴት ፊታቸውን ያየዋል? ብቻ ግን እንደ ሚ/ር አንቶን ለእኔም ቀሪ ዘመኔ ከውንብድና እንዲርቅ ከገንዘብ ቁራኛ እንዲላቀቅ አስቡኝ በልልኝ" አለኝና እያነባ "በል ተነሥ አንጂ ጉዞህን ቀጥል" አለኝ።

"እኔማ ባሕር ዳር ሄጄ አድራ ነገ በጠዋት ልሂድ ወይስ ዛሬውኑ በዚሁ ልቀጥል? እያልኩ እያመነታሁ ነበር" አልኩት።

"የምን ባሕር ዳር ነው!" አለኝ ቆጣ ብሎ፤

በሁኔታው ሣቅሁና "ለማኝኛውም ዶ/ር ክብረ በዓልን ላማክር" ብዬ ስደውል ስልኩ ጥሪ አይቀበልም። ደጋግሜ ሞክርኩ አሁንም መልስ የለም። በጣም አሳሰበኝና፡-

"ሺፈራው ዶ/ር ክብረ በዓል የት እንደለ ታውቃለህ?" አልኩት።

እርሱም እንደጠፋበት ነገረኝና "አንተ ካላወቅህ እኔ የማውቅ ይመስልሃል፤ ክብረ በዓል እኮ በየጊዜው ከእኔ በመንፈስ እየራቀኝ እንደሄደ አውቃለሁ። ከእኔ በመራቁም አልፈርድበትም። አሁን አሁን አብሮ አደጌና የማውቀው መሆኑንም እጠራጠራለሁ" አለኝ ትክዝ ብሎ።

"ዶ/ር ክብረ በዓልን ማንኛችንም በደንብ አናውቀውም። ከእኛ በእጅጉ የገዘፈ ነውና። ለማናኛውም ግን በዚህ ወቅት እርሱን ማጣቴ ረበሸኝ" አልኩት።

"ይገባኛል" አለና መኪናዬ ድረስ ትክሻዬን አቅፎ ሸኘኝ።

በዚህ መሠረት ከቀኑ ወደ ዐሥር ሰዓት አካባቢ ሙሉ ክብ የሠራ አድካሚ የውዴታ ግዴታ ጉዞዬን ጨርሼ፣ ሦስቱን ዕያች ይዤ፣ እርግማንን በበረከት፣ ድፍረትን በይቅርታ፣ ምሥጢርን በመረዳት ለመቀየር ወደ ሞገደኛው ቤተ ክርስቲያን ደን፣ ወደ ‹ሳይት 09›፣ ወደ ቅዱሱ ስፍራ አመራሁ።

በወረትና በጉጉት የጀመርኩት ምሥጢር ማነፍነፍ እንዴት ያለ ዋጋ እንዳስከፈለኝ አስቤ ‹ሲያንሰኝ ነው!› አልኩ። በምን ምክንያት እንዴት ባለ ሰበብ ወደዚህ መንከራተት እንደገባሁ ሳስብ ሕይዎት በዕጣ ፈንታና በአስደናቂ ገጠመኞች የተሞላች መሆኗ ታሰበኝ።

# የመጀመሪያው መጠሪያ

# ምዕራፍ ዐሥሪ ሰባት

መኪናዬን ሁሌ ከማቆምበት አርሶአደር ቤት ግቢ አቁሜ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ አመራሁ። እንደተለመደው ዳገቱን ጨርሼ ከቤተ ክርስቲያኑ ደረስኩ። በስተስሜን በኩል ባለው በር ሄጀ ተሳለምኩና በጉጉት ወደ አባ መዝገበ ሥላሴ አመራሁ። ሁልጊዜም ሥራ ከዜማ ጋር ወይም መጽሐፍትን በማንበብ ተጠምደው በአታቸውን የማይለቁት አባ ግን በቦታው አልነበሩም። ለሠርክ ጸሎት ሄደው ይሆናል ብዬ ሰዓቴን ሳይ ገና ዐሥር ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው። ግራ ተጋባሁ። ልጠይቀው የምችለው ሰውም በአካባቢው አልነበረም። ከቤተ ክርስቲያኑ ደረጃ ሄድኩና ፊቴን ወደ ዕቃ ቤቱ ወደ አባ የሥራ ቦታ አዙሬ የመኝታ ቀረጢቴን ተደግፌ ጋደም አልኩ።

ከፍተኛ ድካምና የቁስል ጥዝጣዜ ስለሚሰማኝ ዐይኔን ክድን አድርጌ ለማረፍ ሞከርኩ። ከአንድ ሰዓት በኋላ የሰው ኮቴ የሰማሁ መሰለኝና አይኔን ገልጨ ሳይ አባ መዝገበ ሥላሴ ከቤተልሔሙ አቅጣጫ ወደ እኔ ሲመጡ አየኋቸው። ከወትሮው በተለየ ነጭ ኮሚስ ከነጭ አስኬማ ጋር ለብሰው በላዩ ላይ ነጭ ጋቢ ቀኝ እጃቸውን አውጥተው አጣፍተው ለብሰዋል።

"ኃይለ ጊዮርጊስ! መጣሀ የኔ ልጅ" አሉኝና እቅፍ አደረጉኝ። ቆይተው ከእቅፋቸው አወጡኝና በሁለት እጆቻቸው ትከሻዬን ይዘው፡-

"የእኔ ልጅ ተሳካልሀ?" አሉኝ ፈገግ ብለው።

"አምን አባታችን እንደ ትእዛዝችሁ፡-

ከማኅበረ ስላሴ ገዳም ዕፀ ሲና፡

ከአባ ጸንጠሌዎን ገዳም ዕፀ ጎርመት፡

ከይምርሐነ ክርስቶስ ደብር ዕፀ ተክሀኖ፡

ይዤ መጥቻለሁ" አልኳቸው ፈገግ ብዬ።

"ድንቅ ነው የኔ ልጅ! ማለፊያ ተግባር ፈጸምክ! የመጀመሪያውን መጨረሻ በአግባቡ ተወጣሀ! " አሉ እራሴን እያሻሸ።

"በል ዕያቹን ስጠኝ" አሉ ቀጠሉና።

በላስቲክ የከተትኳቸውን የጠወለጉትን ዕያች ከቦርሳዬ አውጥቼ ሰጠኋቸው።

"መጣሁ!" ብለው እየተጣደፉ ወደ ቤተልሔሙ አቅጣጫ ሲሄዱ፡-

"እንግዲህ ከእኔ ዘንድ የቀረ ነገር የለም" ብዬ የሆነ እርካታ ተሰማኝና "እፎይ" ብዬ ጋደም አልኩ።

አባ እንደሄዱ በዛው ሲዘገዩ ጊዜ መቀመጡ ሰለቸኝና ቤተ ክርስቲያኑን መዞር ጀመርኩ። የሆነ የጎብረ ዜማ ድምፅ የሰማሁ ይመስለኝና ቆም እያልኩ ጀሮዎቼን አቃንቼ ለመስማት ስሞክር መልሶ ይጠፋል። ትንሽ ቆይቶ ደግሞ እንደገና የሰማሁ ይመስለኛል። በዚህ ሁኔታ ከቤተ ክርስቲያኑ የውስጠኛው ቅፅር አካባቢ ስንቀሳቀስ ቆይቼ ምሽቱ ሲቃረብ አባ መዝገበ ሥላሴ ሲጠሩኝ ሰማኋቸው።

ከዕቃ ቤቱ በር ላይ ቆመው አየኋቸውና ወደዚያው ሄድኩ። ፊታቸው ፈክቷል።

"የእኔ ልጅ ነገ ረፋዱ ላይ ባለፊው መሣሪያህን ይዘህ ለማየት የምከርክበት አካባቢ እንድትገኝ ተነግሮሃል" አሉና፡-

"ብዙ ድካምና ውጣ ውረድ በማሳለፍህ የደከመ ሰውነትክን ምሽቱን ከዚህ ዐረፍ ብለህ አሳልፍ። እራትህም ተዘጋጅቶልሃል" ብለው የተከደነ ሣህንና ትንሽ ማንቆርቆሪያ አሣዩኝ።

"እራትክን በልተህ ከላይ ውጣና ባለፊው ከተኛህበት አነጣጥፊህ ተኛ" አሉኝ።

"እንዴ! እርስዎ የት ሊሄዱ ነው?" አልኳቸው።

"እኔ ብርቱ ተግባር አለብኝ፤ ቢሆንም ከዚህ አካባቢ ነኝ" አሉ።

"ታዲያ ለምን አብሬዎት መጥቼ አላግዘዎትም፤ ብዙም አልደክመኝም እኮ" አልኩ።

የሚከውኑትን ተግባራቸውን ለማወቅ ስለጓጓሁ ነበር እንጂ እንደ እውነቱ ከሆነ በጣም ደክሞኝ ነበር።

"አይይ! የሚታገዝ ነገር የለውም። ይልቁንም አፍክን ሻረውና ዐረፍ በል" ብለውኝ ሄዱ።

መኝታዬን ከላይኛው ደርብ ወጥቼ ከአነጣጠፍኩ በኋላ ወደታች ወርጄ ከዕቃ ቤቱ በረንዳ ቁጭ አልኩና የተቀመጠልኝን ሣህን ከፍቼ በላሁ። ከማንቆርቆሪያው የሚበቃኝን ያክል ጥሩ የገብስ ጠላ ጠጣሁ። በምሽቱ ድባብ እራሴን ዘና ሳደረግ ቆይቼ ጥቅልል ብዬ ተኛሁ።

ጠዋት ስነቃ ፀሐይ ወጥታለች። ተነሥቼ ቤተ ክርስቲያኑ ስደረስ ሥርዓተ-ቅዳሴው ማለቂያ ላይ መሆኑን ተረዳሁ። ከውጭ ቆሜ ሥርዓተ-ቅዳሴው ሲጠናቀቅ ወደ ውስጥ ገብቼ ከቅድስቱ መግቢያ ላይ በግንባሬ ተደፍቼ ጸሎት አድርሼ ቀና ብዬ አካባቢውን ስቃኝ ከአካባቢው ምዕመናን በተጨማሪ በርካታ መነኮሳት መኖራቸውን ተረዳሁ።

"አሁን ድብብቆሽ የለም፣ በተዘጋ በር አፈ-ልቁ ለማዬት የምሞክርበት ምክንያት የለም። ከተቀጠርኩበት ቦት ሄጄ ከመጠበቅ ውጪ" አልኩና ከቤተ ክርስቲያኑ ወጥቼ የስሜኑን አቅጣጫ ተከትዬ የድንጋዩን ካብ ዐልፌ ኮምፓሳችን ወደ ተርገበገበበት፣ በፊት መልካሙ ወደ አንቀላፋበት በኋላም እኔ በድንገት ወደ ተኛሁበት ነፍራ አመራሁ። ዙሪያውን ቃኘሁት አዲስ ነገር የለም።

በፕሮፌሰር ኮሊን የዕይታ መሣሪያ ለማየት ስሞክር ሙሉ ነጭ ጭጋግ ተሞልቶ የነበረውን ማራኪ ደን በአድናቆት እያየሁ ቆምኩ። የፀሐይ ጨረር በረጃጅሞቹ ዕጸሜ ጠገብ ዛፎች ቅርንጫፍ ተፈነጣጥቆ ልዩ ጎበረ ቀለማት ሠርቶ ለደኑ ግርማ ተጨማሪ ውበት ሰጥቶታል። ከእኔ ዕይታ ውጪ የሆነውን አስደናቂ ምሥጢር አስታውሼ ዝም ብዬ ማነብነቤን ቀጠልኩ፡

"መካነ ስውራን መካነ ጎርመት፡

ጥልቅ ምሥጢር የከበረ ዕውቀት፡

የእኛ ሲሆን ከእኛ የተሰወረ፤

ሳቁሳዊ ሳይንስ በላይ ሆኖ ራሱን ያስከበረ፣ ተፈጥሮን ያገበረ፤

አንተን እረዳ ዘንድ በማጎበረ ሥላሴ ገዳም እግሬ የተላጠው፣ በሊማሊሞ ጥምዝምዝ በተከዜ በረሓ የወረድኩት፣ በይምርሐነ ክርስቶስ ገደል የተንከባለልኩት፣ ሲመዘን ኢምንት እንደሆነ እረዳለሁ፣

ጀምስ ብሩስ በበረሓ የቃተተው፣ ጆርጅ ዊልኸልም ሽምፐር ከሀገሩ እንደወጣ የቀረው ከዚህ ድንቅ ምሥጢር ፍንጣቂ ለመቋደስ እንደሆነ ዘግይቼ የተረዳሁ ደካማ አሳሽ እንደሆንኩም አውቃለሁ።

በምን ሥራዬ፣ እንዴት ባለ ዕውቀቴ፣ በየትኛው ንጽሕናዬ፣ መቼ ባሳደግኩት እምነቴ የመሰወሪያውን የብርሃን ግድግዳ አልፋለሁ" እያልኩ ስደነቅ የሰው ዳና ሰማሁና ዘወር አልኩ።

ከቤተ ክርስቲያኑ አቅጣጫ ነጫጭ የለበሱ መነኮሳት ሲመጡ ተመለከትኩና ልቤ ወከክ አለ። እየቀረቡኝ ሲመጡና መልካቸውን ማስተዋል ስጀምር በአድናቆት አፌን ከፍቼ ቀረሁ። የዋግንና የላስታን ተራሮችን አብረውኝ ያቋረጡት አባ ወልደ አረጋዊ፣ የማኅበረ ሥላሴ ገዳሙ አባ ኪዳነ ማርያም፣ የአቡነ እንድርያስ ዋሻው አባ ብርሃነ-መስቀል እና... ሌሎችም በአባ መዝገበ ሥላሴ መሪነት በግርማ ካለሁበት ደረሱ።

መደነቄ ገዝፎ አእምሮዬ በሰማያት እየተንሳፈፈ እያለ አድናቆቴን ወደ ድንጋጤና ልዩ ስሜት የከተተው ግን ከመካከላቸው በዕድሜ ያነሰው ሰው ነበር። ጥቁር የምንኩስና ቀሚስ ለብሶ፣ ወገቡ ላይ በሰፊ መታጠቂያ ታጥቆ፣ እራሱ ላይ በነጭ ሻሽ የተሸፈነ የአመክሮ የምንኩስና አስኬማ /ቆብ/ የደፋ፣ ደረቱ ላይ የሚያበራ መስቀል ያነገተ፣ ከራሱ ጀምሮ ነጭ ነጠላ ትክሻው ላይ ደርቦ በሁለት እጆቹ ደረቱ ላይ አጣብቆ የያዘው ሰው ነበር።

ሳላውቀው እንባ በዐይኖቼ ሞላና፡- "ዶ/ር ክብረ በዓል!" ብዬ ጮህኩ።

"ከእንግዲህ ‹አባ መዐዛ ቅዱሳን› ይባላሉ" አሉኝ አባ ወልደ አረጋዊ ፈገግ ብለው። በአግባቡ የሰማኋቸው አልመሰለኝም።

"ለምን? ለምን ደበቅከኝ?" አልኩ እየተወራጨሁ። "ወንድማማችነታችን የእውነት፣ ፍቅራችንም ከልብ አልነበረም? ሁሉንም ምሥጢሬን ስነግርህ ለምን ይህን ትልቅ ውሳኔህን ደበከኝ?"

"አላስተዋልኩም ደግሞም ራሴን ማመን አልቻልኩም እንጂ ማኅበረ ሥላሴ ገዳምም በአቋራጭ ቀድመህ ደርሰህ ከመናኞቹ ቤት አይቼህ ነበር። አላስተዋልኩትም እንጂ በምሄድበት ሁሉ ወይ ከፊቴ አለዚያም ከኋላዬ ነበርክ። ግን ለምን ሸሸግኸኝ? ለምን አልነገርከኝም?" አልኩት። ብቻ እንደ እብድ ነው ያደረገኝ። ኡኡ ብዬ ማልቀስም ቃጣኝ።

በተለመደው ፈገግታው ታጅቦ በእርጋታ፡-

"ወንድም ሲሳይ! በወንድማማችነታችን መኻል የተለወጠ ነገር የለም። ይሁን እንጂ እጅግ የምወድህ ባልንጀራዬ ብትሆንም" አለና በእጁ ራሱ ላይ ያለውን የምንኩስና ቆብ እያሳዬ "አንተ ለዚች ሚስት አጭታም፣ ለሠርጉም ሚዜ መሆን ስለማትችል ነው" አለኝ።

አዎን ልክ ነህ! በዚህ ውጥንቅጥና አሰልቺ ዓለም በጉጉትና በወረት እየተናጥኩ እንድኖር ለሥጋ የተሸጥሁ ሰው ነኝ" አልኩና ሐዘን በተቀላቀለው ፈገግታ ውስጥ ሁኜ፡-

"እሺ ይሁን! ዶ/ር አባ መዓዛ ቅዱሳን!" አልኩት ወደ ልቤ ተመልሼ።

"ከሐር ተሠርቶ በወርቅ የተከፈፈ ቀሚስ የለበሰውን ሰው በነሐስ ያጌጠ የአቡጀዲ ለምድ አትደርብለት። ‹አባ መዐዛ ቅዱሳን› ብቻ በቂ ነው" አሉኝ ፈገግ ብለው የማኅበረ ሥላሴው አባ ኪዳነ ማርያም።

"የጀመርነው የምርምር ሥራችን፣ ለሀገራችን ልናበረክተው የተነጋገርነው፣ ልቤን ያነሣሣኸው ሁሉ ከእንግዲህ ቀረ ማለት ነው?" አልኩት።

"የሥጋ ፈቃዴን በነጻነት ምርጫዬ ተውኩት እንጂ የዚህ ዓለም ተልዕኮዬንና የምርምር ሥራዬን ተውኩት ማለት እኮ አይደለም። እንዲያውም የምርምር ሥራችንን በትጋትና በትብብር በጥልቀት እንቀጥላለን። እኔና አንተ በአንድ ቀንበር የምንጠመድ አንድ ሞፈር የምንስብ ጥንድ በሬዎች እንሆናለን" ሲለኝ።

"ኢትዮጵያዊው ግሪጎር መንደል (Gregor Mendel)" አልኩት የጀነቲክስ (ዘረመል ሳይንስ) አባት ሊቁ አስትሪያዊው መነኩሴ ትዝ ብሎኝ።

ፈገግ አለና ትክሻዬን ይዞ፡-

"በሙያችን የሀገራችንን የሥነ-ምህዳርና የሥነ-ሕይወት ምሥጢር በጥልቀት እንመራመርበታለን። በዚህ የምርምር ሥራችን ደግሞ

ድካማችንና አገልግሎታችን ለዚች ውድ እናት ሀገራችን በመሆኑ
ምን ያክል ተከፈለን፣ ማንስ አመሰገነን፣ የትኛው ሚዲያ ስማችንን
ሰራን የሚለው አያሳስበንም። ሀገራችንን ከልብ ስለምንወድ
ከጉስቁልናዋ ይልቅ ውበቷ ከችግሮቿ ይልቅ በረከቶቿ ጎልተው
ይታዩናል። ከፖለቲከኞቻችን ግብዝነት ይልቅ ሰፊው ምስኪን
ሕዝብ ጎልቶ ይታየናል። በታሪክ አጋጣሚ በራሳችን ወንድሞች
ግፍና መከራ ቢደርስብንም የአንድ እናት ልጆች በመሆናችን
የሚያመረቅዝ ቂም በልባችን የለም። ይልቁንም ሁላችንንም
የሚያነጻው የይቅርታ መንፈስ ስለወደፊቱ የጋራ ተስፋችን
እንድናስብ ይገፋፋናል እንጂ። ፍትሕን የሚፈጥረው ፍቅርና
ይቅርታ እንጂ በረጅም ጥፍር መቦጫጨር አይደለምና። ሀገራችን
ስንል ደግሞ ሕዝቦቿ፣ ባህሏ፣ ሃይማኖቷ፣ ታሪኳ፣ ወንዞቿና
ተራሮቿ፣ ዐፈርና ውኃው እጽዋቶቿና እንስሳቶቿ ባጠቃላይ ዳር
ድንበሯ ማለታችን ነው። ስለዚህም ነገር ፈጣሪን እናመሰግነዋለን።
ኢትዮጵያዊ እንሆን ዘንድ በኢትዮጵያ ምድር እንድንወለድ የፈቀድክ
አምላክችን ሆይ እናመሰግንሃለን እንለዋለን!" አለኝ። በዙሪያችን
ያሉት ሁሉ በአምንታ እራሳቸውን ሲነቀንቁ ይታዩ ነበር።

ይህን እየተነጋገርን እያለን ግርማ ሞገሳቸው የከበደ ረዘም ያሉ
አዛውንት መነኩሴ ከወደ ደኑ አካባቢ ብቅ ሲሉ ሁሉም በአክብሮት
ራሳቸውን ዝቅ እያደረጉ በመስቀላቸው ተሳለሙ። የሆነ ብርሃን
የከበባቸው ይመስላል። አንዳች ነገር ገፋፋኝና ከእግራቸው ሥር
ወደቅሁ። ትክሻዬን ይዘው ቀና አደረጉኝና በመስቀል አሳልመው
ግንባሬን ሳም አደረጉኝ። መላ ሰውነታቸው ዕጣን ዕጣን ይሸታል።

ቢጫ የመናንያን ልብስ ቀኝ እጃቸውን አውጥተው አጣፍተዋል።
ከወገባቸው በላይ ትክሻቸው ላይ በከፊል ልብስ አልለበሱም።
የፊታቸውና የትክሻቸው ቆዳ ቀለም የቀይ ዳማ የሚባል ሲሆን
የፊታቸው ቆዳ ዐይናቸው አካባቢ ከመሸብሸቡ በስተቀር በምኞት
የሚኖሩ እንጂ በምናኔ ያሉ አይመስልም። የምንኩስና ቆባቸው
በሰሌን ተሠርቶ በቆዳ የተለበደ ነው። ከምንኩስና ቆባቸው
አምልጦ የወጣው ጥጥ መሳዩ ጸጉራቸው ከትካሻቸው ላይ እን
ሐረግ ተጠማዞ ተኝቷል። የፊታቸው ጺም እንዲሁ ረጅም ሪዝ ሆ

አንገታቸውን ሸፍኖታል። ደረታቸው ላይ የመባረኪያ መስቀል ያንጠለጠሉ ሲሆን ቀኝ እጃቸው ላይ እስከ ክንዳቸው ድረስ ከዕንጨት የተሠራ መቁጠሪያ ተጠምጥሞበታል። በእጃቸው ለአባ መዝገበ ሥላሴ የሰጠኋቸውን የዕያቹን ቅርንጫፎች ይዘዋቸዋል። የገረመኝ ነገር ግን እኔ ስሰጣቸው እንደጠወለጉት ሳይሆን ፍጹም ለምልመው ነበር።

የፊታቸው ጸዳል፣ የሚለግሱት የትሕትና ፈገግታ አንዳች መግነጢሳዊ ኃይል ያለው ቢሆንም ግርማቸው ደግሞ ያሸብራል። አባ መዐዛ ቅዱሳን ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ በለሆሳስ "በፍጹም ስውራኖቹ እና በእኛ መካከል ያሉ አባት ናቸው። በዚህ ወቅት ልታገኝ የምትችለው እኒህን ታላቅ አባት ነው። የምትፈልገውን መጠየቅ ትችላለህ" አለኝ።

ፈዝዤ እንደቆምኩ ፈገግ አሉና፡-

"የኔ ልጅ! ቃላችንን አክብረህ ትእዛዛችንን በድካምህ ስለፈጸምክ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁንልህ" አሉና "የሆነው ሆነና ያን ሁሉ ድካም ደክመህ ትእዛዛችን የፈጸምከው ምሥጢራችንን ለማወቅ ባለህ ጉጉት ነው ወይስ የዕድሜህ ማጠር አሳስቶህ?" አሉኝ።

ንግግራቸው አይጠገብም። ምንም መልስ ሳልሰጣቸው ዝም ብለው ቢናገሩኝ ነፍሴ እንዴት በለመለመች። እንደ እውነቱ ከሆነ ምሥጢራቸውን የማወቅ ጉጉቴ በየቀኑ እየደበዘዘ መጥቶ አሁን ፍላጎቱ ያለኝ አይመስለኝም።

"አባታችን ሞትን የፈራሁት መሰለኝ" አልኳቸው።

"እውነት አለህ የእኔ ልጅ! ይሁንና ሞት ብትፈራውም ብትንቀውም የማይቀር ዕዳ ወይም መንገድ ነው። የዕድሜህ ማጠር ወይም መርዘም አያስጨንቅህ፣ የፈጣሪ ፈቃድ ነውና። ይልቁንም በተሰጠችህ እያንዳንዷ ቀን በመልካምና በደስታ ለመኖር ሥጋህን ተጠንቀቀው፣ ነፍስህን ቁጠራት፣ እምነትህን ጠንቅቀው" አሉና ቀጠሉ። እኔ ብቻ ሳልሆን ሁሉም በተመስጦ እያዳመጡ ነበር።

ኢትዮጵያዊነት በአምስት አምዶች የታነጸ መኖሪያ እልፍኝ ነው። ጥልቅና ሰፊ ዕውቀት፣ መዛል የሌለበት ትጋት፣ በትዕግስት የታሸ ጀግንነት፣ ርኩሰት የሌለበት ቅድስና፣ ግብዝነት የሌለበት ምስጢራዊ ሕይወት ነው!"

"የምሥጢር ሙዳይ ሁን እንጂ የእሳት ማንደጃ ወናፍ አትሁን። ለዎች ሊሰሙህ በሚችሉበት ችሎታቸውና ፍላጐታቸው መጠን ብቻ ተናገር፣ ቁጥብ እንጂ ዝርው አትሁን። ለዕውቀት ትጋ። በከፊል በተረዳኸው ነገር ራስክን እንደ አዋቂ አትቁጠር። በከፊል ከማወቅ አለማወቅ ይሻላል። ሥራ ስትሠራ ደግሞ ነገ ትቼው ለምሞተው ወይም ብሠራ የሚጠቀመው ሌላ ነው በሚል ተስፋ ቢስ ሆነህ ሳይሆን ዘላለም እንደምትኖር ያክል በመትጋት ነው። ትጋት ጥሩ ነው። ችኮላህ ግን ውጤት አያመጣም፣ በችኮላ መሥራትና በፍጥነት መሥራት የተለያዩ ናቸው። ርኩሰት የዕውቀትና የሥልጣኔ መገለጫ አይደለምና ማንነትንና ሰብዓዊ ክብርን ከሚያጎድፉ ተግባራት መታቀብን ገንዘብ አድርግ ።"

"እናም በየዕለቱ በኑሮህ ጠንቃቃ ሁን። ያለጸጸት ነገን ለመኖር ዛሬን በቁም ነገር አሳልፍ፤ ውሳኔዎችህ ትክክለኛ መሆናቸውን መርምር፤ ልክ እንደገና ሕይወትን የመኖር ዕድል ቢኖርህ ወይም እንደገና የመወለድ ዕድል ቢኖርህ ደግመህ የምትኖረውንና ለማከናውን የምትመርጠውን ዐይነት ሕይወት ለመኖር ሞክር። እንዲህ ያለ ጥያቄ ብትጠየቅ መልስህ ምንድን ይሆን? እንደገና የመወለድ ምርጫ ቢኖርህ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢትዮጵያዊ ሆነህ ለመወለድ ትመርጣለህ? የያዝከውንስ ሙያ በድጋሚ ትመርጠዋለህን? ያገባሃትን ሚስትስ እንደገና ታገባታለህ ወይስ መነኩሴ ከሆንክ አንደገና የምንኩስና ሕይዎትን ትደግመዋለህን?" አሉና ዕያቹን ወደ አፍንጫቸው አስጠግተው እንደማሽተት አደረጉና፡-

"ተመራማሪ ማለት የሁሉን ምሥጢር የሚፈታ ማለት አይደለም፤ ምርምርም ሁሉን ነገር ለማወቅ ብቻ አይደለም። ከአንተ አቅም በላይ የሆነ ነገር መኖሩን፣ ከምትገነዘበው ጥበብ በላይ የመጠቀ

ኩነት መኖሩን ማወቅ በራሱ የምርምር ውጤት ነው። የኔ ልጅ በምዕራቡ ዓለም በቀሰምከው ዕውቀት ብቻ የሚፈታ ችግር የሚደረስበት ምሥጢር የለም። በምንም መልኩ አሁን ባለህ ዕውቀት ልትረዳውም ልትገልጸውም የማትችል ጥበብ አለ። በድንገት መጥታችሁ በድንገት የምትረዱት ነገር አይኖርም። የምዕራቡ ዓለም ሳይንስና ጥበብ መልካም ቢሆንም አልፋና አሜጋ አድርገህ አትውሰደው። በሀገርህ እንደ ዘበት አልፈኸው የሄድከው የጠለቀ ዕውቀት እንዳለ አስተውል። እዚህ ቦታ አሁን በአንተና በባልደረቦችህ እሳቤ ብቻ የሚተነተን ሳይንሳዊ ምሥጢርና ቁሳዊ ቀመር ያለ አይምሰልህ። ብንፈቅድልህ እንኳን በቃ! በግልፅ ብታየውም ልታየው የምትችለው ነገር በእምነት፣ በፍቅርና በተስፋ ፈጣሪያቸውን የሚያመልኩ ሰዎችንና ለጊዜው ከአንተ መረዳትና አመክንዮ ውጪ የሆኑ የሀገር ተስፋ የሚሆኑ ድርጊቶችን ይሆናል። እናንተ ዓለመ ሁሉ አላችሁ እኛ ደግሞ ይህች ቁራጭ የደን ለምለም ሥፍራ የሰላም ደሴት አለችን። ፈጣሪን በጸጥታ እናመሰግንበታለን።" ንግግራቸው ጠንከር ያሉ ቃላትን ቢይዝም የመደመጥ ውበት አለው።

"የምትፎካከሩባትን፣ ሲያሻችሁ የምትወዷትንና የምታወድሷትን ስትፈልጉ ደግሞ የምታዋርዷትን፣ በለስ ሲቀናችሁ ከላይ ሆናችሁ ስትረግጡ ሌላ ጊዜ በተራችሁ ከሥር ሆናችሁ ስትታሹ የምትኖሩባትን ሀገራችንን፣ የትጋትና የበረከት ምድር መሆኗ ይገለጽ ዘንድ፣ ከራሳችን ላይ ያራቅነውን ጸጋ እንጎናጸፍ ዘንድ፣ ፈጣሪ ለተስፋው የሰነፈውን ልባችንን ያነሣሣው ዘንድ፣ የመከራችን ፍጻሜ ይቀርብ ዘንድ የሰጠንን እናስተውልበት ዘንድ ጎሊናችንን በብርሃኑ እንዲሞላው በዚህ ቦታ እንለምነዋለን። የተናቀውንና የተረሳውን ጥበባችንን የሚፈልገው ትውልድ አስኪመጣ ድረስ በእምነት አደራችንን በአርምሞ የምንጠብቅበት ስፍራ ነውና ከዚህ በላይ አትድፈረው" አሉ።

በዚህ መካከል እንባዬ በዐይኔ ሞላና ድንገት፡-

"ለምን ትሰወሩብናላችሁ? ለምን አብራችሁን ሆናችሁ ከጎናችን ቆማችሁ አትባርኩንም? ለምን ኑሮው ዳገት፣ ሀገራችን ውስጥ መኖር መረገም፣ መሰደድ በረከት እኪመስለን ድረስ፣ ስናጣ የምናገኝ ስናገኝ የምናጣ አልመስለን ብሎ ራእይ አጥተን ስንከሸፍ እንዴት እናንተም ፈጣሪም ዝም አላችሁን?" አልኳቸው በምሬት። የፈጣሪን ወኪል ያገኘሁ መሰለኝና ብሶቴን ከእንባዬ ጋር ገነፈልኩ።

የበለጠ ፈገግ ብለው በተለመደው የነሐሴ ካፊያ በሚመስለው ለስላሳው ድምፃቸው ቀጠሉ፡-

"እኛ አልተሰወርንም! ይልቁንም የተሰወራችሁ እናንተ ናችሁ። ላለፉት በርካታ ዓመታት በተለያየ አቅጣጫ ተጉዘናል። እናም ከመራራቃችን የተነሣ መተያየት አልቻልን ይሆናል። እናንተ አሻግራችሁ ማዶ ማዶ ብቻ ስለምታዩ፣ እኛን እንደወግ አጥባቂ ራሳችሁን እንደ ነጻ ሰው፣ እኛን እንደ ኋለቀር ራሳችሁን እንደ ተራማጅ፣ እኛን እንደ ደናቁርት ራሳችሁን እንደ ሳይንሳዊ ጥበበኞች፣ እኛን የኋላ ታሪክ ናፋቂ ራሳችሁን ባለራእይ አድርጋችሁ የማይወዷችሁን ወዳችሁ የማያከብሯችሁን አክብራችሁ ራሳችሁን ሳይሆን ሌላውን መስላችሁ ከሀገራችሁ ራሳችሁን የሰወራችሁ አንተና መሰሎችህ ናችሁ። ከዚህ ደንዝዛችሁ ማዶ ስትሄዱ ለሥራ ትሾራላችሁ። ከዚህ ስሙን ለመጥራት የምትጸየፉትን ሥራ በባእዳን ሀገር ሲሆን በእጅ በእግራችሁ ቀን ተሌት ትሠሩታላችሁ። አንድ ጊዜ ምዕራባዊያን ሌላ ጊዜ ምሥራቃዊያን እኝከው የጣሉትን የፍለስፍና አገዳ እያላመጣችሁ ጉራማይሌውን ሸውራራ ዕሳቤያችሁን በግብዝነት ሕዝባችሁ ላይ ታቀረሻላችሁ። ስለሆነም በሀገራችሁ የተሰውራችሁ እናንተ እንጂ እኛ አይደለንም። በዚህ የተነሳ በእርግጥ አንተያይም" አሉ።

ንግግራቸው ከነሐሴ ካፊያነት ወደ ሐምሌ ዶፍነት የተለወጠ መሰለኝ። አባ ግን ቀጠሉ-

"እኛማ ሀገራችንን መስለን፣ ሀገራችንን ወደን፣ ተስፋችንን በፈጣሪና

በሀገራችን አድርገን ወፈርና ውኃውን ጣብቀን በዕፅዋቶቿ ውስጥ ደስ ብሎን እንኖራለን። ተስፋችን ከእኛ ጋራ ነውና" አሉና፡-

" የኔ ልጅ ይልቁንም፡-

‹ፈጣሪ ለምን አይሰማንም ሳይሆን ለምን አንሰማውም፡ ፈጣሪ ለምን አይባርከንም ሳይሆን ለምን በረከታችንን አናውቅም ማለትን ተማሩ፤ ለምን ተወን አይደለም ለምን ተውነው በሉ፤ ለምን የብልጽግናን ቁልፍ ደበቀብን ሳይሆን ለምን ችሎታችንን ስንፍና ጉድጓድ ውስጥ ቀበርን፤ አቅማችንን ለምን በልግመት ስልቻ ከተትነው› በሉ!"

"ሌላውን መስላችሁ ሳይሆን ራሳችሁን ሆናችሁ ለማደግ ሞክሩ። ያን ጊዜ ከእኛ ጋር በግልጥ እንተያይ ይሆናል" ሲሉኝ የሚናገሩትን የጥያቄዬን መልስ ከማስተዋል ይልቅ ልቤ ወደ መማረኩ አዘነበለና፡-

"አባታችን እባክዎት የጎሊና ሰላምና ዕረፍት አገኝ ዘንድ፣ ቀሪ ዘመኔ የተባረከ ይሆን ዘንድ እኔም ከእናንተ ጋር አብሬ እንድሄድ ፍቀዱልኝ" አልኳቸው። እንባዬ ግን ዝም ብሎ ይፈሳል።

ፈገግ አሉና፡-

"ዓለሙንና ብልጽግናውን ማግኘት እየቻልክ በፈቃድህ ነቀህ ስትተወው ለነፍስህ ያደላህ፣ ጽድቅን የምትሻ በመሆኑ መልካም ቢሆንም እየፈለከው ግን አለማግኘትህ ወይም አለመቻልህ ድክመት ይሆናል። በዚች ውብና ድንቅ ሀገር ተፈጥረህ የአርባ ቀን እድልን ማማረር ሰብኣዊ ስንፍና እንጂ የአምላክ እርግማን አይደለም። በተስፋ መቁረጥና በአቅመ ቢስነት በቀቢፀ ተስፋ ወደዚህ ስፍራ ልትመጣ አይገባም። ዓለሙንም፣ አምሮቱንም፣ ማድረጉንም፣ አለማድረጉንም፣ ሁሉንም በችሎታ መናቅ አሸናፊነት ነው። ከዚህ ያሉት ሁሉ ሥጋቸውንም ዓለሙንም አሸንፈው ሲያበቃ ድሉን የናቁት ናቸው" ቀጠሉ እየተጠጉኝ።

"አንተ ግን ገና ነህ። ይህ ቦታ ደግሞ የድል ፊላጊዎች ቦታ ሳይሆን የድል አድራጊዎች፣ የሰላም ናፋቂዎች ሳይሆን የሰላም ሰዎች መኖሪያ የትጉሃን ስፍራ ነው። አንተ ደግሞ ከዚህ ደረጃ የደረስክ አይመስልም። ያላሳደግሃቸው ልጆች፣ በቃል ኪዳን የምትጠብቅህ ሚስት፣ ጀምረህ ያላጠናቀቅከው ብዙ ሥራ ያለብህ ሰው ነህና። ሐሳብህ የተበተነ፣ ምኞትህ የበዛ፣ ፍለጋህ ያላለቀ ባተሌ ነህና። በዚህ ሕይወት ትማረክ ዘንድ ደግሞ አንተ የተዘጋጀህ አትመስልም። ገና ብዙ የምትፈልጋቸው ነገሮች አሉህና" ብለው እጃቸውን ሲዘረጉልኝ

አባ ወልደ አረጋዊ የተንበርከክ ምልክት አሳዩኝ። የመሰናበቻ ጸሎት መሆኑ ስለገባኝ ከእግራቸው ሥር ተንበረከኩ።

ዮጠሉና፡-

ለምን ዕያቹን እንድታመጣ እንደፈለግን ብርቱ ምሥጢር ነውና ወንድምህ አባ መዓዛ ቅዱሳን ወደፊት ይነግርሃልና በልብህ ጠብቀው! በእምነትህና በትጋትህ ልክ የሥራ ድርሻ ይኖርሃል። ፈጣሪ ምሕረቱንና ጸጋውን ያብዛልህ ወላዲተ አምላክ አትለይህ" ብለው ትክሻዬ ላይ በግራ እጃቸው ማጣፊያቸው ሥር ይዘውት የነበረውን ምርኩዛቸውን ጣል ሲያደርጉብኝ በቀስታ ልቤን ጉትት አድርጐ ሲወስደኝና ራሴን ለመሳት ሲከጅለኝ ታወቀኝ። ዐይኖቼ የቀስተደመና ቀለማትን ከደኑ ላይ የሚያዩ መሰለኝ። እናም ለራሴ እንዲህ ያልኩ ይመስለኛል፡-

"እኔ ሊቀ ነቢያት ሙሴን አይደለሁ! ሳልታመም አልሞት፣ ሳልሞት ነፍሴ አይወጣ፣ መቃብሬን ሰዎች ሳይቆፍሩት አልቀበር!"

ምን ያክል ሰዓት እንደቆየሁ አላውቅም። ደስ የሚል የሰላም እንቅልፍ ወስዶት እንደቆየ ሰው ከድካምና ከቁስል ጥዝጣዜ ስሜት ነጻ ሆኜ ተነሣሁ። ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማያውቅ የሆነ ብሩህ ስሜት እየተሰማኝ እንደሆነ ይታወቀኛል። ቀና ብዬ ሳይ ዶ/ር ማግዳሊና ሲንቀሳቀስ ያየችው ባለግርማ ሞገሱ የሎል ዛፍ ሥር ነኝ። ከዚህ በፊት ያላስተዋልኩት የጸሎት መቁጠሪያ ተንጠልጥሎበታል።

"የቅዱሳኑን ምሥጢር የምትከድን፡ ዐፈርና ውኃውን የምትጠብቅ፡ የእንስሳት የአዕዋፋቱ መጠለያ፡ የገዳማት የአድባራቱ ሞገስ፡ ቅዱስ ፍጥረት ሆይ! አንተን ሊቆርጥ ምሳር የሚሰል እንዴት የተረገመ ነው?!" አልኩና ተነሥቼ እንደ ሰው እቅፍ አደረኩት።

የሆነ ሰላም እንደ ውኃ ሙላት ከራስ ጸጉሬ እሰከ እግር ጥፍሬ ሲያላብሰኝ ታወቀኝ። እንዲህ ያለ ሰላም በገንዘብም፡ በዕውቀትም፡ በሸመትም፡ በውርስም፡ በገጸ በረከትም የሚገኝ አይመስለኝም። ቢሆን ኖሮ ቀደም ብዬ አውቀው ነበር።

ወፎች ይዘምራሉ፡ ጠጣዎች ያሸካካሉ፡ የዛፎች ቅርንጫፍ በነፋስ ሽውታ እንደ ጸናጽል ይንሿሿሉ። እንደ ከዚህ ቀደሙ ድምፁ የሚያስበረግገኝ ሳይሆን በሆነ ጣዕምና ጎብረ ዝማሬ ለሰላሜ ማጀቢያ የሚያሸበሽቡልኝ መሰለኝ።

ስለብዙ ነገር ፈጣሪን ማመስገን የሚገባኝ ቢሆንም በዚች ምሥጢራዊትና ቅድስት ሀገር እንድኖር የፈቀደልኝን መሆኑን ሳስብ፡-

"ካደረገልኝ ነገር ውጭ ሌላ ሊያደርግልኝ የሚገባው ያላደረገልኝ ምን አለ?" አልኩ!

እጄን ከዛፉ አላቅቄ ዘወር ብዬ ልራመድ ስል የተጠቀለለ ብራና አየሁ። ለእኔ መሆኑ ገባኝና ገልጬ ሳየው በግልፅ ፊደላት፡-

"ኢትክሰት ወኢትንግር ስመ ዝ ጎራ
እስመ አኮ መካነ ሁከት ወነጎርጓር
ዘእንበለ መካነ ጸሎት ወአርምሞ"

"ይህ ተራራ የጸሎትና የአርምሞ እንጂ የግርግርና የወረት አይደለምና ስሙን አትግለጸው" እንደማለት ነው።

"ከእንግዲህ ትእዛዛችሁን የምጥስ እኔ ማነኝ? እንደ ቃላችሁ ይሁን!"

ተፈፀመ//

...በመንገዱ የፍርሀትና የአድናቆት ሀሚመስል ድና ደር ማንሄዱና፡
"ሲኦይ!" አለችኝ ::
"አቤት" ብዬ ፊቴን ወደ አርዕ ሳዞር ፊት ለፊት ወደ ታች እጅን ዘርጊ...
"Oh my God. I think that tree is moving!" (ኦ አምላኬ! ያ ዛፍ ይንቀሳቀሳል) አለች ::
"Yaa every tree moves with the wind" (አዎን ማንኛውም ዛፍ በነፋስ ይንቀሳቀሳል) አልኳት ለማታለል ብዬ:: እንደ እውነቱ ከሆነ እኔም ዘንጊቱን ፍርሀት ውስጥ ነበርኩ::
"No, no I mean it is moving not swinging" (አይደልም አይደልም፣ መወዛወዝ ሳይሆን ይንቀሳቀሳል ነው ያልኩህ) አለች ኮስተር ብላ ::
"What?!" (ምን?!) አልኩ:: ....

"እንዲያው ያለእትማ ለዘመናት ተቆልፎ የኖረ ምሥጢር ነካክቼ ልሰድደ" አልኩና በምፊት፡- "አይ ፕሮፌሰር ሃሮልድ! እግዜር ይይለምት:: በሞኝ ከንድ የዘንዶ ጉድንድ ይለኩበታል የተባለው ተረት በእኔ ደረሰ አልኩ:: ስታዩን በሙሉ ሞኖ አድርጌ ራሴን እጅግ እየተራገምኩ እንዳይደረስ የለም ግዙት በር ላይ ደረስን:: ከአንድ ዛፍ ሥር ቁሞ አልኩና የውስጥ እግሬን ሳየው የተጠበሰ ሥጋ መስሏል ሀልፎ ሀልፎ ደግሞ ውኃ ቋጥሯል:...

..."በፍለጋው በመድከምም ሆነ በመሰላቸት በዚያው መቅረትም አልተፈቀደልህም:: ወደ ቅዱሱ ቦታ ለመመለስ በዘገየህ ቁጥር የጎለኛው ዘመንህ እንደምንጣፍ ወደ አንተ እየተጠቀለለ ይቀርባል::"...

...በወረትና በጉጉት የጀመርኩት ምሥጢር ማነፍነፍ እንዴት ያለ ዋጋ እንዳስከፈለኝ አስቤ ሲያንሰኝ ነው! አልኩ:: በምን ምክንያት እንዴት ባለ ሰበብ ወደዚህ መንከራተት እንደገባው ሳስብ ሕይወት በፅጣ ፈንታና በአስደናቂ ገጠመኞች የተሞላች መሆኗ ታሰበኝ::...

ከመጽሐፉ የተወሰደ

ያታሪ መጽሐፍ ቅኝንር
ነፃነት ጌታቸው 0911 96 74 74
ዋጋ ብር 110.00
ጎተመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር
011 158 53 52